# መጽሐፈ ምሳሌ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

መጽሐፉ ገና ከርእሱ ላይ ጸሓፊው ሰሎሞን መሆኑን ቢገልጽም እንኳ፣ ወደ በኋላ ከሚገኙት ምዕራፎች ጸሓፊው ሰሎሞን ብቻ እንዳልሆነ መረዳት እንችላለን፤ ም22፥17፣ "የጠቢባን ቃል" ይላል፤ እንዲሁም 24፥23 "እነዚህ ደግሞ የጠቢብ ምሳሌዎች ናቸው" ይላል:: በተጨማሪም በም22፥17-21 ላይ ያለው መግቢያ፣ እነዚህ ክፍሎች የተገኙት ከራሱ ከሰሎሞን ብቻ ሳይሆን፣ ከጠቢባን ጉባኤ መሆኑን ያሳያል:: ም30 የያቄ ልጅ የአጉር፣ ም31፥1-9 ደግሞ የንጉሥ ልሙኤል መሆኑን ያመለክታሉ፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስማቸው ተጠቅሶ አይገኝም::

ያም ሆነ ይህ አብዛኛው የመጽሐፉ ክፍል ከሰሎሞን ጋር የተሳሰረ ነው፤ በ10፥1 እና 25፥1 ላይ በሚገኙት ርእሶች የሰሎሞን ስም ተጠቅሶአል፤ ነገር ግን በ25፥1 ላይ ያሉት ምሳሌዎች (ቅኔዎች) የተቀዱት (የተገለበጡት) በሕዝቅያስ ሰዎች እንደ ሆነ ተጠቅሶአል:: ይህም የሚያሳየው የጥበበኞች ወይም የጸሓፊዎች ቡድን አርታዒዎች ሆነው፣ ምሳሌዎቹ የመጽሐፍ ቅርጽ እንዲይዙ በማድረግ በ25-29 ያለውን ክፍል ቀደም ካለው ስብስብ ጋር የጨመሩት መሆኑን ነው:: ሰሎሞን ምሳሌዎችን የመፍጠር የተለየ ችሎታ ያለው መሆኑን የ3,000 ምሳሌዎች አመንጪ ሆኖ በተገለጸበት በ1ነገ4፥32 ላይ ተመልክቶአል:: አቻ ያልተገኘለት ጥበበኛ ንጉሥ መሆኑ ከመገለጹም በላይ (1ነገ4፥29-31)፣ የአያሌ ምሳሌዎችም ባለቤት እርሱ መሆኑ ግልጽ ነው:: መጽሐፉ አጭር መግቢያና (1፥1-7) ረዘም ያለ መደምደሚያ (31፥10-13) አለው:: በመግቢያው ላይ ተተንትኖ የሚታየው ክፍል (1፥8-9፡18) የአጠናቃሪው ወይም የአርታዒው ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ይህ ክፍል ከሌሎች ምዕራፎች ጋር ተመሳስሎ መገኘቱ (6፥1ን ከ11፥15፤ 17፥18፤ 20፥16፤ 27፥13 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም 14፥5፡25፤ ከ19፥5 ጋር ያነጻጽሩ) ሰሎሞንም የዚህ ክፍል ባለቤት መሆኑን በግልጽ ያሳያል:: "እግዚአብሔርን መፍራት" (1፥7) አስፈላጊ መሆኑ በአጽንዖት መገለጹ፣ የተለየ የሆነውን ክፍል በአንድ ላይ ያስተሳስረዋል::

### ዘመኑ

ለመጽሐፈ ምሳሌ እውን መሆን ሰሎሞን ዐቢይ ሚና ይሰጠዋል፤ ይህ ደግሞ ዘመኑን የሰሜንና የደቡብ መንግሥት በመባል ሳይከፋፈል ወደ ነበረበት ወቅት ያደርሰዋል፤ ይኸውም በዐሥረኛው ምእተ ዓመት ቅ.ክ ማለት ነው:: በዘመኑ የነበረው ሰላምና ብልጽግና ይህን መሰል ጥበብና ሥነ ጽሑፍ እውን እንዲሆን ረድቶአል:: ከዚህም በላይ በ22፥17-24፥22 ያሉት ሠላሳ ምሳሌዎች በሰሎሞን ዘመን ገደማ ይፋ ከሆነው ከግብፅ ባለ ሠላሳ ምድብ ትምህርት ዐዘል አባባል ጋር ማለትም፣ "የአመንሞፔ ጥበብ" ከተባለው ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ምሁራን ያትታሉ:: እንደዚሁም ከም1-9 ባለው ክፍል ጥበብ በሰውኛ ዘይቤ መመሰሏ (1፥20 ማብ፤ 3፥15-18፤ 8፥1-36 ይመ)፣ በሁለት ሺህ ዓ.ቅ.ክ በመስጴጦምያና በግብፅ ጽሑፎች ላይ ረቂቅ የሆነ ሐሳብ በሰውኛ ዘይቤ ከመገለጹ ጋር ተመሳሳይነት አለው::

በዚህ መጽሐፍ ላይ የሕዝቅያስ ሰዎች ሚና እንዲኖራቸው መደረጉ (25፥1 ይመ)፣ የመጽሐፉ ዐቢይ ክፍል ከ715-686 ዓ.ቅ.ክ መጠረዙንና አርትዖት የተደረገለት መሆኑን ያመለክታል:: በዚህ መጽሐፍ የሚገኙት ምሳሌዎች ተሰብስበው የተጠረዙበት ዘመን እስከ ሕዝቅያስ ዘመን ድረስ የሚቀጥል ቢሆንም እንኳ፣ የአጉር (ም30)፣ የልሙኤልና (31፥1-9) "ሌሎቹ የጠቢባኑ ቃሎችም" ከሰሎሞን ምሳሌዎች ጋር የተጨመሩት በዚህ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም::

### የጥበብ መጻሕፍት

አይሁድ ብሉይ ኪዳንን ሕግ፣ ነቢያትና ጽሑፎች በማለት ይጠራሉ፤ በሦስተኛው ምድብ ውስጥም የዳዊት መዝሙርና የቅኔ መጻሕፍት የተባሉት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጽሐፈ ምሳሌና መጽሐፈ መክብብ ይካተታሉ:: እነዚህ የጥበብ መጻሕፍትም በእስራኤል ኅብረተ ሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ቍልፍ ሚና ካላቸው (ኤር 18፥18)፣ "የጥበብ ሰዎች" ወይም "ጐምቱ ሊቃውንት" ከተባሉት ጋር የተሳሰሩ ናቸው:: ጠቢባን ሰዎችም ወጣቱን እንዲያስተምሩ፣ ንጉሡንም እንዲመክሩ ይጠበቅባቸው ነበር፤ ካህናቱና ነቢያቱ በመንፈሳዊ ጉዳይ ላይ የሚያተኵሩ ሲሆን፣ ጠቢባኑ ደግሞ ዘወትራዊና ፍልስፍናዊ በሆነው ጉዳይ ላይ ያተኵሩ ነበር:: ከመጽሐፎቻቸውም አንዳንዶቹ፣ ወጣቱ በድሎትና በደስታ እንዴት መኖር እንደሚችል በማስተማር በሕይወት ብሩህ ገጽታ ላይ ያተኵራሉ፤ እንደ መጽሐፈ ኢዮብና እንደ መጽሐፈ መክብብ ያሉት ደግሞ አመራማሪና ሥነ መለኮታዊ የሆኑትን አስቸጋሪ የሕይወት ጥያቄዎች በማንሣት፣ ክፉት ለምን ተከሠተ? ጠማማ የሆነውስ፣ "ለምን ባለ ሀብት ሆነ" (መዝ37 እና 73 ይመ) እያሉ የሕይወትን እንቈቅልሽ ይጠቅሳሉ:: መጻሕፍቱ በእነዚህ አይበገሬ መሳይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኵሩ በመሆናቸውም በአንዳንድ ሊቃውንት ዘንድ፣ "ሕይወትን አደምንነው የሚያሳዩ" የሚል ቅጽል ተሰጥቶአቸዋል:: ፈካ ያለውም ሆነ የደመነው የሕይወት አመለካከት በጥንቱ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ሥነ ጽሑፍ ውስጥም ይገኛል::

ምሳሌ በምሳሌነቱ እንጂ እንደ ትንቢት አንድ ውጤት ወይም አንድ ድርጊት ከሚያስከትለው

የተነሣ እንደሚሠርፅ ተስፋ መቈጠር የለበትም፤ ለምሳሌም 10፥27፣ "እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜን ያረዝማል፤ የክፉ ሰው ዕድሜ ግን በአጭር ይቀጫል" (3፥2 እና ማብ ይመ)። "እግዚአብሔር ጻድቅ እንዲራብ አያደርግም" (10፥3)፤ "የክፉዎች ሆድ ግን እንደ ተራበ ይኖራል" (13፥25)። እነዚህ ጥቅሶች በጥቅሉ ሲታዩ እውነትነት ያላቸው ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ጻድቁ ሥቃይ ውስጥ የሚገባበት፣ ክፉውም የሚበለጽግበት ሁኔታ አለ። ብዙውን ጊዜ ጻድቁም ሆነ ክፉው የእጁን በምድር ላይ ያገኛል (11፥31)፤ አንዳንድ ጊዜ ግን ለሽልማትና ለቅጣት ቀጠሮ የተያዘለት ከመቃብር ባሻገር ነው።

## የመጽሐፈ ምሳሌ ባሕርያት

በኢሳ14፥14፤ በዘኍ23፥7፡18፤ በሕዝ17፥2 ላይ የሚገኘው "ምሳሌ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ቋንቋ የተለያየ ስያሜ አለው፤ ስለዚህ የዚህ ቃል እሳቤ ከአማርኛው ይልቅ ሰፋ ያለ ትርጕም አለው። ይኸውም ከም1-9 ባሉት ክፍሎች ላይ ረዘም ያለ ሐተታ ለምን እንደ ተሰጠ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። ብዙዎቹ ምሳሌዎች የሰውን ጠባይ የሚገልጹ ሆነው እጥር ምጥን ያሉና እምቅነት ያላቸው ናቸው፤ ብዙውን ጊዜም በቃል ለማጥናት የሚያግዙ የቃልና የድምፅ ድግግሞሽ ይገኛሉ።

በመጽሐፉ አያሌ ክፍል ውስጥ (10፥1-22፥16)፣ ምሳሌዎቹ ባለ ሁለት መሥመሮች ናቸው፤ በም10-15 ያሉት ደግሞ ንጽጽሮሽን ዐዝለው ይገኛሉ፤ አንዳንድ ጊዜ ጸሓፊው በድምሩ ያስተዋለውን እንዲህ በማለት ይገልጻል፤ "እጅ መንሻ የሰጪውን ፊት እንደ ዕንቍ ያበራል" (17፥8፤ ከ14፥20 ጋር ያነጻጽሩ)፤ አብዛኛውን ጊዜ ግን ጠባይን ይመዝናል፤ "ጕቦን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል" (15፥27) በማለት። ሌሎቹ በርካታ ምሳሌዎች ደግሞ አንድ ድርጊት ወይም ጠባይ የሚያስከትለውን ዕዳ ወይም የሚያስገኘውን ጥቅም ይገልጻሉ፤ "ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል" (10፥1)። ምሳሌዎች ጥንቱኑ የተጻፉት ለትምህርት ስለ ሆነ፣ አካሄዳቸው በትእዛዛዊ አንቀጽ ነው፤ "ድኻ እንዳትሆን እንቅልፍን አትውደድ"፤ ትእዛዛዊ አንቀጽ በማይውልበት ጊዜ እንኳ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈለገው ጕዳይ ቅል ብጭ ብሎ ይታያል (14፥5 ይመ)።

በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ተዘውትሮ የሚገኘው የዘይቤያዊ ቋንቋ አገባብ ነው፤ "ቀዝቃዛ ውሃ የተጠማችን ነፍስ እንደሚያረካ፣ ከሩቅ አገር የሚመጣ ወሬም እንደዚሁ ነው" (ምሳ25፥25)፤ በም25 ብቻ "እንደ" የሚለው ማነጻጸሪያ ዐሥራ አንድ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። እነዚህ ተነጻጻሪ ዘይቤዎች ምሳሌው ቅልብጭ ብሎ እንዲታይና የላቀ ኀይል እንዲኖረው ያደርጋሉ። ዘይቤዎቹ በሚያስቅና ምፀታዊ በሆነ መልክ ዐልፎ ዐልፎ ገብተው ይገኛሉ፤ "በእርያ አፍንጫ ላይ እንደ ተሰካ የወርቅ ቀለበት፣ ማስተዋል የጐደላት ቈንጆ ሴት እንዲሁ ናት" (11፥22፤ ከ26፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ወይም "መዝጊያ በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣ ሰነፍም ዐልጋው ላይ ይገላበጣል" (26፥14) ተለዋጭ ዘይቤም የዚህኑ ያህል ኀይል አለው፤ "የጠቢብ ትምህርት የሕይወት ምንጭ ናት" (13፥14)፤ እና "ፈውስ የምታመጣ ምላስ የሕይወት ዛፍ ናት" (15፥4)፤ እንዲሁም 16፥24 እንደሚያመለክተው፣ "ደስ የምታሰኝ ቃል የማር ወለላ ናት" ይላል። ዘር የመዝራትና ሰብል የማጨድ ምሳሌም አዎንታዊና አሉታዊ በሆነ እሳቤ ውሎ ይገኛል (ከ11፥18፤ ከ22፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ተገቢውን ሚዛን አጕልቶ ለማሳየት ሲባል አንዳንድ ምሳሌዎች ቀጥታ ንጽጽርን ዐቅፈው ይገኛሉ፤ "አካሄዱ ነውር የሌለበት ድኻ መንገዱ ጠማማ ከሆነ ሀብታም ይሻላል" (28፥6)፤ "ይበልጣል" ወይም "ይሻላል" የሚለው አገባብ (በ15፥16-17፤ 16፥19፡32፤ 17፥1፡12) ውሎ ይገኛል፤ ከዚሁ ለውጥ ያለው አገባብም በ22፥1 ላይ ይገኛል። በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ሌላው ዐይነት ምሳሌ "አኃዛዊ ምሳሌ" የተባለው ዐይነት ነው፤ ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሎ የሚገኘው በ6፥16 ላይ ነው፤ (በዚህ ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)፤ የዚህ ዐይነት አባባል 3 ቍጥር ብዙውን ጊዜ በመጀመሪያው መሥመር ሲገኝ፣ 4 ቍጥር ግን በሁለተኛው መሥመር ላይ ይገኛል (ከ30፥15፡18፡21፡29 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በዚህ ዐይነት የሚደጋገመውም ሥነ ጽሑፋዊ ዐላማን ለማሳካት ሊሆን ይችላል፤ መለስተኛ ለውጥ ጸሓፊውን በአንድ ዐይነት ምሳያ አማካይነት ተቀራራቢ ሐሳብን ለመግለጽ ያስችለዋል (ይህም በ17፥3፤ በ27፥2 ላይ እንደ ተመለከተው ዐይነት ማለት ነው)፤ ወይም ይበልጥ ግልጽነት እንዲኖረው የተለየ አጽንዖት ለማድረግ ሲባል አንድ ቃል ተተክቶ ሊገባ ይችላል (19፥1ን ከ28፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። በ26፥4-5 ላይ እርስ በርሱ የሚቃረን በሚመስል መልክ፣ አንድ ዐይነት ስንኝ ሲደጋገም ይታያል፤ ዐላማው ግን ሁለት የተለያዩ ሐሳቦችን አጕልቶ ለማሳየት ነው (በዚህ ላይ የተደረገውን ማብ ይመ)።

አንዳንድ ጊዜ መጽሐፈ ምሳሌ ቀጥተኛና ከነባራዊ ሕይወትም ጋር የተሳሰረ ነው (ከ6፥6፤ ከ21፥9፤ ከ25፥16፤ ከ26፥3፡11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እንግዲህ እውነት ወደ ሰዎች ልብ ዘልቃ ትገባ ዘንድ፣ ኀጢአተኞችም ከክፉ መንገዳቸው እንዲመለሱ የጥበባዊ ሥነ ጽሑፍ አካሄድ ይህንኑ ፈር ሊከተል ችሉአል።

## ዐላማውና ትምህርቱ

በመግቢያው ላይ እንደ ተመለከተው መጽሐፈ ምሳሌ የተጻፈው፣ "በአእምሮ ላልበሰሉት ጥንቃቄን" ለማሳየት፣ "በዕድሜ ለጋ ለሆኑት ዕውቀትንና ልባምነትን ለመስጠት" ሲሆን፣ "ጥበበኞችን የላቀ ጥበበኛ" (1፥5)፣ ለማድረግም ነው። "ልጄ" በማለት በተደራሲነት ተዘውትሮ የተጠቀሰው (1፥8፡10፤ 2፥1፤ 3፥1፤ 4፥1፤ 5፥1) ወጣቱ እንዲማር፣ የተሳካና የሚያስደስት ሕይወት እንዲኖረውም አጽንዖት እንደ ተሰጠው ያመለክታል። የዕውቀት ሀብት ማግኘትና ከከንቱ ሕይወት መሸሽ ሙሉ ጤናንና የተ

ሳካ ሕይወትን ገንዘብ ለማድረግ ያመቻል:: መጽሐፈ ምሳሌ ሕይወትን እንዴት መምራት እንደሚገባ የሚያስተምር የተግባር መመሪያ ቢሆንም እንኳ፣ ለጥበብ እውን መሆን ዋና መሠረት አድርጎ የቈጠረው እግዚአብሔርን መፍራትን ነው:: ለተሳካና ዘለቄታ ላለው ሕይወት፣ መጽሐፉ ተጀምሮ እስከ ሚጨረስ ድረስ አበክሮ የሚያሳየው፣ እግዚአብሔርን መፍራት የግድ አስፈላጊ እንደ ሆነ ነው (ከ3፥5፤ ከ9፥10፤ ከ22፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: ሰዎች ሁሉ በራሳቸው ሳይሆን (28፥26)፣ በጌታ መታመን አለባቸው (3፥5)፤ "የሕይወት ዛፍ" በመጽሐፉ ላይ መጠቀሱ (3፥18፤ 11፥30፤ 13፥12)፣ በዔድን ገነት የነበረውን በረከት በማስታወስ፣ ጥበብን ያገኘ ሰው በእጅጉ እንደሚባረክ በተምሳሌት ያሳያል::

በም1-9 ላይ የጥበብን መንገድ ከዐመፅ መንገድና (1፥11-18) ከሥነ ምግባር ብልሹነት ጋር ያነጻጽራል (2፥16-18)፤ አመንዝራዋ በአታላይ አንደበቷ ወጣቱን ሰው አባብላ ወደ ቤቷ በማስገባት በመጨረሻ ወደ ሞት ትመራዋለች (ከም5፤6፥24-35፤ 7፤ 9፥13-18 ጋር ያነጻጽሩ):: በሴሰኝነት የተነሣ የሚመጣ ሥነ ምግባራዊ ብልሹነት፣ የጥበብ ተቃራኒ በመሆን የቆመ ምሳሌ ወይም ትእምርት (ምልክት) ነው (ከ22፥14፤ 23፥27፤ 30፥20 ጋር ያነጻጽሩ)::

ከዚህም ጋር፣ መጽሐፈ ምሳሌ ጨቅጫቃ ሴትንና ትዕግሥት አስጨራሽ መንገዷን ይኰንናል (19፥13፤ 21፥9፡19):: ቤት የፍቅር እንጂ የጭቅጭቅ መድረክ መሆን የለበትም (ከ15፥17፤ ከ17፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: ጠብ የሚጭሩና ግልፍተኛ የሆኑ ሰዎች ተወግዘዋል (ከ14፥29፤ ከ26፥21 ጋር ያነጻጽሩ):: ሐሜትም የክፉ ሀብት ምንጭ መሆኑ ተገልጦአል (11፥13፤ 18፥8፤ 26፥22)፤ አንድ ሰው ምላሱን መግታት (መግራት) ከቻለ ዐዋቂ ነው (ከ10፥19፤ ከ17፥27 ጋር ያነጻጽሩ):: ከዚህም ጋር ልጆች ትምህርት ያገኙ ዘንድ አንደበት ተግባር ላይ መዋል አለበት (ከ1፥8፤ ከ22፥6፤ ከ31፥26 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የሚያመሰግኑ ልጆች እንዲሆኑም በሥነ ምግባር ታንጸው ማደግ ይኖርባቸዋል (13፥24 እና ማብ ይመ)::

መጽሐፈ ምሳሌ ጠንቃቃነትንና ታታሪነትን ያሞግሳል (10፥4 እና ማብ፤ 31፥17-19 ይመ)፤ ከርፋፋውን ግን በስንፍናው ይነቀፋል (6፥6 እና ማብ ይመ)፤ "በመከራ ወራት የሚተኛ ልጅ ግን ውርደት ይከተለዋል (10፥5)፤ እንቅልፍንም በሚወዱት ድኽነት ቤቱን እንደሚሠረብቸው ሳይታለም የተፈታ ነው (ከ20፥13 ጋር ያነጻጽሩ):: በጥቅሉ ሲታይ ሀብት ከጽድቅ (ከ3፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ድኽነት ከክፋት ጋር ተሳስሮ ይገኛል (ከ22፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ አንዳንድ ጥቅሶች ግን ሀብትን ከክፉዎች ጋር ያቈራኙታል (15፥16፤ 28፥6):: ሀቀኝነትና ፍትሕ በተደጋጋሚ ተወድሰዋል፤ ንጉሥም የድኾችንና የጕስቍሎችን መብት እንዲያከብር ይጠበቅበታል (ከ31፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: ለድኾች የሚራሩ ይባረካሉና (14፥21 እና ማብ ይመ)፤ አንዳንድ ጥቅሶች ደግሞ ለኀረቤት ዋስ በመሆን መዘዝ እንዳይከተል ያስጠነቅቃሉ (6፥1 እና ማብ ይመ)::

ትዕቢተኛውና እብሪተኛው ያለ ጥርጥር ይጠፋሉ (ከ11፥2፤ ከ16፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ፌዘኛውም ከነእብሪት መንገዱ እንደሚጠፋ የታወቀ ነው (21፥24 እና ማብ፤ 1፥22 ይመ)፤ ሰካሮች የተላሉና ምስሎች ሆነው ተስለዋል (ከ20፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ዋይታቸውና ሥቃያቸውም በ23፥29-35 ላይ ሥዕላዊ በሆነ መልክ ተገልጾአል::

መጽሐፈ ምሳሌ ሥነ መለኮታዊ ከመሆን ይልቅ ወደ ዕለት ተለት ኑሮ ስለሚያደላ የፈጣሪ አምላክ ሥራ ጕልህ ሆኖ እንዲታይ ተደርጎአል፤ ጥበብ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሆና በሰውኛ ዘይቤ በተገለጸችበት ክፍል፣ በ8፥22-31 ላይ፣ ራሷ የፍጥረት ባለቤት ሆና ቀርባለች (የዚህኑ ማብ ይመ):: ሁለት ጊዜ እግዚአብሔር የድኾች ፈጣሪ በመባል ተጠርቶአል (14፥31፤ 17፥5)፤ ይኸውም የሰውን እርምጃ ይመራል (ከ16፥9፤ ከ20፥24 ጋር ያነጻጽሩ):: ዐይኖቹም ሥራውን ሁሉ ይመለከታሉ (ከ5፥21፤ ከ15፥3 ጋር ያነጻጽሩ):: እግዚአብሔር የነገሥታት ሁሉ ገዥ ነው (21፥1)፤ ታሪክም በእርሱ ቍጥጥር ሥር ሆኖ ይጓዛል (የ16፥4፡33 ማብ ይመ)::

## ሥነ ጽሑፋዊ ውቅሩ

የተዘረዘሩት ንኡሳን ርእሶች፣ መጽሐፈ ምሳሌን በየርእሰ ጕዳዩ ቅልብጭ አድርገው ይከፍላሉ፤ በአጭሩ የተመለከተው መነሻ ሐሳብ (ዐላማውንና መሪ ሐሳቡን በመግለጽ 1፥1-7)፣ መጽሐፉን የሚጀምር ክፍል ሲሆን፣ በረጅሙ የሰፈረው መደምደሚያ ደግሞ (ይኸውም በዐዘለው ሐሳብና በቃል አደራደሩ የሚታወቅ ነው 31፥10-31) የመጽሐፉ መቋጫ ነው:: የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች የጥበብን መንገድና ጠቀሜታ ከተላላው መንገድ ጋር የሚያነጻጽሩ ተከታታይ ንግግሮች ናቸው:: ጥበብ በሰውኛ ዘይቤ ከምትናገርበት ክፍል በቀር (1፥20፤ 8፥1፡22፤ 9፥1)፣ እያንዳንዱ ሐሳብ "ልጄ" ወይም "ልጆቼ" በማለት ይጀምራል፤ እነዚህም ክፍሎች በመጽሐፈ መክብብ ላይ ከሚገኙት ትምህርቶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፤ ከዚህም ጋር በግጥም መልክ የሚገኙ ንግግሮችን ዐቅፈው ይዘዋል::

በመጽሐፈ ምሳሌ መግቢያ ንግግር ላይ ዋና ገጽታ ነው የሚባለው፣ ጥበብና ሞኝነት በሰውኛ ዘይቤ በሴቴ ጾታ መመሰላቸው ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው (ወይዘሮ ጥበብ ልብን በመማረክና በማስጠንቀቅ ወይዘሮ ሞኝነት ደግሞ በማታለል) ገራገሩ ወጣት፣ መንገዳቸውን ይከተል ዘንድ ለማባበል ይሞክራሉ:: እነዚህ ንግግሮች በሚገባ ተቀነባብረው ይገኛሉ፤ በቀጥታ ማባበልና ማግባባት የሚጀምረውና (1፥8-33) የሚጨርሰው (ም8-9) የንግግሩ ዋና አካል ሁለት ተመጣጣኝ ክፍሎች አሉት:: አንደኛው ጥበብን የሚያወድስ (ም2-4) ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከሞኝነት የሚያስጠነቅቅ (ም5-7) ነው:: በዚህም

ንግግር ውስጥ ወጣቱ ሰው፣ በዚህ ዓለም ኑሮ አሸብርቀው ለመታየት ሲሉ ሌሎችን በሚመዘብሩ ሰዎች አማካይነት ወደ ሞኝነት ሲሳብ ይታያል፤ ሴቶችም በበኩላቸው ከጋብቻ ውጭ በሚፈጸም ሩካቤ ሥጋ ወጣቱ ደስታን ያገኝ ዘንድ ያባብሉታል (ም5፥6፥20-25፥7) በዚያ ወቅት በነበረው ማኅበራዊ መዋቅር፣ ወጣቱን አጕል ሁኔታ ላይ የሚጥሉት እነዚህ ሁለት ዐበይት ፈተናዎች ነበሩ:: የሁለተኛው ፈተና ተግባርም የወይዘሮ ሞኝነትን ማባበያና ማግባቢያ በትእምርትነት አጕልቶ ማሳየት ነው::

በ10፥1-22፥16 ላይ የሰፈሩት አብዛኞዎቹ የሰሎሞን ምሳሌዎች ብቻቸውን የቆሙት በሁለት ስንኝ ሲሆን፣ አጕልተው የሚያሳዩት ንጽጽሮሽን ነው:: ዐልፎ ዐልፎ ሁለት ወይም ሦስት ምሳሌዎች በተመሳሳይ ርእስ ጒዳይ ላይ የሚያተኵሩ ቢሆንም እንኳ፣ ላይ ላዩን ሲመለከቱት ሆን ተብሎ የተከናወነ የምሳሌዎች ቅደም ተከተል ያለ አይመስልም:: ለዚሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ማስተዋሉ በቂ ነው፤ 11፥24-25 ስለ ልግስና የሚያትት ሲሆን፣ 16፥12-15 አንድን ንጉሥ ይጠቅሳል፤ 19፥4፡6-7 ደግሞ ስለ ወዳጅነት ይናገራል:: ይሁን እንጂ ዐበይት ርእስ ጒዳዮችን በመከተል ሆን ተብሎ የተከናወነ ቅደም ተከተል ስለ መኖሩ አሳማኝ እየሆነ የመጣ ማስረጃ አለ:: በዚህ ጒዳይ ላይ አሁንም የላቀ ጥናት ያሰፈልጋል:: ሁለተኛው የሰሎሞን ምሳሌዎች ስብስብ (ም25-29)፣ ከዚህ ቀደም ብሎ እንደሚገኘው ስብስብ ባለ ሁለት ስንኝ ምሳሌ ሲሆን፣ ባለ ሦስት መሥመር ምሳሌዎችም ይገኛሉ (25፥4-5፡21-22፤ 26፥18-19):: የም27 (ቍ23-17) የመጨረሻዎቹ መሥመሮች የበግንና የፍየልን እንዲሁም የከብትን መንጋ ማርባት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ያመለክታል::

በሠላሳዎቹ የጠቢቡ ምሳሌዎች ውስጥና (22፥17-24፥22) በሌሎቹም ቀጣይ ምሳሌዎች ማለትም በ24፥23-24 ላይ ያሉት፣ በርካታ ባለሁለት ወይም ባለ ሦስት ስንኝ ርእስ ጒዳዮች ሲሆኑ፣ ወደ ም1-9 የአጻጻፍ ስልት የመመለስ ሁኔታ ይታያል (23፥29-35 ይመ)፤ እነዚህ ክፍሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎችን የሚገልጹ ሲሆን፣ የ10፥1-22፥16 አባሪዎች ናቸው (24፥6ን ከ11፥14፤ 24፥16ን ከ11፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: ከም1-9 ያለው ትስስር ደግሞ እጅግ የላቀ ነው፤ (23፥27ን ከ2፥16፤ 24፥33-34ን ከ6፥10-11 ጋር ያነጻጽሩ)::

የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የም25-29 አባሪ በመሆን ያገለግላሉ፤ የአጉር ሐሳብ አኃዛዊ ምሳሌ የጐላበት ሲሆን (30፥15፡18፡21፡24፡29) በ30፥5 ላይ ከመዝ18፥30 ጋር ተጓዳኝ ወይም ተመሳሳይ ሐሳብ አለው (ከዚህም ጋር 30፥6 ከዘዳ4፥2 ጋር ያነጻጽሩ):: የንጉሥ ልሙኤል ናቸው ከተባሉት ዘጠኝ ቍጥሮች በኋላ (31፥1-9)፣ መጽሐፈ ምሳሌ በስተ መጨረሻ የመልካም ሴትን ባሕርይ ያሞግሳል:: "መልካም" የተባለችዋ ሴት፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስለ ጥበብ የተነገረውን አያሌ ድንቅ ባሕርይ በትእምርትነት ወይም በምሳሌነት አካታ ይዛለች:: የመጽሐፈ ምሳሌ ቀዳሚ ዐላማ ወደ ብስለት ክልል በመግባት ላይ ያሉ ወጣት ወንዶችን የሚመለከት ሆኖ ሳለ፣ መልካም ጠባይ ባላት ሴት ላይ ትኵረት መደረጉ የሚያስገርም ነው፤ ዐላማው ግን ዕጥፍ ሊሆን ይችላል፤ ይኸውም፣ (1) አንድ ወጣት ምን ዐይነት ሚስት ማግባት እንዳለበት ምክር ለመስጠት ሲሆን፣ (2) ረቂቅ በሆነ ስልት ወጣቱ ሰው እመቤት ጥበብን እንዲያገባ መምከር ነው፤ ይኸውም ወደ ም1-9 መሪ ሐሳብ መመለስ ነው:: ይህ ሐሳብ በም9 ላይ ጐልብቶ ተገልጾአል፤ በም9፥1-2 ላይ ስለ ጥበብ የተሰጠው ገለጻ መልካም ጠባይ ባላት ሴት መመሰሉ፣ ጥበብም ከጅምሩ በሴት አምሳል በሰውኛ ዘይቤ መቅረቧ፣ ማራኪ የሆነ የሥነ ጽሑፍ ቅንብብን ያሳያል::

አስተዋጽኦ

1. መግቢያ፤ ዕቅድና መሪ ሐሳብ (1፥1-7)
2. የጥበብ ጒዳና ከሁሉም የላቀ መሆኑ (1፥8-9፥18)
   - ሀ. ወጣቱን የሚያጋጥሙት ማግባቢያዎችና ማስጠንቀቂያዎች (1፥8-33)
     1. ደስታን በዐመፅ ለማግኘት ሲባል የተደረገ ማግባቢያ (1፥8-19)
     2. ጥበብን በመተው ስለሚመጣው መዘዝ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (1፥20-33)
   - ለ. ጥበብ ገንዘብ እንድትደረግ የተሰጠ ምክር (ም2-4)
     1. የጥበብን ምክር በመቀበል የሚገኝ ጥቅም (ም2)
     2. የጥበብ ምክርና ጥቅም (3፥1-20)
     3. የጥበብ ምክርና ጥቅም (3፥21-35)
     4. ከጥበብ ጋር መጣበቅ እንዲደረግ የቀረበ ዐደራ (ም4)
   - ሐ. ከሞኝነት ጋር መጣመር እንዳይኖር የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ም5-7)
     1. ዝሙትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ም5)
     2. ጠማማ አካሄድን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (6፥1-19)
     3. ዝሙት መፈጸም የሚያመጣው መዘዝ (6፥20-35)
     4. ከጋለሞታ ወጥመድ ለመራቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ም7)
   - መ. ለወጣቱ የቀረበ ምክር (ም8-9)
     1. የጥበብ ምክር (ም8)
     2. የጥበብና የሞኝነት ግብዣዎች (ም9)

3. ዋናው የሰሎሞን ምሳሌዎች ስብስብ (10፥1-22፥16)
4. ሠላሳዎቹ የጠቢቡ አባባሎች (22፥17-24፥22)
5. የጠቢቡ ተጨማሪ ምሳሌዎች (22፥17-24፥22)
6. ሕዝቅያስ የሰበሰባቸው የሰሎሞን ምሳሌዎች (ም25-29)
7. የአጉር ምሳሌዎች ወይም አባባሎች (ም30)
8. የንጉሥ ልሙኤል አባባሎች (31፥1-9)
9. መደምደሚያ፤ መልካም አርአያ የምትሆን ሚስት (31፥10-31)

## መግቢያ የምሳሌዎቹ ዐላማና ጭብጥ

1 የእስራኤል ንጉሥ፣ የዳዊት ልጅ
የሰሎሞን ምሳሌዎች፤
2 ጥበብንና ተግሣጽን ለመቀበል፤
ጥልቅ ሐሳብ የሚገልጡ ቃላትን
ለማስተዋል፤
3 ጽድቅን፣ ፍትሕንና ሚዛናዊ ብያኔን
በማድረግ፣
የተገራ ጠቢብ ልቦናን ለማግኘት፤
4 ብስለት ለሌላቸው አስተዋይነትን፣
በዕድሜ ለጋ ለሆኑት ዕውቀትንና
ልባምነትን ለመስጠት፤
5 ጥበበኞች ያድምጡ፤ ትምህርታቸውንም
ያዳብሩ፤
አስተዋዮችም መመሪያ ያግኙበት፤
6 ይህም የጠቢባንን ምሳሌዎችንና
ተምሳሌቶችን፣
አባባሎችንና ዕንቆቅልሾችን ይረዱ
ዘንድ ነው።
7 እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት
መጀመሪያ ነው፤
ተላሎች[ሀ] ግን ጥበብንና ተግሣጽን
ይንቃሉ።

## ጥበብን ገንዘብ ለማድረግ የተሰጠ ምክር

8 ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ምክር አድምጥ፤
የእናትህንም ትምህርት አትተው።
9 ለራስህ ሞገስን የሚያጐናጽፍ አክሊል፣
አንገትህን የሚያስውብ ድሪ
ይሆንልሃል።
10 ልጄ ሆይ፤ ኀጢአተኞች ቢያባብሉህ፣
እሺ አትበላቸው፤
11 "ከእኛ ጋር ናና፣
ደም ለማፍሰስ እናድባ፤
በደል በሌለበት ሰው ላይ እንሸምቅ፤
12 እንደ መቃብር፣ ወደ ጒድጓድ[ለ]
እንደሚወርዱ፣
ከነሕይወታቸው እንዳሉ እንዋጣቸው፤
13 ውድ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ በያይነቱ
እናገኛለን፤
ቤቶቻችንንም በዝርፊያ እንሞላለን፤
14 ከእኛ ጋር ዕጣህን ጣል፤
የጋራ ቦርሳ ይኖረናል" ቢሉህ፣
15 ልጄ ሆይ፤ አብረሃቸው አትሂድ፤
በሚሄዱበትም መንገድ እግርህን
አታንሣ፤
16 እግራቸው ወደ ኀጢአት ይቸኵላል፤
ደም ለማፍሰስም ፈጣኖች ናቸው።
17 ወፎች ፊት እያዩ ወጥመድ መዘርጋት፣
ምንኛ ከንቱ ነው!

1፥1 1ነገ4፥29-34፤ ምሳ10፥1፤25፥1፤መክ 1፥1፤ማቴ13፥3
1፥4 ምሳ8፥5:12
1፥5 ምሳ9፥9
1፥6 ዘኍ12፥8፤መሳ 14፥12፤መዝ49፥4፤ ምሳ22፥17፤24፥23፤ ማቴ13፥10-17
1፥7 ዘፀ20፥20፤ዘዳ 4፥6፤ኢዮ23፥15፤መዝ 34፥4-22፤112፥1 ፤ምሳ8፥33-36፤9፥7-9 :10፤12፥1፤13፥18:19 ፤15፥32:33፤ኢሳ33፥6 ፤50፥10፤59፥19፤ኤር 8፥9
1፥8 ቍ8-9፤ዘዳ 21፥18፤ምሳ2፥1፤3፥1፤ 4፥1፤5፥1፤6፥1:20፤7፥ 1፤19፥27፤22፥17፤23 ፥26-28፤ኤር35፥8
1፥9 ምሳ3፥21-22፤ 4፥1-9
1፥10 ቍ15፤ዘዳ13፥8 ፤ኢዮ24፥15፤መዝ1፥1 ፤ምሳ16፥29
1፥11 መዝ10፥8
1፥12 ቍ16-18፤ ኢዮ33፥18፤መዝ30፥3 ፤35፥25
1፥14 ቍ19
1፥15 ዘኍ49፥6፤መዝ 119፥101፤ምሳ4፥14
1፥16 ኢዮ15፥31፤ ምሳ 6፥18፤ኢሳ59፥7

[ሀ] 7 በመጽሐፈ ምሳሌና በብሉይ ኪዳን ሌሎች መጻሕፍት ውስጥ *ተላላ* የሚለው በተደጋጋሚ ተጽፏል፤ ይህም የሞራል ጒድለትን ያመለክታል።

[ለ] 12 በዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል።

1፥1 *ምሳሌዎች፤* ምሳሌ አጭርና ድድርነት ያለው፣ ንጽጽር ወይም ጥያቄ ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ስለ ሰው ባሕርይ መሠረታዊ መርሕን ወይም አስተውሎትን የሚገልጽ አባባል ነው። እነዚህ ምሳሌዎች ሰዎች ሁሉ ኀጢአት ከሚያስከት ለው አሳዛኝ ውድቀት እንዲተርፉ፣ እግዚአብሔርን በማስደሰት የተቃና ሕይወት እንዲኖራቸው ያስተምራሉ (ቍ2-6:15-19)። *ሰሎሞን፤* ጥበቡ፣ ምሳሌዎቹና መዝሙሮቹ ምን ያህል ብዙ እንደ ሆኑ በነገ4፥32 ተጠቅሶአል፤ ስሙም በ10፥1 እና ከማሕ1፥1 ጋር ያነጻጽሩ።

*1፥2-4፤* ቍ2-3 ልጅን ወይም ተማሪን ሲያመለክት፣ ቍ4 ደግሞ አባትን ወይም መምህርን ያመለክታል።

1፥2 *ጥበብ፤* የመጽሐፈ ምሳሌ ቍልፍ የሆነው ይህ ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል። የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ከሥነ ምግባር ውድቀት ተጠብቆ የመኖር ብልኀትን ያመለክታል። የእጅ ባለሙያ የሆነ ሰው ጥበበኛ ወይም ብልኀተኛ ሊባል ይችላል (ዘፀ31፥3)። ምሳሌዎች፣ ሰው ጥበብን ያገኝ ዘንድ ያደፋፍራሉ (4፥5)፤ ጥበብ ከብር ወይም ከዕንቍ የላቀ ነውና (3፥13-14)። አዲስ ኪዳን ክርስቶስን፣ "ከእግዚአ ብሔር የሆነ ጥበብ" ይለዋል (1ቆሮ1፥30 ይመ፤ ከቈላ2፥3 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥3 *ጽድቅን፣ ፍትሕንና ሚዛናዊ ብያኔን፤* 2፥9 ይመ።

1፥4 *አስተዋይነት፤* ሚዛናዊ ፍርድን ወይም ማስተዋልን ያመለክታል (15፥15፤ 19፥25 ይመ)። ይህ ቃል በዕብራይስጡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ውጭ አሉታዊ በሆነ እሳቤ፣ "ጮሌነትን" ወይም "አታላይነትን" ለማመልከት ይውላል (ዘፍ3፥1፤ ኢዮ5፥3)። *ብስለት ለሌላቸው፤* በመጽሐፈ ምሳሌ ብዙ ጊዜ የተጠቀሰ ሌላው ቍልፍ ቃል ነው፤ ይህም በቀላሉ ወደ አንድ ሐሳብ የሚመሩ ትንና "የማመዛዘን ችሎታ" የሌላቸውን (9፥4:16)፣ ያልበሰሉትን፣ ልምድ የሌላቸውንና ቂላቂል የሆኑትን ያመለክታል (ከመዝ 19፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥6 *ዕንቆቅልሾች፤* በዕብራይስጥ ይህ ቃል አንዳንድ ጊዜ ተራ ዛሚ ተለዋዋጭ ዘይቤን ያመለክታል (ከሕዝ17፥2 ጋር ያነጻጽሩ)

*1፥7፤* የዚህ መጽሐፍ መሪ ሐሳብ ነው (9፥10፤ 31፥30 ይመ፤ በኢዮ 28፥28፤ ከመዝ 110፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *እግዚአብሔርን መፍራት፤* በፍቅር እግዚአብሔርን በማክበር ሲሆን ይህም ጌትነቱን ተቀብሎ መኖርንና ለቃሉ መታዘዝን ያካትታል (መክ 12፥13)። እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው (ሚል 1፥14)፤ በእርሱ ፊት በፍርሀትና በአክብሮት በምንቆምበት ጊዜ እንኳ ሐሴት እናደርጋለን (መዝ 2፥11፤ ኢሳ 12፥6 ይመ)። *ተላሎች፤* ዕውቀትንና ተግሣጽን ሁሉ የሚጠሉ (ቍ 22፤ 12፥1) ለጠብም የሚጣደፉና ለቍጣቸው ገደብ የማያበጁለት (20፥3፤ 29፥11)፣ ቸልተኞችና (ቍ32)፣ እግዚአብሔርን መታመኛ ከማድረግ ይልቅ (መዝ 14፥1) በራሳቸው የሚታመኑ (28፥26) ናቸው። *ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ፤* 5፥12 ማብ ይመ።

*1፥8፤* አንድ አባት ልጁን ለዚህ ዓለም ሕይወት ለማዘጋጀት በቤት ውስጥ ያለውን ሚና የሚያሳይ ሲሆን፣ በዚህ መጽሐፍ ላለው ትምህርታዊ ንግግር የታወቀ መግቢያ ነው። በዚህና በ6፥20 ላይ እናትም እንደ አስተማሪ ትቈጠራለች።

1፥9 *ሞገስን የሚያጐናጽፍ ... የሚያስውብ፤* ጥበብን የሚከታተሉ ውበትንና ክብርን በሕይወታቸው ላይ ይደርባሉ።

1፥11 *ደም ለማፍሰስ እናድባ፤* ደም እስከ ማፍሰስ የሚያደርሳቸው እንኳ ቢሆን በስርቆትም ይሁን በጭቆና (ቍ13፥19) ዓላማቸው ራሳቸውን ማበልጸግ ነው። ጸሐፊው በዚያ ባሕል አንድን ወጣት የሚያጋጥሙትን ሁለት ዐበይት ማታለያዎች የከንቱ ሕይወት ምሳሌ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል፤ እነርሱም:- (1) ሌሎችን በመበዝበዝ ሀብትን ማከማቸት፣ (2) የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን በማያከብሩ ጋለሞታ ሴቶች በመጠመድ፣ ሕገ ወጥ በሆነ ሩካቤ ሥጋ ርካታን ለማግኘት መሞከር ናቸው (5፥1-6፤ 6፥24፤ 7፥5 ይመ፤ ከ2፥12-19 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥12 *እንደ መቃብር ... እንዋጣቸው፤* ያለ ገደብ ሰዎቹን የሚያሠቃዩትን ወንጀለኞች ለመግለጽ የገባ ቅኔያዊ ምስያ ነው።

1፥13 *ውድ ... ነገሮችን፤* ሰው፣ በየትም ሥፍራ የማይገኘውን ሀብትና ደስታ ከጥበብ እንደሚያገኝ መጽሐፈ ምሳሌ በንጽጽር ያስተምራል (3፥14-16፤ 16፥16፤ እንዲሁም ኢዮ 28፥12-19 ይመ)።

1፥15 *መንገድ፤* በ2፥8፤ 7፥25 ከተመለከተው ወደ ጥፋት ከሚመራው ከአመንዝራዪቱ ሴት መንገድ ጋር ያነጻጽሩ።

1፥16 በዚህ ቍጥር የቀረበው ሐሳብ ከኢሳ 59፥7 የመጀመሪያ ሁለት መሥመሮች ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፣ በሮሜ 3፥15 ላይም በከፊል ተጠቅሶአል፤ ከምሳ6፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥17 *ወጥመድ፤* ወፎችንና እንስሳት ለማጥመድ ያገለግል

18እነዚህ ሰዎች የሚያደቡት በገዛ ደማቸው
ላይ ነው፤
የሚሸምቁትም በራሳቸው ላይ ብቻ
ነው::
19ያላግባብ ለጥቅም የሚሯሯጡ ሁሉ
መጨረሻቸው እንዲህ ነው፤
የሕይወታቸው መጥፊያም ይኸው ነው::

**ጥበብን ለሚያናንቁ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**

20ጥበብ በጐዳና ላይ ጮኻ ትጣራለች፤
በየአደባባዩ ድምፅዋን ከፍ ታደርጋለች፤
21ዉካታ በበዛባቸው ጐዳናዎች ላይ*
ትጮኻለች፤
በከተማዪቱም መግቢያ በር ላይ እንዲህ
ትላለች፤
22"እናንት ብስለት የሌላችሁ** ማስተዋል
የሌለበት መንገዳችሁን እስከ መቼ
ትወዳላችሁ?
ፌዘኞች በፌዝ ደስ የሚሰኙት፣
ሞኞችስ ዕውቀትን የሚጠሉት እስከ
መቼ ነው?
23ዘለፋዬን ብትሰሙኝ ኖሮ፣
ልቤን ባፈሰስሁላችሁ፣
ሐሳቤንም ባሳወቅኋችሁ ነበር::
24ነገር ግን በተጣራሁ ጊዜ እምቢ
ስላላችሁኝ፣
እጄንም ስዘረጋ ማንም ግድ
ስላልነበረው፣
25ምክሬን ሁሉ ስለ ናቃችሁ፣
ዘለፋዬንም ስላልተቀበላችሁ፣
26እኔ ደግሞ በመከራችሁ እሥቅባችኋለሁ፤
መዓት በሚወርድባችሁም ጊዜ
አፌዝባችኋለሁ፤
27መዓት እንደ ማዕበል ሲያናውጣችሁ፣
መከራም እንደ ዐውሎ ነፋስ
ሲጠራርጋችሁ፣
ሥቃይና ችግር ሲያጥለቀልቃችሁ
አፌዝባችኋለሁ::
28"በዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፤ እኔ ግን
አልመልስላቸውም፤
አጥብቀው ይፈልጉኛል፤ ነገር ግን
አያገኙኝም::
29ዕውቀትን ስለ ጠሉ፣
እግዚአብሔርንም መፍራት
ስላልመረጡ፣
30ምክሬን ለመቀበል ስላልፈለጉ፣
ዘለፋዬን ስለ ናቁ፣
31የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፤
የዕቅዳቸውንም ውጤት ይጠግባሉ::
32ብስለት የሌላቸውን ስድነታቸው
ይገድላቸዋል፤
ተላሎችንም ቸልተኝነታቸው
ያጠፋቸዋል፤
33የሚያዳምጠኝ ሁሉ ግን በሰላም ይኖራል፤
ክፉን ሳይፈራ ያለ ሥጋት ይቀመጣል::"

*21 በዕብራይስጡና በሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች *በቅጥሮች ጫፍ ላይ* ይላሉ::
**22 በዕብራይስጡ *ብስለት የሌለው* የሚለው ቃል በዚህ መጽሐፍ በአጠቃላይ መልካም ምግባር የሌለውንና ክፋትን ለማድረግ ልቡ ያዘነበለ ሰውን ያመለክታል::

1፥18 ቍ11-12 ፤መዝ71፥10
1፥19 ቍ13-14፤ ምሳ4፥14-17፤11፥19
1፥20 ኢዮ28፥12፤ ምሳ7፥10-13፤9፥1-3 ፡13-15
1፥22 መዝ50፥17፤ ምሳ 6፥32፤7፥7፤8፥5 ፤9፥4፡16
1፥24 1ሳሙ8፥19፤ ኢሳ65፥12፤66፥4፤ ኤር7፥13፤26፥5፤35፥17፤36፥31
1፥26 ቍ33፤ዘዳ28፥63 ፤2ነገ19፥21፤መዝ2፥4፤59፥8
1፥27 መዝ18፥18፤ ምሳ5፥12-14
1፥28 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ኢዮ27፥9፤ ምሳ8፥17፤ኤር 11፥11፤ሕዝ8፥18፤ ሆሴ5፥6፤ዘካ7፥13
1፥29 ኢዮ21፥14
1፥30 ቍ25
1፥31 2ዜና36፥16፤ መዝ14፥14፤ኤር6፥19 ፤14፥16፤21፥14፤30፥15
1፥32ምሳ5፥22፤15፥10፤ኢሳ66፥4
1፥33 ቍ21-26፤ዘኍ 24፥21፤ዘዳ33፥28፤ ምሳ3፥23፤መዝ112፥8

ነበር (6፥5፤ 7፥23፤ መክ 9፥12፤ ኢሳ51፥20፤ኤር 5፥26 ይመ)::

1፥18 *የሚሸምቁትም በራሳቸው ላይ ብቻ፤* ክፉዎች ሳያስቡት በራሳቸው ላይ ማሰናከያ ወጥመድ ይዘረጋሉ (29፥6፤ መዝ 35፥8)፤ ከዚህም የተነሣ የወፎችን ያህል እንኳ ለራሳቸው አይጠነቀቁም (7፥22-23 ይመ):: በኢሳ17፥14 እንደ ተመለከተው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚመዘብሩት ሰዎች ዕጣ ፈንታ የዘላለም ጥፋት ነው::

*1፥19፤* ከኢሳ 17፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በአጕል መንገድ የሚገኘውን ትርፍ የሚጠላ ሰው የሚኖረውን የደስታ ሕይወት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (28፥16)

1፥20 *ጥበብ ... ጮኻ ትጣራለች፤* ከዚህ ላይና በ3፥15-18፤8፤9፥1-12 ባለው ክፍል ውስጥ ጥበብ እንደ ሰው ሆና ቀርባለች:: ይህ ቅኔያዊ አገላለጽ በትንቢተ ኢሳይያስም ላይ የተለመደ ነው (ከ55፥12፤ 59፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: *በየአደባባዩ፤* ዙሪያዋን በግንብ በታጠረች ከተማ ውስጥ የሚገኝ አደባባይ ነው::

1፥21 *መግቢያ በር፤* የከተማዋ አለቆች ችሎት የሚቀመጡበትና (31፥23፤ ሩት 4፥11፤ ኢዮ 29፥7 ይመ) ገበያው የሚገኝበት ቦታ ነው (2ነገ 7፥1):: አንድ ወጣት በማኅበረሰብ ውስጥ ገብቶ ሕይወቱን መምራት ሲጀምር ታማኝ ለማድረግና ሕይወቱን ለመቅረጽ የሚሹ ሁለት ድምፆች ያባብሉታል፤ የመጀመሪያው የጥበብ ድምጽ ሲሆን፣ ይህም ጥበብን በሚያስተምሩ መምህራን ዘንድ ተደጋግሞ ይሰማል:: ሁለተኛው ደግሞ የከንቱ ዎች ድምፅ ነው፤ ይህም በቍ10-14 በተመለከቱት ኀጢአተኞችና በ5፥3፤ 6፥24፤ 7፥5 ላይ በተጠቀሱት ዘማውያት ሕይወት እውን ሆኖ ታይቷል:: ስለዚህ አንድ ወጣት በሕይወት ጕዞው ውስጥ ክፉውን ከደጉ ለይቶ ማየትን መለማመድ ይኖርበታል:: እዚህ ላይ በምዕራፍ 8-9 ጥበብ የጥሪ ድምጿን ታሰማለች፤ በተፈጥሮ ሥርዐት መሠረት የጋራ የሆነው የሰው ልምድ በተከማቸበት በከተማው እምብርት ሆና (11፥10 እና ማብ ይመ) ትናገራለች:: ቅዱሳንና እውነተኛ ጥበበኞች ከእምነት አኳያ የሰውን ልምድ በመፈተን፣ ከዚያም በመጽሐፈ ምሳሌ እንደታየው ጥበብ በተሞላበት ትምህርታቸው የመለኮትን ጥበብ በሰው አንደበት የሚገልጹትም በዚሁ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው::

1፥22 *ፌዘኞች፤* ትዕቢተኞችና ትምክሕተኞች የሆኑ (21፥24)፣ ስድብን፣ ጥላቻንና ጠብን የተሞሉ (9፥7-8፤ 22፥10፤ 29፥8)፣ ለግርፋት የሚያበቃ በደል ቢኖርባቸውም እንኳ (19፥25፤ 21፥11) መታረምን የማይፈልጉ ናቸው (13፥1፤15፥12)::

1፥23 *ልቤን ባፈሰስሁላችሁ፤* ጥበብ እንደ ምንጭ ናት፤ ቃሏ ዘወትር ያድሳል ያበረታልም (18፥4 ይመ)::

1፥24 *እምቢ ስላላችሁኝ፤* የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን (ኢሳ 1፥4፤ 5፥24) የኢየሩሳሌም ሕዝብ ደግሞ ኢየሱስን እንደ ተዉት (ማቴ23፥37):: *እጄንም ስዘረጋ፤* እግዚአብሔር ቀኑን ሙሉ እምቢተኞች ወደ ሆኑት ሰዎች እጁን መዘርጋቱን የሚያሳየው ክፍል (ኢሳ65፥2)፣ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

1፥25 *ምክሬን ሁሉ ስለ ናቃችሁ፤* ከ8፥33 ጋር ያነጻጽሩ::

1፥26 *በመከራችሁ እሥቅባችኋለሁ፤* በጥበብ ላይ በመጣቅ በራሳቸው ላይ መከራን ለሚጋብዙት ሞኞች ምላሽ መስጠቱን እንጂ፣ ርኅራኄ የለሽ መሆኑን አያመለክትም:: በእርሱ ላይ ማመጽ የሚችሉ ለሚመስላቸው ነገሥታት ጌታ የሰጠውን መልስ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (መዝ2፥4):: *መዓት በሚወርድባችሁም ጊዜ፤* የክፉና የጨካኝ ሰው ዕድል ፈንታም ይኸው ነው (6፥12-15)::

1፥27 *እንደ ማዕበል፤* 10፥25 ይመ:: *እንደ ዐውሎ ነፋስ፤* የኢዮብ ልጆች በብርቱ ነፋስ በተገደሉ ጊዜ (ኢዮ1፥19) አጽናኞቹ የመከራው መንሥኤ የእርሱ በደል እንደነበረ ደመደሙ (ኢዮ18፥5፡12):: *ሥቃይና ችግር፤* ኢሳ8፥22 ይመ::

1፥28 *እኔ ግን አልመልስላቸውም፤* የእስራኤል ሕዝብ ኀጢአት በሠሩ ጊዜ እግዚአብሔር ሊሰማቸው ፈቃደኛ አልነበረም (ዘዳ1፥45፤ኢሳ1፥15):: *አያገኙኝም፤* ጥበብን የሚያገኙ ግን ሕይወትንና በረከትን ያገኛሉ (ቍ32፤3፥13፤8፥17፡35 ይመ)::

1፥29 *እግዚአብሔርንም መፍራት፤* የቍ7 ማብ ይመ::

1፥31 *ይበላሉ ... ውጤት ይጠግባሉ፤* የሚያገኙት የእጃቸውን ነው (18፥20፤ 31፥31፤ ኢሳ3፥10):: "ማንም ሰው የዘራውን ያጭዳልና" (ገላ6፥7)::

1፥32 *ቸልተኝነታቸው፤* ባዶ የሆነ ነገር ላይ መተማመንና መዘናጋት (ኢሳ32፥9፤ አሞ6፥1፤ ሶፎ1፥12 ይመ)::

1፥33 *በሰላም ... ያለ ሥጋት፤* የእግዚአብሔር ጥበቃ ያለ

## ከጥበብ የሚገኝ በረከት

2 ልጄ ሆይ፤ ቃሌን ብትቀበል፣
ትእዛዜንም በልብህ ብታኖር፣
[2]ጆሮህን ወደ ጥበብ ብታቀና፣
ልብህንም ወደ ማስተዋል ብትመልስ፣
[3]እንዲሁም የመለየት ጥበብን ብትማጠን፣
ድምፅህን ከፍ አድርገህ ማስተዋልን
ብትጣራ፣
[4]እርሷንም እንደ ብር ብትፈልጋት፣
እንደ ተሸሸገ ሀብት አጥብቀህ ብትሻት፣
[5]በዚያን ጊዜ ፈሪሃ እግዚአብሔርን
ትረዳለህ፤
ስምሳክንም ማወቅ ታገኛለህ፡፡
[6]እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤
ከአንደበቱም ዕውቀትና ማስተዋል
ይወጣል፡፡
[7]እርሱ ለቅኖች ድልን ያከማቻል፤
ያለ ነቀፋ ለሚሄዱትም ጋሻ
ይሆናቸዋል፤
[8]የፍትሕን መንገድ ይጠብቃል፤
የታማኞቹንም አካሄድ ያጸናል፡፡
[9]በዚያን ጊዜ ጽድቅን፣ ፍትሕን፣
ሚዛናዊነትን፣
መልካሙንም መንገድ ሁሉ ትገነዘባለህ፤
[10]ጥበብ ልብህ ውስጥ ትገባለችና፤
ዕውቀትም ነፍስህን ደስ ታሰኛለች፤
[11]የመለየት ችሎታ ይጋርድሃል፤

2፥1 ምሳ 1፥8
2፥2 መዝ22፥17፤ 23፥12
2፥3 ያዕ1፥5
2፥4 ኢዮ3፥21፤ ማቴ13፥44
2፥5 ዘዳ4፥6
2፥6 ኢዮ9፥4፤12፥13 ፤22፥22፤መዝ 119፥34
2፥7 ዘፍ6፥9፤15፥1 ፤መዝ84፥11፤ምሳ30፥5-6
2፥8 1ሳሙ2፥9፤ መዝ18፥25፤97፥10
2፥9 ዘዳ1፥16
2፥10 ምሳ14፥33
2፥11 ምሳ4፥6
2፥12 ቍ16፤ምሳ 3፥13-18፤4፥5
2፥13 ምሳ4፥19
2፥14 ምሳ10፥23፤ 15፥21
2፥15 መዝ125፥5፤ ምሳ21፥8
2፥16 ምሳ5፥1-6፥20- 29፤7፥5-27
2፥17 ሚል2፥14
2፥18 ምሳ5፥5፤ 7፥27፤9፥18
2፥19 ምሳ3፥16-18፤ 5፥8፤መክ7፥26
2፥21 መዝ37፥29
2፥22 ዘዳ 28፥63፤ 29፥28፤ኢዮ18፥17፤

ማስተዋልም ይጠብቅሃል፡፡
[12]ጥበብ ንግግራቸው ጠማማ ከሆነ ሰዎች፣
ከክፉዎችም መንገድ ታድንሃለች፤
[13]እነዚህም በጨለማ መንገድ ለመሄድ፣
ቀናውን ጐዳና የሚተዉ ናቸው፤
[14]ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው፣
በክፉት ጐዳና ሐሤት የሚያደርጉ፣
[15]መንገዳቸው ጠማማ፣
በአካሄዳቸው ጠመዝማዞች ናቸው፡፡
[16]ከአመንዝራ ሴትም ትጠብቅሃለች፤
በአንደበቷም ከምታታልል ዘልዛላ
ታድንሃለች፤
[17]ይህችም የልጅነት ባሏን የተወች፣
በስምሳኳ ፊት የገባችውን ኪዳን*
ያቃለለች ናት፡፡
[18]ቤቷ ወደ ሞት ያደርሳል፤
መንገዷም ወደ መናፍስተ ሙታን
ያመራል፡፡
[19]ወደ እርሷ የሚገባ ማንም አይመለስም፤
የሕይወትንም መንገድ አያገኝም፡፡
[20]አንተም በደጋግ ሰዎች ጐዳና ትሄዳለህ፤
የጻድቃንንም መንገድ ይዘህ ትጓዛለህ፡፡
[21]ቅኖች በምድሪቱ ይቀመጣሉና፤
ነቀፋ የሌለባቸውም በእርሷ ላይ ጸንተው
ይኖራሉ፡፡
[22]ክፉዎች ግን ከምድሪቱ ይወገዳሉ፤

*17 ወይም የአምላኳን ኪዳን

በትን ቦታ ይገልጣሉ (ኢሳ32፥18፤ ሕዝ34፥27 ይመ)፡፡

2፥1 *በልብህ ብታኖር፤* ወጣቶች የእግዚአብሔርን ቃል በልባቸው በማኖር ከኀጢአት ይርቁ ዘንድ መዝሙረኛው እንዳበረታታቸው (መዝ119፥111)፡፡

2፥2 *ጆሮህን ... ብታቀና፤* እዚህ ላይ መስማት መታዘዝን ያመለክታል (ኢሳ55፥3፤ኤር13፥15)፡፡ *ልብህንም፤* በ4፥21 እና በ1ነገ3፥9 ላይ "ልብ" ሲባል ማስተዋልን ይመለከታል (ኢዮ 12፥3 ይመ)፡፡

2፥4 *ብር ... ተሸሸገ ሀብት፤* ኢዮ 28፥1-11 ጥንታዊውን የማዕድን አፈላለግ ዘዴ፣ ከጥበብ ፍለጋ ጋር በማነጻጸር (ኢዮ 28፥12 ይመ) ጥበብ እንዴት እንደሚበልጥ ይገልጻል፡፡

2፥5 *ፈሪሃ እግዚአብሔርን፤* የ1፥7 ማብ ይመ፡፡ *አምላክንም ማወቅ፤* እግዚአብሔር እኔነት ያለው አምላክ እንደ ሆነ ማስተዋልንና (ፊል3፥10)፣ የሚያስተምረን ትምህርትም ምን እንደ ሆነ ማወቅን ያመለክታል፡፡ *አምላክ፤* (በዕብራይስጥ፣ "ኤሎሂም" የዘፍ2፥4 ማብ ይመ) ይህ ስያሜ ከዚህ ሌላ በመጽሐፈ ምሳሌ ቍ17፤ 3፥4፤ 25፥2፤ 30፥9 ተጠቅሶአል፡፡

2፥7 *ያከማቻል፤* ትእዛዛቱን በልቡ የሚያኖረውን ማለት ነው (ቍ11)፣ *ጋሻ፤* በመዝ18፥2፡35 ላይም ከድል ጋር ተዛምዶ አል፤ ከ30፥5 ጋር ያነጻጽሩ፡፡ *ያለ ነቀፋ፤* መንፈሳዊና ሞራላዊ ታማኝነት ያላቸውን ያመለክታል፡፡ እንዲህ ሲባል ግን ኀጢአት አልባ መሆንን አያሳይም (19፥1፤ እንዲሁም የኢዮ 1፥1 ማብ ይመ)፡፡

2፥8 *ይጠብቃል ... ያጸናል፤* መዝ91፥3-7፡11-12 ይመ፡፡

*2፥9-11፤* ጌታን የሚያውቁና እርሱ የሚሰጠውን ጥበብ የሚያስተውሉ ምን ዐይነት መንገድ መከተል እንዳለባቸው ያውቃሉ (ከዕብ5፥11-14 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

2፥9 *ጽድቅን፣ ፍትሕን፣ ሚዛናዊነትን፤* 1፥3፤ ፊል4፥8 ይመ፡፡ *መልካሙንም መንገድ፤* በመዝ23፥3 "በጽድቅ መንገድ" የተባለውን ይመ፡፡

2፥10 *ነፍስህን ደስ ታሰኛለች፤* የጥበበኛ ሰው ቃል የሌላውን ሰው ነፍስ "ደስ እንደምታሰኝ" ማለት ነው (16፥24 ይመ)፤ ከ3፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

2፥11 *ይጋርድሃል ... ይጠብቅሃል፤* ታማኝ የሆኑትን እግዚአብሔር እንደሚከልል ማለት ነው (ቍ8)፡፡

*2፥12-19፤* ጠማማ መንገድን እንከተል ዘንድ ሰዎች ከሚያቀርቡት ማታለያ (ቍ12-15)፣ ከአመንዝራዪቱም ማሰናከያ (ቍ16-19) ጥበብ ታድናለች፤ የ1፥11 ማብ ይመ፡፡

2፥12 *ንግግራቸው ጠማማ ከሆነ፤* ከቍ14 ጋር ያነጻጽሩ፡፡ የሰው ንግግር ምን ያህል አታላይ እንደ ሆነ በ8፥13፤ 10፥31-32፤ 17፥20 ላይም ተጠቅሶአል፡፡

2፥13 *በጨለማ መንገድ፤* ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ይወዳሉ (ዮሐ3፥19-21፤ ኢዮ24፥15-16፤ ኢሳ29፥15፤ ሮሜ13፥12 ይመ)፡፡ *ቀናውን ጐዳና፤* 3፥6፤ 9፥15-16 ይመ፡፡

2፥14 *ደስ የሚላቸው፣ በክፉት ... ሐሤት የሚያደርጉ፤* በ1፥10-16 ላይ እንደ ተጠቀሱት ኀጢአተኞች ያሉ ናቸው፡፡

2፥15 *መንገዳቸው ጠማማ፤* ኢሳ59፥7-8 ይመ፡፡

2፥16 *ከአመንዝራ ... ዘልዛላ፤* ይህ አባባል በ5፥20 እና በ7፥5 ላይም ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ አባባሉ ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "እንግዳ" ወይም "ባዕድ" (ከ5፥10 ጋር ያነጻጽሩ) ማለት ነው፤ ምክንያቱም ከሚስት ሌላ የምትወደድ ማንኛውም ሴት ከድንበር ውጪ እንደ ሆነች ጣዖት አምላኪ ባእድ ትቈጠር ነበር፡፡ ከ1ነገ 11፥1 ጋር ያነጻጽሩ፡፡ "ዘልዛላ" የሚለው ቃል በ6፥24 "ምግባረ ብልሹ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ፡፡ *በአንደበቷም ከምታታልል፤* በ6፥24 ላይ "ለስላሳ አንደበት"፣ በ7፥21 ላይም "ለስላሳ ንግግር" ከሚለው ጋር አንድ ነው፤ ከ5፥3 ጋር ያነጻጽሩ፡፡

2፥17 *የልጅነት ባሏን፤* ወጣት ሳለች ያገባችው የትዳር ጓደኛዋን ያመለክታል (ከኢሳ54፥6 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ *በአምላኳ ፊት ... ኪዳን፤* በእግዚአብሔር ፊት የተነገረ የጋብቻ ቃል ኪዳን ሊሆን ይችላል (ሕዝ16፥8፤ ሚል2፥14 ይመ)፡፡ የዚህ ሐሳብ ሌላው አማራጭ ሰባተኛውን ትእዛዝ መተላለፍ ነው (ዘፀ20፥14)፡፡

2፥18 *ወደ ሞት ያደርሳል፤* በ7፥27 መሠረት፣ ቤቷ ወደ መቃብር የሚመራ አውራ ጐዳና ነው፤ ምግባረ ብልሹነትም በእርሱ የተጠመዱትን ሁሉ ወደ ጥፋትና ወደ ሞት ይመራቸዋል (ከ5፥5፤ 9፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ *ወደ መናፍስተ ሙታን፤* ኢዮ 26፥5፤ ኢሳ14፥9፤ 26፥14 እና ማብ ይመ፡፡ በሞት የተለዩት፣ "በሞት ማደሪያ" (7፥27)፣ በመቃብር ውስጥ ይገኛሉ፡፡

2፥21 *በምድሪቱ ይቀመጣሉና፤* እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር ይወርሱ ዘንድ ተስፋ ተሰጥቶአቸው ነበር (ዘፍ17፥8፤ ዘዳ 4፥1)፤ መዝ37፥29፤ ደግሞ፣ "ጻድቁ ምድሪቱን ይወርሳል" ይላል (መዝ 37፥9፡11፤ ማቴ5፥5 ይመ)፤ *ነቀፋ የሌለባቸውም፤* የቍ7ን ማብ ይመ፡፡

2፥22 *ከምድሪቱ ይወገዳሉ፤ ... ከእርሷ ይነቀላሉ፤* በዘዳ 28፥63 ላይ ሕዝቡ ባይታዘዙት ከምድሪቱ እንደሚነቀሉ እግዚ

ታማኝነት የጐደላቸውም ከእርሷ
ይነቀላሉ።

## ከጥበብ የሚገኝ ተጨማሪ በረከት

3 ልጄ ሆይ፣ ትምህርቴን አትርሳ፤
ትእዛዛቴን በልብህ ጠብቅ፤
2 ቀኖችን ይጨምሩልሃል ዓመቶችንም
ያረዝሙልሃል፤
ሕይወት፣ ሀብትንና ሰላምን ያበዙልሃል።

3 ፍቅርና ታማኝነት ከቶ አይለዩህ፤
በዐንገትህ ዙሪያ እሰራቸው፤
በልብህም ጽላት ላይ ጻፋቸው።
4 በዚያን ጊዜ ሞገስንና መልካም ስምን፣
በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ታገኛለህ።
5 በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤
በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤
6 በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤
እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።[a]

7 በራስህ አስተያየት ጠቢብ ነኝ አትበል፤
እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፉም ራቅ።
8 ይህም ለሰውነትህ ጤንነትን፣
ለዐጥንትህም ልምላሜን ያመጣልሃል።

9 እግዚአብሔርን በሀብትህ፣
ከምርትህ ሁሉ በኵራት አክብረው፤
10 ይህን ብታደርግ፣ ጎተራህሞልቶ
ይትረፈረፋል፤
መጥመቂያህም በአዲስ የወይን ጠጅ
ቲፍ ብሎ ይሞላል።

11 ልጄ ሆይ፤ የእግዚአብሔርን
ተግሣጽ አትናቅ፤
በዘለፋውም አትመረር፤
12 አባት ደስ የሚሰኝበትን ልጁን
እንደሚቀጣ[b] ሁሉ፣
እግዚአብሔርም የሚወደውን
ይገሥጻልና።

13 ጥበብን የሚያገኛት፣
ማስተዋልንም ገንዘቡ የሚያደርጋት ሰው
ቡሩክ ነው፤
14 እርሷ ከብር ይልቅ ትርፍ የምታመጣ፣
ከወርቅም ይልቅ ጥቅም የምታስገኝ
ናትና።
15 ከቀይ ዕንቍ ይበልጥ ውድ ናት፤
አንተ ከምትመኘውም ሁሉ
የሚስተካከላት የለም።
16 በቀኝ እጇ ረጅም ዕድሜ አለ፤
በግራ እጇም ሀብትና ክብር ይዛለች።
17 መንገዷ ደስ የሚያሰኝ ነው፤
ጐዳናዋም ሁሉ ሰላም ነው።
18 ለሚያቅፏት የሕይወት ዛፍ ናት፤
የሚይዟትም ይባረካሉ።

መዝ5፥4፤37፥9:28-29፤ምሳ10፥30
3፥1 መዝ44፥17፤ ምሳ1፥8
3፥2 ዘዳ5፥16፤11፥21 ፤30፥15:16፤1ነገ3፥13:14፤ምሳ9፥6:10-11
3፥3 ዘፀ13፥9፤ዘዳ6፥6፤መዝ85፥10፤ምሳ6፥21፤7፥3፤2ቆሮ3፥3
3፥4 1ሳሙ2፥26፤ ሉቃ2፥52
3፥5 መዝ4፥5
3፥6 ኢዮ33፥11፤ መዝ5፥8፤ምሳ16፥3፤ ኢሳ30፥11፤40፥3፤ ኤር42፥3
3፥7 ዘፀ20፥20፤ዘዳ4፥6፤ኢዮ1፥1፤መዝ111፥10፤ምሳ26፥5:12
3፥8 ኢዮ21፥24፤ መዝ38፥3ምሳ4፥22
3፥9 ዘፀ22፥29፤ዘዳ26፥1-15
3፥10 ኢዮ22፥21፤ መዝ144፥13፤ኢል2፥24፤ሚል3፥10-12
3፥11 ኢዮ5፥17፤ ምሳ1፥8-9
3፥12 ዘዳ8፥5፤ኢዮ5፥17፤ምሳ13፥24፤ዕብ12፥5-6፤ራእ3፥19
3፥14 ኢዮ28፥15፤ ምሳ8፥19፤16፥16
3፥15 ኢዮ28፥17-19
3፥16 ዘፍ15፥15፤ 1ነገ3፥13:14 3፥17 ማቴ11፥28-30 3፥18 ዘፍ2፥9፤2፥12፤4፥3-9:8፤8፥17-21፤ምሳ10፥11፤ራእ2፥7

[a] 6 ወይም ጐዳናህን ያቀናልሃል
[b] 12 ወይም እንደሚገሥጽ

አብሔር አስጠንቅቆአል። ክፉ ሰዎችና ልጆቻቸው ይነቀላሉ (መዝ 37፥9:28)።

3፥2 ... *ዓመቶችንም ያረዝሙልሃል፤* እግዚአብሔርን መፍራት (10፥27፤ 19፥23) ለሰውነት ጤንነት ይሰጣል (ቍ8)፤ "የሕይወት ዘመንንም ያረዝማል" (10፥27፤ እና 9፥10-11 ይመ)። *ሀብትንና፤* ሰሎሞን ጥበብን ለማግኘት በጸለየ ጊዜ፣ ትእዛዙን ካከበረ (1ነገ3፥13-14)፣ እግዚአብሔር ሀብትንና ረጅም ዕድሜን እንደሚሰጠው ቃል ገባለት። ብዙውን ጊዜ ጻድቃን ባለ ጠጎችና ደስተኞች ናቸው (12፥21)። ለጊዜው ቢሆንም እንኳ (መዝ 73፥17-19) አንዳንድ ጊዜ ክፉዎች ብርቱዎችና ባለጠጎች ናቸው (መዝ 73፥3:12)። ኢዮብ ም1-2 መከራና ሞት የእግዚአብሔርን ሰው እንደሚፈትኑት ያመለክታል።

3፥3 *በዐንገትህ ዙሪያ እሰራቸው፤* እንደ ውብ ያንገት ጌጥ (ከ1፥9፤ 3፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። *በልብህ ጽላት ላይ ጻፋቸው፤* ኤር 31፥33 ይመ።

3፥4 *ሞገስንና፤* 8፥35፤ ዘፍ6፥8 ይመ። *በእግዚአብሔርና በሰው፤* ሉቃ2፥52፤ ሮሜ12፥17፤ 2ቆሮ8፥21 ይመ።

3፥5 *በፍጹም ልብህ፤* እንደ ካሌብ (ዘኍ14፥24፤ ዘዳ1፥36) ወይም የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነበረው እንደ ንጉሥ ሕዝቅያስ (ኢሳ38፥3)። በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን ያገለግል ዘንድ ዳዊት ሰሎሞንን መከረው (1ዜና28፥9)። *በእግዚአብሔር ታመን፤* በእግዚአብሔር በመታመን ከአደጋ እንደዳኑት የእስራኤል አባቶች (መዝ 22፥4-5)፣ መንገድህን ለጌታ አሳልፈህ ስጥ (መዝ 37፥5)።

3፥6 *እርሱን ዕወቅ፤* እግዚአብሔርን ምንጊዜም አስታውስ፤ በሙሉ ልብና በታማኝነት አገልግለው (1ዜና28፥9፤ ሆሴ4፥1፤ 6፥6 ይመ)። *ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል፤* ከመንገድህ ዕንቅፋትን ያስወግዳል፤ ወዳሰብኸው ዓላማም ይመራሃል (11፥5፤ ኢሳ45፥13 ይመ)።

3፥7 *እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፉም ራቅ፤* "ፍጹምና ቅን" ከነበረው ከኢዮብ ጋር ያነጻጽሩ። (ኢዮ1፥1፤ የ1፥7 ማብ ይመ።

3፥8 *ለዐጥንትህም፤* መላ ሰውነትን ይመለከታል፤ መልካም ዜናና በጎ ቃል ለዐጥንት ጤንነትን እንደሚያመጣ በሌላም ቦታ ተገልጾአል (15፥30፤ 16፥24 ይመ፤ ከ17፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥9 *በኵራት፤* እስራኤላውያን፣ በያመቱ ከሚመረተው የወይራ ዘይት፣ ወይንና እህል በኵራቱን፣ ማለት የመጀመሪያውን እንዲሰጡ ይጠበቅባቸው ነበር (ዘሌ23፥10፤ ዘኍ18፥12-13 ይመ)።

3፥10 *ሞልቶ ይትረፈረፋል፤* ለጌታ ዐሥራቱንና መሥዋዕቱን ለሚያመጡ፣ እርሱ በረከትን አብዝቶ እንዲሰጣቸው ቃል ገብቶአል (ሚል3፥10፤ እንዲሁም ዘዳ28፥8:12፤ 2ቆሮ9፥8 ይመ)።

*3፥11-12፤* ጻድቃን ሁልጊዜ የተሳካ ኑሮ እንዲኖራቸው የሚያስጠነቅቅ ነው (ቍ2 እና የዚያኑ ማብ ይመ)፤ በመከራና በፈተና ጊዜም እግዚአብሔር ያስተምራቸዋል (12፥1፤ ኢዮ5፥17፤ 36፥22፤ መዝ119፥71 ይመ)። ክርስቲያኖች መከራን ይቋቋሙ ዘንድ ለማበረታታት በዕብ12፥5-6 ላይ እነዚሁ ሁለት ጥቅሶች ተጠቅሰዋል (ዕብ12፥7)። "እግዚአብሔር ለእኛ ጥቅም ሲል ይቀጣናል" (ዕብ12፥10)።

3፥12 *አባት ... እንደሚቀጣ፤* እግዚአብሔር 40 ዓመት በምድረ በዳ በመፈተን (ዘዳ8፥2-5)፣ በልጅ የተመሰለውን ሕዝቡን እስራኤልን ቀጣ።

*3፥13-18፤* በዚህ ክፍል ያለው ግጥም፣ "ቡሩክ ነው" በማለት ጀምሮ "ይባረካሉ" በሚለው በመደምደም፣ ጥበብን ያሞግሳል (ከኢዮ5፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥14 *ከብር ይልቅ ትርፍ የምታመጣ ከወርቅም፤* የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ሕግጋት መጠበቅም ይህን ዐይነት በረከት እንደሚያስገኙ መዝሙረኛው በተመሳሳይ ሁኔታ ይገልጻል (መዝ 19፥10፤ 119፥72:127)።

*3፥15-18፤* ጥበብ በሰውኛ ዘይቤ (እንደ ሰው ሆና) ተገልጻለች (የ1፥20 ማብ ይመ)።

3፥15 *ቀይ ዕንቍ፤* በኢዮ 28፥18 ላይ ከጥበብ ያነሰ ክብሬታ እንዳለው ተገልጾአል፤ ልባም ሴት ከዕንቍ ትበልጣለች (31፥ 10)።

3፥16 *ረጅም ዕድሜ፤* የቍ2 ማብ ይመ። *ሀብትና ክብር፤* 8፥18፤ 22፥4 ይመ።

3፥17 *መንገዷ ደስ የሚያሰኝ፤* የ2፥10 ማብ ይመ። *ሰላም፤* በዕብራይስጥ "ሻሎም" የሚባል ሲሆን በቍ2 ላይ 'ተድላ'። ተብሎ ተተርጕሞአል (16፥7፤ መዝ119፥165 ይመ)።

3፥18 *የሕይወት ዛፍ፤* የሕይወት ምንጭ ማለት ነው። ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በቀጥታም ባይሆን በኤደን ገነት የነበረችውን ዛፍ ሳያመለክት አይቀርም (ዘፍ2፥9 እና ማብ ይመ፤ ከምሳ 11፥30፤ 13፥12፤ 15፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

19 *እግዚአብሔር* በጥበብ ምድርን *መሠረተ*፤
በማስተዋል ሰማያትን በየስፍራቸው
አጸና፤
20 በዕውቀቱ ቀላያት ተከፈሉ፤
ደመናትም ጠልን አንጠበጠቡ።
21 ልጄ ሆይ፤ ትክክለኛ ፍርድንና አስተውሎ
መለየትን ጠብቅ፤
እነዚህ ከእይታህ አይራቁ፤
22 ለነፍስህ ሕይወት፣
ለዐንገትህም ጌጥ ይሆናሉ።
23 ከዚያም መንገድህን በሰላም ትሄዳለህ፤
እግርህም አይሰናከልም፤
24 ስትተኛ አትፈራም፤
ትተኛለህ እንቅልፍህም ጣፋጭ
ይሆናል።
25 ድንገተኛን መከራ፣
በክፉዎች ላይ የሚደርሰውንም ጥፋት
አትፍራ፤
26 *እግዚአብሔር* መታመኛህ ይሆናልና፤
እግርህንም በወጥመድ ከመያዝ
ይጠብቃል።
27 ማድረግ እየቻልህ
ለሚገባቸው መልካም ነገር ከማድረግ
አትከልክል።
28 አሁን በእጅህ እያለ፣
ጐረቤትህን፣ "ቈይተህ ተመለስ፤ ነገ
እሰጥሃለሁ" አትበለው።
29 አንተን ተማምኖ በአጠገብህ በተቀመጠ፣
በጐረቤትህ ላይ ክፉ አትምከርበት።

3፥19 ዘፍ1፥31፤ኢዮ 28፥25-27፤መዝ136፥5-9፤ምሳ8፥27-29
3፥21 ምሳ1፥8-9፤ 4፥20-22፤6፥20
3፥22 ዘዳ30፥20፤ ምሳ1፥8-9፤4፥13
3፥23 መዝ37፥24፤ 119፥11፤ምሳ1፥33፤4፥12
3፥24 ዘሌ26፥6፤ኢዮ11፥18፤መዝ91፥5፤ 112፥8፤ኤር31፥26
3፥26 1ሳሙ2፥9፤ 2ነገ18፥5፤ኢዮ4፥6፤5፥19
3፥28 ዘሌ19፥13፤ ዘዳ24፥15፤ሉቃ10፥25-37
3፥29 ዘካ8፥17
3፥31 መዝ37፥1፤ ምሳ24፥1-2
3፥32 ኢዮ29፥4፤ መዝ101፥4
3፥33 ኢዮ5፥3፤መዝ 37፥22፤ምሳ14፥11፤ ዘካ5፥4
3፥34 2ነገ19፥21፤ መዝ18፥25-27፤ 40፥4፤ማቴ23፥12፤ያዕ4፥6፤1ጴጥ5፥5
4፥1 ኢዮ8፥10፤ምሳ 1፥8፤19፥20
4፥4 1ነገ9፥4፤ምሳ 7፥2
4፥5 ምሳ2፥12፤3፥13-18

30 ምንም ጕዳት ሳያደርስብህ፣
ያለ ምክንያት ሰውን አትክሰስ።
31 በክፉ ሰው አትቅና፤
የትኛውንም መንገዱን አትምረጥ፤
32 *እግዚአብሔር* ጠማማን ሁሉ ይጸየፋልና፤
ለቅን ሰው ግን ምስጢሩን
ይገልጥለታል።
33 *የእግዚአብሔር* ርግማን በክፉዎች ቤት
ላይ ነው፤
የጻድቃንን ቤት ግን ይባርካል።
34 እርሱ በዕቡያን ፌዘኞች ላይ ያፌዛል፤
ለትሑታን ግን ሞገስን ይሰጣል።
35 ጠቢባን ክብርን ይወርሳሉ፤
ሞኞችን ግን ለውርደት ያጋልጣቸዋል።

## ጥበብ ከሁሉ በላይ መሆኗ

**4** ልጆቼ ሆይ፤ የአባትን ምክር አድምጡ፤
ልብ ብላችሁ ስሙ፤ ማስተዋልንም
ገንዘብ አድርጉ።
2 በጎ ትምህርት እሰጣችኋለሁ፤
ስለዚህ ትምህርቴን አትተዉ።
3 በአባቴ ቤት ገና ለግላጋ ወጣት፣
ለእናቴም አንድ ልጇ ብቻ በነበርሁ
ጊዜ፣
4 አባቴ እንዲህ ሲል አስተማረኝ፤
"ቃሌን በሙሉ በልብህ ያዝ፤
ትእዛዜንም ጠብቅ፤ በሕይወት
ትኖራለህ።
5 ጥበብን አግኝ፤ ማስተዋልን ያዝ፤
ቃሌን አትርሳ፤ ከእርሷም ዘወር

*3፥19-20፤* በፍጥረት ውስጥ የጥበብ ሚና በይበልጥ የተገለጸው በ8፥22-31 ላይ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በጥበቡ ነው፤ ይህም ጥበብ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሰርፆ ይገኛል። በጥበብ መመራት ጌታን መምሰል ነው፤ እግዚአብሔር ከደነገገው የፍጥረት ሥርዐት ጋርም መስማማት ነው።

3፥19 *ምድርን መሠረተ፤* የዓለም አፈጣጠር ከሕንጻ ግንባታ ጋር ተነጻጽሮአል (1ነገ5፥17፤ 6፥37፤ እንዲሁም 8፥29፤ ኢዮ 38፥4-6፤ መዝ104፥5፤ ዘካ12፥1 ይመ)። *ሰማያትን በየስፍራቸው አጸና፤* ኢሳ 42፥5፤ 51፥16 ይመ።

3፥20 *ተከፈሉ፤* "ተከፈቱ" ማለት ነው። እግዚአብሔር ምንጮችንና ሸለቆዎችን ከፈተ (ዘፍ7፥11፤ 49፥25፤ መዝ74፥15 ይመ)። ከጠፈር በላይና ከጠፈር በታች ያሉትን ውሆች መለየቱን ያመለክታል (ዘፍ1፥7፤ መዝ42፥7 እና ማብ ይመ)። *ጠልን፤* ዝናብንም ጭምር ሳያመለክት አይቀርም (ዘዳ33፥13፤ 2ሳሙ1፥21 ይመ)።

3፥22 *ለዐንገትህም ጌጥ፤* የቍ3ን ማብ ይመ።

3፥23 *በሰላም ... እግርህም አይሰናከልም፤* ከ10፥9 ጋር ያነጻጽሩ።

3፥24 *ስትተኛ አትፈራም፤* እግዚአብሔር በሰጠው ኪዳን በተዘረዘሩት በረከቶች ውስጥ ተገልጦአል (ዘሌ26፥6፤ ኢዮ11፥18-19፤ ሚክ4፥4፤ ሶፎ3፥13 ይመ፤ እንዲሁም ምሳ1፥33 እና ማብ ይመ)። *እንቅልፍህም ጣፋጭ ይሆናል፤* 6፥22፤ መዝ4፥8 ይመ።

3፥25 *ድንገተኛን መከራ ... ጥፋት፤* እግዚአብሔር ቅዱሳንን ከሚያስፈራ ፍላጻና ቀሣፊ በሽታ ይከልላቸዋል (10፥25፤ መዝ91፥3-8፤ ኢዮ5፥21 ይመ። *ክፉዎች፤* 1፥26-27 እና ማብ ይመ።

3፥26 *እግርህንም በወጥመድ ከመያዝ ይጠብቃል፤* በ1፥18 በ7፥22-23 ላይ ማስተዋል የጐደለው ሰው መጨረሻው ምን እንደ ሆነ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

3፥27 *ለሚገባቸው፤* በተለይም ምስኪኖችንና ድኾችን ማለት ነው። *መልካም ነገር ... አትከልክል፤* ሐሥ 9፥36፤ ገላ6፥10፤ 1ዮሐ 3፥17-18 ይመ።

*3፥28፤* ሉቃ11፥5-8፤ ያዕ2፥15-16 ይመ።

3፥30 *ያለ ምክንያት ... አትክሰስ፤* ኢዮ2፥3 ይመ።

3፥31 *በክፉ ሰው፤* በ1፥10-16 ላይ እንደ ተመለከቱት ኀጢአተኞች ማለት ነው (ከ16፥29 ጋር ያነጻጽሩ)። *አትቅና፤* 24፥19፤ መዝ37፥1፡7 ይመ።

3፥32 *ይጸየፋልና፤* በሌላ ቦታ የአሕዛብ የሃይማኖት ሥርዐትና የሥነ ምግባር ጕድለት ምን ያህል አስከፊ እንደ ሆነ የሚገልጽ (ዘዳ18፥9፡12) ቃል ነው፤ በመጽሐፈ ምሳሌም በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል (6፥16፤ 8፥7፤ 11፥20)። *ለቅን ሰው ግን ምስጢሩን ይገልጥለታል፤* ዘፍ18፥17-19፤ ኢዮ29፥4፤ መዝ25፥14፤ ዮሐ15፥15 ይመ።

*3፥33፤* ይህ ንጽጽር በዘዳ11፥26-28 ላይም ይገኛል። *የእግዚአብሔር ርግማን በክፉዎች ቤት ላይ ነው፤* ኢሱ7፥24-25፤ ዘካ5፥3 ይመ። *የጻድቃንን ቤት ግን ይባርካል፤* ኢዮ42፥12-14 ይመ።

3፥34 *በዕቡያን ፌዘኞች፤* የ1፥26 ማብ ይመ። *ሞገስን ይሰጣል፤* ፍቅሩን ይገልጽለታል (ቍ4 ይመ)።

4፥1-4 *ልጆቼ ሆይ፤ የአባትን ምክር አድምጡ፤* ሰሎሞን ስለ እግዚአብሔር መንገድ የተማረው ከአባቱ ነው፤ አሁን ደግሞ እርሱ በበኩሉ ለልጆቹ ምክርን ይሰጣል። እግዚአብሔር፣ ልጆቹ በቅድስና እንዲኖሩና የእርሱን መንገድ እንዲከተሉ ይፈልጋል፤ ይህንም በመጀመሪያ መማር ያለባቸው ከቤተ ክርስቲያን ከሚገበዩት ዕውቀት ብቻ ሳይሆን፣ ወላጆች ከሚሰጡት ትምህርትና በቤት ውስጥ ከሚያሳዩት አርአያነት ነው (ዘዳ6፥7 ይመ)።

4፥3 *ለግላጋ ወጣት፤* ሰሎሞን፣ ገና ወጣት፣ ብዙ የማያውቅ (1ዜና23፥5፤ 29፥1) በነበረበት ጊዜ፣ አባቱ ዳዊት ስለ እርሱ የተናገረውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። ይህ የጥበብ መምህራን አንዳንድ ጊዜ እንደሚያደርጉት የግል ሕይወት ታሪክን የሚገልጽ አጻጻፍ ዐይነት ነው (24፥30-34) እንዲሁም መጽሐፈ መክብብን ይመ። *አንድ ልጇ ብቻ፤* ከዚህም የተነሣ እጅግ በጣም የተወደደ ልጅ ነበር (ከዘፍ37፥3፤ ከዘካ12፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥4 *በሙሉ ልብህ፤* 3፥5 ማብ ይመ።

4፥5 *ጥበብን አግኝ፤ ማስተዋልን ያዝ፤* ጥበብ ገንዘብ ለመሆን የምትችለው አስፈላጊነቷን አስተውሎ ለሚፈልጋት ሰው ነው (8፥17)፤ አስተዋይ ሰው ከትምህርት ዕውቀት ያገኛል (9፥9)፤

አትበል።
6 ጥበብን አትተዋት፤ እርሷም ከለላ
ትሆንሃለች፤
አፍቅራት፤ እርሷም ትጠብቅሃለች።
7 ጥበብ ታላቅ ነገር ናት፤ ስለዚህ ጥበብን
አግኛት፤
ያለህን ሁሉ[*] ብታስከፍልህም ማስተዋልን
ገንዘብህ አድርጋት።
8 ክብርን ስጣት፤ ከፍ ከፍ ታደርግሃለች፤
እቀፋት ታከብርሃለች፤
9 በራስህ ላይ ሞገሳማ አክሊል
ትደፋልሃለች፤
የክብር ዘውድም ታበረክትልሃለች።
10 ልጄ ሆይ፤ አድምጠኝ፤ ቃሌንም
ልብ በል፤
የሕይወት ዘመንህም ትበዛለች።
11 በጥበብ ጐዳና አስተምርሃለሁ፤
ቀጥተኛውንም መንገድ አሳይሃለሁ።
12 ስትሄድ እርምጃህ አይሰናከልም፤
ስትሮጥም አትደናቀፍም።
13 ምክርን አጥብቀህ ያዛት፤ አትልቀቃት፤
ጠብቃት፤ ሕይወትህ ናትና።
14 ወደ ኀጥኣን ጐዳና እግርህን አታንሣ፤
በክፉ ሰዎች መንገድ አትሂድ፤
15 ከዚያ አትድረስ አትንዘበት፤
ሽሸው፤ መንገድህን ይዘህ ሂድ።
16 ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና፤
ሰውን ካላሰናከሉ እንቅልፍ ባይናቸው
አይዞርም።
17 የክፋት እንጀራ ይበላሉ፤
የዐመፅ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ።
18 የጻድቃን መንገድ ሙሉ ቀን እስኪሆን
ድረስ፣
ብርሃኑ እየጐላ እንደሚሄድ የማለዳ
ውጋጋን ነው።
19 የክፉዎች መንገድ ግን እንደ ድቅድቅ
ጨለማ ነው፤
ምን እንደሚያሰናክላቸውም አያውቁም።
20 ልጄ ሆይ፤ የምነግርህን አስተውል፤
ቃሌንም በጥንቃቄ አድምጥ።
21 ከእይታህ አታርቀው፤
በልብህም ጠብቀው፤
22 ለሚያገኘው ሕይወት፤
ለመላው የሰው አካልም ጤንነት ነውና።
23 ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤
የሕይወት ምንጭ ነውና።
24 ጥመትን ከአፍህ አስወግድ፤
ብልሹ ንግግርም ከከንፈሮችህ ይራቅ።
25 ዐይኖችህ በቀጥታ ይመልከቱ፤
ትክ ብለህም ፊት ለፊት እይ።
26 የእግርህን ጐዳና አስተካክል፤[+]
የጸናውን መንገድ ብቻ ያዝ።
27 ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፤
እግርህን ከክፉ ጠብቅ።

## ከአመንዝራነት መጠንቀቅ

5 ልጄ ሆይ፤ ጥበቤን ልብ በል፤
የማስተዋል ቃሌንም በጥሞና
አድምጥ፤
2 ይህም ልባምነትን ገንዘብ እንድታደርግ፣
ከንፈሮችህም ዕውቀትን እንዲጠብቁ
ነው።

[*]7 ወይም *ያገኘኸውን ሁሉ*
[+]26 ወይም *ተመልከት*

4፥6 ምሳ2፥11፤ 2ተሰ2፥10
4፥7 ምሳ23፥23፤ ማቴ13፥44-46
4፥8 ምሳ3፥18
4፥9 ምሳ1፥8-9
4፥10 ዘዳ11፥21፤ መዝ34፥11-16፤ምሳ 1፥8-9
4፥11 1ሳሙ12፥23፤2 ሳሙ22፥37፤መዝ5፥8
4፥12 ኢዮ18፥7፤ ምሳ3፥23
4፥13 ምሳ3፥22
4፥14 መዝ1፥1፤ምሳ 1፥15
4፥16 መዝ36፥4፤ ሚክ7፥3
4፥17 ዘፍ49፥5፤ መዝ73፥6፤መዝ73፥6 ፤ምሳ1፥10-19፤14፥22 ፤ኢሳ59፥6፤ኤር22፥3፤ ዕን1፥2፤ሚል12፥16
4፥18 2ሳሙ23፥4፤ ኢዮ17፥9፤22፥28፤ ዳን12፥3፤ማቴ5፥14፤ ዮሐ8፥12፤ፊል2፥15
4፥19 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ3፥23፤ምሳ2፥13፤ 13፥9፤ኢሳ8፥15
4፥20 መዝ34፥11-16፤ምሳ1፥8-9፤5፥1
4፥21 ምሳ3፥21
4፥22 ምሳ3፥8
4፥23 2ነገ10፥31፤ ምሳ10፥11፤ሉቃ6፥45
4፥25 ኢዮ31፥1
4፥26 ዕብ12፥13
4፥27 ዘሌ10፥11፤ ዘዳ5፥32
5፥1 ምሳ1፥8፤4፥20

ከተግሣጽም ያተርፋል (3፥11) የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ያከብራል (10፥8)፤ የወላጆችንና የሌሎችን በጎ ምክር ይቀበላል (ቍ1፤ 13፥10)፤ ጥበብንም ከብር፣ ከወርቅ፣ ወይም ውድ ከሆነ አልማዝ የላቀ አድርጎ ይቆጥራታል (3፥14-15፤ 23፥23) ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብ በምልአት የተገለጸበት ጌታ ነው (1ቆሮ 1፥30፤ ቈላ2፥2-3)።

4፥6 *አፍቅራት፤* ጥበብን መውደድ ባለጠጋ መሆን ነው (8፥21)፤ እርሷን መጥላትም ሞትን መጋበዝ ነው (8፥36)።

4፥7 *ታላቅ ነገር ናት፤* ወይም "የመጀመሪያ ናት" ማለት ነው (1፥7)። *ያለህን ሁሉ ብታስከፍልህም፤* እጅግ ክቡር የሆነውን ዕንቍ ለመግዛት ያለውን ሁሉ እንደ ሸጠው ነጋዴ (ማቴ 13፥45-46)።

4፥9 *ሞገሳማ አክሊል፤* በደስታ ጊዜ፣ ሰርግ ወይም በዓል ሲሆን፣ የአበባ ጕንጕን ወይም አክሊል ይደረግ ነበር (ሕዝ16፥ 12፤ 23፥42 ይመ)።

4፥10 *የሕይወት ዘመንህም ትበዛለች፤* የ3፥2 ማብ ይመ።

4፥11 *ቀጥተኛውንም መንገድ፤* ቀና የሆነውን መንገድ ማለት ነው (የ3፥6፤ የመዝ23፥3 ማብ ይመ)

4፥12 *ስትሮጥም አትደናቀፍም፤* ከአንዳንድ መሰናክል መኖር ወይም ከብርሃን ዕጦት የተነሣ ነው (ቍ19፤ 3፥23፤ 10፥9፤ መዝ18፥36፤ ኢሳ40፥30-31 ይመ) የሰንፍና ጐዳና ጠማማና ቆሻሻ የተጠራቀመበት ሲሆን፣ የጥበብ ጐዳና ግን ቀጥ ያለና ለስላሳ ነው።

4፥14 *በክፉ ሰዎች መንገድ፤* 1፥15 እና ማብ፤ መዝ1፥1፤ 17፥4-5 ይመ።

4፥16 *ክፉ ካላደረጉ አይተኙምና፤* መዝ36፥4፤ ሚክ2፥1 ይመ፤ ለእግዚአብሔር ቤት፣ ቋሚ የሆነ ቦታ እስኪያገኝ ድረስ ዕረፍት ያልነበረውን የዳዊትን ልብ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (መዝ132፥ 3-5)። በዐመፅ ሥራቸው አንዳች ትርፍ ሳያገኙ ቀኑ ስላለፈባቸው፣ ክፉዎች ሊተኙ አይችሉም።

4፥17 *እንጀራ ይበላሉ ... ጠጅ ይጠጣሉ፤* ምቾት የሚያገኙት ወይም የሚደረጁት በክፋትና በዐመፅ ነው (13፥2፤ ኢዮ 15፥16 ይመ)።

4፥18 *የጻድቃን መንገድ ... ብርሃኑ እየጐላ እንደሚሄድ፤* የእግዚአብሔር መንገድ የሚከተሉ የሚያስፈልጋቸው ጥበቃና ምሪት አላቸው (ቍ11-12 ይመ)፤ ሌሎችንም ወደ ጽድቅ መንገድ ለመምራት ይችላሉ (ዳን12፥3)።

4፥19 *ድቅድቅ ጨለማ፤* ወደ ጥፋት የሚመራ አደገኛ መንገድ ነው (የ2፥13 ማብ፤ እንዲሁም ኢሳ59፥9-10፤ ኤር23፥ 12፤ ዮሐ11፥10፤ 12፥35 ይመ)።

4፥21 *በልብህም፤* 3፥1፡3 ይመ።

4፥22 *ጤንነት፤* የአካልን፣ የስሜትንና የመንፈስን ጤንነት ያመለክታል (3፥8 እና ማብ ይመ)።

4፥23 *የሕይወት ምንጭ፤* በጎ የሆነ ነገር በልባችን ብናኖር (2፥1)፣ ቃላችንና ተግባራችን መልካም ይሆናል፤ "በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና" (ማቴ12፥34 ይመ፤ ከማር7፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥24 *ጥመትን ከአፍህ አስወግድ፤* የ2፥12 ማብ እንዲሁም 19፥1 ይመ። *ብልሹ ንግግርም፤* 6፥12፤ 19፥28፤ ኤፌ4፥29፤ ያዕ 3፥6 ይመ።

4፥25 *ዐይኖችህ በቀጥታ ይመልከቱ፤* ከንቱ የሆነውን ነገር አይመልከቱ ማለት ነው (መዝ119፥37)።

4፥26 ... *ጐዳና አስተካክል፤* ማንኛውንም የመልካም ሥነ ምግባር ዕንቅፋት (ቍ11-12፤ ኢሳ26፥7 ይመ) የሆነውን አስወግድ ማለት ነው።

4፥27 *ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፤* በዘዳ5፥32-33፤ 28፥ 14፤ በኢያ1፥7 ላይም የሚገኝ ማስጠንቀቂያ ነው። *እግርህን ከክፉ፤* 1፥15 ይመ።

*5፥1-6፤* ጥበብ ከዘማዊት ሴት ለመጠበቅ ትረዳለች።

5፥2 *ከንፈሮችህም ዕውቀትን እንዲጠብቁ፤* በትንቢተ ሚል

3 የአመንዝራ ሴት ከንፈር ማር
ያንጠባጥባልና፣
እንደበቷም ከቅቤ ይለሰልሳል፤
4 በመጨረሻ ግን እንደ እሬት ትመራለች፤
ሁለት አፍ እንዳለውም ስል ሰይፍ
ትሆናለች።
5 እግሮቿ ወደ ሞት ይወርዳሉ፤
እርምጃዎቿም በቀጥታ ወደ ሲኦል[ሀ]
ያመራሉ።
6 ስለ ሕይወት መንገድ ደንታ የላትም፤
መንገዶቿ ዘወርዋራ ናቸው፤ ለእርሷ ግን
አይታወቃትም።

7 እንግዲህ፣ ልጆቼ ሆይ፤ አድምጡኝ፤
ከምነግራችሁ ቃል ፈቀቅ አትበሉ።
8 መንገድህን ከእርሷ አርቅ፤
በደጃፏም አትለፍ፤
9 ይኸውም ጉብዝናህን ለሌሎች፣
ዕድሜህንም ለጨካኞች እንዳትሰጥ ነው፤
10 ባዕዳን በሀብትህ እንዳይፈነጥዙ፣
ልፋትህም የሌላውን ሰው ቤት
እንዳያበለጽግ ነው።
11 በዕድሜህ መጨረሻ ታቃሥታለህ፤
ሥጋህና ሰውነትህ ሲከዳህ።
12 እንዲህም ትላለህ፤ "ምነው! ተግሣጽን
ጠላሁ፤
ልቤስ ምነው! መታረምን ናቀ፤
13 የመምህሮቼን ቃል አልሰማሁም፤
አስልጣኞቼንም አላደመጥኋቸውም፤
14 በመላው ጉባኤ ፊት፣
ወደ ፍጹም ጥፋት ተቃርቤአለሁ።"

15 ከገዛ ማጠራቀሚያህ ውሃ፣
ከገዛ ጕድጓድህም የሚፈልቀውን
ውሃ ጠጣ።
16 ምንጮችህ ተርፈው ወደ ሜዳ፣
ወንዞችህስ ወደ አደባባይ ሊፈሱ
ይገባልን?
17 ለአንተ ብቻ ይሁኑ፤
ባዕዳን አይጋሩህ።
18 ምንጭህ ቡሩክ ይሁን፤
በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ።
19 እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ፣ እንደ
ተዋበች ሚዳቋ ናት፤
ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤
ፍቅሯም ሁልጊዜ ይማርክህ።
20 ልጄ ሆይ፤ በአመንዝራ ሴት ፍቅር
ለምን ትሰክራለህ?
የሌላይቱንስ ሴት ብብት ስለምን
ታቅፋለህ?
21 የሰው መንገድ በእግዚአብሔር ፊት
ግልጥ ነውና፤
እርሱ መሄጃውን ሁሉ ይመረምራል።
22 ክፉውን ሰው የገዛ መጥፎ ሥራው
ያጠምደዋል፤

[ሀ]5 ወይም መቃብር

5፥3 መዝ55፥21፤ ምሳ7፥5
5፥4 መክ7፥26
5፥5 መዝ9፥17፤ምሳ 2፥18፤7፥26-27
5፥6 ምሳ9፥13፤ 30፥20
5፥7 ምሳ1፥8-9
5፥8 ምሳ2፥16-19፤ 6፥20-29፤7፥1-27
5፥10 ምሳ29፥3
5፥12 ምሳ12፥1
5፥14 ምሳ1፥24-27፤ 6፥33፤31፥3
5፥18 ዘዳ20፥7፤ምሳ 2፥17፤መክ9፥9፤ማሕ 4፥12-15፤ሚል2፥14
5፥19 ማሕ4፥5፤ 8፥14
5፥21 ኢዮ10፥4፤ 14፥6፤ምሳ15፥3፤መዝ 119፥168፤ኤር29፥23 ፤32፥19፤ዕብ4፥13
5፥22 ዘኍ32፥23፤ ኢዮ18፥9፤መዝ7፥15-16፤መዝ9፥16፤ምሳ1፥ 31-32

2፥7 ላይ 'የካህን ተግባር'። መሆኑ ተገልጾአል።

5፥3 *ከንፈር ማር ያንጠባጥባልና፤* አንዳንዶች መሳሳምን ያመለክታል ቢሉም (መሓ4፥11፤ 5፥13፤ 7፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የዘማዊቱን ሴት ማራኪ ንግግር ሳያመለክት አይቀርም (ከ16፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። *የአመንዝራ ሴት፤* የ2፥16 ማብ ይመ። *ከቅቤ ይለሰልሳል፤* 2፥16 ይመ። እንደበቷ የሚያባብል ነው (መዝ 55፥21 ይመ)፤ ነገር ግን በማታለልና (29፥5) በግብዝነት (መዝ5፥9) የተሞላ ነው።

5፥4 *እሬት፤* እጅግ መራራ ተክል ነው፤ አመንዝራ ማራኪ መስላ ብትታይም እንደ እሬት መራራ ናት።

5፥5 *ወደ ሞት ይወርዳሉ፤* ምግባረ ብልሹ መሆኗ ሕይወቷን በአጭር ያስቀረዋል (የ2፥18 ማብ ይመ)።

5፥6 *መንገዶቿ ዘወርዋራ ናቸው፤* 2፥15፤ 10፥9 ይመ። *አይታወቃትም፤* አታስተውለውም ማለት ነው።

*5፥7-14፤* ከሥነ ምግባር ውጪ መሆን ስለሚያስከትለው ውጤት አባት (መምህር)፣ ልጁን (ተማሪን) ያስጠነቅቃል።

5፥8 *ከእርሷ አርቅ፤* ዘፍ39፥12፤ 2ጢሞ2፥22 ይመ። *በደጃፏም፤* ከ7፥25፤ 9፥14 ጋር ያነጻጽሩ።

5፥9 *ለጨካኞች፤* ቂም ይዞ የሚበቀል ባልን ሳይመለከት አይቀርም (6፥34-35 ይመ)።

5፥10 *ባዕዳን በሀብትህ እንዳይፈነጥዙ፤* ጥበብን ወደሚያከብር ሰው የሚመጣውን ሀብትና ሞገስ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (3፥16-18)። ከሥነ ምግባር ውጪ መሆን ውሎ አድሮ ለቁራሽ እንጀራ እጦት ይዳርጋል (6፥26)።

5፥11 *ሥጋህና ሰውነትህ ሲከዳህ፤* ከሥነ ምግባር ውጪ ከመሆን የተነሣ የሚመጣውን መዘዝ ሊያመለክት ይችላል (1ቆሮ 6፥18 ይመ፤ ከ3፥8፤ ከ4፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህ ይልቅ ግን፣ እርጅናን ተከትሎ የሚመጣውን የዐቅም መዳከም የሚያመለክት ይመስላል።

5፥12 *ተግሣጽን ጠላሁ ... መታረምን ናቀ፤* አንድ ሰው የሽምግልና ዘመኑ ሲደርስ፣ በወጣትነት ዘመኑ ያሳለፈውን ሕይወት ተመልሶ በሚያይበት ጊዜ በስንፍና ጎዳና በመመላሱ ይጸጸታል (1፥7፡22፡29-30 ይመ)።

5፥13 *አልሰማሁም፤* መምህራን የሚሰጡት ትምህርት በጥሞና እንዲደመጥ ደጋግመው ቢያስጠነቅቁም፣ ተቀባይ አላገኙም (1፥8፤ 3፥1፤ 4፥1፤ 5፥1)።

5፥14 *ፍጹም ጥፋት፤* በአካል፣ በንብረትና በማኅበራዊ ሕይወት ረገድ ከጕዳት አፋፍ ላይ መድረሱን ያመለክታል። *በመላው ጉባኤ ፊት፤* ሕግን የተላለፈ ሰው፣ "ለውርደትና ለዱላ" የተጋለጠ ነበር (6፥33)፤ ዐልፎ ተርፎም ሞት ይደርስበት ነበር (ዘዳ22፥22)። ራሳቸውን ለዝሙት አሳልፈው የሚሰጡት ሐዘንና ስደት ይደርስባቸው ዘንድ እግዚአብሔር ወስኖአል፤ ይኸውም በሁለት ረገድ ነው፤ ትዳራቸው ይፈርሳል፤ በግል ሕይወታቸውም ሥቃይ ይደርስባቸዋል (ቈላ3፥5 ይመ)። ቅድመ ጋብቻ ሩካቤ ሥጋ መፈጸምና ለጋብቻ ቃል ኪዳን ታማኝ አለመሆን፣ የማያመልጡት ጦስ ማስከተሉ አይቀርም (ቍ5፥11)፤ ጅማሬው ጣፋጭ የመሰለው ድርጊት (ቍ3)፣ ፍጻሜው መራራ ይሆናል። እግዚአብሔር አይዘበትበትም ሰው ሁሉ የዘራውን ያጭዳል (ገላ 6፥7)።

5፥15 *ከገዛ ማጠራቀሚያህ ... ከገዛ ጕድጓድህም፤* ማሕ 4፥12፡15 ይመ። ውሃ የተጠማ ሰውን እንደሚያረካ ሁሉ፣ ሚስትህ የደስታ ምንጭ ትሁንልህ። የውሃ ጕድጓድና የውሃ ማጠራቀሚያ የግል ይዞታዎች ነበሩ፤ ከፍተኛ ጠቀሜታም ነበራቸው (2ነገ18፥31፤ ኤር38፥6)።

5፥16 *ምንጮችህ ... ወንዞችህስ፤* በቍ15 "ማጠራቀሚያ" "ጕድጓድ"፣ በቍ18 "ምንጭ" ተብለው የተገለጹት ሲሆን፣ 'ሚስትን' ያመለክታሉ (ማሕ 4፥12፡15 ይመ)። *ወደ አደባባይ፤* ባል ታማኝ ሆኖ፣ ካልተገኘ ሚስት ለዝሙት ልትጋለጥ ትችላለች።

5፥18 *ምንጭህ፤* የቍ16 ማብ ይመ። *በልጅነት ሚስትህም፤* ወጣት ሳለህ ያገባሃት የትዳር ጓደኛህ ናት። (የ 2፥17 ማብ ይመ)።

5፥19 *ዋላ ... ሚዳቋ፤* የሚስትን ውበት ይገልጻሉ (ማሕ 2፥9 ይመ)። *ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤* ማሕ7፥7-8 ይመ። *ይማርክህ፤* "ያስደስትህ" ወይም "ያስፈንጥዝህ" እንደ ማለት ነው፤ የጋብቻ ፍቅር ከወይን ይልቅ እንደሚጣፍጥ በማሕ4፥10 ላይ ተገልጾአል (ከማሕ7፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥20 *ለምን ... ?* በትዳር ውስጥ ተድላ መኖሩ ከታወቀና ከትዳር ውጭ የሚደረገው ሩካቤ ሥጋም ፈጽሞ ጥፋትን የሚያስከትል (ቍ14) መሆኑ ግልጽ ከሆነ፣ "ታዲያ በዝሙት ሕይወት ውስጥ መኖር ለምን አስፈለገ?" ማለት ነው።

5፥21 *በእግዚአብሔር ፊት፤* 15፥3፤ ኢዮ31፥4፤ 34፥21፤ ኤር16፥17 ይመ። *መሄጃውን ሁሉ ይመረምራል፤* ኢዮ7፥18፤ 34፥23፤ መዝ11፥4፤ 26፥2፤ 139፥23፤ ኤር17፥10 ይመ።

5፥22 *ያጠምደዋል፤* 1፥18 እና ማብ፤ ዘዳ7፥25፤ 12፥30

የኀጢአቱም ገመድ ጠፍሮ ይይዘዋል።
23 ከተግሣጽ ጒድለት የተነሣ ይሞታል፤
ከተላላነቱም ብዛት መንገድ ይስታል።

## ከተላላነት መራቅ

6 ልጄ ሆይ፤ ለጒረቤትህ ዋስ ብትሆን፣
ስለ ሌላውም ሰው እጅ መትተህ
ቃል ብትገባ፣
2 በተናገርኸው ነገር ብትጠመድ፣
ከአፍህ በወጣውም ቃል ብትያዝ፣
3 ልጄ ሆይ፤ ራስህን ለማዳን ይህን አድርግ፤
በጎረቤትህ እጅ ስለወደቅህ፣
ሂደህ ራስህን አዋርድ፤
ጎረቤትህን አጥብቀህ ነዝንዘው።
4 ዐይኖችህ እንቅልፍ አይያዛቸው፣
ሽፋሽፍቶችህም አያንጐላጁ።
5 ከአዳኝ እጅ እንዳመለጠች ሚዳቋ፣
ከአጥማጅ ወጥመድ እንዳፈተለከች
ወፍ ራስህን አድን።
6 አንተ ታካች፤ ወደ ጒንዳን ሂድ፤
ዘዴውን አስተውለህ ጠቢብ ሁን፤
7 አዛዥ የለውም፤
አለቃም ሆነ ገዥ የለውም፤
8 ሆኖም ግን በበጋ ምግቡን ያከማቻል፤
በመከርም ወቅት ቀለቡን ይሰበስባል።
9 አንተ ታካች፤ እስከ መቼ ትተኛለህ?

5፥23 ኢዮ4፥21፤ 34፥21-25፤ምሳ10፥21፤11፥5
6፥1 ኢዮ17፥3፤ምሳ 1፥8፤11፥15፤17፥18፤ 22፥26-27
6፥4 መዝ132፥4
6፥5 2ሳሙ2፥18፤ መዝ91፥3፤ኢሳ13፥14
6፥6 ቊ6-11፤ምሳ 20፥4
6፥8 ምሳ10፥4፤ 30፥24-25
6፥9 ምሳ24፥30-34 ፤26፥13-16
6፥10 ምሳ24፥33፤ መክ4፥5
6፥11 ቊ10-11፤ ምሳ20፥13፤24፥30-34
6፥13 መዝ35፥19፤ ምሳ16፥30፤ኢሳ58፥9
6፥14 ቊ16-19፤ መዝ140፥2
6፥15 ኢዮ5፥3፤መዝ 55፥15፤ምሳ14፥32፤29፥1
6፥16 ቊ16-19፤ ምሳ 3፥32፤8፥13፤ 15፥8፡9፡26፤16፥5
6፥17 ዘዳ19፥10፤ ኢዮ41፥34፤መዝ10፥5 ፤ምሳ1፥16፤12፥22፤ ኢሳ1፥21፤59፥7፤

ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?
10 ጥቂት ማንቀላፋት፤ ጥቂት ማንጐላጀት፤
እጅን አጣጥፎ "እስቲ ጥቂት ልረፍ"
ማለት፤
11 ድኽነት እንደ ወንበዴ፣
ዕጦትም መሣሪያ እንደ ታጠቀ ሰው[+]
ከተፍ ይልብሃል።
12 ወሮበላና ጨካኝ፣
ነውረኛ አንደበቱን ይዞ የሚዞር፣
13 በዐይኑ የሚጠቅስ፣
በእግሩ ምልክት የሚሰጥ፣
በጣቶቹ የሚጠቊም፣
14 በልቡ ተንኰል ክፋትን የሚያውጠነጥን፣
ምንጊዜም ጠብ ይጭራል።
15 ስለዚህ በቅጽበት መዓት ይወርድበታል፤
በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም።
16 *እግዚአብሔር* የሚጠላቸው ስድስት
ነገሮች አሉ፤
የሚጸየፋቸውም ሰባት ናቸው፤
እነርሱም፦
17 ትዕቢተኛ ዐይን፣
ሐሰተኛ ምላስ፣
ንጹሕ ደም የሚያፈሱ እጆች፣
18 ክፋትን የሚያውጠነጥን ልብ፣
ወደ ክፋት የሚቻኰሉ እግሮች፣

[+]11 *ወይም እንደ ባዘኔ/ እጦት እንደ ለማኝ*

ይመ። በመክ7፥26 ላይ ኀጢአተኛው "ልቧ ወጥመድ በሆነ" ሴት ተጠምዷል። *የኀጢአቱም ገመድ፤* ኢዮ36፥8፤ መክ4፥12፤ ኢሳ 5፥18 ይመ።

*5፥23፤* በ1፥29-32፤ በ7፥21-25 ላይ የሰነፍ አሟሟት በተመሳሳይ መልክ ተገልጾአል፤ ከኢዮ36፥12 ጋር ያነጻጽሩ። *ከተግሣጽ፤* ቊ12 ይመ።

6፥1 *ለጎረቤትህ ዋስ ብትሆን ... እጅ መትተህ ቃል ብትገባ፤* ለሌላ ሰው ዕዳ ዋስ መሆንን (ከ22፥26 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም በሌላ ግዴታ ውስጥ መግባትን ያመለክታል፤ ዕዳውን መክፈል ካልተቻለም፣ ፍጹም ድኽነት ውስጥ ሊያስገባ (ከ22፥27 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም ባሪያ ሊያስደርግ ይችላል። ለምሳሌ ይሁዳ፣ ወንድሙ ብንያም ወደ አባታቸው ወደ ያዕቆብ በደህና እንዲመለስ ኀላፊነት ወስዶ ቃል ገባ (ዘፍ43፥9)፤ ነገር ግን ብንያም ወደ ያዕቆብ በደህና የማይመለስ በመሰለው ጊዜ፣ እርሱ ባሪያ ሆኖ ለዮሴፍ ይገዛ ዘንድ ጥያቄ አቀረበ (ዘፍ 44፥32-33)። እንዲህ ዐይነቱ ድርድር አጋና በመማታት (እጅ በመማታት) ይጸድቅ ነበር (11፥15፤ 17፥18፤ 20፥16፤ 22፥26 ይመ፤ ከኢዮ17፥3 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥2 *ብትጠመድ...ብትያዝ፤* ከቊ5፤ 5፥22 ጋር ያነጻጽሩ።

6፥3 *ራስህን ለማዳን፤* ከኀላፊነት ነጻ መሆን ማለት ነው። *በጎረቤትህ እጅ ስለ ወደቅህ፤* የእርሱን ኀላፊነት ተሸክመሃልና። *አጥብቀህ ነዝንዘው፤* በሉቃ11፥8 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሰው ዕረፍት በመንሣት መላልሰህ ጠይቅ ማለት ነው።

6፥4 *እንቅልፍ አይያዛቸው ... አያንጐላጁ፤* በመዝ132፥4 ላይ ዳዊት እንዳደረገው ማለት ነው።

6፥5 *ወጥመድ ... ወፍ፤* መዝ124፥7 ይመ።

6፥6 *ታካች፤* ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ፍላጎቱም ያልተሟላለት ሰነፍ ሰው ነው (10፥26፤13፥4፤15፥29፤19፥24፤ 22፥13፤24፥30፤26፥13-16 ይመ)። ታካች ወይም ሰነፍ ሰው፦ (1) ሥራውን በወቅቱ የማይጀምር (ቊ9-10 ይመ፤ ከ22፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) የጀመረውን የማይፈጽም (12፥27)፤ (3) ከከባድ ሥራ የሚያመልጥበትን መንገድ የሚፈልግ ነው (2፥4)። ስንፍና ወይም ዋልጌነት ካላመኑት ይልቅ ያመኑትን ይፈታተናል።

6፥7 *አዛዥ የለውም፤* በ30፥27 ላይ ከተጠቀሰው አንበጣ ጋር ያነጻጽሩ።

6፥9 *አንተ ታካች፤' እስከ መቼ ትተኛለህ?* ታካቹ ለእንቅልፍ ያለው ፍቅር በ26፥14 ላይም ተገልጾአል።

*6፥10-11፤* በ24፥33-34 ላይ ተደግሞአል።

6፥11 *ድኽነት ... ዕጦት፤* በ10፥5፤ 19፥15፤ 20፥13 ላይ ከመጠን በላይ ከሆነ እንቅልፍ ጋር የተያያዘ ነው። የድኽነት መፍትሔው ታታሪነት ነው (12፥11፤14፥23፤28፥19 ይመ)። *እንደ ወንበዴ፣ ... መሣሪያ እንደ ታጠቀ፤* ችግርን በወቅቱ ካልተቋቋሙት ድኽነት ሥር ይሰዳል (ከማቴ 24፥43 ጋር ያነጻጽሩ)።

*6፥12-14፤* ተንኰል ያለበትን የልቡን መሻት ይፈጽም ዘንድ የመግባቢያ መሣሪያ የሆኑትን አፍ፣ ዐይን፣ እግርና ጣት አታላይ በሆነ ስልት የሚጠቀመውን በግልጽ ያሳያል። እዚህ ላይ በተለይ አንድን ሰው ለማጥፋት ሲባል የሚካሄደውን የስም ማጥፋት ዘመቻ ያመለክታል።

6፥12 *ወሮበላና፤* ዋጋ ቢስና ምናምንቴ ሰው ነው (መሳ 19፥22፤ 1ሳሙ25፥25፤ ኢዮ43፥18)፤ የዘዳ13፥13 ማብ ይመ። *ነውረኛ አንደበቱን፤* 2፥12 እና ማብ እንዲሁም 19፥28 ይመ።

6፥13 *በዐይኑ የሚጠቅስ፤* ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሐሳቡን የሚገልጽ (10፥10፤ 16፥30 ይመ)።

6፥14 *ክፋትን ... የሚያውጠነጥን፤* ቊ18፤ 3፥29፤ ሚክ2፥1 ይመ። *ጠብ ይጭራል፤* ስም በማጥፋት አለመተማመንን ይፈጥራል፤ አለመተማመንም ውሎ አድሮ መለያየትንና ግጭትን ይወልዳል።

6፥15 *በቅጽበት መዓት ይወርድበታል፤* ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመለክታል (1፥26፤ 24፥22፤ ኢዮ 34፥20 ይመ)። *በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም፤* በሌላ ሰው ላይ ሊያደርስ ያሰበው ክፉ ነገር፣ በእርሱ ላይ ይደርስበታል፤ የሚደርስበት ቅጣትም ካሰበው ክፋት ጋር የሚተካከል ይሆናል።

*6፥16-19፤* የቊ12-15 ፍሬ ሐሳብ በይበልጥ የሚያብራራ ሲሆን፣ በዚህ ላይ የተጠቀሰው ክፉ ሰው ድንገተኛ አደጋ ለምን እንደሚደርስበት ይገልጻል (ቊ15)።

6፥16 *ስድስት ... ሰባት፤* በዕብራይስጥ የግጥም ባሕል፣ ተመሳሳይ ሐሳብ ያላቸው ስንኞች የሚገልጹበት ስልት ነው፤ (በመግቢያው፣ "የምሳሌዎቹ ጠባይ" የሚለውን ይመ) እንዲህ ዐይነቱ የሐሳብ አደራደር በብሉይ ኪዳን፣ የጥበብ ጽሑፍ ውስጥ የተለመደ ነው (30፥15፤ 18፡21፡29፤ እንዲሁም ኢዮ5፥19 ይመ)። *የሚጸየፋቸውም፤* 3፥32 እና ማብ ይመ።

6፥17 *ትዕቢተኛ ዐይን፤* ኵራት ያለበትን ልብ ያሳያል፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ይፈርድበታል (21፥4፤ 30፥13፤ መዝ18፥27፤ 101፥5 ይመ)። *ሐሰተኛ ምላስ፤* 2፥12 እና 12፥19፤ 17፥7፤ 21፥6 ይመ። *ንጹሕ ደም የሚያፈሱ እጆች፤* 1፥11፡16 እና ማብ፤ 28፥17 ይመ።

6፥18 *ክፋትን የሚያውጠነጥን ልብ፤* 1፥31፤ 24፥2፤ ዘፍ6፥5 ይመ። *ወደ ክፋት የሚቻኰሉ እግሮች፤* 1፥16 እና ማብ

19በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር ሐሰተኛ
ምስክር፣
በወንድማማቾች መካከል ጠብን
የሚጭር ሰው።

**ከዝሙት መራቅ**

20ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ትእዛዝ አክብር፤
የእናትህንም ትምህርት አትተው።
21ምንጊዜም በልብህ አኑራቸው፤
በአንገትህም ዙሪያ እሰራቸው።
22በምትሄድበት ሁሉ ይመሩሃል፤
በምትተኛበት ጊዜ ይጠብቁሃል፤
በምትነቃበት ጊዜም ያነጋግሩሃል።
23እነዚህ ትእዛዞች መብራት ናቸውና፤
ይህችም ትምህርት ብርሃን፣
የተግሣጽ እርምትም የሕይወት መንገድ
ናት፤
24እርሷም ከምግባረ ብልሹ ሴት፣
ልዝብ አንደበት ካላት ዘልዛላ ሴት
ትጠብቅሃለች።
25ውበቷን በልብህ አትመኝ፤
በዓይኗም አትጠመድ፤
26ጋለሞታ ሴት ቍራሽ እንጀራ
ታሳጣሃለችና፤
አመንዝራዪቱም በሕይወትህ በራሱ ላይ
ትሸምቃለች።
27ለመሆኑ ልብሱ ሳይቃጠል፣
በጕያው እሳት መያዝ የሚችል ሰው
አለን?
28አንድ ሰው እግሮቹ ሳይቃጠሉ፣
በፍም ላይ መሄድ ይችላልን?
29ከሰው ሚስት ጋር የሚተኛም እንደዚሁ
ነው፤
የሚደርስባትም ከቅጣት አያመልጥም።
30ሌባ በተራበ ጊዜ ራቡን ለማስታገሥ
ቢሰርቅ፣
ሰዎች አይንቁትም።
31በቤቱ ያለውን ሀብት ሁሉ የሚጠይቀው
ቢሆንም፣
ከተያዘ ሰባት እጥፍ መክፈል አለበት።
32የሚያመነዝር ሰው ግን ማመዛዘን
ይጐድለዋል፤
እንዲህ የሚያደርግ ሁሉ ራሱን
ያጠፋል።
33መደብደብና ውርደት ዕጣው ነው፤
ኀፍረቱም ከቶ አይወገድም፤
34ቅናት የባልን ቍጣ ይቀሰቅሳልና፤
በሚበቀልበትም ጊዜ ምሕረት
አያደርግም።
35 ምንም ዐይነት ካሣ አይቀበልም፤
የቱንም ያህል ብዙ ቢሆን መማለጃን
እሺ አይልም።

**ከአመንዝራ ሴት መራቅ**

7 ልጄ ሆይ፤ ቃሌን ጠብቅ፤
ትእዛዜንም በውስጥህ አኑር።
2ትእዛዜን ጠብቅ፤ በሕይወት ትኖራለህ፤
ትምህርቴንም እንደ ዐይንህ ብሌን
ተንከባከበው።
3በጣትህ ላይ እሰረው፤
በልብህ ጽላት ላይ ጻፈው።
4ጥበብን፣ "እኅቴ ነሽ" በላት፤
ማስተዋልንም፣ "ዘመዴ ነህ" በለው፤
5ከአመንዝራ ሴት፣
በአንደበቷም ከምታታልል ዘልዛላ ሴት
ይጠብቁሃል።
6በቤቴ መስኮት፣
በዐይነ ርግቡ ወደ ውጭ ተመለከትሁ።
7ማስተዋል የጐደለውን ወጣት፣

ኤር2፥34፤ሚክ7፥2
6፥18 ኢዮ15፥31
6፥19 ቍ12-15፤ዘጸ 19፥16፤መዝ12፥2፤ ምሳ15፥18፤ዘካ8፥17
6፥20 ምሳ1፥8፤ 3፥21
6፥21 ዘዳ6፥8፤ምሳ 3፥3፤7፥1-3
6፥23 መዝ119፥105 ፤ምሳ10፥17
6፥24 ዘፍ39፥8፤ መዝ 55፥21፤ምሳ 2፥16፤7፥5
6፥26 ምሳ7፥22-23
6፥29 ዘፀ20፥14፤ ምሳ2፥16-19፤5፥8
6፥31 ዘፀ22፥14
6፥32 ዘፀ20፥14፤ ምሳ 7፥7፤9፥4፡16
6፥33 ምሳ5፥9-14
6፥34 ዘፍ34፥7፤ ዘኍ5፥14
6፥35 ኢዮ31፥9-11 1ማሕ 8፥7
7፥1 ምሳ1፥8
7፥2 ምሳ4፥4
7፥3 ምሳ3፥3
7፥5 ቍ21፤ኢዮ31፥ 9፤ምሳ2፥16፤6፥24
7፥7 ምሳ1፥22፤ 6፥32

ይመ።

6፥19 *ሐሰተኛ ምስክር፤* በሐሰተኛ ምስክር የተነሣ የደረሰውን ጕዳትና (12፥17-18፤ 25፥18፤ የመዝ5፥9 ማብ ይመ)፣ በደለኛ የሚቀበለውን ቅጣት መጽሐፈ ምሳሌ በአጽንኦት ይገልጻል (ቍ15፤ እንዲሁም 19፥5:9፤ 21፥28 ይመ)። *በውሸት ላይ ውሸት የሚጨምር፤* 14፥5:25 ይመ። *ጠብን የሚጭር፤* የቍ14 ማብ ይመ።

6፥20 *ልጄ ... የአባትህን ... የእናትህንም፤* መጽሐፈ ምሳሌ ለቤተ ሰብ የሚሰጠው ግምት እጅግ ከፍ ያለ ነው፤ (1) ቤተ ሰብ ሲባል አባትንና እናትን እንዲሁም ልጆችን ያመለክታል። (2) አባትና እናት ለልጆቻቸው በሚደረግ መንፈሳዊ እንክብካቤ ረገድ ሊተጋገዙ ይገባል (1፥8-9፤ 4፥1-5)። (3) አስተዋይ ልጆች ወላጆቻቸውን ያከብራሉ፤ ለእነርሱም ይታዘዛሉ (1፥8፤ 2፥1፤ 3፥1፤ 10፥1)። (4) ለጋብቻ ቃል ኪዳን ታማኝ መሆንና እርስ በርስ መዋደድ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶአቸዋል (5፥15-20)።

*6፥21፤* 1፥9፤ 3፥3 እና ማብ ይመ።

6፥22 *በምትሄድበት፤* ከ4፥11 ጋር ያነጻጽሩ። *በምትተኛበት ጊዜ፤* የ3፥24 ማብ ይመ። *ይጠብቁሃል፤* 4፥6 ይመ።

6፥23 *መብራት ... ብርሃን፤* የእግዚአብሔር ቃል "ለእግሬ መብራት፣ ለመንገዴ ብርሃን" እንደ ሆነው (መዝ119፥105 ይመ፤ ከመዝ19፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሕይወት መንገድ፤* 3፥22፤ 4፥22 ይመ። ቅጣት የሚጠላ ሰው የሚሄድበትን የሞት መንገድ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

*6፥24፤* የ2፥16፤ 5፥3 ማብ ይመ።

6፥25 *አትመኝ፤* ምኞት ፍትወትና ምንዝርና በጣም የተያያዙ መሆናቸውን ጌታ ኢየሱስ አስተምሮአል (ማቴ5፥28፤ ከዘፀ 20፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። *አትጠመድ፤* 5፥20 ይመ።

6፥26 *ቍራሽ እንጀራ ታሳጣሃለችና፤* ዝሙት አዳሪና (29፥3) አመንዝራ (5፥10) ሁለቱም አንድን ሰው ለድኽነት ይዳርጉታል (1ሳሙ2፥36 ይመ)።

6፥29 *ከቅጣት አያመልጥም፤* ቍ33-34፤ እንዲሁም የ5፥14 ማብ ይመ።

6፥31 *ሰባት ዕጥፍ፤* የዕብራውያን ሕግ ለማንኛውም ዐይነት ስርቆት ከአምስት እጥፍ የበለጠ እንዲከፈል አይጠይቅም (ዘፀ22፥1-9)። እዚህ ላይ ቍጥር 7 ትእምርት (ምሳሌያዊ ምልክት) ነው፤ ይኸውም በሙሉ የሚከፈል መሆኑን የሚያመለክት ነው።

6፥32 *ራሱን ያጠፋል፤* 5፥14 እና ማብ፤ 7፥22-23 ይመ።

6፥33 *ውርደት፤* አምኖን ትዕማርን ከደፈራት በኋላ ውርደት ደርሶበታል (2ሳሙ13፥13-22)።

6፥34 *ቅናት፤* የቅናት ብርታት ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ በ27፥4፤ በማሕ8፥6 ላይም ተገልጾአል።

*7፥1፤* 2፥1 እና ማብ ይመ።

7፥2 *ዐይንህ ብሌን፤* በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ያለበት በጣም አስፈላጊ የሆነ የሰውነት ክፍል ነው (ዘዳ32፥10 እና ማብ ይመ)።

7፥3 *በጣትህ ላይ እሰረው፤* ሁልጊዜ እንድታስታውሰው (6፥21፤ ዘዳ6፥8 ይመ)።

7፥4 *ጥበብን፤* በጥበብ አስተማሪ ትምህርት ውስጥ ይገኛል (ቍ1-3)። *እኅቴ ... ዘመዴ፤* ጥበብን የልብ ጓደኛ አድርጋት ማለት ነው፤ እዚህ ላይ "እኅቴ" የሚለው ቃል የገባው "ሙሽራዬ" የሚለውን ትርጕም ይዞ ነው (ማሕ4፥9-10:12፤5፥1-2 ይመ)።

*7፥5፤* የ2፥16 ማብ ይመ።

7፥7 *ማስተዋል የጐደለውን፤* (6፥32፤ 9፥4:16 ይመ።

ብስለት ከሌላቸው መካከል አየሁት፤
ከጎልማሶችም መካከል ለየሁት።
8የቤቷን አቅጣጫ ይዞ፣
በቤቷ ማእዘን አጠገብ ባለው መንገድ
ያልፍ ነበር፤
9ቀኑ መሸትሸት ብሎ ጀንበሯ ልትጠልቅ
ነው፣
የሌሊቱ ጨለማ በመግባት ላይ ነበር።
10 ከዚያም አንዲት ሴት ልታገኘው
ወጣች፤
እንደ ዝሙት አዳሪ ለብሳ፣ ለማሳሳት
ታጥቃ።
11ጯኺና ማን አለብኝ ባይ ናት፤
እግሮቿ አርፈው ቤት አይቀመጡም፤
12አንዴ በመንገድ፣ አንዴ በአደባባይ፤
በየማእዘኑም ታደባለች።
13አፈፍ አድርጋ ይዛ ሳመችው፤
ኀፍረቷንም ጥላ እንዲህ አለችው፤
14"በቤቴ የኅብረት መሥዋዕት* ማቅረብ
ነበረብኝ፤
ዛሬ ስእለቴን ፈጸምሁ፤
15ስለዚህ አንተን ለማግኘት ወጣሁ፤
ፈልጌህ ነበር፤ ይኸው አገኘሁህ።
16ዐልጋዬን ከግብፅ የመጣ፣
ጌጠኛ በፍታ አልብሼዋለሁ።
17ዐልጋዬን፣
የከርቤ፣ የዓልሙንና የቀረፋ ሽቱ
አርከፍክፌበታለሁ።
18ና፤ እስኪነጋ በጥልቅ ፍቅር እንርካ፤
በፍቅር ራሳችንን እናስደስት።
19ባሌ እቤት የለም፤
ሩቅ አገር ሄዷል።

7፥9 ኢዮ24፥15
7፥11 ምሳ9፥13
7፥12 ምሳ8፥1-36፤ 23፥26-28
7፥13 ዘፍ39፥12፤ ምሳ1፥20
7፥14 ዘሌ7፥11-18
7፥17 ዘፍ37፥25፤ አስ1፥6፤ኢሳ57፥7፤ ሕዝ23፥41፤አሞ6፥4
7፥18 ዘፍ39፥7
7፥21 ቍ5
7፥22 ኢዮ18፥10
7፥23 ኢዮ15፥22፤ 16፥13፤ምሳ6፥26፤ መክ7፥26
7፥24 ምሳ1፥8-9፤ 8፥32
7፥25 ምሳ5፥7-8
7፥27 መሳ16፥19፤ ምሳ2፥18፤ራእ22፥15
8፥1 ኢዮ28፥12

20በገንዘብ የተሞላ ቦርሳ ወስዷል፤
ጨረቃዋ ሙሉ እስክትሆን
አይመለስም።"
21በሚያግባቡ ቃላት አሳተችው፤
በለሰለሰ አንደበቷ አታለለችው።
22ለዕርድ እንደሚነዳ በሬ፣
ፍላጻ ጒበቱን እስኪወጋው ድረስ፣
ወደ ወጥመድ† እንደሚገባ አጋዘን‡
23ወደ ወጥመድ በራ እንደምትገባ ወፍ፣
ሳያንገራግር ተከተላት፤
ነገሩ ሕይወቱን እንደሚያሳጣው
አላወቀም።

24ልጆቼ ሆይ፤ አሁንም አድምጡኝ፤
የምለውንም ልብ ብላችሁ ስሙኝ።
25ልባችሁን ወደ መንገዷ አታዘንብሉ፤
ወደ ስሕተት ጐዳናዋም አትግቡ።
26አዋርዳ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፤
የገደለቻቸውም ስፍር ቍጥር የላቸውም።
27ቤቷ ወደ ሲኦል§ የሚወስድ፣
ወደ ሞት ማደሪያም የሚያወርድ
ጐዳና ነው።

## የጥበብ ጥሪ

8 ጥበብ ጮኻ አትጣራምን?
ማስተዋልስ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ
አታሰማምን?
2በመንገድ አጠገብ ባሉ ኰረብቶች፣
መንገዶቹ በሚገናኙበትም ላይ
ትቆማለች፤

*14 በተለምዶ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።
†22 የሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትም) ትርጒም እና ዕብራይስጡ *ተላላ* ይላሉ።
‡22 የዚህ ስንኝ የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም።
§27 ወይም *መቃብር*

*ብስለት ከሌላቸው፤* የ1፥4 ማብ ይመ።

7፥8 *የቤቷን አቅጣጫ ይዞ፤* 5፥8 ይመ።

7፥9 *የሌሊቱ ጨለማ፤* ሰው የማያየው መስሎት ነበር (2፥13 እና ማብ ይመ)።

7፥10 *እንደ ዝሙት አዳሪ ለብሳ፤* የሰውን ስሜት ለመሳብ ሲባል፣ እጅግ በሚያብረቀርቅና ቅጥ ባጣ አለባበስ (ሕዝ 16፥16)፤ ማንም ለይቶ እንዳያውቃት በመሸፋፈን (ዘፍ38፥14-15 ይመ)።

7፥11 *ጯኺ፤* በ9፥13 ላይ 'ጥበብ የለሽ' የተባለችውን ያመለክታል።

7፥12 *ታደባለች፤* የምታጠምደውን ለማያዝ ዝግጁ መሆን ያመለክታል (ቍ22 ይመ)።

7፥13 *ሳመችው፤* የድፍረት ሰላምታ ነው (ዘፍ29፥11 ይመ)።

7፥14 *የኅብረት መሥዋዕት፤* መሥዋዕት አቅራቢ የሆነው ሰውና ቤተሰቡ ለመሥዋዕት ከቀረበው ሥጋ የተወሰነውን ክፍል መብላት ይችሉ ነበር (ዘሌ7፥12-15)። *ዛሬ ስእለቴን ፈጸምሁ፤* ስእለትን ለመፈጸም የሚቀርበው መሥዋዕት ከኅብረት መሥዋዕት ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ የቀረበው ሥጋም በዕለቱ ወይም በሁለተኛው ቀን መበላት ነበረበት (ዘሌ7፥15-16)። አንድ ወጣት በሃይማኖታዊ ሥርዐት ውስጥ የመካፈል ዕድል የነበረው ቢሆንም፣ ለከንቱ ፈንጠዝያና ለጥጋብ ቢያውለው ከመሥዋዕቱ ዐላማ ጋር የማይጣጣም ይሆናል (ከአሞ5፥21-22 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥16 *ከግብፅ የመጣ ጌጠኛ በፍታ፤* በ31፥22 ላይ በፍታ የባለ ጸጋ ልብስ መሆኑ ተመልክቶአል፤ የግብፅ በፍታ እጅግ የከበረ ዋጋ ነበረው (ኢሳ19፥9፤ ሕዝ27፥7 ይመ)።

7፥17 *የከርቤ፣ የዓልሙንና የቀረፋ፤* የፍቅርን ስሜት የሚገልጹ መልካም መዐዛ ያላቸው ቅመሞች እንደ ሆኑ በመዝ 45፥8፤ በማሕ4፥14፤ 5፥5 ላይም ተገልጾአል።

7፥18 *በጥልቅ ፍቅር እንርካ፤* በ9፥17፤ 30፥20፤ በማሕ 4፥16፤ 5፥1 ላይ ደግሞ ወሲብ ከመብላትና ከመጠጣት ጋር ተነጻጽሮአል። *በፍቅርም ሐሤት እናድርግ፤* ማሕ4፥10 ይመ።

7፥19 *እቤት የለም፤* በዚህም ምክንያት ኩኑ ሊያውቅ አይችልም (ከ6፥34-35 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሩቅ አገር፤* ሀብታም ነጋዴ ሳይሆን አይቀርም።

7፥20 *በገንዘብ፤* ለመገበያየት የሚያገለግሉ የተለያየ ክብደት ያላቸው የብር ሽርፍራፊዎች ነበሩ፤ በሳንቲም መልክ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ የዋሉት ግን ከጊዜ በኋላ ነው (የዘፍ 20፥16 ማብ ይመ)።

7፥21 *በሚያግባቡ ቃላት ... በለሰለሰ አንደበቷ፤* የ2፥16፤ 5፥3 ማብ፣ እንዲሁም 6፥24፤ 7፥5 ይመ። *አሳተችው፤* ከ5፥23 ጋር ያነጻጽሩ።

7፥22 *ለዕርድ እንደሚነዳ በሬ፤* የሚጠብቀውን ክፉ ነገር ከቶ አይገነዘብም። *ወጥመድ፤* ኢሳ51፥20 ይመ።

7፥23 *ጒበቱን እስኪወጋው፤* የክፉ ሰው አስፈሪ ዕጣ ፈንታ ምን እንደ ሆነ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢዮ20፥24-25 ላይ ተገልጾአል። *ወደ ወጥመድ በራ እንደምትገባ፤* የ1፥17-18፤ የ5፥22 ማብ ይመ።

*7፥24፤* 5፥7 ይመ።

7፥25 *መንገዷ፤* 1፥15 ይመ።

7፥26 *አዋርዳ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፤* 9፥18፤ ኢሳ 5፥14 ይመ።

7፥27 *ወደ ሲኦል የሚወስድ ... ጐዳና ነው፤* የ2፥18፤ የ5፥ 5 ማብ፣ እንዲሁም 14፥12፤ 16፥25፤ ማቴ7፥13 ይመ፤ ከ1ቆሮ 6፥9-10 ያነጻጽሩ።

*8፥1-36፤* በ1፥20-23 እንደ ተመለከተው፣ እዚህም ላይ ጥበብ እንደ ሰው ሆና የቀረበች ስትሆን፣ ሰዎች ሁሉ ትምህርቷን ይቀበሉ ዘንድ ትጣራለች።

3ወደ ከተማዪቱ በሚያስገቡት በሮች
አጠገብ፣
በመግቢያዎቹ ላይ፣ ድምጿን ከፍ
አድርጋ እንዲህ ስትል ትጮኻለች፤
4"ሰዎች ሆይ፤ የምጠራውኮ እናንተን ነው፤
ለሰው ልጆች ሁሉ ድምፄን ከፍ
አደርጋለሁ::
5እናንተ ብስለት የጐደላችሁ ጠንቃቃነትን
ገንዘብ አድርጉ፤
እናንተ ተላሎች፣ ማስተዋልን አትርፉ::
6የምናገረው ጠቃሚ ነገር ስላለኝ
አድምጡኝ፤
ቀና ነገር ለመናገር ከንፈሮቼን
እከፍታለሁ::
7አንደበቴ እውነትን ይናገራል፤
ከንፈሮቼ ክፋትን ይጸየፋሉና::
8ከአንደበቴ የሚወጡት ቃሎች ሁሉ
ጽድቅ ናቸው፤
አንዳቸውም ጠማማና ግራ የሚያጋቡ
አይደሉም::
9በጥልቅ ለሚያስተውሉ ሁሉም ቀና
ናቸው፤
ዕውቀት ላላቸውም ስሕተት
የለባቸውም::
10ከብር ይልቅ ምክሬን፣
ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ ዕውቀትን ምረጡ፤
11ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ይበልጥ ውድ ናትና፤
ከምትመኙት ነገር ሁሉ አንዳች
የሚስተካከላት የለም::
12"እኔ ጥበብ ከማስተዋል ጋር አብሬ
እኖራለሁ፤
ዕውቀትና ልባምነት ገንዘቦቼ ናቸው::
13እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን
መጥላት ነው፤
እኔም ትዕቢትንና እብሪትን፣
ክፉ ጠባይንና ጠማማ ንግግርን
እጠላለሁ::
14ምክርና ትክክለኛ ፍርድ የእኔ ናቸው፤
ማስተዋል አለኝ፤ ብርታት አለኝ::
15ነገሥታት በእኔ ይነግሣሉ፤
ገዦችም ትክክል የሆነውን ሕግ
ይደነግጋሉ፤
16መሳፍንት በእኔ ይገዛሉ፤
በምድር ላይ የሚገዙ መኳንንትም ሁሉ
በእኔ ያስተዳድራሉ::[a]
17የሚወዱኝን እወዳቸዋለሁ፤
ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል::
18ሀብትና ክብር፣
ዘላቂ ብልጽግናና ስኬት በእኔ
ዘንድ አሉ::
19ፍሬዬ ከንጹሕ ወርቅ ይበልጣል፤
ስጦታዬም ከነጠረ ብር::
20እኔ በጽድቅ መንገድ፣ እሄዳለሁ፤
በፍትሕም ጐዳና እገዛለሁ፤
21 ለሚወዱኝ ብልጽግና እሰጣለሁ፤
ግምጃ ቤታቸውንም እሞላለሁ::
22እግዚአብሔር ከቀድሞ ሥራዎቹ በፊት፣
የተግባሮቹ መጀመሪያ[b] አድርጎ
አመጣኝ፤[c]
23ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ፣
ከጥንት ከዘላለም ተሾምሁ::[d]

8፥3 ምሳ7፥6-13
8፥4 ኢሳ42፥2
8፥5 ምሳ1፥4:22፣
8፥7 ዮሐ8፥14
8፥10 ኢዮ28፥17፤መዝ19፥10
8፥11 ቍ19፤ኢዮ 28፥17-19፤ምሳ3፥13-15
8፥12 ምሳ1፥4
8፥13 ዘፍ22፥12፤ዘፀ 20፥20፤ኢዮ28፥28፤ ኤር44፥4
8፥14 ኢዮ9፥4፤ምሳ 21፥22፤መክ7፥19
8፥15 መዝ2፥10
8፥16 2ዜና1፥10፤ ምሳ29፥4
8፥17 1ሳሙ2፥30፤ 1ዜና16፥11፤ምሳ1፥2 8፤3፥13-18፤ማቴ7፥7 -11፤ዮሐ14፥21-24
8፥18 ዘዳ8፥18፤1ነገ 3፥13
8፥19 ኢዮ28፥17-19፤ምሳ3፥13-14
8፥20 መዝ5፥8
8፥21 ምሳ15፥6፤ 24፥4

[a]16 አያሌ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች *በምድር ላይ በጽድቅ የሚገዙ* ይላሉ::
[b]22 ወይም *የመንገዱ፣ የግዛቱ*
[c]22 ወይም *እግዚአብሔር በሥራው መጀመሪያ ያዘኝ ወይም እግዚአብሔር በሥራው መጀመሪያ አመጣኝ*
[d]23 ወይም *ተሠራሁ*

8፥1 *ጮኸ ... ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፤* 1፥20 ይመ::
*8፥2-3፤* የ1፥20-21 ማብ ይመ::
8፥4 *ለሰው ልጆች፤* ቍ31 ይመ::
8፥5 *ብስለት የጐደላችሁ ... ተላሎች፤* በ1፥22:32 ላይ ጥበብ ባደረገችው ንግግር ውስጥ ጐዳዩ የሚመለከታቸው ተደራስያን ናቸው:: *እናንተ ተላሎች ማስተዋልን አትርፉ፤* የ1፥4 ማብ ይመ::
8፥6 *ጠቃሚ ነገር ... ቀና ነገር፤* ፊል4፥8 ይመ::
8፥7 *ከንፈሮቼ ክፋትን ይጸየፋሉና፤* የ3፥32፤ 12፥22 ይመ::
8፥8 *ጠማማና ግራ የሚያጋቡ፤* ፊል2፥15 ይመ፤ ከምሳ 2፥15 ጋር ያነጻጽሩ (የ2፥5 ማብ ይመ)::
8፥9 *በጥልቅ ለሚያስተውሉ፤* አንድ ሰው አስተዋይ እየሆነ በሄደ ቍጥር የጥበብን ምክር ያደንቃል፤ ለቃሏም ልዩ ትኩረት ይሰጣል:: *ዕውቀት ላላቸውም፤* በተለይም እግዚአብሔርን ስለ ማወቅ ያመለክታል::
8፥10 *ክብር ... ወርቅ፤* ቍ19፤ 2፥4፤ 3፥14 እና ማብ ይመ::
*8፥11፤* ከ3፥15 ጋር አንድ ነው (የዚያኑ ማብ ይመ)::
8፥12 *ከማስተዋል ጋር አብሬ እኖራለሁ፤* ከኢዮ28፥20 ጋር ያነጻጽሩ:: *ዕውቀትና ልባምነት፤* 1፥4 እና ማብ ይመ::
8፥13 *እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን መጥላት ነው፤* እግዚአብሔርን መፍራት ከክፋት ሊያርቀን ይገባል (16፥6)፤ እንዲሁም እርሱን ከሚያሳዝነን፣ ራሳችንና የምንወዳቸውን ሊያጠፋ ከሚችል ኀጢአት እንድንርቅ ያደርጋል:: *ትዕቢትንና እብሪትን ... እጠላለሁ፤* 16፥18፤1ሳሙ2፥3፤ኢሳ13፥11፤ እንዲሁም መዝ 10፥2 እና ማብ ይመ:: *ክፉ ጠባይንና ጠማማ ንግግርን፤* የ2፥12 ማብ፤ እንዲሁም 6፥12:16-19 ይመ::
8፥14 *ምክርና ትክክለኛ ፍርድ ... ማስተዋል ...ብርታት፤* እነዚህ የጌታና (2፥6-7፤ ኢዮ12፥13:16፤ ኢሳ40፥13-14፤ ሮሜ 16፥27) የጌታ መንፈስ ባሕርያት ናቸው (ኢሳ 11፥2):: *ምክር፤* 1፥25፤ 19፥20 ይመ:: *ብርታት፤* ከመክ 9፥16 ጋር ያነጻጽሩ::
8፥15 *ነገሥታት በእኔ ይነግሣሉ፤* 29፥4 ይመ:: ሰሎሞን እስራኤልን ለመግዛት ጥበብን እንዲሰጠው ጸለየ (1ነገ3፥9፤ 2ዜና 1፥10 ይመ)::
8፥17 *እወዳቸዋለሁ፤* በረከቴን አፈስላቸዋለሁ (4፥6 እና ማብ፤ እንዲሁም ዮሐ14፥21 ይመ):: *ተግተው የሚሹኝም፤* 2፥4-5፤ ኢሳ55፥6፤ ያዕ1፥5 ይመ::
8፥18 *ሀብትና ክብር፤* 21፥21 ይመ::
8፥19 *ፍሬዬ፤* በ3፥18 ላይ ጥበብ፣ "የሕይወት ዛፍ" ተብላለች (የዚያኑ ማብ ይመ):: *ከንጹሕ ወርቅ ... ከነጠረ ብር፤* ቍ 10፤ ኢዮ28፥15፤ እንዲሁም 3፥14 እና ማብ ይመ::
8፥20 *መንገድ ... ጐዳና፤* 3፥17 ይመ:: *ጽድቅ፤* ቍ15 ይመ::
8፥21 *ብልጽግና እሰጣለሁ፤* ቍ18፤ ዘዳ8፥12 ይመ:: *ግምጃ ቤታቸውንም እሞላለሁ፤* የ3፥10 ማብ እንዲሁም 24፥4 ይመ::
*8፥22-31፤* በፍጥረት ጊዜ ጥበብ የነበራትን ሚና የሚገልጽ መዝሙር ነው:: በ1፥20-23፤ 3፥15-18፤ 9፥1-12 እንደ ሆነው እዚህም ጥበብ እንደ ሰው ሆና ቀርባለች:: ስለዚህ እነዚህ ቍጥሮች ክርስቶስን በቀጥታ የሚገልጹ ናቸው ተብለው መተርጐም የለባቸውም፤ ይሁን እንጂ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመለኮት ቃልና (ዮሐ1፥1-3) የእግዚአብሔር ጥበብ (1ቆሮ 1፥24:30፤ ቈላ2፥3) ተብሎ ለመገለጹ በከፊል እንደ ጻራ በከፊል ደግሞ እንደ ፍንጭ ሆነው ያገለግላሉ:: እዚህ ላይ ጥበብ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሆና ከመገለጿም በላይ፣ ዓለም የተፈጠረው በእርሱ ጥበብ ነው::
8፥22 *አድርጎ አመጣኝ፤* ጥበብን ይመለከታል (3፥19፤ መዝ104፥24 ይመ):: *የተግባሮቹ መጀመሪያ፤* ኢዮብ ስለ ታላቁ እንስሳ የሰጠውን ሐሳብ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኢዮ40፥19)::
8፥23 *ከዘላለም፤* ክርስቶስንም ሊገልጽ ይችላል (ዮሐ1፥1

24ከውቅያኖሶች በፊት፣
የውሃ ምንጮች ከመፍለቃቸው በፊት
ተወለድሁ፤
25ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ፣
ከኰረብቶችም በፊት ተወለድሁ፤
26ምድርን ወይም ሜዳዎቿን፣
ወይም ምንም ዐይነት የዓለም ትቢያን
ከመፍጠሩ በፊት እኔ ተወለድሁ።
27ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ፣
በውቅያኖስ ላይ የአድማስ ምልክት
ባደረገ ጊዜ እኔ እዚያ ነበርሁ፤
28ደመናትን በላይ ባጸና ጊዜ፣
የውቅያኖስን ምንጮች በመሠረተ ጊዜ፣
29ለባሕር ድንበርን በከለለ ጊዜ፣
ውሆችም የእርሱን ትእዛዝ እንዳያልፉ፣
የምድርንም መሠረቶች ወሰን ባበጀ
ጊዜ፣
30በዚያን ጊዜ ከጐኑ ዋና ባለሙያ ነበርሁ።
ሁልጊዜ በፊቱ ሐሤት እያደረግሁ፣
ዕለት ተዕለት በደስታ እሞላ ነበር፤
31የእርሱ በሆነው መላው ዓለም ሐሤት
እያደረግሁ፣
በሰው ልጆች ደስ እሰኝ ነበር።
32"እንግዲህ፣ ልጆቼ ሆይ፤ አድምጡኝ፤
መንገዴን የሚጠብቁ ቡሩካን ናቸው።
33ምክሬን አድምጡ፤ ጥበበኞች ሁኑ፤
ቸልም አትበሉት።
34በየለቱ ደጃፌ ላይ የሚጠብቅ፣
በበራፌ ላይ የሚጠባበቅ፣
የሚያዳምጠኝ ሰው ቡሩክ ነው።
35የሚያገኘኝ ሁሉ ሕይወትን ያገኛልና፤
ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስን
ይቀበላል።
36የሚያጣኝ ሁሉ ግን ራሱ ይጐዳል፤
የሚጠሉኝም ሁሉ ሞትን ይወዳሉ።

8፥24 ዘፍ7፥11
8፥25 ኢዮ15፥7፤ 38፥6
8፥26 መዝ90፥2
8፥27 ኢዮ22፥14፤ 26፥7
8፥28 ዘፍ1፥7፤ኢዮ 9፥8፤26፥10፤36፥29
8፥29 ዘፍ1፥9፤ 1ሳሙ2፥8፤ኢዮ38፥5: 8፤መዝ16፥6
8፥30 ምሳ3፥19-20፤ ራእ3፥14
8፥31 ኢዮ28፥25-27፤38፥4-38፤መዝ 104፥1-30፤ምሳ30፥4 ፤ዮሐ1፥1-4፤ቆላ1፥15-20
8፥32 2ሳሙ22፥22፤ መዝ18፥21፤ሉቃ11፥ 28
8፥34 1ነገ10፥8
8፥35 ኢዮ33፥26፤ ምሳ9፥6፤3፥13-18፤ ዮሐ5፥39-40
8፥36 ኢዮ28፥22፤ ምሳ15፥32፤ኢሳ3፥9፤ ኤር40፥2
9፥1 ኤፌ2፥20-22፤ 1ጴጥ2፥5
9፥2 ኢሳ25፥6፤ 62፥8፤ሉቃ14፥16-23
9፥3 ቁ14፤ምሳ1፥20 ፤8፥1-3
9፥4 ቁ16፤ምሳ1፥22 ፤6፥32
9፥5 መዝ42፥2፤ 63፥1፤143፥6፤ኢሳ 44፥3፤55፥1፤ዮሐ7፥3 7-38
9፥6 ምሳ3፥1-2፤ 8፥35

## ጠቢብነትና ተላላነት

9ጥበብ ቤቷን ሠራች፤
ሰባቱን ምሰሶዎቿንም ጠርባ አቆመች፤
2ፍሪዳዋን አረደች፤ የወይን ጠጇን
ጠመቀች፤
ማእዷንም አዘጋጀች።
3ሴት አገልጋዮቿንም ላከች፤
ከከተማዪቱም ከፍተኛ ቦታ ተጣራች።
4እርሷም ማመዛዘን ለጐደላቸው፣
"ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ ወደዚህ ኑ!"
አለች።
5"ኑ፤ ምግቤን ተመገቡ፤
የጠመቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ።
6የሞኝነት መንገዳችሁን ተዉ፤ በሕይወት
ትኖራላችሁ፤
በማስተዋልም መንገድ ተመላለሱ።
7"ፌዘኛን የሚገሥጽ ሁሉ ስድብን በራሱ
ላይ ያመጣል፤
ክፉውን ሰው የሚዘልፍ ሁሉ ውርደት
ያገኘዋል።
8ፌዘኛን አትዝለፈው፤ ይጠላሃል፤
ጠቢብን ገሥጸው፤ ይወድሃል።
9ጠቢብን አስተምረው፣ ይበልጥ ጥበበኛ
ይሆናል፤
ጻድቁን ሰው አስተምረው፤ ዕውቀቱን
ይጨምራል።

ይመ፤ ከሚክ5፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። *ዓለም ከመፈጠሩ፤* እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠር ከመጀመሩ በፊት ጥበብ በዚያ ነበረች (ኢየሱስ በዮሐ17፥5 የተናገረውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥24 *ተወለድሁ፤* በሌላ ቦታ ግን ቃሉ፣ (ኢዮ38፥8-9)፤ ሕላዌ ያገኙትን ተራሮችና መሬትን ያመለክታል (መዝ90፥2፤ ኢዮ 15፥7)። *የውሃ ምንጮች ከመፍለቃቸው፤* መዝ 104፥10 ይመ።

8፥25 *ተራሮች፤* መዝ 90፥2 ይመ።

8፥27 *ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ፤* 3፥19 ይመ። *በውቅያኖስ ላይ የአድማስ ምልክት ባደረገ ጊዜ፤* ኢዮ26፥10 ይመ።

8፥28 *የውቅያኖስን ምንጮች፤* በመሬት ላይ የሚገኙ ምንጮችና ወራጅ ውሆች ናቸው (የ3፥20 ማብ ይመ፤ ከዘፍ7፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥29 *ለባሕር ድንበርን፤* ዘፍ1፥9፤ ኢዮ38፥10-11፤ መዝ104፥9 ይመ። *የምድርንም መሠረቶች፤* የ3፥19 ማብ ይመ።

8፥30 *ባለሙያ፤* እንዲህ ያለው ባለሙያ አንዳንድ ጊዜ ጥበበኛ ይባል ነበር፤ ለምሳሌ ንድፉን በማውጣት የመገናኛውን ድንኳን የሠራውን ባስልኤልን ተመልከት (ዘፀ31፥3)። እዚህ ላይ ቃሉ በአጽንዖት የሚያሳየው በአፈጣጠር ወቅት በጕልሕ የተገለጸውን ጥበብ ነው። *ሐሤት እያደረግሁ ... በደስታ እሞላ፤* ዓለም ሲፈጠር የተሰማውን የመላእክት እልልታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኢዮ 38፥7)።

8፥31 *በሰው ልጆች ደስ እሰኝ፤* ከቍ4 ጋር ያነጻጽሩ፤ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው፣ የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ ወይም የበላይ መሆኑን ያመለክታል (ዘፍ1፥26-28 ይመ)።

8፥32 *ቡሩካን፤* ጥበብን ከማግኘት ጋር የተያያዙ በረከቶች በ3፥13-18 ላይ ተመልክተዋል፤ እንዲሁም መዝ119፥1-2፤ 128፥1 ይመ።

8፥34 *ደጃፌ ላይ የሚጠብቅ፤* በዝሙት አዳሪዋ አጠገብ እንዳይታለፍ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (5፥8)።

8፥35 *ሕይወትን ያገኛልና፤* 3፥2፤ 4፥22 እና ማብ ይመ። *ሞገስን፤* 3፥4፤ 12፥2፤ 18፥22 ይመ።

8፥36 *የሚጠሉኝም ሁሉ ሞትን ይወዳሉ፤* 1፥28-33፤ 5፥12:23፤ 7፥27 እና ማብ ይመ።

9፥1 *ቤቷን ሠራች፤* ጥበብናስንፍና ሁለቱም የሰው ልጆችን የሚጋብዙበት ቤት አላቸው (14፥7:8፤ 8፥34 ይመ)፤ ጥበብ ግን በእርሷ ዘንድ ስንፍና ስለሌለ (ቍ14)፣ ቤቷን ሠርታለች (የ14፥1 ማብ ይመ)። የልባምን ሴት መልካም ምግባር ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (31፥10-27)። *ሰባቱን ምሰሶዎቿንም፤* ትልቅ ቤት መሆኑን ያመለክታል፤ "ሰባት" የጥበብን ሰባት ዐበይት መልኮች ሳያመለክት አይቀርም።

*9፥2፤* ቍ17 እና ማብ ይመ። ጥበብ ያዘጋጀችው ግብዣ በ7፥17 ላይ ዝሙት አዳሪዋ ሽቶ በማርከፍከፍ ካዘጋጀችው መኝታ ጋር ያነጻጽራል። *የወይን ጠጇን ጠመቀች፤* ይበልጥ ተወዳጅ ለማድረግ ማጣፈጫ ጨምራበታለች (ማሕ8፥2 ይመ)።

9፥3 *ከከተማዪቱም ከፍተኛ ቦታ ተጣራች፤* በቍ14 ላይ ስለ ስንፍና የተነገረውን ይመ፤ እንዲሁም 8፥1-3 ይመ።

9፥4 በቍ16 ላይ ስንፍና ተመሳሳይ ግብዣ ታቀርባለች። *ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ፤* 1፥4 እና 8፥5 ማብ ይመ። *ማመዛዘን ለጐደላቸው፤* ቍ16፤ 7፥7 ይመ።

*9፥5፤* በቍ2 ላይ ጥበብ ለሰው ልጆች የሰጠቻቸው ስጦታዎች እንደ ትልቅ ግብዣ ተቈጥረው በተምሳሌት ተገልጠዋል (ኢሳ 55፥1-2 እና ማብ ይመ፤ ከዮሐ6፥27:35 ጋር ያነጻጽሩ)።

9፥6 *የሞኝነት መንገዳችሁን ተዉ፤* 1፥22 ይመ። *በሕይወት ትኖራላችሁ፤* ቍ 11፤ 8፥35፤ እንዲሁም የ3፥2 ማብ ይመ።

9፥7 *ፌዘኛን የሚገሥጽ ሁሉ ስድብን በራሱ ላይ ያመጣል፤* 1፥22 እና ማብ ይመ። ከ1፥30 ጋር ያነጻጽሩ። *ውርደት ያገኘዋል፤* ከ1ጴጥ4፥4 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥8 *ይጠላሃል፤* 15፥12:32 ይመ። *ጠቢብን ገሥጸው፤ ይወድሃል፤* 10፥8፤ 17፥10 ይመ።

9፥9 *ይበልጥ ጥበበኛ ይሆናል፤* 18፥15፤ 21፥11 ይመ።

*9፥10-12፤* ይህ የጥበብ ማጠቃለያ ቃል በም1-9 ላይ ያለውን መልእክት ዐቢይ ሐሳብ ባጭሩ ያቀርባል።

[10]"የጥበብ *መጀመሪያ እግዚአብሔርን*
*መፍራት* ነው፤
ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው፤
[11]*ዘመንህ* በእኔ ምክንያት ይረዝማልና፤
ዕድሜም በሕይወትህ ላይ
ይጨመርልሃል::
[12]ጠቢብ ብትሆን ጥበበኛነትህ ለራስህ ነው፤
ፌዘኛ ብትሆን የምትጐዳው ያው
አንተው ነህ::"
[13]ጥበብ የለሽ ሴት ለፍላፊ ናት፤
እርሷም ስድና ዕውቀት የለሽ ናት::
[14]በቤቷ ደጃፍ ላይ ትጐለታለች፤
በከተማዪቱ ከፍተኛ ቦታ በመቀመጫ
ላይ ትቀመጣለች::
[15]በዚያ የሚያልፉትን፣
መንገዳቸውን ይዘው የሚሄዱትን
ትጣራለች::
[16]እርሷም ማመዛዘን ለጐደላቸው፣
"ማስተዋል የሌላችሁ ሁሉ ወደዚህ ኑ!"
ትላለች::
[17]የስርቆት ውሃ ይጣፍጣል፤
ተሸሽገው የበሉት ምግብ ይጥማል::"
[18]እነርሱ ግን ሙታን በዚያ እንዳሉ፣
ተጋባዦቿም በሲኦል[a] ጥልቀት ውስጥ
እንደ ሆኑ አያውቁም::

## የሰሎሞን ምሳሌዎች

# 10

የሰሎሞን ምሳሌዎች፤
ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፤
ተላላ ልጅ ግን ለእናቱ ሐዘንን
ያተርፋል::
[2]ያላግባብ የተገኘ ሀብት አይጠቅምም፤
ጽድቅ ግን ከሞት ይታደጋል::
[3]እግዚአብሔር ጻድቁ እንዲራብ
አያደርግም፤
የክፉዎችን ምኞት ግን ያጨናግፋል::
[4]ሰነፍ እጆች ሰውን ያደኸያሉ፤
ትጉ እጆች ግን ብልጽግናን ያመጣሉ::
[5]ሰብሉን በበጋ የሚሰበስብ ጠቢብ ልጅ
ነው፤
በመከር ጊዜ የሚተኛ ግን ውርደት
ይከተለዋል::
[6]በረከት በጻድቃን ራስ ላይ ነው፤
መዓት ግን የክፉዎችን አፍ ይዘጋል::[b]
[7]የጻድቃን መታሰቢያቸው በረከት ነው፤
የክፉዎች ስም ግን እንደጠፋ ይቀራል::
[8]በልቡ ጠቢብ የሆነ ትእዛዝ ይቀበላል፤
ለፍላፊ ተላላ ግን ወደ ጥፋት ያመራል::
[9]ሐቀኛ ሰው ያለ ሥጋት ይራመዳል፤
በጠማማ ጐዳና የሚሄድ ግን ይጋለጣል::

9፥7 ምሳ23፥9፤ ማቴ7፥6
9፥8 መዝ141፥5፤ ምሳ15፥12
9፥9 ምሳ1፥5፥7፤ 12፥15፥13፥10፥14፥6፤15፥31፤19፥25
9፥10 ዘዳ4፥6፤መዝ 22፥3፤ምሳ1፥7፥30፥3
9፥11ዘፍ15፥15፤ዘዳ 11፥21፤ምሳ3፥1-2፤ 10፥27
9፥13 ምሳ5፥6፤ 7፥11
9፥14 ቁ-3፤ሕዝ 16፥25
9፥15 ምሳ1፥20
9፥16 ምሳ1፥22
9፥17 ምሳ20፥17
9፥18 ምሳ2፥18፤ 7፥26-27
10፥1 1ነገ4፥32፤ ምሳ 1፥1፥15፥20፤ 17፥21፥19፥13፥23፥2 2-25፥27፥11፥29፥3
10፥2 ቁ-16፤ምሳ 11፥4፥11፥19፥12፥28 ፥13፥11፥21፥6
10፥3 ምሳ13፥25፤ ማቴ6፥25-34
10፥4 ምሳ6፥6-8፤ 12፥24፥19፥15፥21፥5 ፥24፥30-34
10፥5 ምሳ24፥30-34
10፥6 ቁ-8፥11፥14፤ ምሳ12፥13፥13፥3፤ ሚክ10፥12
10፥7 ኢዮ18፥17፤ መዝ 9፥6፥112፥6፤ መዝ109፥13
10፥8 ቁ-14፤ኢዮ 33፥33፤ማቴ7፥24-27
10፥9 መዝ25፥21፤ 37፥24፤ምሳ28፥18፤

[a]18 ወይም *መቃብር*
[b]6 ወይም *የክፉዎች አፍ ግን መዓትን ይሰውራል*፤ እንዲሁም ቁ 11 ይመ::

9፥10 *የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው*፤ 1፥7 እና ማብ ይመ:: *ቅዱሱንም ... ማወቅ*፤ የ2፥5 ማብ ይመ:: "ቅዱሱ" የሚለው ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ ከዚህ ሌላ የሚገኘው በ30፥3 ላይ ብቻ ነው::

9፥11 *ዘመንህ ... ይረዝማልና*፤ የ3፥2 ማብ፤ እንዲሁም 3፥16፤ 10፥27፤ 14፥27፤19፥23 ይመ::

9፥12 *ጥበበኛነትህ ለራስህ ነው*፤ ጥበብ ከምትሰጣቸው ስጦታዎች ውስጥ አንዳንዶቹን በ3፥16-18፤ በ4፥22 ማብ ይመ:: *የምትጐዳው*፤ 1፥26 እና ማብ ይመ፤ 19፥29 ይመ::

9፥13 *ጥበብ የለሽ ሴት ለፍላፊ ናት*፤ "መለፍለፍ" በሰው የተመሰለችውን ስንፍናን በ2፥16 እና በ7፥11 ላይ ከተጠቀሰችው "ዘማዊና ዘልዛላ ሴት" ጋር ያያይዛታል:: *ስድና ዕውቀት የለሽ*፤ ማስተዋል፣ ጭምትነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር የላትም (1፥3-4፡ 22፡29፤ 5፥6 ይመ)::

9፥14 *ትጐለታለች*፤ በቍ1 ላይ ጥበብ ቤቷን እንዴት እን ደሠራች ይመ::

9፥15 *ትጣራለች*፤ በቍ3፤ 8፥1፡4 ላይ ያለውን የጥበብን ጥሪ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

*9፥16*፤ የስንፍና አጠራር ከጥበብ አጠራር ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ4 እና የ1፥21 ማብ ይመ)::

9፥17 *የስርቆት ውሃ ... ተሸሽገው የበሉት ምግብ*፤ ስን ፍና ያዘጋጀችው "ግብዣ"፣ ከጥበብ ወይንና ሥጋ (ቍ2) ጋር ሲነጻ ጸር በጣም መናኛ ነው፤ ያውም እንኳ የተሰረቀ ነው፤ ይህ "ምግብ" ዘማዊት ሴት ባቀረበችው ሕገወጥ ሩካቤ ሥጋ የተገኘ ውን ስርቆት ደስታ ያመለክታል (7፥18 እና ማብ ይመ፤ ከ5፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ):: *ይጥማል*፤ ይሁን እንጂ ኢዮ20፥12-14 ይመ::

9፥18 *ሙታን በዚያ እንዳሉ ተጋባዦቿም በሲኦል ጥልቀ ት ውስጥ እንደ ሆኑ*፤ ከ2፥18፤5፥5፤7፥27 ጋር ተመሳሳይ ነው::

10፥1 *የሰሎሞን ምሳሌዎች*፤ ከዚህ ምዕራፍ ጀምሮ እስከ 22፥16 ድረስ ለሰፈሩት ምሳሌዎች ሁሉ የተሰጠ ርእስ ነው:: በዕ ብራይስጥ፣ "ሰሎሞን" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት የተነባቢ ፊደ ላት አኃዛዊ ዋጋ ጠቅላላ ድምር 375 ሲሆን፣ ይኸውም ከ10፥1 ጀምሮ እስከ 22፥16 ድረስ ከሰፈሩት 375 ምሳሌዎች ጋር እኩል ነው፤ እነዚህም በዛ ያለ ቍጥር ካላቸው ምሳሌዎች የተመረጡ ናቸው (ከ1ነገ4፥32 ጋር ያነጻጽሩ):: *ጠቢብ ልጅ*፤ ቍ5፤ 15፥20፤ 17፥21፡25፤ 29፥3፡15 ይመ፤ በሌላ ቦታ በሚገኝ ስብስብ "ጻድቅ ሰው" (23፥24-25) እና፣ "ሕግን የሚጠብቅ ሰው" (28፥7) ተብሎ ተገልጾአል:: "አላዋቂ ልጅ" ለሥነ ምግባር እውነት ግድ የለሽ የሆነና ማስተዋል የጐደለው፣ ደንታ ቢስ በመሆንም ወደ ጥፋት ጐዳና የሚጓዝ ልጅ ነው::

10፥2 *ያላግባብ የተገኘ ሀብት አይጠቅምም*፤ ወዲያውኑ ይወድማል (21፥6)፤ የእግዚአብሔርንም ፍርድ ያስከትላል (1፥19 እና ማብ 10፥16፤ ሕዝ7፥19 ይመ):: *ጽድቅ ግን ከሞት ይታደ ጋል*፤ 2፥16-18፤ 3፥2፤ 13፥21 ይመ::

10፥3 *ጻድቁ እንዲራብ አያደርግም*፤ 13፥25፤ 28፥25፤ መዝ34፥9-10፤ 37፥19-25 ይመ:: ይሁን እንጂ የምሳ3፥2 ማብ ይመ:: *የክፉዎችን ምኞት ግን ያጨናግፋል*፤ ዘኍ11፥34፤ መዝ 112፥10 ይመ::

*10፥4*፤ ብዙዎቹ ምሳሌዎች ታታሪነትንና የሚያስገኘውን ጥቅም ያሞግሳሉ፤ ስንፍናን ግን የረሀብና የድኽነት መንሥኤ ነው በማለት ይኰንናሉ (16፥6-11 እና ማብ፤ 12፥11፡24፡27፤ 13፥4፤ 14፥23፤ 18፥9፤ 27፥23-27፤ 28፥19 ይመ)::

10፥5 *በመከር ጊዜ የሚተኛ*፤ የሚከናወን ሥራ እያለ መተኛት በ6፥9-11፤ 19፥15፤ 20፥13 ላይም ተኰንኖአል:: ውር ደት ይከተለዋል፤ 17፥2፤ 28፥7፤ 29፥15 ይመ::

10፥6 *በረከት*፤ የእግዚአብሔር ስጦታና ችሮታ ነው (3፥13-18፤ 28፥20፤ ዘፍ49፥26፤ ዘዳ33፥16 ይመ):: *ራስ*፤ 11፥26 ይመ:: *መዓት ግን የክፉዎችን አፍ ይዘጋል*፤ በምላሳቸው የሚሩት እሳት ውሎ አድሮ ራሳቸውን ያጠፋቸዋል (መዝ140፥9፤ ዕን2፥17 ይመ፤ ይሁን እንጂ ከምሳ2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥7 *የጻድቃን መታሰቢያቸው*፤ ቅዱሳንን ለማስታወስ ነው (22፥1 ይመ)::

10፥8 *ጠቢብ...ትእዛዝ ይቀበላል*፤ 9፥8-9 እና ማብ ይመ:: *ለፍላፊ ተላላ ... ጥፋት ያመራል*፤ ቍ10፡14፡18፡19 ይመ::

10፥9 *ሐቀኛ ሰው ያለ ሥጋት ይራመዳል*፤ 2፥7 እና ማብ፤ እንዲሁም 3፥23፤13፥6፤መዝ23፥4፤ ኢሳ33፥15-16 ይመ:: *በጠማማ ጐዳና የሚሄድ ግን ይጋለጣል*፤ 26፥26፤ ሉቃ8፥17፤ 1ጢሞ5፥24-25፤ 2ጢሞ3፥9 ይመ::

10በተንኰለኛ ዐይን የሚጠቅስ ሐዘን
ያስከትላል፤
ለፍላፊ ተላላም ወደ ጥፋት ያመራል።
11የጻድቅ አንደበት የሕይወት ምንጭ ናት፤
መዓት ግን የክፉዎችን አፍ ይዘጋል።
12ጥላቻ ጠብን ያነሣሣል፤
ፍቅር ግን ስሕተትን ሁሉ ይሸፍናል።
13ጥበብ በአስተዋይ ሰው ከንፈር ትገኛለች፤
በትር ግን ማመዛዘን ለጐደለው ሰው
ጀርባ ነው።
14ጠቢባን ዕውቀት ያከማቻሉ፤
የተላላ አንደበት ግን ጥፋትን ይጋብዛል።
15የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው
ነው፤
ድኽነት ግን የድኾች መጥፊያ ናት።
16የጻድቃን ደመወዝ ሕይወት
ታስገኝላቸዋለች፤
የክፉዎች ትርፍ ግን ቅጣትን
ታመጣባቸዋለች።
17ተግሣጽን ነቅቶ የሚጠብቅ የሕይወትን
መንገድ ያሳያል፤
እርምትን የማይቀበል ግን ሌሎችን ወደ
ስሕተት ይመራል።
18ጥላቻውን የሚሸሽግ ሐሰተኛ አንደበት
ያለው ነው፤
ሐሜትን የሚዘራ ሁሉ ተላላ ነው።
19 ከቃላት ብዛት ኀጢአት አይታጣም፤
አንደበቱን የሚገታ ግን ጠቢብ ነው።
20የጻድቅ አንደበት የነጠረ ብር ነው፤
የክፉ ሰው ልብ ግን ርባና የለውም።
21የጻድቃን ከንፈሮች ብዙዎችን ያንጻሉ፤
ተላሎች ግን ከማመዛዘን ጒድለት
ይሞታሉ።
22የእግዚአብሔር በረከት ብልጽግናን
ታመጣለች፤
መከራንም አያክልባትም።
23ተላላ ሰው በክፉ ተግባር ይደሰታል፤
አስተዋይ ሰው ግን በጥበብ ደስ ይለዋል።
24ክፉ ሰው የፈራው ይደርስበታል፤
ጻድቅ የሚመኘው ይፈጸምለታል።
25ዐውሎ ነፋስ ሲነሣ ክፉዎች ተጠራርገው
ይወሰዳሉ፤
ጻድቃን ግን ለዘላለም ጸንተው ይኖራሉ።
26ሆምጣጤ ጥርስን፣ ጢስ ዐይንን
እንደሚጐዳ፣
ሰነፍም ለሚልኩት እንዲሁ ነው።
27እግዚአብሔርን መፍራት ዕድሜን
ያረዝማል፤
የክፉዎች ዕድሜ ግን በአጭር ይቀጫል።
28የጻድቃን አለኝታ ደስታ ነው፤
የክፉዎች ተስፋ ግን ከንቱ ሆኖ
ይቀራል።

10፥10 መዝ35፥19
10፥11 ቍ6፡27፤ ምሳ 3፥18፤4፥23፤11፥30፤13፥12፡14፡19፤14፥27፤15፥4፤16፥22
10፥12 ምሳ17፥9፤ 1ቆሮ13፥4-7፤ 1ጴጥ4፥8
10፥13 ቍ31፤ዘጸ 25፥2፤መዝ37፥30፤ምሳ14፥3፤15፥7፤26፥3
10፥14 ቍ6፤መዝ 59፥12፤ምሳ11፥13፤12፥23፤14፥3፤18፥6፡7 ማቴ12፥37
10፥15 ምሳ18፥11፤ ምሳ19፥7
10፥16 ዘጸ30፥15፤ ምሳ11፥18-19፤15፥6፤ ሮሜ6፥23
10፥17 ምሳ6፥23፤ 15፥5
10፥18 መዝ31፥18
10፥19 ኢዮ1፥22፤ 6፥24፤ምሳ17፥28፤20፥25፤21፥33፤ያዕ1፥19፤3፥2-12
10፥21 ምሳ5፥22-23፤ኢሳ5፥13፤ኤር 5፥4፤ሆሴ4፥1፡6፡14
10፥22 ዘፍ13፥2፤ 49፥ 25፤ዘጸ8፥18፤ዘኍ25፥9፤መዝ128፥2
10፥23 ምሳ2፥14
10፥24 ዘፍ42፥36፤ መዝ37፥4፤145፥17-19፤ኢሳ65፥7፤ሕዝ 11፥8
10፥25 መዝ20፥8፤ ምሳ12፥3፡7፤ማቴ 7፥24-27
10፥26 ምሳ13፥17፤ 25፥13፤26፥6፤ኢሳ 65፥5
10፥27 ቍ11፤ዘጸ 11፥9፤ኢዮ15፥32፤ ምሳ9፥10-11፤19፥23፤22፥4
10፥28 አስ7፥10፤ኢዮ8፥13፤መዝ 112፥10፤ምሳ11፥7

10፥10 *በተንኰለኛ ዐይን የሚጠቅስ፤* የ6፥13 ማብ ይመ። *ለፍላፊ ተላላም፤* ቍ8 እና ማብ ይመ።

10፥11 *የሕይወት ምንጭ፤* ሕይወትን የምትሰጥ ጥበብ ናት (13፥14፤ 14፥27፤ 16፥22 እንዲሁም መዝ 37፥30 ይመ)። *መዓት ... ይዘጋል፤* ዐመፅ አንደበቱን ይቈጣጠራል ማለት ሳይሆን አይቀርም፤ ይሁን እንጂ የቍ6 ማብ ይመ።

10፥12 *ጠብን ያነሣሣል፤* የ6፥14 ማብ ይመ። *ስሕተትን ሁሉ ይሸፍናል፤* ይቅርታ እንዲነግሥ ያደርጋል (17፥9 ይመ)። ይህ ስንኝ በያዕ5፥20፤ 1ጴጥ4፥8 ላይ ተጠቅሶአል።

10፥13 *በትር ... ጀርባ፤* 14፥3፤ 19፥29 ይመ።

10፥14 *ዕውቀት ያከማቻሉ፤* ከሰነፍ ልፍለፋ ይልቅ ማለት ነው፤ ጠቢባን ግን ዕውቀትን ገንዘብ በማድረጋቸው ባለጠጎች ይሆናሉ፤ 2፥1 እና ማብ ይመ። *ጥፋትን ይጋብዛል፤* አላዋቂ ወይም ሰነፍ የሆነ ሰው ለአፉ ለከት ስለ ሌለው፣ በራሱ ላይ ችግርን ይጋብዛል (ቍ8፡10፤ 13፥3 ይመ)።

10፥15፤ ስለ ሀብትና ድኽነት የተሰጠ አስተያየት ነው። *የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው ነው፤* ሀብት ወዳጅ ያፈራል (14፥20፤ 19፥4)፤ *መታፈርን* ያስገኛል (18፥23፤ 22፥7)፤ ዘላቂ ዋስትና የሚገኘው ግን በእግዚአብሔር ብቻ ነው (መዝ 52፥7)። *ድኽነት ... የድኾች መጥፊያ ናት፤* ድኽነት ተቀባይነትን አያስገኝም (18፥23)፤ ወዳጅን ያርቃል (19፥4፡7)፤ ዋስትናም ይሰጣል፤ ቍ4 እና ማብ ይመ።

10፥16 *የጻድቃን ደመወዝ ሕይወት ታስገኝላቸዋለች፤* ሀብት ሳይሆን (ቍ15) ጽድቅ የሕይወት ዋስትና የሚሰጠው ነው (የ3፥2 ማብ፤ እንዲሁም 3፥16፤ 4፥22 ይመ)። *የክፉዎች ትርፍ ግን ቅጣትን ታመጣባቸዋለች፤* 1፥13፡31 እና ማብ ይመ። "የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነው" (ሮሜ6፥23)።

10፥17 *የሕይወትን መንገድ፤* የ6፥23 ማብ ይመ። *እርምትን የማይቀበል፤* 5፥12፤ 15፥10 ይመ።

10፥18 *ጥላቻውን የሚሸሽግ* ወዳጅ በመምሰል (26፥24፡26፡28 ይመ)።

10፥20 *የነጠረ ብር፤* ጻድቅ የሚናገረው ነገር ክቡር ነው፤ ትልቅ ዋጋም አለው (3፥14፤ 8፥10፤ 25፥11 ይመ)። *የክፉ ሰው ልብ፤* ሐሳቡና ዕቅዱ ጠማማ ነው (6፥14፡18 ይመ)።

10፥21 *ብዙዎችን ያንጻሉ፤* ቍ11 እና ማብ ይመ። *ከማመዛዘን ጒድለት ይሞታሉ፤* 5፥23 እና ማብ፤ እንዲሁም 7፥7፤ 9፥16 ይመ።

10፥22 *የእግዚአብሔር በረከት ብልጽግናን ታመጣለች፤* ብልጽግና የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ የሰው የድካም ፍሬ አይደለችም (የቍ6፤ የ3፥10፤ እንዲሁም 8፥21፤ ዘፍ24፥35፤ 26፥12 ይመ)። *መከራንም አያክልባትም፤* በቍ2 ላይ፣ "ያላግባብ የተገኘ" ሀብት እንደ ተባለው አይደለም (የቍ2 ማብ ይመ)፤ ከ15፥6 ጋር ያነጻጽሩ።

10፥23 *በክፉ ... ይደሰታል፤* 2፥15፤ 15፥21፤ 26፥19 ይመ።

10፥24 *ክፉ ሰው የፈራው፤* መከራንና ጭንቀትን ነው (1፥27 እና ማብ፤ 3፥25፤ ኢዮ15፥21፤ ኢሳ66፥4 ይመ)። *ጻድቅ የሚመኘው፤* መዝ37፥4፤ 145፥19፤ ማቴ5፥6፤ 1ዮሐ5፥14-15 ይመ።

*10፥25፤* ቤቱን በዐለት ላይ የሠራውን ልባሙን ሰውና ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራውን ሰነፉን ሰው ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ማቴ7፥24-27)። *ክፉዎች ይወሰዳሉ፤* መዝ37፥10፤ ኢሳ28፥18 ይመ። *ጻድቃን ... ጸንተው ይኖራሉ፤* የማይናወጡና የማይደነግጡ ሆነው (3፥25 እና ማብ፤ እንዲሁም 12፥3፡7፤ 14፥11 መዝ 15፥5፤ 1ቆሮ15፥58 ይመ)።

10፥26 *ሆምጣጤ፤* 25፥20፤ መዝ69፥21 ይመ። *ሰነፍም፤* የ6፥6 ማብ ይመ። *ለሚልኩት፤* እንደ መልእክተኛ (ከ25፥13፤ 26፥6 ጋር ያነጻጽሩ) ወይም እንደ ሠራተኛ በመሆን ዐደራ ሲጣልበት ማለት ነው።

10፥27 *እግዚአብሔርን መፍራት፤* የ1፥7 ማብ ይመ። *ዕድሜን ያረዝማል፤* የ3፥2 ማብ ይመ። *ዕድሜ ... በአጭር ይቀጫል፤* ኢዮ22፥16፤ መዝ37፥36፤ 55፥23 ይመ።

10፥28 *የጻድቃን አለኝታ፤* ቍ24 እና ማብ፤ መዝ9፥18 ይመ። *ደስታ፤* የተመኙት ወይም የልፋታቸው ዋጋ በመገኘቱ ነው (ከ11፥23 ጋር ያነጻጽሩ)። *የክፉዎች ተስፋ ግን ከንቱ ሆኖ*

29 የእግዚአብሔር መንገድ ለጻድቃን
መጠጊያ፣
ክፉ ለሚያደርጉ ግን መጥፊያቸው ነው።
30 ጻድቃን ፈጽሞ አይነቀሉም፤
ክፉዎች ግን በምድር አይኖሩም።
31 የጻድቃን አንደበት ጥበብን ያፈልቃል፤
ጠማማ ምላስ ግን ትቈረጣለች።
32 የጻድቃን ከንፈሮች ተገቢውን ነገር
ያውቃሉ፤
የክፉዎች አንደበት ግን የሚያውቀው
ጠማማውን ብቻ ነው።

# 11

እግዚአብሔር የተጭበረበረ
ሚዛንን ይጸየፋል፤
ትክክለኛ መለኪያ ግን ደስ ያሰኘዋል።
2 ትዕቢት ስትመጣ ውርደትም ትከተላለች፤
በትሑት ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች።
3 ቅኖችን ትክክለኛነታቸው ትመራቸዋለች፤
ወስላቶች ግን በገዛ አታላይነታቸው
ይጠፋሉ።
4 በቍጣ ቀን ሀብት ፋይዳ የለውም፤
ጽድቅ ግን ከሞት ትታደጋለች።
5 ለፍጹማን ሰዎች ጽድቃቸው መንገዳቸውን
ታቃናላቸዋለች፤
ክፉዎች ግን በገዛ ክፋታቸው
ይወድቃሉ።
6 ቅኖችን ጽድቃቸው ትታደጋቸዋለች፤
ወስላቶች ግን በክፉ ምኞታቸው
ይጠመዳሉ።

10፥29 ምሳ21፥15፤ ሆሴ14፥9
10፥30 መዝ37፥9፡ 28-29፤ምሳ2፥20-22
10፥31 ቍ13፤መዝ 52፥4፤ምሳ15፥2፥31፥ 26
10፥32 መዝ59፥7፤ መክ10፥12
11፥1 ዘሌ19፥36፤ ዘዳ25፥13-16፤ኢዮ 6፥2፤ምሳ20፥10፡23፤ 6፥11፤ሕዝ45፥10
11፥2 ምሳ16፥18፤ 18፥12፤29፥23
11፥3 ቍ5፤ምሳ13፥6
11፥4 ኢዮ20፥20፤ ምሳ10፥2፤ሕዝ7፥19 ፤27፥27
11፥5 ቍ3፤1ነገ 8፥36፤ምሳ21-23፤ 13፥6፤21፥7
11፥6 አስ7፥9
11፥7 ኢዮ8፥13፤ ምሳ10፥28
11፥8 ምሳ21፥18
11፥9 ምሳ12፥6፤ ኤር45፥5
11፥10 2ነገ11፥20፤ አስ8፥17
11፥11 ምሳ14፥34፤ 29፥8
11፥12 ኢዮ6፥24፤ ምሳ14፥21
11፥13 ምሳ10፥14፤ 20፥19
11፥14 2ሳሙ15፥34 ፤ምሳ15፥22፤20፥18 ፤24፥6
11፥15 ምሳ6፥1፤ 17፥18፤22፥26-27

7 ክፉ ሰው ሲሞት ተስፋው ከንቱ
ትሆናለች፤
በኀይሉ የተመካበትም ሁሉ እንዳልነበረ
ይሆናል።
8 ጻድቅ ከመከራ ይድናል፤
ይልቁን መከራው በክፉው ላይ
ይደርሳል።
9 ክፉ ሰው ባልንጀራውን በአፉ ያጠፋል፤
ጻድቃን ግን በዕውቀት ያመልጣሉ።
10 ጻድቃን ሲሳካላቸው ከተማ ደስ ይላታል፤
ክፉዎች ሲጠፉ እልልታ ይሆናል።
11 በቅኖች በረከት ከተማ ከፍ ከፍ ትላለች፤
በክፉዎች አንደበት ግን ትጠፋለች።
12 ማመዛዘን የጐደለው ሰው ባልንጀራውን
ያንኳስሳል፤
አስተዋይ ግን አንደበቱን ይገዛል።
13 ሐሜተኛ ምስጢር አይጠብቅም፤
ታማኝ ሰው ግን ምስጢር ይጠብቃል።
14 በአመራር ጉድለት መንግሥት
ይወድቃል፤
የመካሮች ብዛት ግን ድልን እርግጠኛ
ያደርጋል።
15 ለማይታወቅ ሰው ዋስ የሚሆን መከራ
ያገኘዋል፤
ዋስትና ለመስጠት እጅ የማይመታ ግን
ምንም አይደርስበትም።
16 ርኅሩኅ ሴት ክብር ታገኛለች፤

*ይቀራል፤* 11፥7፡23 ይመ።

10፥29 *የእግዚአብሔር መንገድ፤* እርሱ የቀየሰው ጐዳና፣ ጥበብ የተሞላ ሕይወት (መዝ27፥11፤ 143፥8፤ ማቴ22፥16፤ ሐሥ 18፥25 ይመ)። *ክፉ ለሚያደርጉ ግን መጥፊያቸው፤* የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ፈቃደኞች ባልሆኑት ላይ ፍርድ ይመጣል (21፥15፤ 2ቆሮ2፥15-16፤ 2ጴጥ2፥21 ይመ)።

10፥30 *ፈጽሞ አይነቀሉም፤* 2፥21 እና ማብ፤ 10፥23፤ 12፥3፤ መዝ 125፥1 ይመ። *በምድር አይኖሩም፤* የ2፥22 ማብ ይመ።

10፥31 *ጠማማ ምላስ፤* የ2፥12 ማብ ይመ። *ትቈረጣለች፤* መዝ12፥3 ይመ፤ ከማቴ5፥30 ጋር ያነጻጽሩ።

11፥1 *የተጭበረበረ ሚዛንን ይጸየፋል፤* ተመሳሳይ ውግዘት በሙሴ ሕግ (ዘሌ19፥35 እና ማብ ይመ) እና በነቢያት መጻሕፍት ይገኛል (አሞ8፥5፤ ሚክ6፥11)። እንዲሁም 16፥11፤ 20፥10፡ 23 ይመ። *ትክክለኛ መለኪያ፤* መመዘኛውን ድንጋይ በሚዛን ላይ በማስቀመጥ ብር ይመዘን ነበር። ትክክል ያልሆነን ሚዛን ለማጭበርበሪያነት ይጠቀሙበት ነበር።

11፥2 *ትዕቢት ስትመጣ፣ ውርደትም ትከተላለች፤* ከጥፋት ጋር ሆና ማለት ነው (16፥18 ይመ፤ በኢሳ10፥12 እና እንዲሁም በ14፥13-15 ላይ ትዕቢተኛዋ አሦር እንዴት እንደ ተዋረደች ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)። *በትሑት ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች፤* ከክብር ጋር ማለት ነው (የ15፥33 ማብ ይመ)።

11፥3 *ትክክለኛነታቸው ትመራቸዋለች፤* በዘፍ39፥6-12 የዮሴፍን ድርጊት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። *ወስላቶች ... ይጠፋሉ፤* 2፥22 እና ማብ እንዲሁም 19፥3 ይመ። *አታላይነታቸው፤* ከሉቃ 20፥23 ጋር ያነጻጽሩ።

11፥4 *በቍጣ ቀን፤* የፍርድን ቀን ያመለክታል (ኢሳ 10፥3፤ ሶፎ1፥18 ይመ)። *ጽድቅ ግን ከሞት ትታደጋለች፤* 2፥16-18፤ 3፥2፤ 10፥2፤ 13፥21 ይመ።

11፥5 *ለፍጹማን፤* የ2፥7 ማብ ይመ። *መንገዳቸውን ታቃናላቸዋለች፤* ከግባቸው ይደርሱ ዘንድ ታስችላቸዋለች (የ3፥6 ማብ፤ እንዲሁም ቍ3፤ 10፥9 ይመ)። *ክፉዎች ... ይወድቃሉ፤* 5፥22 እና ማብ ይመ።

11፥6 *ጽድቃቸው ትታደጋቸዋለች፤* ቍ3-4 ይመ። *ይጠመዳሉ፤* 5፥22 እና ማብ ይመ።

11፥7 *ተስፋው ከንቱ ትሆናለች፤* ቍ23፤ 10፥28 ይመ።

11፥8 *ጻድቅ ከመከራ ይድናል፤* የእግዚአብሔርን መንገድ የሚከተሉ ሁሉ ምንም ችግር አያጋጥማቸውም ማለት አይደለም። ችግር ሲያጋጥማቸው ግን፣ እግዚአብሔር በወሰነው ቀን ከችግራቸው እንደሚላቀቁ የተረጋገጠ ነው። በመጽሐፈ አስቴር በመርዶክዮስ ላይ ሊደርስ የነበረውን መከራና የሐማን መሰቀል ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

11፥9 *ባልንጀራውን ... ያጠፋል፤* የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ (ከ10፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። *በዕውቀት፤* የክፉዎችን ዕቅድ በማስተዋልና ሀቅ ማዛባታቸውን በመረዳት ሊሆን ይችላል (ከዮሐ2፥25 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥10 *ከተማ ደስ ይላታል፤* 28፥12፤ 29፥2 ይመ። ስለ ዚህ የዚያች ከተማ ሕይወት ራሱ የጥበብ ትምህርት ቤት ነው (የ1፥21 ማብ ይመ)። *እልልታ፤* በአሦር መውደቅ የነበረውን ደስታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኢሳ30፥32፤ ናሆ3፥19 ይመ፤ ከ2ዜና 21፥20 ጋር ያነጻጽሩ)።

11፥11 *በቅኖች በረከት፤* የእነርሱ መልካም ዝና፣ ለፍትሕ ያላቸው በጎ ምኞትና እንዲሁም ብልጥግናቸው (ቍ10) ለከተማዋ ሞገስ ያስገኝላታል። *በክፉዎች አንደበት፤* በማታለላቸው፣ በሸንፈታቸውና ጥልን በማዛመታቸው አገር ትጠፋለች (ቍ9፤ 6፥12-14 ይመ)።

11፥12 *ባልንጀራውን ያንኳስሳል፤* ንቀቱን በግልጽ ያሳያል (10፥18፤ 14፥21 ይመ)። *አንደበቱን ይገዛል፤* 10፥19 ይመ።

11፥14 በ15፥22፤ 20፥18፤ 24፥6 ላይ የሚገኘው አቻ ሐሳብ ይመ። *መካሮች፤* 2ሳሙ16፥23፤ ኢሳ1፥26 ይመ።

*11፥15-16፤* ከ6፥1 ጋር ያነጻጽሩ። *ርኅሩኅ ሴት ክብር ታገኛለች፤* ገደብ የሌለው የኀይል እርምጃ ግን ዐላፊ ጠፊ የሆነውን ሀብት ብቻ ያስገኛል።

*11፥15፤* የ6፥1 ማብ ይመ።

*11፥16፤* መልካም ስም ከብዙ ሀብት እንደሚበልጥ (22፥

ጉልበተኛ ሰዎች ግን ብልጽግናን ብቻ
ያገኛሉ::
17 ደግ ሰው ራሱን ይጠቅማል፤
ጨካኝ ግን በራሱ ላይ መከራ ያመጣል::
18 ክፉ ሰው የሚያገኘው ትርፍ መቅኖ
የለውም፤
ጽድቅን የሚዘራ ግን አስተማማኝ ዋጋ
ያገኛል::
19 እውነተኛ ጻድቅ ሕይወትን ያገኛል፤
ክፋትን የሚከተል ግን ወደ ሞቱ
ይጓዛል::
20 *እግዚአብሔር* ልበ ጠማሞችን ይጸየፋል፤
በመንገዳቸው ነቀፋ በሌለባቸው ሰዎች
ግን ደስ ይሰኛል::
21 ክፉ ሳይቀጣ እንደማይቀር ዕወቅ፣
ጻድቃን ግን በነጻ ይሄዳሉ::
22 በእርያ አፍንጫ ላይ እንደተሰካ የወርቅ
ቀለበት፣
ማስተዋል የጐደላት ቆንጆ ሴት እንዲሁ
ናት::
23 የጻድቃን ምኞት ምንጊዜም ፍጻሜው
ያማረ ነው፤
የክፉዎች ተስፋ ግን በቍጣ ያከትማል::
24 አንዱ በለጋስነት ይሰጣል፤ ሆኖም ይበልጥ
ያገኛል፤
ሌላው ያለመጠን ይሰስታል፤ ግን
ይደኸያል::
25 ለጋስ ይበለጽጋል፤
ሌሎችን የሚያረካም ራሱ ይረካል::

11፥16 ምሳ31፥31
11፥18 ዘፀ1፥20፤ ኢዮ4፥8፤ሆሴ10፥12-13
11፥19 ዘዳ30፥15፤ 1ሳሙ2፥6፤መዝ89፥48፤ምሳ1፥18-19፤ 10፥2፤መክ7፥2፤ኤር 43፥11
11፥20 ዘኍ14፥8፤ 1ዜና29፥17፤መዝ15፥2፤101፥1-4፤119፥1፤ ምሳ3፥32፤12፥2፡22 ፤15፥9
11፥21 ምሳ16፥5
11፥25 1ዜና29፥17 ፤ምሳ22፥9፤ኢሳ 32፥8፤2ቆሮ9፥6-9
11፥27 መዝ7፥15-16
11፥28 ኢዮ31፥24-28፤መዝ49፥6፤52፥7፡8፤62፥10፤92፥12-14፤ ኤር9፥23
11፥29 ምሳ14፥19
11፥30 ዘፍ2፥9፤ ምሳ10፥11
11፥31 ኤር25፥29፤ 49፥12፤1ጴጥ4፥18
12፥1 ምሳ5፥11-14 ፤9፥7-9፤13፥1፡18፤ 15፥5፡10፡12፡32
12፥2 2ሳሙ15፥3፤ ኢዮ33፥26፤ መዝ 84፥11፤ምሳ11፥20
12፥3 ምሳ10፥25

26 በድብቅ እህል የሚያከማቸውን ሕዝብ
ይረግመዋል፤
አውጥቶ የሚሸጥ ግን በረከት ይጐናጸፋል::
27 በጎ ነገርን ተግቶ የሚሻ በጎ ነገር
ይጠብቀዋል፤
ክፉ ነገር የሚፈልገውን ግን ክፉ
ያገኘዋል::
28 በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤
ጻድቃን ግን እንደ አረንጓዴ ቅጠል
ይለመልማሉ::
29 ቤተ ሰቡን የሚያውክ ሰው ነፋስን
ይወርሳል፤
ተላላም ሰው የጠቢብ ሎሌ ይሆናል::
30 የጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ ናት፤
ነፍሳትን የሚማርክም ጠቢብ ነው::
31 ጻድቃን ለሠሩት ሥራ በምድር
የእጃቸውን የሚያገኙ ከሆነ፣
የክፉዎችና የኀጢአተኞችማ የቱን ያህል
የባሰ ይሆን?

**12** ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን
ይወዳል፤
መታረምን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው::
2 መልካም ሰው ከ*እግዚአብሔር* ዘንድ ሞገስ
ያገኛል፤
ተንኰለኛውን ግን *እግዚአብሔር*
ይፈርድበታል::
3 ሰው በክፋት ላይ ተመሥርቶ ሊጸና
አይችልም፤
ጻድቃን ግን ከቦታቸው አይነቃነቁም::

1) እንድንገነዘብ ያደርጋል፤ ጨካኝ ከሆኑት ሀብታሞች ይልቅ ርኅራኄ ያላት ሴት ክብር እንደምታገኝ ያመለክታል:: *ርኅሩኅ ሴት፤* 31፥28፡30 ይመ::

11፥17 *ራሱን ይጠቅማል፤* ማቴ5፥7 ይመ:: *በራሱ ላይ መከራ ያመጣል፤* ዘፍ34፥25-30፤ 49፥7 ይመ::

11፥18 *መቅኖ የለውም፤* ረድኤትና ዘለቄታ ስለሌለው ነው፤ (የ10፥2፡16 ማብ እንዲሁም ሐጌ1፥6 ይመ):: *አስተማማኝ ዋጋ ያገኛል፤* 10፥24፤ ገላ6፥8-9፤ ያዕ3፥18 ይመ::

11፥19 *ሕይወትን ያገኛል፤* የ10፥16 ማብ እንዲሁም 12፥28፤ 19፥23 ይመ:: *ወደ ሞቱ ይጓዛል፤* 5፥23፤ 21፥16፤ ሮሜ 6፥23፤ ያዕ1፥15 ይመ::

11፥20 *ልበ ጠማሞችን ይጸየፋል፤* 3፥32 እና ማብ፤ 16፥5 ይመ:: *ነቀፋ በሌለባቸው፣* የ2፥2 ማብ ይመ::

11፥21 *ሳይቀጣ እንደማይቀር፤* 6፥29 ይመ:: *በነጻ ይሄዳሉ፤* መዝ118፥5 ይመ::

11፥22 *የወርቅ ቀለበት፤* ብዙ ጊዜ ሴቶች በአፍንጫቸው ላይ ያደርጉት ነበር (ዘፍ24፥47፤ ሕዝ16፥12 ይመ):: *ማስተዋል የጐደላት፤* በማስተዋል ላደረገችው ተግባር ዳዊት አቢግያን አመስግኖአታል (1ሳሙ25፥33)::

*11፥23፤* 10፥24፡27 እና ማብ ይመ:: *በቍጣ፤* የእግዚአብሔር ፍርድ ነው (ቍ4፤ ኢሳ10፥3፤ ሶፎ1፥18፤ ሮሜ2፥8-9 ይመ)::

*11፥24፤* ልግስና በረከትን ለማግኘት በር ከመክፈቱም በላይ ወደ ላቀ ብልጽግና ይመራል (3፥9-10 እና ማብ፤ መክ 11፥1-2 እና ማብ፤ መዝ112፥9፤2ቆሮ9፥6-9 ይመ):: በአንጻሩ ግን ንፉግ ሰው ወዳጅ አያፈራም፤ የማታ ማታም ራሱን ይጐዳል (21፥13)::

11፥25 *ለጋስ ይበለጽጋል፤* ምግቡን ለድኾች በማካፈል ስለሚበላ ነው (22፥9):: “በልግስና የሚዘራ በልግስና ያጭዳል” (2ቆሮ 9፥6ይመ፤ ከሉቃ6፥38 ጋር ያነጻጽሩ):: *ይረካል፤* ሮሜ 15፥32 ይመ::

11፥26 *በድብቅ ... የሚያከማቸውን፤* የእህል ዕጥረት በሚደርስበት ወቅት ዋጋ ለመጨመር ሳይሆን አይቀርም:: *በረከት ይጐናጸፋል፤* 10፥6 ይመ:: *አውጥቶ የሚሸጥ፤* ረሀብ በግብፅ ላይ በደረሰ ጊዜ ዮሴፍ እንዳደረገው ነው (ዘፍ41፥53-57)::

11፥27 *በጎ ነገርን ተግቶ የሚሻ በጎ ነገር ይጠብቀዋል፤* በቍ25 ላይ እንደ ተመለከተው ሰው (ከማቴ 7፥12 ጋር ያነጻጽሩ):: *ክፉ ነገር የሚፈልገውን ግን ክፉ ያገኘዋል፤* ክፋት የተሞላበት ዕቅዱ ዙሮ ዙሮ ራሱን የሚያጠፋው ይሆናል (ቍ8 እና ማብ፤ 1፥18 ይመ)::

11፥28 *በሀብቱ የሚታመን፤* ብዙ ጊዜ ክፉዎችን ያመለክታል (መዝ49፥6፤ 62፥10 ይመ፤ ከማር10፥25፤ ከ1ጢሞ 6፥17 ጋር ያነጻጽሩ):: *እንደ አረንጓዴ ቅጠል፤* መዝ1፥3 ይመ::

11፥29 *ቤተ ሰቡን የሚያውክ ሰው ነፋስን ይወርሳል፤* ስምዖንና ሌዊ በሴኬም ላይ የፈጸሙት የጭካኔ ተግባር በውርሳቸው ላይ ችግር አስከትሎአል (ዘፍ34፥25፤ 49፥7፤ 15፥27 እና ማብ ይመ:: *የጠቢብ ሎሌ፤* ክፉ ሰው የደግ ሰው አገልጋይ እንደሚሆን (14፥19 ይመ፤ ከ17፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

11፥30 *የጻድቅ ፍሬ፤* ጥበበኛ ሰው የሚያስገኘው ውጤት ነው (8፥18-19):: *የሕይወት ዛፍ፤* የ3፥18 ማብ ይመ:: *ነፍሳትን የሚማርክም፤* ሰዎች ወደ ጥበብና ወደ ጽድቅ እንዲፈልሱ የሚያደርግ ነው (ዳን12፥3፤ 1ቆሮ9፥19-22፤ ያዕ5፥20 ይመ)::

11፥31 *ጻድቃን ለሠሩት ... የሚያገኙ፤* ሙሴና ዳዊት እንኳ ለፈጸሙት መተላለፍ ቅጣት ደርሶባቸዋል (ዘኍ20፥11-12፤ 2ሳሙ12፥10 ይመ):: *የክፉዎችና የኀጢአተኞችማ የቱን ያህል፤* 1፥18፡31 እና ማብ፤ መዝ11፥6፤ 73፥18-19 ይመ::

12፥1 *ተግሣጽ፤* በቃልና በተግባር የሚሰጥ ሥልጠና ነው:: *ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል፤* 1፥7፤ 10፥17 እንዲሁም 6፥23 እና ማብ ይመ:: *መታረምን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው፤* 1፥22 ይመ፤ 5፥12 እና ማብ ይመ::

12፥2 *ሞገስ ያገኛል፤* 3፥4፤ 8፥35 ይመ:: *ተንኰለኛውን ... ይፈርድበታል፤* ከኢዮ5፥12፤ ከ1ቆሮ3፥19 ጋር ያነጻጽሩ::

12፥3 *ሊጸና አይችልም፤* 11፥5 ይመ:: *ጻድቃን ግን ከቦታቸው አይነቃነቁም፤* 2፥21፤ እንዲሁም 10፥25፡30 እና ማብ

4መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት፤
አሳፋሪ ሚስት ግን አጥንቱ ውስጥ
እንዳለ ንቅዘት ናት።

5የጻድቃን ሐሳብ ቀና ነው፤
የክፉዎች ምክር ግን ሽር አለበት።

6የክፉዎች ቃል ደም ለማፍሰስ ታደባለች፤
የቅኖች ንግግር ግን ይታደጋቸዋል።

7ክፉ ሰዎች ይገለበጣሉ፤ ድራሻቸውም
ይጠፋል፤
የጻድቃን ቤት ግን ጸንቶ ይኖራል።

8ሰው በጥበቡ ይመሰገናል፤
ጠማማ ልብ ያላቸው ግን የተናቁ
ናቸው።

9የሚበላው ሳይኖረው ከሚኵራራ ይልቅ፣
ራሱን ዝቅ አድርጎ ሠራተኛ የሚያሳድር
ይሻላል።

10ጻድቅ ሰው ለእንስሳቱ ይራራል፤
ክፉዎች ራሩ ቢባል እንኳ ዞሮ ዞሮ
ሥራቸው ጭካኔ ነው።

11መሬቱን የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ
ያገኛል፤
ከንቱ ተስፋን የሚያሳድድ ግን ማመዛዘን
ይጐድለዋል።

12ኀጥአን የክፉዎችን ምርኮ ይመኛሉ፤
የጻድቅ ሥር ግን ይንሰራፋል።

13ክፉ ሰው በእኩይ ንግግሩ ይጠመዳል፤
ጻድቅ ሰው ግን ከመከራ ያመልጣል።

14ሰው ከከንፈሩ ፍሬ የተነሣ በበጎ ነገር
ይሞላል፤
እንደ እጁ ሥራም ተገቢውን ዋጋ
ያገኛል።

15ተላላ ሰው መንገዱ ትክክል መስሎ
ይታየዋል፤
ጠቢብ ሰው ግን ምክር ይሰማል።

16ተላላ ሰው ቍጣው ወዲያውኑ
ይታወቅበታል፤
አስተዋይ ሰው ግን ስድብን ንቆ
ይተዋል።

17ሐቀኛ ምስክር በእውነት ይመሰክራል፤
ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸት ይናገራል።

18ግድ የለሽ ቃል እንደ ሰይፍ ይወጋል፤
የጠቢብ አንደበት ግን ፈውስን ያመጣል።

19እውነት የሚናገሩ ከንፈሮች ለዘላለም
ጸንተው ይኖራሉ፤
ሐሰተኛ አንደበት ግን ለቅጽበት ያህል
ብቻ ነው።

20ክፋትን በሚያውጠነጥኑ ሰዎች ልብ
አታላይነት አለ፤
ሰላምን የሚያራምዱ ግን ደስታ
አላቸው።

21ጻድቃን ጕዳት አያገኛቸውም፤
ክፉዎች ግን በመከራ የተሞሉ ናቸው።

22እግዚአብሔር ሐሰተኛ ከንፈርን
ይጸየፋል፤
በእውነተኞች ሰዎች ግን ደስ ይለዋል።

23አስተዋይ ሰው ዕውቀቱን ይሰውራል፤
የተላሎች ልብ ግን ድንቍርናን ይነዛል።

24ትጉ እጆች ለገዥነት ሲያበቁ፣
የስንፍና ፍጻሜ ግን የባርነት ሥራ ነው።

12፥4 ሩት3፥11፤ምሳ 18፥22፤31፥10-11
12፥6 ምሳ11፥9፤ 14፥3
12፥7 መዝ37፥36፤ ምሳ10፥25፤14፥11፤1 5፥25
12፥8 ኢሳ19፥14፤ 29፥24
12፥10 ዘኍ22፥29
12፥11 ምሳ28፥19
12፥13 መዝ59፥12፤ ምሳ10፥6፤18፥7፤ 21፥23
12፥14 ምሳ13፥2፤1 4፥14፤15፥23፤18፥20
12፥15 ምሳ9፥7-9፤ 14፥12፤16፥2:25፤19፥ 20
12፥16 1ሳሙ25፥25 ፤ኢዮ5፥2፤ምሳ29፥11
12፥17 መዝ12፥2፤ ምሳ14፥5:25
12፥18 መዝ55፥21 ፤ምሳ15፥4፤25፥18
12፥20 ሮሜ14፥19
12፥21 ኢዮ4፥7
12፥22 1ነገ13፥18፤ መዝ18፥19፤ምሳ6፥17 ፤11፥20
12፥23 መዝ38፥51 59፥7፤ምሳ10፥14፤18 ፥2

ይመ።

12፥4 *መልካም ሴት፤* እንደ ሩት ያለች ሴት ናት (ሩት 3፥11)። እንደዚህ ያለችው ሴት በ31፥10-31 ላይ በዝርዝር ተገልጻለች። *ለባሏ ዘውድ ናት፤* ሞገስንና ደስታን ታስገኝለታለች (4፥9 እና ማብ ይመ)። *ንቅዘት፤* ዕን3፥16 ይመ። *ዐጥንቱ፤* የ3፥8 ማብ ይመ።

12፥5 *የክፉዎች ምክር ሸር አለበት፤* መዝ1፥1 ይመ።

*12፥6፤* ክፉዎች በሐሰት በመመስከር ሰዎችን ይኰንናሉ፤ ጻድቃን ግን እውነቱን ተናግረው በደል የሌለበትን ሰው ነጻ ያወጣሉ። *ደም ለማፍሰስ ታደባለች፤* የ1፥11 ማብ እንዲሁም 1፥16 ይመ።

12፥7፤ 10፥25 እና ማብ ይመ።

12፥8 *በጥበቡ ይመሰገናል፤* 3፥4 ማብ ይመ። *ጠማማ ልብ ያላቸው ግን የተናቁ ናቸው፤* ዘዳ32፥5፤ ቲቶ3፥11 ይመ።

12፥10 *ለእንስሳቱ ይራራል፤* የጽድቅ መንገድ ለእንስሳትም ሳይቀር በመራራት ይገለጣል። እንስሳት በተለያየ መንገድ ሰዎችን ያገለግላሉ፤ ስለዚህ በአጓጉል ሁኔታ እንዲያዙ ወይም ጭካኔ እንዲደርስባቸው ከቶ አይገባም (ዘፍ1፥28፤ 9፥3፤ 24፥32፤ ዘዳ25፥4 ይመ)። *ክፉዎች ራሩ ቢባል እንኳ ዞሮ ዞሮ ሥራቸው ጭካኔ ነው፤* ይኸውም በሰውና በእንስሳት ላይ ይገለጣል።

12፥11፤ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ በ28፥19 ላይ ተደግሞአል። *ከንቱ ተስፋን የሚያሳድድ፤* በቀላሉ ገንዘብ የሚገኝበትን ዘዴ የሚያውጠነጥን።

12፥12 *የክፉዎችን ምርኮ ይመኛሉ፤* 1፥13 እና ማብ፤ 21፥10 ይመ። *የጻድቅ ሥር ... ይንሰራፋል፤* ሥር እንደ ሰደደ ዛፍ ፍሬ ያፈራል (ቈ3:7፤ 11፥30፤ መዝ1፥3፤ እንዲሁም 10፥25 እና ማብ ይመ)።

12፥13 *ክፉ ሰው በእኩይ ንግግሩ ይጠመዳል፤* 1፥18 እና ማብ፤ 29፥6 ይመ። *ጻድቅ ሰው ... ከመከራ ያመልጣል፤* 11፥8-9 እና ማብ፤ 21፥23፤ 2ጴጥ2፥9 ይመ።

*12፥14፤* አንድ ገበሬ ከድካሙ በኋላ አዝመራ እንደሚያፍስ፣ በጥበብ የሚናገር ሰውም ከአንደበቱ ከሚወጣው ቃል መልካም ፍሬ ያገኛል 11፥31 እና ማብ፤ ኢዮ34፥11 ይመ)።

12፥15 *ትክክል መስሎ፤* ነገር ግን በሞት ይደመደማል (1፥25:30፤ 14፥12፤ 16፥25 ይመ)።

12፥16 *ስድብን ንቆ ይተዋል፤* ራሱን ይቆጣጠራል (29፥11፤ 2ሳሙ16፥11-12 ይመ)።

12፥17 *ሐሰተኛ ምስክር ... ውሸት ይናገራል፤* የ6፥19 ማብ ይመ።

12፥18 *ግድ የለሽ ቃል፤* ከመዝ106፥33 ጋር ያነጻጽሩ። *እንደ ሰይፍ ይወጋል፤* የመዝ5፥9 ማብ ይመ። *የጠቢብ አንደበት ... ፈውስን ያመጣል፤* በሚያባብልና በሚያጽናና ቃል (4፥22፤ 15፥4 ይመ)።

12፥19 *ለቅጽበት ያህል ብቻ ነው፤* ውሸት ሐሰት መሆኑ ይገለጣል፤ ውሸታሙም ይቀጣል (19፥9፤ መዝ52፥4-5 ይመ)።

12፥20 *ልብ አታላይነት፤* 6፥14 እና ማብ እንዲሁም 1፥31፤ 24፥2፤ ዘፍ6፥5 ይመ። *ሰላምን የሚያራምዱ ... ደስታ አላቸው፤* "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው" (ማቴ5፥9)።

12፥21 *ጕዳት አያገኛቸውም፤* 1፥33 እና ማብ፤ 2፥8፤ መዝ91፥10-12፤ 121፥7 ይመ። *በመከራ የተሞሉ ናቸው፤* 1፥31 እና ማብ፤ 11፥5:8፤ 22፥8፤ ኢዮ4፥8 ይመ።

*12፥22፤* የዚህን ጥቅስ ቃል አሰካክ ከ11፥1:20 ጋር ያነጻጽሩ። *ይጸየፋል፤* የ3፥32 ማብ ይመ። *በእውነተኞች ሰዎች፤* 16፥13 ይመ።

*12፥23፤* *ዕውቀቱን ይሰውራል፤* ዕውቀትን ያከማቻል (10፥14 ይመ)። *ድንቍርናን ይነዛል፤* ቍ16፤ 13፥16፤ 15፥2፤ 29፥11 ይመ።

12፥24 *ትጉ እጆች ... የስንፍና፤* ይህ ሁኔታ በ10፥4 ላይም በንጽጽር ተገልጧል። *ለገዥነት ሲያበቁ፤* ከ17፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

25 ሥጉ ልብ ሰውን በሐዘን ይወጥራል፤
መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል።
26 ጻድቅ ሰው ለወዳጁ መልካም ምክር
ይሰጣል፤[w]
የክፉዎች መንገድ ግን ወደ ስሕተት
ይመራቸዋል።
27 ሰነፍ አድኖ ያመጣውን እንኳ
አይጠብስም፤[r]
ትጉ ሰው ግን ለንብረቱ ዋጋ ይሰጣል።
28 በጽድቅ መንገድ ላይ ሕይወት አለ፤
በዚያ ጐዳና ላይ ሞት የለም።

13 ጠቢብ ልጅ የአባቱን ምክር
በማስተዋል ይሰማል፤
ፌዘኛ ግን ተግሣጽን አያዳምጥም።
2 ሰው ከከንፈሩ ፍሬ መልካም ነገር
ያገኛል፤
ወስላቶች ግን ዐመፅን ይናፍቃሉ።
3 አንደበቱን የሚጠብቅ ሕይወቱን
ይጠብቃል፤
አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ግን
ይጠፋል።
4 ሰነፍ አጥብቆ ይመኛል፤ አንዳችም
አያገኝም፤
የትጉዎች ምኞት ግን ይረካል።
5 ጻድቅ ሐሰትን ይጠላል፤
ክፉ ሰው ግን ኀፍረትንና ውርደትን
ያመጣል።
6 ጽድቅ ቅን የሆነውን ሰው ትጠብቀዋለች፤
ክፋት ግን ኀጢአተኛውን ትጥለዋለች።
7 ምንም ሳይኖረው ባለጠጋ መስሎ የሚታይ
ሰው አለ፤
ሌላው ድኻ መስሎ ይታያል፤ ግን ብዙ
ሀብት አለው።
8 የሰው ሀብቱ ለሕይወቱ ቤዛ ሊሆነው
ይችላል፤
ድኻው ግን ሥጋት የለበትም።
9 የጻድቃን ብርሃን ደምቆ ይበራል፤
የክፉዎች መብራት ግን ይጠፋል።
10 ትዕቢት ጠብን ብቻ ያስፋፋል፤
ጥበብ ግን ምክርን በሚቀበሉ ዘንድ
ትገኛለች።
11 ያላግባብ የተገኘ ገንዘብ እየተመናመነ
ያልቃል፤
ገንዘቡን ጥቂት በጥቂት የሚያከማች ግን
ይጠራቀምለታል።
12 ለነገ የሚባል ተስፋ ልብን ያሳምማል፤
የተሳካ ምኞት ግን የሕይወት ዛፍ ነው።
13 ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት
ያመጣል፤
ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን
ይቀበላል።
14 የጠቢብ ትምህርት የሕይወት ምንጭ ናት፤
ሰውን በሞት ወጥመድ እንዳይያዝ

[w]26 ወይም *ለወዳጁ መሪ ነው።* ሆኖም የዕብራይስጡ ፍቺ በውል አይታወቅም።
[r]27 ለዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም

12፥24 ምሳ10፥4
12፥25 ምሳ15፥13
12፥26 መዝ95፥10
12፥28 ዘዳ30፥15፤ ምሳ10፥2
13፥1 ምሳ12፥11 15፥5
13፥2 ምሳ12፥14
13፥3 ኢዮ1፥22፤ መዝ12፥2፤34፥13፤ ምሳ10፥6፤18፥7፡20-21፤21፥23
13፥4 ምሳ21፥25-26
13፥5 መዝ119፥128
13፥6 ምሳ11፥3፡5፤ ኤር44፥5
13፥7 2ቆሮ6፥10፤ ራእ3፥17
13፥8 ምሳ15፥16
13፥9 ኢዮ18፥5፤ ምሳ4፥18-19
13፥10 መሳ19፥30፤ ምሳ9፥9
13፥11 ምሳ10፥2
13፥12 ምሳ10፥11
13፥13 ዘፀ9፥20፤ ዘኁ15፥31፤ምሳ 16፥20
13፥14 ምሳ10፥11፤ 14፥27

*የባርነት ሥራ፤* መሳ1፥28፤ እንዲሁም 2ሳሙ20፥24 ይመ።

12፥25 *ሥጉ ልብ፤* መዝ94፥19 ይመ። *መልካም ቃል ... ደስ ያሰኘዋል፤* 15፥23 ይመ።

12፥26 *ለወዳጁ መልካም ምክር ይሰጣል፤* ይህ ሐረግ "ጻድቅ ሰው ወዳጁን በትክክለኛው መንገድ ይመራል" የሚል ትርጒም አለው፤ እዚህ ላይ ምናልባት የወዳጆቹን ማንነት የሚገልጽ ነው። (18፥24፤ 22፥24 ይመ)። *ወደ ስሕተት ይመራቸዋል፤* 5፥23፤ 14፥22 ይመ።

12፥27 *አድኖ ያመጣውን እንኳ አይጠብስም፤* ከምግብ ሳሕን ላይ፣ ምግቡን አንሥቶ መብላት እንኳ ከባድ ሥራ ይሆንበታል (19፥24)። *ለንብረቱ ዋጋ ይሰጣል፤* ከመክ5፥19 ጋር ያነጻጽሩ።

12፥28 *ሕይወት አለ፤* ከ3፥2፤ 11፥4 ጋር ያነጻጽሩ። *ሞት የለም፤* ቀጥታ ሲተረጐም፣ "መሞት አይኖርም" ማለት ነው። የጻድቅ መንገድ ወደ ሞት የሚመራ አይደለም። ጥበብ "ከሕይወት ዛፍ" ጋር ተመሳሳይ መሆኗ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (3፥18 እና ማብ ይመ፤ ከ14፥32 ያነጻጽሩ)።

13፥1 *የአባቱን ምክር ... ይሰማል፤* 1፥8፤ 4፥1 ይመ። *ፌዘኛ ግን ተግሣጽን አያዳምጥም፤* 1፥22፤ 9፥7-8 እና ማብ ይመ።

*13፥2፤* 12፥14 እና ማብ ይመ። *ዐመፅን ይናፍቃሉ፤* 4፥17 እና ማብ ይመ።

13፥3 *አንደበቱን የሚጠብቅ ሕይወቱን ይጠብቃል፤* አንድ ሰው አስተዋይ ወይም ጥበበኛ መሆኑ በግልጽ ከሚታወቅባቸው መመዘኛዎች አንዱ አንደበቱን መቈጣጠር መቻሉ ነው። "አንደበት የሕይወትና የሞት ኀይል አላት" (18፥21፤ 10፥19፤ 21፥23፤ ያዕ3፥2 ይመ)። *አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ግን ይጠፋል፤* 12፥18 እና ማብ፤ እንዲሁም 10፥14፤18፥7፤ 2ጢሞ3፥3-4 ይመ።

13፥4 *ሰነፍ፤* 6፥6 እና ማብ ይመ። *አጥብቆ ይመኛል፤ አንዳችም አያገኝም፤* ሥራ ስለማይወድ እርካታ አያገኝም (21፥25-26 ይመ)፤ *የትጉዎች ምኞት ግን ይረካል፤* ትጋት ትርፍን ያስገኛል (6፥6፤ እንዲሁም የ10፥4፡24 ማብ ይመ)።

13፥5 *ኀፍረትንና ውርደትን ያመጣል፤* እንደ ሰነፍ ወይም እንደ ውለታ ቢስ ልጅ (10፥5፤ 19፥26)።

*13፥6፤* ይህ ንጽጽር የ2፥21-22፤ 10፥9፤ 11፥3፡5 (ማብ ይመ) ሐሳብን በድጋሚ ይገልጻል። ከ21፥12፤ ከመዝ25፥21 ጋር ያነጻጽሩ።

*13፥7፤* በሁሉም በኩል የታየው አስመሳይነት ርባና የለሽ በመሆኑ፣ ወደ ከንቱ መንገድ ይመራል (14፥8 እና ማብ እንዲሁም 11፥24፤ 12፥9 ይመ)።

13፥8 *ለሕይወቱ ቤዛ፤* ሕይወትን ለማጥፋት ለመጡ ወንበዴዎች የሚከፈል ሀብት አለ ማለት ነው (10፥15 እና ማብ፤ ኤር41፥8 ይመ)። *ድኻው ግን ... ሥጋት የለበትም፤* ድኻ ሀብት ይወሰድብኛል ብሎ አይፈራም።

13፥9 *ብርሃን ... መብራት፤* የሕይወት ተምሳሌት ናቸው (ከኢዮ3፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። *ደምቆ ይበራል፤* ደስታና ብልጽግና አለው (የ4፥18 ማብ ይመ)። *የክፉዎች መብራት ... ይጠፋል፤* ሕይወቱ ታልፋለች (20፥20፤ 24፥20፤ ኢዮ 18፥5፤ 21፥17 ይመ)።

13፥10 *ትዕቢት፤* 11፥2 እና ማብ ይመ።

13፥11 *ያላግባብ የተገኘ ገንዘብ እየተመናመነ ያልቃል፤* በዝርፊያ (መዝ62፥10) ወይም በማታለል (ምሳ21፥6) የተገኘ ገንዘብ ቁም ነገር ላይ ሳይሆን በኖ ይጠፋል፤ የ10፥2 ማብ እንዲሁም ኤር17፥11 ይመ። *ይጠራቀምለታል፤* የ10፥4 ማብ ይመ።

13፥12 *ለነገ የሚባል ተስፋ ልብን ያሳምማል፤* ከዘፍ30፥1 ጋር ያነጻጽሩ። *የተሳካ ምኞት ... የሕይወት ዛፍ ነው፤* ሕይወትን ያድሳል፤ ብርቱም ያደርጋል (የ3፥18 ማብ ይመ እንዲሁም 10፥28፤ 13፥19 ይመ)።

13፥13 *ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል፤* 1፥29-31፤ እንዲሁም 5፥12 እና ማብ ይመ። *ትእዛዝን የሚያከብር ... ወሮታን ይቀበላል፤* ጥበብ የምትሰጠውን በረከት ያገኛል (3፥2 እና ማብ፤ 3፥16-18፤ 13፥21 ይመ)።

13፥14 *የሕይወት ምንጭ፤* የ10፥11 ማብ ይመ። *በሞት*

ታደርገዋለች::
[15]መልካም ማስተዋል ሞገስን ታስገኛለች፣
የከዳተኞች መንገድ ግን አስቸጋሪ ነው::[a]
[16]አስተዋይ ሰው ሥራውን በዕውቀት
ያከናውናል፣
ተላላ ግን ሞኝነቱን ይገልጣል::
[17]ክፉ መልእክተኛ መከራ ውስጥ ይገባል፣
ታማኝ መልእክተኛ ግን ፈውስን
ያመጣል::
[18]ተግሣጽን የሚንቅ ወደ ድኽነትና ኀፍረት
ይሄዳል፣
እርምትን የሚቀበል ሁሉ ግን ይከበራል::
[19]ምኞት ስትፈጸም ነፍስን ደስ ታሰኛለች፣
ተላሎች ግን ከክፋት መራቅን ይጸየፋሉ::
[20]ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፣
የተላሎች ባልንጀራ ግን ጕዳት ያገኘዋል::
[21]መጥፎ ዕድል ኀጢአተኛን ይከታተላል፣
ብልጽግና ግን የጻድቃን ዋጋ ነው::
[22]ደግ ሰው ለልጅ ልጆቹ ውርስ ትቶ
ያልፋል፣
የኀጢአተኞች ሀብት ግን ለጻድቃን
ይከማቻል::
[23]የድኾች ዕርሻ የተትረፈረፈ ምርት
ያስገኛል፣
የፍትሕ መጓደል ግን ጠራርጎ
ይወስደዋል::
[24]በአርጩሜ ከመቅጣት የሚሳሳለት ልጁን
ይጠላል፣
የሚወደው ግን በጥንቃቄ ይቀጣዋል::
[25]ጻድቅ እስኪጠግብ ድረስ ይበላል፣
የክፉዎች ሆድ ግን እንደ ተራበ
ይኖራል::

# 14

[1]ጠቢብ ሴት ቤቷን ትሠራለች፣
ተላላ ሴት ግን በገዛ እጇ
ታፈርሰዋለች::
[2]አካሄዱ ቅን የሆነ ሰው እግዚአብሔርን
ይፈራል፣
መንገዱ ጠማማ የሆነ ግን ይንቀዋል::
[3]የተላላ ሰው ንግግር ለጀርባው በትር
ታስከትልበታለች፣
የጥበበኛ ከንፈር ግን ትጠብቃቸዋለች::
[4]በሬዎች በሌሉበት ጎንዳው ባዶ ይሆናል፣
በበሬ ጕልበት ግን ብዙ ምርት ይገኛል::
[5]ታማኝ ምስክር አይዋሽም፣
ሐሰተኛ ምስክር ግን ውሸትን
ይዘከዝካል::
[6]ፌዘኛ ጥበብን ይሻል፣ ሆኖም አያገኛትም፣
ዕውቀት ግን ለአስተዋዮች በቀላሉ
ትገኛለች::
[7]ከተላላ ሰው ራቅ፣
ከከንፈሮቹ ዕውቀት አታገኝምና::
[8]የአስተዋዮች ጥበብ መንገዳቸውን ልብ
ማለት ነው፣
የተላሎች ሞኝነት ግን መታለል ነው::
[9]ተላሎች በሚያቀርቡት የበደል ካሳ
ያፌዛሉ፣
በቅኖች መካከል ግን በጎ ፈቃድ
ትገኛለች::
[10]እያንዳንዱ ልብ የራሱን መራራ ሐዘን
ያውቃል፣

13፥16 አሰ5፥11፤ መዝ38፥5፤መክ10፥3
13፥17 ምሳ10፥26፤ 25፥13
13፥18 መዝ141፥5፤ ምሳ1፥7፤12፥1፤ 25፥12፤መክ7፥5
13፥19 ምሳ10፥11
13፥20 2ዜና10፥8
13፥21 2ሳሙ3፥39፤መዝ25፥13፤32፥10፤ ኤር40፥3፤50፥7፤ ሕዝ14፥13፤18፥4
13፥22 አሰ8፥2፤ ኢዮ27፥17፤መክ2፥26
13፥24 2ሳሙ7፥14፤ምሳ3፥12፤19፥18፤ 22፥15፤23፥13-14፤ 29፥15፡17፤ኤፌ6፥4፤ ዕብ12፥7
13፥25 ምሳ10፥3
14፥1 ሩት3፥11፤ ምሳ24፥3
14፥3 ምሳ10፥13፡ 14፤12፥6፤መክ10፥12
14፥4 መዝ144፥14
14፥5 መዝ12፥2፤ ምሳ12፥17
14፥6 ምሳ9፥9
14፥8 ቆላ15፡24፤ ምሳ15፥28፤21፥29

[a]15 ወይም *የከዳተኞች መንገድ ግን አይጸናም*

*ወጥመድ፤* የ1፥17፤ የ5፥22 ማብ፤ እንዲሁም 7፥23፤ 22፥5 ይመ::

13፥15 *ሞገስን ታስገኛለች፤* 3፥4፤ 8፥35 ይመ:: *አስቸጋሪ፤* የቍ13 ማብ ይመ::

*13፥16፤* 12፥23 እና ማብ ይመ::

13፥17 *መከራ ውስጥ ይገባል፤* የላኩትን ሰዎች ዓላማ ባለማከበሩ ሊሆን ይችላል:: *ፈውስን ያመጣል፤* ሐቀኛና ጥበብ የተሞላበት ዘዴው ለገራ ቀኝ ወገን የሚበጅ ይሆናል (25፥13 ይመ፤ ከ12፥18፤ ከ15፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥18 *ወደ ድኽነትና ኀፍረት ይሄዳል፤* 5፥10-12 እና ማብ ይመ:: *እርምትን የሚቀበል ... ይከብራል፤* ቍ1፤ 3፥16-18፤ 8፥35፤ 10፥17ይመ::

13፥19 *ምኞት ስትፈጸም፤* ቍ12 ይመ:: *ተላሎች ... ከክፋት መራቅን ይጸየፋሉ፤* በ5፥12 ምክርን እንዴት እንደሚጠሉ የሚያመለክተውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

13፥20 *ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፤* ጓደኞችን በጥንቃቄ መምረጥ ይገባል (2፥20፤ 12፥26 ይመ):: *የተላሎች ባልንጀራ ... ጕዳት ያገኘዋል፤* 1፥10፡18፤ 2፥12፤ 16፥29፤ 22፥24-25 ይመ::

*13፥21፤* ቍ13 እና ማብ ይመ::

13፥22 *ለጻድቃን ይከማቻል፤* የክፉ ሰው ሀብት ብዙውን ጊዜ እንደዚህ እንደሚሆን ኢዮብ ተናግሮአል (ኢዮ27፥16-17 ይመ፤ ከምሳ28፥8 ጋር ያነጻጽሩ)::

13፥23 *የፍትሕ መጓደል ... ጠራርጎ ይወስደዋል፡* አንዳንድ ሰዎች ድኻ ሆነው ዕድሜአቸውን የሚገፉት፣ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ሥር የሰደደው ፍትሕ አልባነት ተጠቂዎች በመሆናቸው ነው (ከመዝ35፥10 ጋር ያነጻጽሩ፣ ያዕ5፥1-6 ይመ)::

13፥24 *በአርጩሜ ከመቅጣት የሚሳሳለት ልጁን ይጠላል፤* ቂልነት እንዲወገድና ልጅም የጥፋትን መንገድ እንዳይከተል ለማድረግ (19፥18፤ 23፥13-14)፣ ወላጆች የማረሚያ አርጩሜ እንዲጠቀሙ ተመክረዋል (22፥15):: አርጩሜው "ጥበብን ያስገኛል" (29፥15)፤ ጤነኛና ደስተኛ ቤተ ሰብ እንደሚገኝም ያደርጋል (29፥17):: ሥነ ሥርዐት የሚመሠረተው በፍቅር ነው (3፥11-12 እና ማብ ይመ):: *በአርጩሜ፤* ማንኛውንም ዐይነት ቅጣት የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ሳይሆን አይቀርም::

*13፥25፤* የቍ13፡18፡21 ትምህርትን ግልጽ በሆነ መልክ የሚያብራራ ነው፤ 10፥3 እና ማብ ይመ::

14፥1 *ጠቢብ ሴት ቤቷን ትሠራለች፤* ቤተ ሰቧን ደግፋ የምትይዝ ምሰሶ ከመሆኗም በላይ፣ ታታሪነቷ ለቤተ ሰቧ አርአያነት አለው (31፥10-13 ይመ):: በ9፥1 ላይ ጥበብ የሠራችውን ቤት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

14፥2 *እግዚአብሔርን ይፈራል፤* የ1፥7 ማብ ይመ::

14፥3 *ለጀርባው በትር፤* 10፥13፤ 19፥29፤ 26፥3 ይመ::

14፥4 ሰዎች ለከብቶቻቸው ተገቢ ክብካቤ እንዲያደርጉ የሚያሳስብ ሳይሆን አይቀርም፣ እድገትና ፍሬ ከመገኘቱ በፊት ዋጋ መክፈል ያስፈልጋል::

*14፥5፤* የ6፥19 ማብ ይመ::

14፥6 *ፌዘኛ፤* 1፥22 እና ማብ ይመ:: *ጥበብን ይሻል፤ ሆኖም አያገኛትም፤* እግዚአብሔርን ካለመፍራቱና ተግሣጽን ካለመቀበሉ የተነሣ ነው::

14፥8 *የተላሎች ሞኝነት ... መታለል ነው፤* አላዋቂ የሆነ ሰው አስተዋይነት ነው ብሎ የገመተው ነገር መልካም ውጤት አያስገኝለትም፤ እንዲያውም በራሱ ላይ ጥፋት ሊያስከትልበት ይችላል::

14፥9 *የበደል ካሳ ያፌዛሉ፤* ከ19፥28 ጋር ያነጻጽሩ:: *በቅኖች መካከል ... በጎ ፈቃድ፣* 11፥27 እና ማብ ይመ::

14፥10 *የራሱን መራራ ሐዘን ያውቃል፤* 1ነገ8፥38 ይመ::

ደስታውንም ማንም ሊጋራው አይችልም።

11የክፉዎች ቤት ይፈርሳል፤
የቅኖች ድንኳን ግን ይስፋፋል።

12ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ
አለ፤
በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ያደርሳል።

13በሣቅ ጊዜ እንኳ ልብ ይተክዛል፤
ደስታም በሐዘን ሊፈጸም ይችላል።

14ልባቸውን ከጽድቅ የሚመልሱ የእጃቸውን
ሙሉ ዋጋ ይቀበላሉ፤
ደግ ሰውም ወሮታውን ያገኛል።

15ተላላ ሰው ሁሉን ያምናል፤
አስተዋይ ግን እርምጃውን ያስተውላል።

16ጠቢብ ሰው ጥንቁቅ ነው፤ ከክፉም
ይርቃል፤
ተላላ ግን ችኩልና ደንታ ቢስ ነው።

17ግልፍተኛ ሰው የቂል ተግባር ይፈጽማል፤
መሠሪም ሰው አይወደድም።

18ብስለት የሌላቸው ተላላነትን ይወርሳሉ፤
አስተዋዮች ግን ዕውቀትን እንደ ዘውድ
ይጭናሉ።

19ክፉዎች በደጎች ፊት፣
ኀጥአንም በጻድቃን ደጅ ያጐነብሳሉ።

20ድኾችን ወዳጆቻቸው እንኳ ይጠሏቸዋል፤
ባለጠጎች ግን ብዙ ወዳጆች አሏቸው።

21ጎረቤቱን የሚንቅ ኀጢአት ይሠራል፤
ለተቸገሩት የሚራራ ግን ቡሩክ ነው።

22ክፉ ነገር የሚያቅዱ ከትክክለኛው
መንገድ ይወጡ የለምን?
በጎ ነገር የሚያቅዱ ግን ፍቅርንና
ታማኝነትን ያተርፋሉ።[ሯ]

23ለፍተው የሠሩት ሁሉ ትርፍ ያስገኛል፤
ከንቱ ወሬ ግን ወደ ድኽነት ያመራል።

24ጠቢባን ብልጥግና ዘውዳቸው ነው፤
የተላሎች ተላላነት ግን ፍሬው ከንቱነት
ነው።

25እውነተኛ ምስክር ሕይወት ያድናል፤
ሐሰተኛ ምስክር ግን አባይ ነው።

26እግዚአብሔርን የሚፈራ ጽኑ እምባ
አለው፤
ልጆቹም መጠጊያ ይኖራቸዋል።

27እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት
ምንጭ ነው፤
ሰውን ከሞት ወጥመድ ያድነዋል።

28የሕዝብ ብዛት የንጉሥ ክብር ሲሆን፣
የዜጐች ማነስ ግን ለገዥ መጥፊያው
ነው።

29ታጋሽ ሰው ትልቅ ማስተዋል አለው፤
ግልፍተኛ ሰው ግን ቂልነትን ይገልጣል።

30ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት
ይሰጣል፤
ቅናት ግን ዐጥንትን ያነቅዛል።

[ሯ]22 ወይም ታማኝነትን ያሳያሉ

14፥11 ኢዮ8፥22፤ መዝ72፥71፤ምሳ3፥33፤12፥7፤21፥12
14፥12 ምሳ12፥15፤ 16፥25
14፥13 መክ2፥2፤ 7፥3:6
14፥14 2ዜና15፥7፤ ምሳ1፥31፤12፥14
14፥15 ቍ8
14፥16 ዘፀ20፥20፤ 1ሳሙ25፥25፤ምሳ 22፥3
14፥17 ቍ29፤2ነገ 5፥12፤አስ5፥9፤ምሳ15፥18፤16፥28፤26፥21፤ 28፥25፤29፥22
14፥19 ምሳ11፥29
14፥20 ምሳ19፥4:7
14፥21 ምሳ11፥12፤ 19፥17
14፥22 ምሳ4፥16-17
14፥24 ቍ8
14፥25 ምሳ12፥17
14፥26 መዝ9፥9፤ ምሳ18፥10
14፥27 መዝ18፥5፤ ምሳ10፥11፤13፥14
14፥28 2ሳሙ19፥7
14፥29 ቍ17፤2ነገ 5፥12፤ምሳ17፥27፤ መክ7፥8-9
14፥30 ምሳ17፥22

ከሐና (1ሳሙ1፥10) እና ከጴጥሮስ (ማቴ 26፥75) የሕይወት ልምድ ጋር ያነጻጽሩ። *ደስታውንም … ሊጋራው፤* ከማቴ13፥44፤ ከ1ጴጥ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ።

*14፥11፤* 10፥25 እና ማብ ይመ።

14፥12 *መስሎ የሚታይ፤* አንድ ነገር እውነት ወይም ሐሰት፣ ትክክል ወይም ስሕተት፣ የሚጠቅም ወይም የማይጠቅም እንደሆነ ለመለየት፤ የሰው ጥበብ ሐቅ የጐደለው ሚዛን ነው። ትክክለኛው የሕይወት መንገድ የትኛው እንደ ሆነ በግል ጽ የሚያሳየው፣ ተጽፎ የሚገኘውና የማይሻረው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። የሰው መንገድ በውስጡ ሞትን ያዘለ ነው፤ የጌታ መንገድ ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይመራል። *በመጨረሻ … ወደ ሞት ያደርሳል፤* 5፥4:23፤ 7፥21-27፤ ማቴ 7፥13-14 ይመ።

14፥13 *በሣቅ ጊዜ … ልብ ይተክዛል፤* ከዕዝ3፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ። *ደስታም በሐዘን ሊፈጸም ይችላል፤* ሄሮድስ ሕዝብ ባመሰገነው ጊዜ "ለእግዚአብሔር ክብር ባለመስጠቱ" እንደ ተቀሠፈ ሁሉ (ሐሥ21፥23 ይመ)፣ እጉል ፈንጠዝያም ሐዘንን ያስከትላል።

*14፥14፤* 1፥31፤ 12፥14 እና ማብ፤ እንዲሁም 11፥5:8፤ 18፥20፤ 22፥8፤ ኢዮ4፥8 ይመ።

14፥15 *ተላላ፤* የ1፥4 ማብ ይመ። *እርምጃውን ያስተውላል፤* 4፥26 እና ማብ ይመ፤ 21፥29 ይመ።

14፥16 *ጥንቁቅ ነው፤ ከክፉም ይርቃል፤* የ1፥7፤ 3፥7 ማብ ይመ። *ችኩልና፤* ከ21፥24 ጋር የነጻጽሩ። *ደንታ ቢስ፤* በአነጋገር (12፥18፤ 13፥3 እና በተግባር ነው (መሳ9፥4)።

14፥17 *ግልፍተኛ፤* ቲቶ1፥7 ይመ። *መሠሪም፤* ከ12፥2፤ ከኢዮ5፥12-13፤ ከ1ቆሮ3፥19 ጋር ያነጻጽሩ።

14፥18 *ዕውቀትን እንደ ዘውድ ይጭናሉ፤* ዕውቀት ከማግኘታቸው የተነሣ በረከትንና ሞገስን አግኝተዋል (የ4፥9 ማብ እንዲሁም ቍ24፤ 12፥4፤ መዝ103፥4 ይመ)።

14፥19 *በጻድቃን ደጅ፤* ርዳታ ለመጠየቅ ይሆናል (ከ1ሳሙ2፥36 ጋር ያነጻጽሩ)። *ክፉዎች … ያጐነብሳሉ፤* ከ17፥2 ጋር ያነጻጽሩ።

14፥20 *ወዳጆቻቸው እንኳ ይጠሏቸዋል፤* ድኻ አንዳንድ ጊዜ በዘመዶቹ እንኳ ሳይቀር የተናቀ ነው (19፥7 ይመ)።

14፥21 *ለተቸገሩት የሚራራ … ቡሩክ ነው፤* ርኅራኄ ከሚገለጥባቸው መንገዶችም፦ አንዳንዶቹ ምግብ ማካፈል (22፥9)፣ ገንዘብ ማበደር (28፥8)፣ እንዲሁም ስለ ሰዎች መብት መከራከር (31፥9) ናቸው። ይህን የሚያደርግ ሰው፣ "እግዚአብሔርን ያከብራል" (ቍ31 ይመ፤ ከ17፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ምንም ነገር አይጐድልበትም (28፥27 ይመ)፤ ከ21፥13፤ ከመዝ41፥1 ጋር ያነጻጽሩ።

14፥22 *ክፉ ነገር የሚያቅዱ፤* 3፥29፤ 6፥14:18፤ ሚክ2፥1 ይመ። *ከትክክለኛው መንገድ ይወጡ፤* 5፥23፤ 12፥26 ይመ። *ፍቅርንና ታማኝነትን ያተርፋሉ፤* የታማኝ ጓደኛን ድጋፍና እንክብካቤ ያገኛሉ (ከ3፥3፤ 16፥6፤ 20፥28 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ርዳታና ጥበቃ ሳያመለክት አይቀርም።

14፥23 *ለፍተው የሠሩት … ትርፍ ያስገኛል፤* የ10፥4 ማብ እንዲሁም 21፥5 ይመ።

14፥24 *ብልጥግና ዘውዳቸው ነው፤* ጠቢባን ሀብትን ያገኛሉ፤ ይህም እንደ ዘውድ ሞገስ ይሰጣቸዋል (10፥22 ይመ)። *ፍሬው ከንቱነት ነው፤* ለውርስ የሚሆን ምንም ነገር የለውም (ቍ1፤ 3፥35 ይመ)።

*14፥25፤* ቍ5፤ 12፥17፤ እንዲሁም የ6፥19 ማብ ይመ።

14፥26 *እግዚአብሔርን የሚፈራ፤* 1፥7፤ 3፥7 እና ማብ ይመ። *እምባ … መጠጊያ፤* የአባትየው መልካም አካሄድ ለእርሱና ለልጆቹ በረከትን ያስገኛል (20፥7)፤ ወይም እግዚአብሔርን መፍራት ለልጆቹ መጠጊያ የሚሆን ጽኑ ምሽግ ነው (18፥10፤ መዝ71፥7፤ ኢሳ33፥6 ይመ)።

*14፥27፤* የ10፥11 ማብ፤ እንዲሁም 13፥14 ይመ።

14፥29 *ታጋሽ ሰው፤* 15፥18፤ 16፥32፤ 19፥11፤ ያዕ1፥19 ይመ።

14፥30 *ለሰውነት ሕይወት ይሰጣል፤* በ3፥7-8:16-18 ላይ እግዚአብሔርን መፍራትና በጥበብ መመላለስ የሚያስገኘውን በረከት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። *ቅናት … ዐጥንትን ያነቅዛል፤* የ3፥8 ማብ፤ 12፥4፤ መዝ37፥7-8 ይመ።

31 ድኾችን የሚያስጨንቅ ፈጣሪያቸውን
ይንቃል፤
ለተቸገሩ የሚራራ ሁሉ ግን ስምባከን
ያከብራል።
32 ክፉዎች በክፋታቸው ይወድቃሉ፤
ጻድቃን ግን በሞት ጊዜ እንኳ መጠጊያ
አላቸው።
33 ጥበብ በአስተዋዮች ልብ ታድራለች፤
በተላሎች መካከል ራሷን ትገልጣለች።[ኀ]
34 ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤
ኀጢአት ግን ለየትኛውም ሕዝብ
ውርደት ነው።
35 ጠቢብ አገልጋይ ንጉሥን ደስ ያሰኛል፤
አሳፋሪ አገልጋይ ግን ቍጣውን በራሱ
ላይ ያመጣል።

15 የለዘበ መልስ ቍጣን ያበርዳል፤
ክፉ ቃል ግን ቍጣን ይጭራል።
2 የጠቢብ አንደበት ዕውቀትን
ታወድሳለች፤
የተላሎች አንደበት ግን ቂልነትን
ያፈልቃል።
3 *የእግዚአብሔር* ዐይኖች በሁሉም ስፍራ
ናቸው፤
ክፉዎችንም ደጎችንም ነቅተው
ይመለከታሉ።
4 ፈውስ የምታመጣ ምላስ የሕይወት ዛፍ
ናት፤
አታላይ ምላስ ግን መንፈስን
ትሰብራለች።

14፥31 ዘጸ24፥14፤ ኢዮ20፥19፤ምሳ 17፥5፤ማቴ10፥42
14፥32 ኢዮ13፥15፤ መዝ34፥21፤ምሳ6፥15
14፥33 ምሳ2፥6-10
14፥34 ምሳ11፥11
14፥35 አስ8፥2፤ ማቴ24፥45-51፤ 25፥14-30
15፥1 1ነገ12፥7፤ 2 ዜና10፥7፤ምሳ25፥15
15፥2 ቍ7፤መዝ 59፥7፤ምሳ10፥31፤ መክ10፥12
15፥3 2ዜና16፥9፤ ኢዮ10፥4፤31፥4፤ 34፥21፤ምሳ5፥21፤ ኤር16፥17፤ዕብ4፥13
15፥4 መዝ5፥9፤ምሳ 10፥11፤12፥18
15፥5 ምሳ10፥17፤ 12፥1፤13፥1
15፥6 ምሳ8፥21፤ 10፥16
15፥7 ቍ2፤ምሳ 10፥13
15፥8 ቍ29፤ኢዮ 35፥13፤መዝ51፥17፤ ምሳ6፥16፤21፥27፤28 ፥9፤ኢሳ1፥13፤ዮሐ 9፥31
15፥9 ዘዳ7፥13፤ ምሳ6፥16፤11፥20፤
15፥10 ምሳ1፥31- 32፤12፥1
15፥11 1ሳሙ2፥3፤ 2ዜና6፥30፤ኢዮ26፥6 ፤መዝ44፥21፤ራእ 2፥23
15፥12 ምሳ9፥8፤ 12፥1
15፥13 ቍ15፤ምሳ

5 ተላላ የአባቱን ምክር ይንቃል፤
መታረምን የሚቀበል ግን አስተዋይነቱን
ያሳያል።
6 የጻድቃን ቤት በብዙ ሀብት የተሞላ ነው፤
የክፉዎች ገቢ ግን መከራን
ታመጣባቸዋለች።
7 የጠቢባን ከንፈር ዕውቀትን ታስፋፋለች፤
የተላሎች ልብ ግን እንዲህ አይደለም።
8 *እግዚአብሔር* የክፉዎችን መሥዋዕት
ይጸየፋል፤
የቅኖች ጸሎት ግን ደስ ያሰኘዋል።
9 *እግዚአብሔር* የክፉዎችን መንገድ
ይጸየፋል፤
ጽድቅን የሚከታተሉትን ግን
ይወዳቸዋል።
10 ከመንገድ የሚወጣ ሰው ጥብቅ ቅጣት
ይጠብቀዋል፤
እርምትን የሚጠላ ይሞታል።
11 ሲኦልና የሙታን ዓለም[ሠ] *በእግዚአብሔር*
ፊት የተገለጡ ናቸው፤
የሰዎች ልብማ የቱን ያህል የታወቀ ነው!
12 ፌዘኛ መታረምን ይጠላል፤
ጠቢባንንም አያማክርም።
13 ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል፤
የልብ ሐዘን ግን መንፈስን ይሰብራል።
14 አስተዋይ ልብ ዕውቀትን ይሻል፤
የተላላ አፍ ግን ቂልነትን ያመነዥካል።

ኀ33 ዕብራይስጡ፣ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጕሞች *በተላሎች ልብ ግን አትታወቅም* ይላሉ።
ሠ11 በዕብራይስጡ *ሲኦልና አባዶን* ይላል።

14፥31 *ፈጣሪያቸውን ይንቃል፤* ምክንያቱም እግዚአብሔር ድኻንና ሀብታምን፣ ሁለቱንም በአምሳሉ ፈጥሮአል (22፥2፤ ኢዮ 31፥15፤ ያዕ3፥9 ይመ)። *ለተቸገሩ የሚራራ፤* የቍ21 ማብ ይመ። *ለምባከን ያከብራል፤* የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽማል ማለት ሲሆን፣ ይህም ራሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል ማለት ነው (19፥17፤ ማቴ25፥40 ይመ)።

14፥32 *ክፉዎች ... ይወድቃሉ፤* 1፥26-27 እና ማብ፤ 11፥5፤ 24፥16 ይመ። *ጻድቃን ... በሞት ጊዜ እንኳ መጠጊያ አላቸው፤* በእግዚአብሔር ማመናቸው ከሞት ባሻገር ተስፋ ይሰጣቸዋል (የ12፥28 ማብ፤ መዝ49፥14-15፤ 73፥24 ይመ)።

14፥33 *በተላሎች መካከል ራሷን ትገልጣለች፤* አንዳንድ ጊዜ አላዋቂዎች እንኳ በጥቂቱ ጥበብን ያሳያሉ ማለት ሊሆን ይችላል (ከሐሥ17፥27-28፤ ከሮሜ1፥19-20)።

14፥34 *ጽድቅ ሕዝብን ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤* የ11፥11 ማብ ይመ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብራ ብትገኝ እስራኤል፣ ብልጽግናና ክብር እንደምታገኝ ተስፋ ተሰጥቶአት ነበር (ዘዳ28፥1-4)። *ኀጢአት ግን ለየትኛውም ሕዝብ ውርደት ነው፤* የከነዓን ሰዎች የተባረሩት ከሚዘገንን ኀጢአታቸው የተነሣ ነው (ዘሌ18፥24-25)፤ በኋላም እስራኤል ተመሳሳይ ፍርድ ደርሶባታል (ዘዳ28፥15-68 ይመ፤ ከ2ሳሙ12፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥35 *ቍጣውን ... ያመጣል፤* 16፥14፤ 19፥12፤ ዳን2፥12 ይመ።

15፥1 *የለዘበ መልስ፤* ቍጣ በሚያጋጥምበት ጊዜ፣ ነገሩን በርጋታ መቅረብ ዕርቅና ሰላም እንዲወርድ ይረዳል (ከ1ሳሙ 25፥21-34 ጋር ያነጻጽሩ)። በመጽሐፈ መሳፍንት 8፥1-3 ላይ ጌዴዎን የኤፍሬምን ሰዎች ቍጣ እንዴት እንዳበረደ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (እንዲሁም ከምሳ15፥18፤ ከመክ10፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *ክፉ ቃል ግን ቍጣን ይጭራል፤* የናባል የንቀት ንግግር ዳዊትን ለጦርነት አነሣሣው (1ሳሙ25፥10-13)።

15፥2 *ቂልነትን ያፈልቃል፤* ቍ7:28፤ 12፥23፤ 13፥16 ይመ።

15፥3 *የእግዚአብሔር ዐይኖች በሁሉም ስፍራ ናቸው፤* 5፥21፤ ኢዮ31፥4፤ 34፥21፤ ኤር16፥17 ይመ።

15፥4 *ፈውስ የምታመጣ ምላስ፤* የ12፥18 ማብ ይመ። *የሕይወት ዛፍ፤* የ3፥18 ማብ ይመ። *አታላይ ምላስ ... መንፈስን ትሰብራለች፤* በተለይም በፍርድ ቤት የሚሰጥ የሐሰት ምስክርነትን (6፥16፤ 22፥22 ይመ) ወይም በማኅበረ ሰብ ውስጥ የሚነዛ ሐሜትን ያመለክታል።

*15፥6፤* 10፥2:16:22 እና ማብ ይመ። *በብዙ ሀብት፤* 8፥18:21፤ 24፥4፤ ዘካ8፥12፤ እንዲሁም የ3፥10 ማብ ይመ።

15፥8 *የክፉዎችን መሥዋዕት ይጸየፋል፤* ልባቸውን በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ያላደረጉ ሰዎች፣ መሥዋዕት በማቅረባቸው የሚያገኙት በረከት አይኖርም (21፥3:27፤ መክ 5፥1፤ ኢሳ 1፥11-15፤ ኤር6፥20 ይመ)። *የቅኖች ጸሎት፤* 3፥23 ይመ።

15፥9 *ጽድቅን የሚከታተሉትን፤* 21፥21፤ 1ጢሞ6፥11 ይመ።

15፥10 *ከመንገድ፤* ትክክለኛ ወይም "ቀጥተኛ" የሆነ መንገድ ነው (2፥13 ይመ)። *እርምትን የሚጠላ ይሞታል፤* 5፥12:23 እና ማብ ይመ።

15፥11 *ሲኦልና የሙታን ዓለም በእግዚአብሔር ፊት የተገለጡ ናቸው፤* የሙታን ዓለም የሆነው መቃብር እንኳ ከእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ አይደለም (ኢዮ26፥6፤ መዝ139፥8 ይመ)። ስለዚህ እርሱ የሰውን የልብ ሐሳብ ያውቃል (ከ1ሳሙ 16፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

*15፥12፤* 1፥30፤ 10፥8፤ 13፥1፤ 17፥10 ይመ። *ፌዘኛ፤* የ1፥22 ማብ ይመ።

15፥13 *ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል፤* ከ14፥30 ጋር ያነጻጽሩ። *የልብ ሐዘን ... መንፈስን ይሰብራል፤* የኢዮብንና (ኢዮ3) የዳዊትን (መዝ51፥8:10) ታላቅ ኀዘን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

15፥14 *የተላላ አፍ ... ቂልነትን ያመነዥካል፤* የመገናኛ አውታሮችና የመዝናኛ መንገዶች በተራቀቁበት በአሁኑ ጊዜ ልባችንንና አእምሮአችንን በጥንቃቄ መጠበቅ አለብን። መንፈስ

15 የተጨቈኑ ሰዎች ዘመናቸው ሁሉ የከፋ
ነው፤
በደስታ የተሞላ ልብ ግን የማይቋረጥ
ፈንጠዝያ አለው።

16 *እግዚአብሔርን* ከመፍራት ጋር ያለ
ጥቂት ነገር፣
ሁከት ካለበት ትልቅ ሀብት ይበልጣል።

17 ፍቅር ባለበት ጐመን መብላት፣
ጥላቻ ባለበት የሰባ ፍሪዳ ከመብላት
ይሻላል።

18 ግልፍተኛ ሰው ጠብ ያነሣሣል፤
ታጋሽ ሰው ግን ጠብን ያበርዳል።

19 የሀኬተኛ መንገድ በእሾህ የታጠረች
ናት፤
የቅኖች መንገድ ግን የተጠረገ አውራ
ጐዳና ነው።

20 ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል፤
ተላላ ሰው ግን እናቱን ይንቃል።

21 ማመዛዘን የጐደለው ሰው ቂልነት
ያስደስተዋል፤
አስተዋይ ሰው ግን ቀጥተኛውን መንገድ
ይከተላል።

22 ምክር ሲጓደል ዕቅድ ይፋለሳል፤
በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል።

23 ሰው ተገቢ መልስ በመስጠት ደስታን
ያገኛል፤
በወቅቱም የተሰጠ ቃል ምንኛ መልካም
ነው!

24 ወደ ሲኦል[a] ከመውረድ እንዲድን፣
የሕይወት መንገድ ጠቢቡን ሰው ወደ
ላይ ትመራዋለች።

25 *እግዚአብሔር* የትዕቢተኛውን ቤት
ያፈርሰዋል፤
የመበለቲቱን ዳር ድንበር ግን
እንዳይደፈር ይጠብቃል።

26 *እግዚአብሔር* የክፉውን ሰው ሐሳብ
ይጸየፋል፤
የንጹሓን ሐሳብ ግን ደስ ያሰኘዋል።

27 ስስታም ሰው በቤተ ሰቡ ላይ ችግር
ያመጣል፤
ጉቦን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል።

28 የጻድቅ ሰው ልብ የሚሰጠውን መልስ
ያመዛዝናል፤
የክፉ ሰው አፍ ግን ክፋትን ያጒርፋል።

29 *እግዚአብሔር* ከክፉዎች ሩቅ ነው፤
የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል።

30 ብሩህ ገጽታ ልብን ደስ ያሰኛል፤
መልካም ዜናም ዐጥንትን ያለመልማል።

31 ሕይወት ሰጪ የሆነውን ተግሣጽ
የሚሰማ፣
በጠቢባን መካከል ይኖራል።

32 ተግሣጽን የሚንቅ ራሱን ይንቃል፤
እርምትን የሚቀበል ግን ማስተዋልን
ያገኛል።

33 *እግዚአብሔርን* መፍራት ጥበብን መማር
ነው፤[b]
ትሕትናም ክብርን ትቀድማለች።

**16** የልብ ዕቅድ የሰው ነው፤
የአንደበት መልስ ግን

[a]24 ወይም *መቃብር*
[b]33 *ወይም ጥበብ እግዚአብሔርን መፍራት ታስተምራለች።*

12፥25፤17፥22፤18፥14
15፥14 ምሳ18፥15
15፥15 ቍ13
15፥16 ቍ17፤መዝ37፥16-17፤ምሳ13፥8፤16፥8፤17፥1
15፥17 ቍ16፤ምሳ17፥1፤መክ4፥6
15፥18 ዘፍ13፥8፤ምሳ6፥16-19፤14፥17
15፥19 ምሳ22፥25
15፥20 ምሳ10፥1
15፥21 ምሳ2፥14
15፥22 1ነገ1፥12፤መዝ16፥7፤ምሳ11፥14፤24፥6
15፥23 ምሳ12፥14፤25፥11
15፥25 ዘዳ19፥14፤ምሳ12፥7፤23፥10-11
15፥26 መዝ94፥11፤18፥26፤ምሳ6፥16
15፥27 ዘፀ23፥8፤መዝ15፥5፤ኢሳ1፥23፤33፥15
15፥28 መዝ59፥7፤ምሳ14፥8
15፥29 ቍ8፤ኢዮ15፥31፤መዝ145፥18-19፤ኢሳ59፥2፤ዮሐ9፥31
15፥30 ምሳ25፥25
15፥31 ምሳ9፥7-9፤12፥1
15፥32 ምሳ1፥7፤9፥7-9፤12፥1፤መክ7፥5
15፥33 ምሳ1፥7፤16፥18፤18፥12፤22፥4፤29፥23፤ኢሳ66፥2
16፥1 ቍ9፤ምሳ19፥21

ቅዱስን ለሚያሳዝንና የእግዚአብሔርንም ጽድቅ ለሚያጐድፍ ሁኔታ ራሳችንን ካጋለጥን፣ ከንቱ መሆናችንን ይፋ እናደርጋለን (ሮሜ1፥32 እና ማብ ይመ)። አስተዋይ የሆኑት በጎ፣ ትክክለኛና ንጹሕ በሆነ ነገር አእምሮአቸውን ያንጻሉ (ፊል4፥8)።

15፥15 *በደስታ የተሞላ ልብ ... የማያቋርጥ ፈንጠዝያ አለው፤* በእግዚአብሔር በዓል ቀን እንደሚሆነው ሁሉ፣ ሕይወት ደስታና ርካታ የተሞላበት ነው (ቍ13፤ 14፥30 ይመ፤ ከዘሌ 23፥39-41 ጋር ያነጻጽሩ)።

15፥16 *ሁከት ... ትልቅ ሀብት፤* በ10፥2 ላይ "ያላግባብ የተገኘ ሀብት" የተባለው ነው።

15፥17 *የሰባ ፍሪዳ፤* እንዲህ ያለው ሥጋ ልዩ ለሆነ ጊዜ ወይም ለመዝናኛ ወቅት የተመደበ ነው (ከ7፥14፤ ከማቴ22፥4፤ ከሉቃ15፥23 ጋር ያነጻጽሩ)።

15፥18 *ጠብ ያነሣሣል፤* የ6፥14 ማብ ይመ። *ታጋሽ ሰው፤* 14፥29፤ 16፥32፤ 19፥11፤ ያዕ1፥19 ይመ።

15፥19 *የሀኬተኛ፤* የ6፥6 ማብ ይመ። *እሾህ የታጠረች ናት፤* መንገዱ ያልተጠረገበት ዋና ምክንያት ከስንፍናው የተነሣ ነው (24፥30-31፤ ሆሴ2፥6 ይመ)። *አውራ ጐዳና፤* ቅኖች ሊያድጉና ከግብ ሊደርሱ ይችላሉ (የ3፥6 ማብ ይመ)።

*15፥20፤* 10፥1 ማብ ይመ።

*15፥21፤* 10፥23 ላይ ያለው እዚህ ለየት ባለ መልክ ተገልጾአል።

*15፥22፤* በ11፥14፤ 20፥18፤ 24፥6 መካከል ያለውን አቻ የሆነ አገላለጽ ያስተውሉ።

15፥23 *ተገቢ መልስ፤* ከኢሳ50፥4 ጋር ያነጻጽሩ። *በወቅቱ የተሰጠ ቃል ምንኛ መልካም ነው፤* ከ24፥26 ጋር ያነጻጽሩ።

15፥24 *ወደ ሲኦል ከመውረድ እንዲድን፤* የ2፥18 ማብ ይመ። *ወደ ላይ ትመራዋለች፤* ወደ ሕይወት በሚመራና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ማለት ነው (ቍ19፡21)።

15፥25 *የትዕቢተኛውን ቤት ያፈርሰዋል፤* 2፥22፤ 14፥11፤ እንዲሁም 10፥25 እና ማብ ይመ። *የመበለቲቱን ዳር ድንበር ... እንዳይደፈር ይጠብቃል፤* በጥንት ዘመን በድንበር ላይ የሚቆም ድንጋይ ያንድን ሰው የሀብት ይዞታ ለይቶ ያመለክት ነበር። እንዲህ ያለውን ድንጋይ ከድንበር የሚያነሣ ማንም ቢኖር፣ የሌላ ሰው መሬት እንደ ወሰደ ይቈጠር ነበር (22፥28፤ ኢዮ 24፥2፤ መዝ68፥5 እንዲሁም ዘዳ19፥14 እና ማብ ይመ)።

15፥26 *የክፉውን ሰው ሐሳብ ይጸየፋል፤* ከቍ8-9 ጋር ያነጻጽሩ። *የንጹሓን፤* 22፥11፤ መዝ24፥4 ይመ።

15፥27 *ስስታም ሰው በቤተ ሰቡ ላይ ችግር ያመጣል፤* 1፥19፤ 11፥29፤ 28፥25 ይመ። የአካን ቤተ ሰብ በሙሉ እንዲጠፉ የተደረገው በኢያሪኮ ከተማካሳየው ስግብግብነት የተነሣ ነው (ኢሱ 7፥24-26)። *ጉቦን የሚጠላ ... በሕይወት ይኖራል፤* 17፥8፤ 28፥16፤ ዘዳ16፥19፤ 1ሳሙ12፥3፤ መክ7፥7፤ 1ጢሞ6፥10 ይመ።

15፥28 *የሚሰጠውን መልስ ያመዛዝናል፤* ከ10፥32፤ ከ1ጴጥ 3፥15 ጋር ያነጻጽሩ። *ክፋትን ያጒርፋል፤* ቍ2፤ እንዲሁም 7፥12፡23 ይመ።

15፥29 *ከክፉዎች ሩቅ ነው፤* 1፥28 እና ማብ ይመ።

15፥30 *ብሩህ ገጽታ ልብን ደስ ያሰኛል፤* ከቍ13፤ 1፥15፤ ከኢዮ29፥24 ጋር ያነጻጽሩ። *መልካም ዜናም ዐጥንትን ያለመልማል፤* 3፥8 እና ማብ፤ እንዲሁም ፊል2፥19 ይመ።

15፥31 *ሕይወት ሰጪ የሆነውን ተግሣጽ የሚሰማ፤* 1፥23፤ 6፥23 እና ማብ ይመ።

15፥32 *ተግሣጽን የሚንቅ ራሱን ይንቃል፤* የ5፥12 ማብ እንዲሁም 1፥7፤ 5፥23፤ 8፥36 ይመ። *እርምትን የሚቀበል፤* ከቍ5፡31 ጋር ያነጻጽሩ።

15፥33 *እግዚአብሔርን መፍራት፤* የ1፥7 ማብ ይም። *ትሕትናም ክብርን ትቀድማለች፤* 22፥24፤ 25፥6-7፤ ማቴ 23፥12፤ ሉቃ14፥11፤ 18፥14፤ 1ጴጥ5፥6 ይመ። ጥበብም ከትሕትና ጋር ትመጣለች (11፥2፤ 13፥10)።

16፥1 *የአንደበት መልስ፤* ዕቅድ ብናዘጋጅም፣ ያወጣነውን

*ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።*

2 ለሰው *መንገዱ* ሁሉ ንጹሕ *መስሎ*
*ይታየዋል*፤
*መነሻ ሐሳቡ ግን በእግዚአብሔር*
*ይመዘናል*።

3 የምታደርገውን ሁሉ *ለእግዚአብሔር*
ዐደራ ስጥ፤
ዕቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል።

4 *እግዚአብሔር* ሁሉንም ነገር ለራሱ
ዐላማ ሠርቶአል፤
ክፉዎችንም እንኳ ለጥፋት ቀን
አዘጋጅቶአል።

5 *እግዚአብሔር* በልብ የሚታበዩትን ሁሉ
ይጸየፋል፤
እነርሱም ከቅጣት እንደማያመልጡ
በእርግጥ ዕወቅ።

6 በፍቅርና በታማኝነት ኀጢአት ይሰረያል፤
*እግዚአብሔርን* በመፍራት ሰው ከክፋት
ይርቃል።

7 የሰው መንገድ *እግዚአብሔርን* ደስ
ሲያሰኘው፣
ጠላቶቹ እንኳ አብረውት በሰላም
እንዲኖሩ ያደርጋል።

8 ከጽድቅ ጋር ጥቂቱ ነገር፣
በግፍ ከሚገኝ ብዙ ትርፍ ይሻላል።

9 ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል፤

16፥2 1ሳሙ2፥3፤ 2ዜና6፥30፤ምሳ12፥15፤20፥27፤21፥2፤30፥12፤ሉቃ16፥15
16፥3 2ዜና20፥20፤ መዝ20፥4፤37፥5-6፤ ምሳ3፥5-6
16፥4 ዘፀ9፥16፤ 2ዜና 34፥24፤መዝ 18፥18፤ሮሜ9፥22
16፥5 መዝ40፥4፤ ምሳ6፥16፤11፥20-21
16፥6 ዘፍ20፥11፤ዘፀ 1፥17፤20፥20
16፥7 ዘፍ39፥21፤ መዝ105፥15፤ኤር39፥12፤40፥1፤42፥12፤ዳን 1፥9
16፥8 መዝ37፥16፤ ምሳ15፥16፤መክ4፥6
16፥9 ቍ1፤ኢዮ 33፥29፤መዝ90፥12
16፥10 ምሳ17፥7
16፥11 ምሳ11፥1 ፤ሕዝ45፥10
16፥12 ምሳ25፥5፤ 26፥28፤29፥14፤31፥5
16፥13 ምሳ22፥11
16፥14 ዘፍ40፥2፤ኢ ዮ29፥24፤ምሳ20፥2፤25፥15፤29፥8መክ10፥4
16፥15 ዘፍ40፥2፤ ኢዮ29፥24፤ምሳ 19፥12፤25፥2-7
16፥16 ኢዮ28፥15፤ መዝ49፥20፤ምሳ3፥13 -14
16፥17 ምሳ19፥16

*እግዚአብሔር* ግን እርምጃውን
ይወስንለታል።

10 የንጉሥ ከንፈሮች እንደ አምላክ ቃል
ይናገራሉ፤
እንደበቱ ፍትሕን ያዛባ ዘንድ አይገባም።

11 ሐቀኛ መስፈሪያና ሚዛን *ከእግዚአብሔር*
ናቸው፤
በከረጢት ውስጥ ያሉት *መመዘኛዎችም*
ሁሉ *ሥራዎቹ* ናቸው።

12 ክፋትን ማድረግ ለነገሥታት አጸያፊ
ነው፤
ዙፋን የሚጸናው በጽድቅ ነውና።

13 ነገሥታት በታማኝ ከንፈሮች ደስ
ይላቸዋል፤
እውነት የሚናገረውን ሰው ይወዱታል።

14 የንጉሥ ቍጣ የሞት መልእክተኛ ነው፤
ጠቢብ ሰው ግን ቍጣውን ያበርዳል።

15 የንጉሥ ፊት ሲፈካ ሕይወት አለ፤
በጎነቱም ዝናብ እንዳዘለ የበልግ ደመና
ነው።

16 ከወርቅ ይልቅ ጥበብን ማግኘት፣
ከብርም ማስተዋልን መምረጥ ምንኛ
ይበልጣል!

17 የቅኖች ጐዳና ከክፋት የራቀ ነው፤
*መንገዱንም* የሚጠብቅ ሕይወቱን
ይጠብቃል።

ዕቅድ በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋል ችሎታ የሚመጣው ግን ከእግዚአብሔር ነው (ከቍ9 እና 33፤21፥31 ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥2 *ንጹሕ መስሉ ይታየዋል፤* 14፥12 ይመ። *መነሻ ሐሳቡ ... ይመዘናል*፤ 24፥12፤ መዝ139፥23፤ 1ቆሮ4፥4-5፤ ዕብ 4፥12 ይመ።

16፥3 *አደራ ስጥ፤* 1ጴጥ5፥7 ይመ። *ዕቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል፤* ዐላማህ ከግብ ይደርሳል (3፥5-6 እና ማብ፤ መዝ 1፥3፤ 55፥22፤ 90፥17 ይመ)።

16፥4 *እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለራሱ ዓላማ ሠርቶአል*፤ እግዚአብሔር በሕይወትና በታሪክ ሂደት ሁሉ ላይ ባለሥልጣን (መክ7፥14፤ ሮሜ8፥28 ይመ)። *ክፉዎችንም እንኳ ለጥፋት ቀን አዘጋጅቶአል፤* እግዚአብሔር በክፉ ሰዎች ሕይወት ላይ እንኳ ኀይሉን ይገልጻል (ከዘፀ9፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ክፉ የሆነውም ሁሉ ይፈረድበታል (ከሕዝ38፥22-23፤ ከሮሜ2፥5-22 ጋር ያነጻጽሩ)።

*16፥5፤* 11፥20-21 እና ማብ ይመ።

16፥6 *በፍቅርና በታማኝነት ኀጢአት ይሰረያል*፤ እግዚአብሔር የሚፈልገው በጎ ሥነ ምግባር "ፍቅርና ታማኝነት ነው" በማለት ሊጠቃለል ይችላል (3፥3፤ ሆሴ4፥1)። ሕዝቡ በኀጢአታቸው በሚናዘዙበትና ሕይወታቸውን በእርሱ ፈቃድ በሚመሩበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር መተላለፋቸውን ይቅር ይላቸዋል፤ ሊያመጣባቸው ያለውን ፍርዱንም ይተዋል (ኢሳ1፥18-19፤ 55፥7፤ ኤር3፥22፤ ሕዝ18፥23፡30-32፤ 33፥11-12፡14-16፤ ሆሴ14፥1-2፡4 ይመ። *እግዚአብሔርን በመፍራት፤* የ1፥7 ማብ ይመ።

16፥7 *ጠላቶቹ እንኳ አብረውት በሰላም እንዲኖሩ ያደርጋል፤* በእግዚአብሔር ሰዎች በአሳና በኢዮሳፍጥ ዘመነ መንግሥት እንደ ነበረው ዐይነት ማለት ነው (2ዜና14፥6-7፤ 17፥10)። *በሰላም፤* 3፥17 እና ማብ፤ ሮሜ12፥18፤ ዕብ12፥14 ይመ።

*16፥8፤* 10፥2 ማብ ይመ።

16፥9 *እግዚአብሔር ... እርምጃውን ይወስንለታል፤* ቍ1 3-4 (ማብ ይመ) እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት እንደሚቈጣጠር በአጽንዖት ይገልጻሉ (19፥21፤ 22፥24፤ መዝ 37፥23፤ ኤር 10፥23 ይመ)።

16፥10 *እንደ አምላክ ቃል ይናገራሉ፤* አንድ ንጉሥ ፍትሕ ይሰጥ ዘንድ ጕዳይ ሲቀርብለት ብይን ይሰጥ የነበረው የእግዚአብሔር ወኪል በመሆን ነው (ዘዳ1፥17 ይመ)። ስለዚህ ትክክል የሆነውን ከስሕተት በመለየት የእግዚአብሔርን ፍርድ በሥራ ላይ ለማዋል (1ነገ3፥9)፣ ከመለኮት የሆነ የጥበብ ስጦታ ያስፈልገው ነበር። ይህን ሲያደርግም ለሕዝቡ የሚሰጠው ፍርድ እንደ መለኮት ቃል ይቈጠር ነበር (1ነገ3፥38፤ እንዲሁም 2ሳሙ 14፥17፡20፤ 19፥27 ይመ)።

*16፥11፤* የ11፥1 ማብ ይመ። *ሐቀኛ መስፈሪያና ... ከእግዚአብሔር ናቸው፤* ከ21፥2፤ 24፥12 ከኢዮ6፥2፤ 31፥6 ያነጻጽሩ። *በከረጢት ውስጥ ያሉት መመዘኛዎችም ሁሉ፤* ለክፍያ የሚውሉ የብር ክፍልፋዮችን ለመመዘንና ለመለካት፣ ነጋዴዎች የተለያየ መጠን ያላቸውን ድንጋዮች ይይዙ ነበር (ከሚክ6፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥12 *ዙፋን የሚጸናው በጽድቅ ነውና፤* ይህ የሚሆነው ንጉሥ "ድኾችን በሐቅ ሲዳኝ" (29፥14)፣ መማለጃ ወይም ጕቦን አልቀበልም ሲልና (29፥4)፣ ማንኛውንም ክፉ አማካሪ ከአጠገቡ ሲያርቅ ነው (25፥5)። 14፥34፤ ዘዳ17፥19-20፤ ኢሳ16፥5፤ ሮሜ 13፥3 ይመ።

16፥13 *በታማኝ ከንፈሮች፤* የለበጣ አንደበትን ሲቃወም ነው (ከ20፥28 ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥14 *የሞት መልእክተኛ፤* የተቈጣ ንጉሥ ግራ ቀኙን ሳያይ ፈጥኖ የሞት ፍርድ ሊያስተላልፍ ይችላል (19፥12፤ አስ7፥7፤ ማቴ22፥7፤ ሉቃ19፥27 ይመ)። *ጠቢብ ሰው ... ቍጣውን ያበርዳል፤* ናቡከደነፆር በተቈጣ ጊዜ ዳንኤል ያደረገውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ዳን2፥12-16)።

16፥15 *ፊት ሲፈካ፤* ከዘኍ6፥25 ጋር ያነጻጽሩ። *በጎነቱም ዝናብ እንዳዘለ የበልግ ደመና ነው፤* ቡቃያ ያፈራ ዘንድ በተለይ የገብስና የስንዴ መከር እንዲደርስ የበልግ ዝናብ እጅግ አስፈላጊ ነበሩ፤ ይኸውም ወደ ፊት ለሚመጣው በጎ ነገር ምልክት ነበረ። በ19፥12 የተመለከተውን "ጠል" ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ፤ መዝ72፥6 ይመ።

*16፥16፤* 3፥4 እና ማብ፤ 8፥10፡19 ይመ።

16፥17 *የቅኖች ጐዳና፤* የ15፥19 ማብ ይመ። *ከክፋት የራቀ፤* በክፉዎች ጐዳና ላይ ያለውን እሾህና ወጥመድ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (22፥5)።

አይለያትም፤
የተላሎች ዐይኖች ግን እስከ ምድር
ዳርቻ ይንከራተታሉ።
25ተላላ ልጅ በአባቱ ላይ ሐዘን ያስከትላል፤
ለወለደችውም ምሬት ይሆንባታል።
26ንጹሑን ሰው መቅጣት ተገቢ አይደለም፤
ሹሞችን ስለ ቅንነታቸው መግረፍ
መልካም አይደለም።
27ዐዋቂ ሰው ንግግሩ ቍጥብ ነው፤
አስተዋይም መንፈሱ የረጋ ነው።
28አላዋቂ እንኳ ዝም ቢል ጠቢብ፣
አንደበቱንም ቢገዛ አስተዋይ ይመስላል።

**18** ወዳጅነትን የማይፈልግ ሰው የራ
ሱን ፍላጎት ብቻ ይከተላል፤
ቅን የሆነውን ፍርድ ሁሉ ይቃወማል።
2ተላላ ከማስተዋል ርካታን አያገኝም፤
የራሱን ሐሳብ በመግለጥ ግን ደስ
ይለዋል።
3ክፋት ስትመጣ ንቀት ትከተላለች፤
ከዕፍረትም ጋር ውርደት ትመጣለች።
4ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሆች
ናቸው፤
የጥበብም ምንጭ እንደሚንዶለዶል
ፏፏቴ ነው።
5ለክፉ ሰው ማድላት፣
ንጹሑንም ፍትሕ መንሣት ተገቢ
አይደለም።
6የተላላ ከንፈር ጠብ ያመጣበታል፤
አፉም በትር ይጋብዛል።
7ተላላ ሰው አፉ መጥፊያው ነው፤
ከንፈሮቹም ለነፍሱ ወጥመድ ናቸው።
8የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጕርሻ ነው፤
ወደ ሰው ውስጣዊ ክፍል ዘልቆ ይገባል።
9ለሥራው ደንታ የሌለው ሰው፣
የአጥፊ ወንድም ነው።
10*የእግዚአብሔር* ስም ጽኑ ግንብ ነው፤
ጻድቅ ወደ እርሱ በመሮጥ ተገን
ያገኝበታል።
11የባለጠጎች ሀብት የተመሸገ ከተማቸው
ነው፤
እንደማይወጣ ረጅም ግንብም
ይቈጥሩታል።
12ከውድቀቱ በፊት ሰው ልቡ ይታበያል፤
ትሕትና ግን ክብርን ትቀድማለች።
13ከማዳመጡ አስቀድሞ የሚመልስ፣
ቂልነትና ዕፍረት ይሆንበታል።
14በሕመም ጊዜ፣ ሰውን መንፈሱ
ትደግፈዋለች፤
የተሰበረውን መንፈስ ግን ማን ሊሸከም
ይችላል?
15የአስተዋይ ልብ ዕውቀትን ይገበያል፤
የጠቢብም ጆሮ አጥብቆ ይሻታል።
16እጅ መንሻ ለሰጪው መንገድ
ትከፍትለታለች፤
ታላላቅ ሰዎች ፊትም ታቀርበዋለች።
17አስቀድሞ ጕዳዩን የሚያሰማ ትክክለኛ

17፥24 ኢዮ31፥1
17፥25 ምሳ10፥1
17፥26 መዝ94፥21
17፥27 ኢዮ6፥24፤ ምሳ14፥29
17፥28 ኢዮ2፥13፤ 13፥5፤ምሳ10፥19
18፥2 ምሳ12፥23
18፥4 መዝ18፥16
18፥5 መዝ82፥2፤ ምሳ17፥15፤24፥23-25፤28፥21
18፥6 ምሳ10፥14
18፥7 መዝ64፥8፤ 140፥9፤ምሳ10፥14፤12፥13፤13፥3፤መክ10፥12
18፥8 ምሳ26፥22
18፥9 ምሳ28፥24
18፥10 መዝ20፥1፤ 61፥3፤ምሳ14፥26
18፥11 ምሳ10፥15
18፥12 ምሳ11፥2፤ 15፥33፤16፥18
18፥13 ምሳ20፥25
18፥14 ምሳ15፥13፤ 17፥22
18፥15 ምሳ15፥14
18፥16 ዘፍ32፥13፤ 1ሳሙ10፥4፤ምሳ19፥6

17፥24 *እስከ ምድር ዳርቻ ይንከራተታሉ፤* በምኞት ዓለም ውስጥ ይኖራሉ፤ ይህንም ያንንም ይናፍቃሉ፤ ጥበብን መሻት ግን ይሳናቸዋል (12፥11 ይመ፤ ከዘዳ30፥11-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

*17፥25፤* ቍ21 ይመ። *ምሬት፤* 14፥10 እና ማብ ይመ።

17፥26 *ንጹሑን ሰው መቅጣት፤* ቍ15 እና ማብ ይመ። *ሹሞችን ... መግረፍ፤* ኤርምያስ የደረሰበትን በትርና ውርደት፣ ይህንኑንም እንዴት እንደታገሠ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኤር20፥2፤ ቍ10 እና ማብ ይመ)።

17፥27 *ንግግሩ ቍጥብ ነው፤* 10፥19 ይመ። *መንፈሱ የረጋ፤* 16፥32 ይመ።

17፥28 *አላዋቂ ... ዝም ቢል ጠቢብ፤* በኢዮ13፥5 ላይ የኢዮብን የሽሙጥ ንግግር ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

18፥1 *የራሱን ፍላጎት ብቻ ይከተላል፤* ጠብ ጫሪና ግል ፍተኛ ነው (ከ17፥14፤ ከገላ5፥20 ጋር ያነጻጽሩ)።

18፥2 *የራሱን ሐሳብ በመግለጥ፤* ከመክ 10፥3 ጋር ያነጻ ጽሩ።

18፥3 *ንቀት ... ከዕፍረትም ጋር ውርደት፤* ከ3፥35፤ 6፥33፤ 10፥5፤ 11፥2፤ ከመዝ31፥19፤ ከኢሳ22፥18 ጋር ያነጻጽሩ።

18፥4 *ጥልቅ ውሆች፤* በቀላሉ የማይደረስበት ማለት ነው (ከ20፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። *የጥበብም ምንጭ እንደሚንዶለዶል ፏፏቴ ነው፤* የጥበበኛ ሰው አንደበት አንጀት እንደሚያርስ የሕ ይወት ምንጭ ነው (1፥23፤ 13፥14፤ እንዲሁም የ10፥11 እና ማብ ይመ)።

18፥5 *ለክፉ ሰው ማድላት፤* 17፥15 እና ማብ ይመ። ማን ኛውም ዐይነት አድልዎ በሕግ ተወግዞአል (ዘሌ19፥15፤ ዘዳ 1፥17፤ 16፥19 ይመ)። *ንጹሑንም ፍትሕ መንሣት፤* 17፥26፤ 31፥5፤ ሚል3፥5 ይመ።

18፥6 *ጠብ ያመጣበታል፤* ተላላ ሰው ጠብ ውስጥ ለመግ ባት ይቸኩላል (17፥14:19፤ 20፥3 ይመ)። *በትር ይጋብዛል፤* በጀርባው ላይ በትር ይወርድበታል (10፥13፤ 19፥29 ይመ)።

*18፥7፤* 10፥14 እና ማብ ይመ።

18፥8 *የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጕርሻ ነው፤* እንደ አስተዋይ ሰው ንግግር ማራኪነት አለው (ከ16፥21:23 ጋር ያነጻ ጽሩ)፤ ዳሩ ግን መለያየትን ይፈጥራል (11፥13፤ 26፥20:22 ይመ)። *ውስጣዊ ክፍል ዘልቆ ይገባል፤* በልብ ውስጥ ይውጠነጠ ናል፤ ለረዥም ጊዜም ልብ ውስጥ ተሰንቅሮ ይኖራል።

18፥9 *ለሥራው ደንታ የሌለው፤* 10፥4 እና ማብ ይመ።

18፥10-11 *የእግዚአብሔር ስም፤* ማንነቱን፣ ሥልጣኑንና ባሕርዩን ያመለክታል (ከዘፀ 3፥14-15፤ ከሐሥ 4፥12 ጋር ያነጻ ጽሩ)። ጻድቅ ችግር ሲያጋጥመው፣ መጠጊያና ርዳታ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ልቡን ያቀናል። ግራ የተጋባ ሀብታም ግን ያከማቸው ሀብት በችግር ጊዜ የሚታደገው ይመስለዋል። *ጽኑ ግንብ፤* መዝ18፥2፤ 91፥2፤ 144፥2 ይመ። *ተገን ያገኝበታል፤* 29፥25፤ መዝ27፥5 ይመ።

18፥11 *ሀብት የተመሸገ ከተማቸው ነው፤* ከ10፥15 ጋር ተመሳሳይ ነው (የዚያኑ ማብ ይመ)። *እንደማይወጣ ረጅም ግንብም፤* እግዚአብሔር ግን ትቢያ ሊያደርገው ይችላል (ኢሳ 25፥12 ይመ)።

18፥12 *ሰው ልቡ ይታበያል፤* በራስ መኵራራትንና መተ ማመንን ያመለክታል። ኵራ መንዛትና ዕብሪት ከኵራት ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ወደ ጥፋትም ይመራሉ (ከ15፥33፤ ከ16፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። ትዕቢት አታላይ ነው (ኤር49፥16)፤ ለእግዚአ ብሔርና ለሰው በጎ ምላሽ እንዳይሰጥ ያደርጋል። እግዚአብሔር የሚኵራራውን ይጸየፋል፤ ለትሑቱ ግን ጸጋንን ሞገስን ይሰጠዋል (ያዕ4፥6)።

*18፥14፤* 15፥13፤ 17፥22 እና ማብ ይመ።

18፥16 *እጅ መንሻ ... መንገድ ትከፍትለታለች፤* ጉቦ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድርና ውጤታማ እንደሚያደርግ ያመለክታል (የ17፥8 ማብ ይመ)።

*18፥17፤* የግራ ቀኝ ተከራካሪዎችን ጉዳይ መስማት እንዳ ለባቸው ለዳኞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ሲሆን (ከዘዳ1፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ለብዙ ሁኔታ በጥቅም ላይ ይውላል።

ይመስላል፤
ይኸውም ባላንጣው መጥቶ
እስከሚመረመር ድረስ ነው።

18 ዕጣ መጣጣል ሙግትን ያስቆማል፤
ኀይለኛ ባላንጣዎችንም ይገላግላል።

19 የተበደለ ወንድም ከተመሸገ ከተማ
ይበልጥ የማይበገር ነው፤
ጠቡም እንደ ጠንካራ የግንብ መዝጊያ
ነው።

20 ሰው በአንደበቱ ፍሬ ሆዱ ይጠግባል፤
በከንፈሩም ምርት ይረካል።

21 አንደበት የሞትና የሕይወት ኀይል
አላት፤
የሚወዷትም ፍሬዋን ይበላሉ።

22 ሚስት የሚያገኝ መልካም ነገርን ያገኛል፤
*ከእግዚአብሔርም* ዘንድ ሞገስን
ይቀበላል።

23 ድኻ በመለማመጥ ምሕረት ይለምናል፤
ሀብታም ግን በማናለብኝነት ይመልሳል።

24 ወዳጅ የሚያበዛ ሰው ራሱን ለጥፋት
ይዳርጋል፤
ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚቀርብ
ጓደኛም አለ።

19 ንግግሩ ጠማማ ከሆነ አጕል ሰው
ይልቅ፣
ያለ ነውር የሚሄድ ድኻ ሰው ይሻላል።

2 ዕውቀት አልባ የሆነ ቀናዒነት መልካም
አይደለም፤
ጥድፊያም መንገድን ያስታል።
3 ሰው በራሱ ተላላነት ሕይወቱን ያበላሻል፤
በልቡ ግን እግዚአብሔርን ያማርራል።

18፥18 ምሳ16፥33
18፥19 1ሳሙ17፥28
18፥20 ምሳ12፥14
18፥21 መዝ12፥4፤ 13፥2-3፤ማቴ12፥37
18፥22 ኢዮ33፥26፤ ምሳ12፥4፤19፥14፤31፥10
18፥24 1ሳሙ20፥42፤ዮሐ15፥13-15
19፥1 ምሳ28፥6
19፥2 ምሳ29፥20
19፥3 መዝ14፥1፤ ምሳ9፥13፤24፥9፤ኢሳ 32፥6፤ያዕ1፥13-15
19፥4 ቍ7፤ምሳ 14፥20
19፥5 ቍ9፤ዘፀ23፥1፤ዘዳ19፥19፤መዝ56፥7፤ምሳ21፥28
19፥6 ምሳ17፥8፤ 18፥16፤29፥26
19፥7 ቍ4፤ምሳ 10፥15
19፥8 ምሳ16፥20
19፥9 ቍ5፤ዘዳ 19፥19
19፥10 ምሳ26፥1፤ 30፥21-23፤መክ 10፥5-7
19፥11 2ነገ5፥12
19፥12 አስ1፥12፤ 7፥7፤መዝ72፥5-6፤ 133፥3፤ምሳ16፥14-15፤20፥2
19፥13 አስ1፥18፤ ምሳ10፥1፤21፥9
19፥14 ምሳ18፥22፤ 2ቆሮ12፥14

4 ሀብት ብዙ ወዳጅ ታፈራለች፤
ድኻን ግን ወዳጁ ገሸሽ ያደርገዋል።

5 ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት አያመልጥም፤
ውሸት የሚነዛም ሳይቀጣ አይቀርም።

6 ብዙ ሰዎች በገዥ ዘንድ ሞገስ ለማግኘት
ያሸረግዳሉ፤
ስጦታን ከሚሰጥ ሰው ጋር ሁሉም ወዳጅ
ነው።

7 ድኻ በሥጋ ዘመዶቹ ሁሉ የተጠላ ነው፤
ታዲያ ወዳጆቹማ የቱን ያህል ይሸሹት!
እየተከታተለ ቢለማመጣቸውም፣
ከቶ አያገኛቸውም።[ሀ]

8 ጥበብን ገንዘቡ የሚያደርጋት ነፍሱን
ይወዳል፤
ማስተዋልን የሚወዳት ይሳካለታል።
9 ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት አያመልጥም፤
ውሸት የሚነዛም ይጠፋል።

10 ተላላ ተንደላቆ መኖር አይገባውም፤
ባሪያ የመሳፍንት ገዥ ከሆነማ የቱን
ያህል ይከፋ!

11 ጥበብ ሰውን ታጋሽ ታደርገዋለች፤
በደልን ንቆ መተውም መከበሪያው ነው።

12 የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤
በፊቱ ሞገስ ማግኘትም በሣር ላይ
እንዳለ ጠል ነው።
13 ተላላ ልጅ ለአባቱ መጥፊያ ነው፤
ጨቅጫቃ ሚስትም እንደማያቋርጥ
ጠፈጠፍ ናት።

14 ቤትና ሀብት ከወላጆች ይወረሳሉ፤
አስተዋይ ሚስት ግን *ከእግዚአብሔር*

[ሀ] 7 ለዚህ ዐረፍተ ነገር የገባው የዕብራይስጡ ትርጓሜ በትክክል አይታወቅም

18፥18 *ዕጣ መጣጣል ሙግትን ያስቆማል፤* የ16፥33 ማብ ይመ፤ ከማቴ27፥35 ጋር ያነጻጽሩ።

18፥19 *የተበደለ ወንድም፤* ያዕቆብ ከይስሐቅ ምርቃትን በመቀበሉ ዔሳው ያደረበትን ታላቅ ቍጣ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ዘፍ27፥41)።

18፥20፤ 12፥14 እና ማብ ይመ።

18፥21 *አንደበት የሞትና የሕይወት ኀይል አላት፤* የ13፥3 ማብ ይመ። *ፍሬዋን፤* ቍ20 ይመ።

18፥22 *ሚስት የሚያገኝ መልካም ነገርን ያገኛል፤* 12፥4 እና ማብ፤ 19፥14 ይመ። *ከእግዚአብሔርም ዘንድ ሞገስን ይቀበላል፤* በ8፥35 ላይ ጥበብን የሚፈልግ ሞገስን ያገኛል ተብሉ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ነው።

18፥24 *ወዳጅ የሚያበዛ ሰው ራሱን ለጥፋት ይዳርጋል፤* ማንም ሰው ወዳጁን በጥንቃቄ መምረጥ ይኖርበታል (12፥26 እና ማብ፤ 17፥17 ይመ)።

19፥1 *ያለ ነውር፤* የ2፥7 ማብ ይመ። *ንግግሩ ጠማማ ... ይልቅ፤* ሀብታም ቢሆንም እንኳ፣ ጠባዩ ምሳሌ የሚሆን አይደለም (28፥6 ይመ)።

19፥2 *ዕውቀት አልባ የሆነ ቀናዒነት፤* ከሮሜ 10፥2 ጋር ያነጻጽሩ። *ጥድፊያም፤* ችኮላ ወደ ድኸነት (21፥5) ወይም ወደ ስሕተት (29፥20) ሊመራ ይችላል። *መንገድን ያስታል፤* ለዚህ ሐረ ግ የተሰጠው የዕብራይስጡ ትርጕም ብዙውን ጊዜ ኀጢአትን ያመለክታል።

19፥3 *በልቡ ግን እግዚአብሔርን ያማርራል፤* ላጋጠመው ችግር እግዚአብሔርን ጥፋተኛ ያደርጋል (ዘፍ 4፥5፤ ኢሳ 8፥21 ይመ፤ ከሰቆ3፥39 ጋር ያነጻጽሩ)።

19፥4 *ሀብት ብዙ ወዳጅ ታፈራለች፤* ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው ዘወትር የሚታየውን እውነታ እንጂ መሆን የሚገባውን አይደለም። ንብ ጣፋጭ ወደ ሆነው ነገር እንደምትሳብ ሁሉ የአፍ ወዳጅም ሀብት ወዳለው ሰው ይነጕዳል፤ ከዚህም የተነሣ የድኻ ወዳጅ ጥቂት ነው፤ (ከቍ6 ጋር ያነጻጽሩ)። ሀብት ወይም ሥልጣን ላለው ሰው አድልዎ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን አዲስ ኪዳን ያስጠነቅቃል (ያዕ2፥1-9)።

*19፥5፤* የ6፥19 ማብ ይመ።

19፥6 *ሞገስ ለማግኘት ... ያሸረግዳሉ፤* ከኢዮ11፥19 ጋር ያነጻጽሩ። *ስጦታን ከሚሰጥ ሰው ... ወዳጅ፤* ልግስናን (ቍ4) ወይም መማለጃን (18፥16) ሊያመለክት ይችላል።

19፥7 *ድኻ ... የተጠላ፤* የቍ4፤14፥20፤ ኢዮ19፥19፤ መዝ 38፥11 ይመ።

19፥8 *ነፍሱን ይወዳል፤* ከ8፥35-36 ጋር ያነጻጽሩ። *ይሳካለታል፤* 13፥13 እና ማብ ይመ።

19፥10 *ተላላ ተንደላቆ መኖር አይገባውም፤* ክብር አይገባውም ማለት ነው (26፥1)። ምቾት አላዋቂውን በአላዋቂነቱ እንዲጸና የማድረግ አዝማሚያ አለው። *ባሪያ የመሳፍንት ገዥ ከሆነማ የቱን ያህል ይከፋ!* ጥበብ ስለ ሌለውና ፈላጭ ቈራጭ የመሆን አዝማሚያም ስለሚያሳይ ነው (17፥2፤ 29፥2፤ ኢሳ3፥4 ይመ)።

19፥11 *ታጋሽ፤* 14፥29፤ 15፥18፤ 16፥32፤ መክ7፥9፤ ያዕ 1፥19 ይመ። *በደልን ንቆ መተውም፤* ራሱን የመግዛት ችሎታ አለው (12፥16፤ 29፥11፤ 2ሳሙ16፥11-12 ይመ)።

19፥12 *የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤* 16፥14 እና ማብ ይመ። *በፊቱ ሞገስ ... እንዳለ ጠል ነው፤* 16፥15 እና ማብ ይመ።

19፥13 *ተላላ ልጅ፤* 17፥21፡25 ይመ። *ጨቅጫቃ ሚስትም፤* በ21፥9፡9፤ በ25፥24፤ በ27፥15 ላይም ተወግዛለች።

19፥14 *አስተዋይ ሚስት፤* 12፥4 እና ማብ፤ እንዲሁም 18፥22 ይመ።

ዘንድ ናት።
15 ስንፍና ከባድ እንቅልፍ ላይ ይጥላል፤
ዋልጌም ሰው ይራባል።
16 ትእዛዛትን የሚያከብር ሕይወቱን
ይጠብቃል፤
መንገዱን የሚንቅ ግን ይሞታል።
17 ለድኻ የሚራራ ለእግዚአብሔር
ያበድራል፤
ስላደረገውም ተግባር ዋጋ ይከፍለዋል።
18 ገና ተስፋ ሳለ፣ ልጅህን ሥርዐት
አስይዘው፤
ሲሞት ዝም ብለህ አትየው።
19 ግልፍተኛ ሰው ቅጣትን መቀበል
ይገባዋል፤
በምሕረት ካለፍከው ሌላም ጊዜ
አይቀርልህም።
20 ምክርን ስማ፤ ተግሣጽን ተቀበል፤
በመጨረሻም ጠቢብ ትሆናለህ።
21 በሰው ልብ ብዙ ሐሳብ አለ፤
የሚፈጸመው ግን የእግዚአብሔር ሐሳብ
ነው።
22 ሰው የሚመኘው ጽኑ ፍቅር ነው፤
ውሸታም ከመሆንም ድኻ መሆን
ይሻላል።^
23 እግዚአብሔርን መፍራት ወደ ሕይወት
ይመራል፤
እንዲህ ያለውም ሰው እፎይ ብሎ
ያርፋል፤ መከራም አያገኘውም።
24 ሰነፍ እጁን ከወጭቱ ያጠልቃል፤
ወደ አፉ ግን መመለስ እንኳ ይሳነዋል።
25 ፌዘኛን ግረፈው፤ ብስለት የሌለውም
ማስተዋልን ይማራል፤
አስተዋይን ዝለፈው፤ ዕውቀትን
ይገበያል።
26 አባቱን የሚዘርፍ፣ እናቱንም
የሚያሳድድ፣
ዕፍረትና ውርደት የሚያመጣ ልጅ
ነው።
27 ልጄ ሆይ፤ እስቲ፣ ምክርን ማዳመጥ
ተው፤
ከዕውቀትም ቃል ትስታለህ።
28 ዐባይ ምስክር በፍትሕ ላይ ያፌዛል፤
የክፉዎችም አፍ በደልን ይሰለቅጣል።
29 ለፌዘኞች ቅጣት፣
ለተላሎችም ጀርባ ጅራፍ
ተዘጋጅቶአል።

20 የወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ
መጠጥም ጠበኛ ያደርጋል፤
በእነዚህ የሳተ ሁሉ ጠቢብ አይደለም።
2 የንጉሥ ቍጣ እንደ አንበሳ ግሣት ነው፤
የሚያስቈጣውም ሰው ሕይወቱን
ለመከራ ይዳርጋል።
3 ከጠብ መራቅ ለሰው ክብሩ ነው፤
ተላላ ሁሉ ግን ለጥል ይቸኵላል።
4 ሰነፍ ሰው በወቅቱ አያርስም፤
ስለዚህ በመከር ወራት ይፈልጋል፤
አንዳችም አያገኝም።
5 የሰው ልብ ሐሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው፤
አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ
ያወጣዋል።
6 ብዙ ሰው ጽኑ ፍቅር እንዳለው ይናገራል፤
ታማኝን ሰው ግን ማን ሊያገኘው
ይችላል?
7 ጻድቅ ነቀፋ የሌለበት ሕይወት ይመራል፤

19፥15 ምሳ10፥4፤ 20፥13
19፥16 ምሳ16፥17፤ ሮሜ10፥5
19፥17 ዘዳ24፥14: 19፤ምሳ14፥21፤22፥9፤ ማቴ10፥42
19፥18 ምሳ13፥24፤ 23፥13-14
19፥20 ምሳ4፥1፤ 12፥15
19፥21 መዝ33፥11 1 ምሳ16፥9፤20፥24 ፤ኢሳ8፥10፤14፥24 :27፤31፥2፤40፥8፤46፥ 10፤48፥14፤55፥11፤ ኤር44፥29፤ሰቆ3፥37
19፥23 ኢዮ4፥7፤ ምሳ10፥27
19፥24 ምሳ26፥15
19፥25 መዝ141፥5 ፤ምሳ9፥9፤21፥11
19፥26 ምሳ28፥24
19፥27 ምሳ1፥8
19፥28 ኢዮ15፥16
19፥29 ዘዳ25፥2
20፥1 ዘሌ10፥9፤ 1ሳሙ25፥36፤1ነገ 20፥16፤ምሳ31፥4፤ ዕን2፥5
20፥2 አስ7፥7፤ምሳ 16፥14፤19፥12
20፥3 ዘፍ13፥8፤ 1ሳሙ25፥25
20፥4 ምሳ6፥6፤ መክ10፥18
20፥5 መዝ18፥16
20፥6 መዝ12፥1
20፥7 መዝ26፥1፤ 37፥25-26፤112፥2

^22 ወይም የሰው ስስት ውርደት/ ኀፍረት ያመጣበታል።

*19፥15፤* 6፥11፤ 10፥4 እና ማብ ይመ።

*19፥16፤* 13፥13፤ 15፥10፤ 16፥17 እና ማብ ይመ።

19፥17 *ለድኻ የሚራራ፤* የ14፥21 ማብ፤ እንዲሁም 14፥31 ይመ። *ለእግዚአብሔር ያበድራል፤* ለድኾች በልግስና መስጠት ራሱ ጌታን ማገልገል ነው፤ እግዚአብሔር በልግስና የሚሰጡትን ይባርካቸዋል (6፥1 እና ማብ ይመ)።

19፥18 *ልጅህን ሥርዐት አስይዘው፤ ሲሞት ዝም ብለህ አትየው፤* የ13፥24 ማብ ይመ።

19፥19 *ግልፍተኛ ሰው፤* ከ14፥16-17:29፤ 15፥18 ጋር ያነጻጽሩ።

*19፥21፤* 16፥1 እና ማብ ይመ።

19፥22 *የሚመኘው ጽኑ ፍቅር ነው፤* ይሁን እንጂ እንዲህ ያለውን ታማኝነት ማግኘት አስቸጋሪ ነው (ከ20፥6፤ 14፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። *ውሸታም ከመሆንም ድኻ መሆን ይሻላል፤* ቍ1:28፤ 6፥12 ይመ።

19፥23 *እግዚአብሔርን መፍራት፤* የ1፥7 ማብ ይመ። *ወደ ሕይወት ይመራል፤* የ10፥11 ማብ ይመ። *መከራም አያገኘውም፤* 3፥21፤ 4፥26 እና ማብ ይመ።

19፥24 *ሰነፍ፤* የ6፥6 ማብ ይመ።

19፥25 *ፌዘኛን ግረፈው፤* ቍ29፤14፥3፤ እንዲሁም የ1፥22፤ 17፥10 ማብ ይመ። *ብስለት የሌለውም፤* ገራገር የሆነ ሰው ማለት ነው (የ1፥4 ማብ ይመ)።

19፥26 *አባቱን የሚዘርፍ፣ እናቱንም የሚያሳድድ፤* ወላጆች ሲታመሙና ዕድሜ ሲጫናቸው፣ ልጆቻቸው እንዲንከባከቧቸው ይጠበቃል (ከኢሳ51፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። በእነርሱ ላይ ማመፅና (ከመሳ17፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ) ጕዳት ማድረስ ቀደም ባለው ዘመን ትልቅ ወንጀል ነበር። *ዕፍረትና ውርደት፤* 10፥5፤ 13፥5 ይመ።

*19፥27፤* 5፥1-2 ይመ።

19፥28 *ዐባይ ምስክር፤* ቍ5፤ እንዲሁም የ6፥19 ማብ ይመ። *በደልን ይሰለቅጣል፤* "ኀጢአትንም እንደ ውሃ የሚጠጣ ሰው" ተብሎ የተገለጸውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ኢዮ15፥16፤ እንዲሁም 34፥7 ይመ)።

19፥29 *ለፌዘኞች ቅጣት፤* ቍ25 ይመ። *ለተላሎችም ጀርባ ጅራፍ፤* 10፥13፤ 14፥3፤ 26፥3 ይመ።

20፥1 *የወይን ጠጅ ፌዘኛ፣ ብርቱ መጠጥም ጠበኛ፤* ጠጥተው የሚሰክሩ ፌዘኞችና ጠበኞች ይሆናሉ (ሆሴ7፥5 ይመ)። መጽሐፈ ምሳሌ ስካርን ከድኽነት (23፥20-21)፣ ከጠብ (23፥29-30) እና ፍርድን ከማጓደል (31፥4-5) ጋር ያዛምደዋል። *የሳተ ሁሉ፤* ዘፍ9፥21፤ ኢሳ28፥7 ይመ።

*20፥2፤* 16፥14 እና ማብ ይመ።

20፥3 *ለጥል ይቸኵላል፤* 6፥14፤ 17፥14:19፤ 18፥6 ይመ።

20፥4 *በወቅቱ፤* ሰነፉ ገበሬ የአየሩን ጠባይ ምክንያት በማድረግ ዛሬ ማከናወን ያለበትን ሥራ፣ "ነገ ከነገ ወዲያ አከናውነዋለሁ" እያለ ያንቀላፋል፤ በዚህም ምክንያት በምርት ወራት የሚያገኘው ፍሬ አይኖረውም።

*20፥5፤* የሰው ሐሳብ ጥልቅ በመሆኑ፣ ለሌላው ሰው ግልጽ ሆኖ ላይታየው ይችላል፤ ጥበበኛ ሰው ግን ወደ ልቡ ዘልቆ በመግባት የውስጥ ሐሳቡን ለይቶ ማየት ይችላል። *ቀድቶ ያወጣዋል፤* ከጕድጓድ ውሃ እንደ መቅዳት ነው።

20፥6 *ጽኑ ፍቅር፤* የ19፥22 ማብ ይመ። *ታማኝን ሰው ግን ማን ሊያገኘው ይችላል?* ከመክ7፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ።

*20፥7፤* ይህ ምሳሌ የተነገረው በዘፀ20፥5-6 በተመለከተው

ከእርሱም በኋላ የሚከተሉት ልጆቹ
ቡሩካን ናቸው::
[8]ንጉሥ ለፍርድ ዙፋኑ ላይ በሚቀመጥበት
ጊዜ፣
ክፋውን ሁሉ በዐይኖቹ አበጥሮ ይለያል::
[9]ለመሆኑ፣ “ልቤን በንጽሕና ጠብቄአለሁ፤
ንጹሕ ነኝ፤ ኀጢአት የለብኝም” የሚል
ማን ነው?
[10]ሁለት ዐይነት ሚዛን፣ ሁለት ዐይነት
መስፈሪያ፣
ሁለቱንም እግዚአብሔር ይጸየፋቸዋል::
[11]ሕፃን እንኳ ጠባዩ ንጹሕና ቅን መሆኑ፣
ከአድራጎቱ ይታወቃል::
[12]የሚሰሙ ጆሮዎች፣ የሚያዩ ዐይኖች፣
ሁለቱንም እግዚአብሔር ሠርቷቸዋል::
[13]እንቅልፍ አትውደድ፤ አለዚያ ድኻ
ትሆናለህ፤
ዐይንህን ክፈት፤ የተትረፈረፈ ምግብ
ይኖርሃል::
[14]ዕቃ የሚገዛ፣ “የማይረባ ነው፤ የማይረባ
ነው” ብሎ ያራክሳል፤
ሲመለስ ግን በግገርው ይኰራራል::
[15]ወርቁም አለ፤ ቀዩም ዕንቍ
ተትረፍርፎአል፤
ዕውቀት የሚናገሩ ከንፈሮች ግን ብርቅ
ጌጦች ናቸው::
[16]ለማይታወቅ ሰው ዋስ የሆነውን ልብሱን
ግፈፈው፤
ለዘልዛላ ሴት የተዋሰውን በቃሉ ያዘው::
[17]ሰው በማጭበርበር ያገኘው ምግብ
ይጣፍጠዋል፤
በመጨረሻ ግን አፉን ኰረት ሞልቶት

20፥8 ቍ26፤1ነገ 7፥7፤ምሳ25፥4-5
20፥9 1ነገ8፥46፤ ኢዮ15፥14፤መክ 7፥20፤1ዮሐ1፥8
20፥10 ቍ23፤ምሳ 11፥1
20፥11 መዝ39፥1
20፥12 መዝ94፥9
20፥13 ምሳ6፥11፤ 19፥15
20፥16 ዘፀ22፥26፤ ምሳ27፥13
20፥17 ኢዮ20፥14፤ ምሳ9፥17፤ሰቆ3፥16
20፥18 ምሳ11፥14፤ 24፥6
20፥19 ምሳ11፥13
20፥20 ዘፀ21፥17፤ ኢዮ18፥5፤ምሳ30፥11
20፥22 ምሳ24፥29፤ ኢሳ37፥20፤ኤር 1፥19፤42፥11፤ሮሜ 12፥19
20፥23 ቍ10፤ዘዳ 25፥13
20፥24 ኢዮ33፥29፤ መዝ 90፥12፤ምሳ 19፥21፤ኤር10፥23
20፥25 ምሳ10፥19፤ 18፥13፤መክ5፥2፡4-5 ፤ኤር44፥25
20፥26 ቍ8
20፥27 መዝ119፥ 105፤ምሳ16፥2
20፥28 መዝ40፥11 ፤ምሳ16፥12፤ኢሳ 16፥5

ያገኘዋል::
[18]ምክር ጠይቀህ ዕቅድ አውጣ፤
ጦርነት የምትገጥም ከሆነ መመሪያ
ተቀበል::
[19]ሐሜተኛ ምስጢር ያባክናል፤
ስለዚህ ለፍላፊን ሰው አርቀው::
[20]አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ፣
መብራቱ በድቅድቅ ጨለማ ይጠፋል::
[21]ከጅምሩ ወዲያው የተገኘ ርስት፣
በመጨረሻ በረከት አይኖረውም::
[22]“ለደረሰብኝ በደል ብድሬን ባልመልስ!”
አትበል፤
እግዚአብሔርን ጠብቅ፤ እርሱ
ይታደግሃል::
[23]ሁለት ዐይነት ሚዛን በእግዚአብሔር
ዘንድ አጸያፊ ነው፤
አባይ ሚዛን አይወደድም::
[24]የሰው አካሄዱ በእግዚአብሔር ይመራል፤
ሰውስ የገዛ መንገዱን እንዴት ማስተዋል
ይችላል?
[25]በችኰላ ስእለት መሳል፣
ከተሳሉም በኋላ ማቅማማት ለሰው
ወጥመድ ነው::
[26]ጠቢብ ንጉሥ ክፋዎችን አበጥሮ ይለያል፤
የመውቂያ መንኰራኵርንም በላያቸው
ላይ ይነዳል::
[27]የሰው መንፈስ ለእግዚአብሔር መብራት
ነው፤*
ውስጣዊ ማንነቱንም ይፈትሻል::
[28]ፍቅርና ታማኝነት ንጉሥን ይጠብቁታል፤

*27 ወይም የእግዚአብሔር መብራት የሰውን መንፈስ ይመረምራል

መሠረት ነው:: *ልጆቹ ቡሩካን ናቸው፤* 13፥22፤ እንዲሁም የ14፥26 ማብ ይመ::

20፥8 *ክፋውን ሁሉ ... ይለያል፤* 16፥10፤ መዝ11፥4 ይመ::

20፥9 *በንጽሕና ጠብቄአለሁ ... ንጹሕ ... ኀጢአት የለብኝም፤* ኀጢአት የሌለበት ማንም ሰው የለም (ከኢዮ14፥4፤ ከሮሜ3፥23 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይሁን እንጂ ኀጢአታቸው የተሰረየ ላቸው ሁሉ፣ “ንጹሕ እጅና ንጹሕ ልብ” አላቸው (መዝ24፥4፤ እንዲሁም 51፥1-2፡9-10 ይመ)::

*20፥10፤* የ11፥1 ማብ ይመ፤ ከ16፥11 ጋር ያነጻጽሩ::

*20፥11፤* አንድ ልጅ ከሕፃንነት ዘመኑ ጀምሮ የሚፈጽመው ድርጊት፣ የወደፊት የሕይወቱን አቅጣጫ ያመለክታል::

20፥13 *እንቅልፍ ... ድኻ ትሆናለህ፤* 24፥33-34 ይመ::

20፥14 *የማይረባ ነው፤ የማይረባ ነው፤* ብዙውን ጊዜ የዕቃ ዋጋ የሚወሰነው በክርክር ነበር፤ በዚህም ምክንያት ገዥ ዕቃውን በርካሽ ዋጋ ለመግብየት የዕቃውን ጥራት ያጣጥል ነበር::

20፥15 *ወርቁም ... ቀዩም ዕንቍ፤* ቀደም ባለው ዘመን ከወርቅና ከቀይ እንቍ ይልቅ ጥበብ ትከብር ነበር (3፥14-15፤ 8፥10-11)::

*20፥16፤* የ6፥1 ማብ ይመ:: *ልብሱን ግፈፈው፤* ልብስ በዕዳ መያዣነት ይወሰድ ነበር (ዘዳ24፥10-13):: ማንም ሰው ታማኝነቱ ለማይታወቅ እንግዳ ወይም ቋሚ ነገረ ቢስ መሆኗን አገር ሳወቃት ዘልዛላ ሴት ዕዳ ዋስ ቢሆን፣ የለበሰው ልብስ ሊወሰድበት እስከሚችል ድረስ ተጠያቂ ይሆን ነበር::

20፥17 *ይጣፍጠዋል፤* በ19፥17 ላይ በዝሙት ዐዳሪዋ የተዘጋጀውን ጣፋጭ “ምግብ” ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ:: በክፉ ሰው አንደበት ላይ ክፋት ማራኪ እንደ ሆነ፣ በሆዱ ውስጥ ግን ወደ መራራነት እንደሚለወጥ ሶፋር የተባለው ሰው አስተውሎአል (ኢዮ 20፥12-18)፤ የ10፥2 ማብ ይመ::

20፥18 *ምክር ... መመሪያ፤* 15፥22፤ ሉቃ14፥31 ይመ::

20፥20 *አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ፤* የሞት ቅጣት ይደርስበት ነበር (ዘሌ 20፥9 ይመ፤ ከምሳ 30፥11፡17 ጋር ያነጻጽሩ):: *መብራቱ ... ይጠፋል፤* ይሞታል ማለት ነው (የ13፥9 ማብ ይመ)::

20፥21 *ከጅምሩ ወዲያው የተገኘ ርስት ... በረከት አይኖረውም፤* ከ19፥26 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም ሀብቱን ያባከነውን ልጅ ታሪክ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ሉቃ15፥12-13)::

20፥22 *ብድሬን ባልመልስ!* በቀል የማንም ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ነው፤ ለክፋዎች እንደ ሥራቸው ይከፍላቸዋል (ዘዳ 32፥35፤ መዝ94፥1 ይመ):: *እግዚአብሔርን ጠብቅ፤* መዝ27፥14፤ 37፥34 ይመ::

*20፥23፤* ቍ10 እንዲሁም የ11፥1 ማብ ይመ::

*20፥24፤* 3፥5-6፤ 16፥9 እና ማብ ይመ::

20፥25 *በችኰላ ... መሳል፤* ሰዎች ከልብ ላቀረቡት ልመና ጌታ በቸርነቱ መልስ ሲሰጣቸው፣ የተለየ ስጦታ ያበረክታሉ (ዘሌ27፥1-25፤ ዘዳ23፥21፤ መሳ11፥30-31፡34-35፤ 1ሳሙ 1፥11 ይመ):: አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ያለው ስእለት በችኰላ ይደረግና ሳይፈጸም ይቀራል (ከመክ5፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ)::

20፥26 *የመውቂያ መንኰራኵርንም፤* እህሉን ከገለባ የሚለይ መሣሪያ ነው (ከኢሳ 28፥27-28 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እንደዚሁም ክፋዎች ከጻድቃን እንዲለዩ፣ እንደ ሥራቸውም እንዲቀጡ ይደረጋል::

*20፥27፤* ኅሊና ሰውን ስለ ኀጢአቱ ለመውቀስ የሰውን ውስጣዊ ክፍል ይመረምራል፤ የ15፥11 ማብ ይመ::

20፥28 *ፍቅርና ታማኝነት ንጉሥን ይጠብቁታል፤ ... ይ*

በፍቅርም ዙፋኑ ይጸናል።
[29]የጎልማሶች ክብር ብርታታቸው፣
የሽማግሌዎችም ሞገስ ሽበታቸው ነው።
[30]የሚያቈስል በትር ክፋትን ያስወግዳል፤
ግርፋትም የውስጥ ሰውነትን ያጠራል።

# 21

[21]የንጉሥ ልብ *በእግዚአብሔር* እጅ
ነው፤
እርሱም እንደ ቦይ ውሃ ደስ ወዳሰኘው
ይመራዋል።
[2]ለሰው መንገዱ ሁሉ ቀና ይመስለዋል፤
*እግዚአብሔር* ግን ልብን ይመዝናል።
[3]ከመሥዋዕት ይልቅ ጽድቅንና ፍትሕን
ማድረግ፣
*በእግዚአብሔር* ዘንድ ተቀባይነት
አለው።
[4]ትዕቢተኛ ዐይን፣ እብሪተኛ ልብ፣
የክፉዎችም መብራት ኀጢአት ናቸው።
[5]የትጉህ ሰው ዕቅድ ወደ ትርፍ
ያመራል፤
ችኩላም ወደ ድኽነት ያደርሳል።
[6]በሐሰተኛ አንደበት የተገኘ ሀብት፣
በኖ የሚጠፋ ተን፣ ለሞትም የሚያበቃ
ወጥመድ ነው።”
[7]ክፉዎችን ዐመፃቸው ይጠራርጋቸዋል፤
ቅን ነገር ማድረግ አይወዱምና።
[8]የበደለኛ መንገድ ጠማማ ነው፤
የንጹሕ ሰው ጠባይ ግን ቀና ነው።

20፥29 ምሳ16፥31
20፥30 መዝ51፥2፤ ምሳ22፥15፤ኢሳ1፥5
21፥1 አስ5፥1፤ኤር 39፥11-12
21፥2 ምሳ16፥2
21፥3 1ሳሙ15፥22፤ ኢሳ1፥11፤ሚክ6፥6-8
21፥4 ኢዮ41፥34
21፥5 ምሳ10፥4
21፥6 ምሳ10፥2
21፥7 ምሳ11፥5
21፥8 ምሳ2፥15
21፥9 ቍ19፤ምሳ 19፥13፤25፥24
21፥11 ምሳ19፥25
21፥12 ምሳ14፥11
21፥13 ዘፀ11፥6፤ ኢዮ29፥12
21፥14 ዘፍ32፥20
21፥15 ምሳ10፥29
21፥16 ሕዝ18፥24
21፥17 ምሳ23፥20-21፡29-35

[9]ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት
ከመኖር፣
በጣራ ላይ ጥግ ይዞ መኖር ይሻላል።
[10]ክፉ ሰው ክፋትን አጥብቆ ይመኛል፤
ባልንጀራውም ከእርሱ ዘንድ ርኅራኄን
አያገኝም።
[11]ፌዘኛ ሲቀጣ፣ አላዋቂ ጥበብን ያተርፋል፤
ጠቢብ ሰው ቢማር ዕውቀትን ያገኛል።
[12]ጻድቁ” የክፉዎችን ቤት ልብ ብሎ
ይመለከታል፤
ክፉዎችንም ያጠፋቸዋል።
[13]ሰው የድኾችን ጩኸት ሳለመስማት
ጆሮውን ቢዘጋ፣
እርሱም ይጮኻል፤ መልስም አያገኝም።
[14]በስውር የተደረገ ስጦታ ቍጣን
ያበርዳል፤
በጕያ የተሸሸገ እጅ መንሻም ታላቅ
ቍጣን ጸጥ ያደርጋል።
[15]ፍትሕ ሲሰፍን ጻድቁን ደስ ያሰኘዋል፤
ክፉ አድራጊዎችን ግን ያሸብራል።
[16]የማስተዋልን መንገድ የሚስት ሰው፣
በሙታን ጉባኤ ያርፋል።
[17]ቅንጦትን የሚወድ ይደኸያል፤
የወይን ጠጅና ዘይት የሚወድም ባለጠጋ

”6 አንዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች፣ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጌት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አያሌ የዕብራይስጥ ጽሑፎች ግን *ሞትን ለሚሹ በኖ እንደሚጠፋ ተን ነው* ይላሉ።
”12 *ወይም ጻድቁ ሰው*

*ጸናል*፤ በጎ አድራጎትና ቸርነት ንጉሥን በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ያደርጋሉ፤ ሕዝቡንም ታማኝ ዜጎች እንዲሆኑለት ያበረታታሉ (ከ3፥3፤ 14፥22፤ 16፥12፤ 29፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

20፥29 ***ብርታታቸው***፤ ከኤር9፥23 ያነጻጽሩ። ***የሽማግሌዎችም ሞገስ ሽበታቸው***፤ የ16፥31 ማብ ይመ።

20፥30 ***የሚያቈስል በትር ክፋትን ያስወግዳል***፤ ክፋትን ለመግታት ጠበቅ ያለ ቅጣት አስፈላጊ ነው። ተላሎች በበትር የሚመቱ መሆናቸውን ብዙ ጥቅሶች ያመለክታሉ (10፥13፤14፥3፤ 19፥29)፤ ዳሩ ግን ተላሎች ምንጊዜም ልበ ቢስ በመሆናቸው፣ በትር ቢወርድባቸውም እንኳ ከጥፋታቸው አይመለሱም ይሆናል (ከ17፥10፤ 27፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፥1 ***የንጉሥ ልብ በእግዚአብሔር እጅ ነው***፤ እግዚአብሔር በመሪዎች ላይ የበላይ ገዥ ስለ ሆነ፣ በታሪክ ውስጥ የማዳን ዕቅዱ ይከናወን ዘንድ በውሳኔያቸው ላይ ተጽእኖ ያደርጋል (ከዘፀ10፥1-2፤ ከዕዝ7፥21፤ ከኢሳ10፥5-7፤ 45፥1-6 ጋር ያነጻጽሩ)። በእርሱ ፈቃድ መሠረት ኀላፊነታቸውን እንዲወጡ እግዚአብሔር መሪዎችን ይመራ ዘንድ የቅዱሳን ጸሎት እንደሚያስፈልግና በልመናቸውም መሠረት እንደሚያከናውን አዲስ ኪዳን ያስተምረናል (1ጢሞ2፥1-3)።

21፥2 ***ቀና ይመስለዋል***፤ 14፥12፤ 16፥2 ይመ። ***ልብን ይመዝናል***፤ 24፥12፤ ኢዮ31፥6፤ መዝ139፥23፤ 1ቆሮ4፥4-5፤ ዕብ 4፥12 ይመ።

21፥3 ***ከመሥዋዕት ይልቅ … ተቀባይነት አለው***፤ ማንኛውም ምእመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልተመላለሰ መሥዋዕቱ፣ አምልኮውና ስጦታው በጌታ ፊት ተቀባይነት የላቸውም (ከሆሴ6፥6፤ ከሚክ6፥7-8፤ ከሮሜ12፥1-2፤ ከዕብ10፥5-9 ጋር ያነጻጽሩ)። ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መባ ከቅድስና ሕይወት ጋር እንዲያያዝ ያስፈልጋል፤ ይህ ካልሆነ ግን መባው በጌታ ፊት አስጸያፊ ይሆናል (ቍ27)።

21፥4 ***ትዕቢተኛ ዐይን***፤ የ6፥17 ማብ፤ እንዲሁም 16፥5፡18 ይመ። ***መብራት***፤ ዐይን/ነው (20፥27፤ ሉቃ11፥34 ይመ)።

21፥5 ***የትጉህ ሰው ዕቅድ ወደ ትርፍ ያመራል***፤ የ10፥4 ማብ ይመ። ***ችኩላም***፤ በጥድፊያ የሚከናወነውን ተግባር (19፥2) ወይም በአቋራጭ ሀብታም ለመሆን የሚደረገውን መዋከብ ያመለክታል (13፥11 እና ማብ፤ 20፥21፤ 28፥20 ይመ)።

21፥6 ***በሐሰተኛ አንደበት የተገኘ ሀብት***፤ የ10፥2 ማብ ይመ፤ ከ19፥1 ጋር ያነጻጽሩ። ***በኖ የሚጠፋ ተን***፤ 13፥11 እና ማብ፤ መክ1፥14 ይመ። ***ለሞትም የሚያበቃ ወጥመድ***፤ ከ5፥22፤ 7፥23 ጋር ያነጻጽሩ።

21፥7 ***ክፉዎችን ዐመፃቸው ይጠራርጋቸዋል***፤ 1፥18-19 እና ማብ ይመ።

21፥9 ***በጣራ ላይ ጥግ***፤ በአገራችን በአንዳንድ ቦታ እንደሚታየው ሁሉ የቤት ጣራ ጠፍጣፋ ሆኖ በላዩ ላይ ትናንሽ ክፍሎችን መሥራት ይቻል ነበር (ዘዳ22፥8፤ 2ነገ4፥10 ይመ)። ***ከጨቅጫቃ ሚስት***፤ የ19፥13 ማብ ይመ።

21፥10 ***ክፋትን አጥብቆ ይመኛል***፤ 4፥16፤ 10፥23 ይመ። ***ባልንጀራውም … ርኅራኄን አያገኝም***፤ ከ14፥21 ጋር ያነጻጽሩ።

*21፥11*፤ 19፥25 እና ማብ ይመ።

21፥12 ***ጻድቁ***፤ ከኢዮ34፥17 ጋር ያነጻጽሩ። ***የክፉዎችን ቤት … ያጠፋቸዋል***፤ 10፥25 እና ማብ፤ 14፥11 ይመ።

21፥13 ***የድኾችን ጩኸት***፤ በተቸገርን ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማልን ዘንድ፣ የወገኖቻችንን ችግር በመስማት በፍቅር ልንደርስላቸው ይገባል (ከማቴ25፥31-46፤ ከሉቃ16፥19-31፤ ከያዕ2፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። ***እርሱም … መልስም አያገኝም***፤ የ1፥28 ማብ ይመ። የሀብታሙን ሰውና (ሉቃ 16፥19-31) ርኅራኄ ያሌለውን አገልጋይ (ማቴ18፥23-34) ዕጣ ፈንታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

21፥14 ***ስጦታ … እጅ መንሻም***፤ የ17፥8 ማብ እንዲሁም 18፥16፤ 19፥6 ይመ። ***ቍጣን ያበርዳል … ታላቅ ቍጣን***፤ ግፍ ደርሶበት የተናደደውን ወገን ሳይመለከት አይቀርም (6፥34-35 ይመ)።

21፥15 ***ጻድቁን ደስ ያሰኘዋል***፤ 11፥10 እና ማብ ይመ። ***ክፉ አድራጊዎችን … ያሸብራል***፤ 10፥29 እና ማብ፤ ሮሜ13፥13 ይመ።

*21፥16*፤ ተታሎ ራሱን ለዝሙት ዐዳሪዎ በሸጠው ሰው ታሪክ ውስጥ ሥዕላዊ መልክ ተገልጾአል (2፥18፤ 5፥13፤ 7፥22-23፤ 9፥18 ይመ)።

21፥17 ***የወይን ጠጅና ዘይት***፤ ሁለቱም ከቅንጦት ግብዣ

አይሆንም።

18ክፉ ሰው ለጻድቅ፣
ወስላታም ለቅን ሰው ወጆ ይሆናል።

19ከጨቅጫቃና ከቍጡ ሚስት ጋር
ከመኖር፣
በምድር በዳ መኖር ይሻላል።

20በጠቢብ ቤት ምርጥ ምግብና ዘይት
ተከማችቶ ይገኛል፤
ተላላ ሰው ግን ያለ የሌለውን
ያሚጥጣል።

21ጽድቅንና ፍቅርን የሚከተል፤
ሕይወትን ብልጽግናንና[ሀ] ክብርን ያገኛል።

22ጠቢብ የኀያላንን ከተማ ቅጥር ጥሶ
ይገባል፤
መታመኛ ምሽጋቸውንም ያፈርሳል።

23አንደበቱንና ምላሱን የሚቈጣጠር፣
ራሱን ከመቅሠፍት ይጠብቃል።

24ትዕቢተኛና ኵሩ ሰው፣ "ፌዘኛ"
ይባላል፤
በጠባዩም እብሪተኛ ነው።

25ታካችን የሚገድለው ምኞቱ ነው፤
እጆቹ መሥራት አይፈልጉምና።

26ክፉ ሰው ቀኑን ሙሉ ይመኛል፤
ጻድቅ ግን አንዳች ሳያስቀር ይሰጣል።

27የክፉ ሰው መሥዋዕት አጸያፊ ነው፤
በክፉ ዐላማ ሲያቀርብማ የቱን ያህል
አስከፊ ይሆን!

28ሐሰተኛ ምስክር ይጠፋል፤[ለ]

21፥18 ምሳ11፥8፤ ኢሳ43፥3
21፥19 ቍ9
21፥21 መዝ25፥13፤ ማቴ5፥6
21፥22 ምሳ8፥14
21፥23 መዝ34፥13፤ ምሳ10፥19፤12፥13፤ 13፥13
21፥24 ኤር43፥2
21፥25 ምሳ13፥4
21፥26 ዘሌ25፥35፤ 2ሳሙ17፥27
21፥27 1ነገ14፥24፤ ምሳ15፥8
21፥28 ምሳ19፥5፤ ኢሳ29፥21
21፥29 ምሳ14፥8
21፥30 2ዜና13፥12፤ ኢዮ5፥13፤12፥13፤15፥25፤ ኢሳ8፥10
21፥31 መዝ33፥12-19፤ ኢሳ31፥1
22፥1 መክ7፥1
22፥2 ኢዮ31፥15፤ ምሳ29፥13፤ ማቴ5፥45
22፥3 ምሳ14፥16፤ 27፥12
22፥4 ምሳ10፥27፤ 15፥33፤ ሶፎ4፥36
22፥5 ምሳ15፥19
22፥6 ዘፍ14፥14፤ ዘዳ6፥7፤ ኤፌ6፥4

እውነቱን የሚናገር ግን ጸንቶ ይኖራል።

29ክፉ ሰው በአጕል ድፍረት ይቀርባል፤
ቅን ሰው ግን አደራረጉን ያስተውላል።

30እግዚአብሔርን ለመቋቋም የሚያስችል፣
አንዳችም ጥበብ ማስተዋልና ዕቅድ
የለም።

31ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል፤
ድል ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

22 መልካም ስም ከብዙ ብልጽግና
ይመረጣል፤
መከበርም ከብርና ከወርቅ ይበልጣል።

2ባለጠጋና ድኻ የሚጋሩት ነገር፣
እግዚአብሔር የሁላቸውም ፈጣሪ መሆኑ
ነው።

3አስተዋይ ሰው አደጋ ሲያይ መጠጊያ
ይሻል፤
ብስለት የጐደለው ግን በዚያው
ይቀጥላል፤ መከራም ያገኘዋል።

4ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት፣
ሀብትን፣ ክብርንና ሕይወትን ያስገኛል።

5በክፉዎች መንገድ ላይ እሾህና ወጥመድ
አለ፤
ነፍሱን የሚጠብቅ ግን ከእነዚህ
ይርቃል።

6ልጅን የሚሄድበትን መንገድ
አስተምረው፤[ሐ]

[ሀ]21 ወይም ጽድቅን
[ለ]28 ወይም እርሱን የሚሰማውም ሁሉ ለዘላለም ይጠፋል
[ሐ]6 ወይም አስጀምረው

ጋር የተያያዙ ናቸው (23፥20-21፤ አሞ6፥6 ይመ)።

21፥18 *ክፉ ሰው ለጻድቅ ... ወጆ፤* ከ11፥8 ሐሳብ ጋር ተቀራራቢ ነው። በኢሳ43፥34 ላይ ፋርስ ከይሁዳ የተማረኩትን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስለሆነች፣ እግዚአብሔር ለፋርስ በወጆነት ሦስት አገሮችን ሰጠ (የኢሳ43፥4 ማብ ይመ)።

21፥19፤ የ19፥13 ማብ ይመ።

21፥20 *ምርጥ ምግብና ... ተከማችቶ፤* 3፥10 እና ማብ፤ 8፥21 ይመ። *ዘይት፤* የወይራ ዘይት ነው (የቍ17 ማብ እንዲሁም ዘዳ 7፥13 ይመ)።

21፥21 *ጽድቅንና ... የሚከተል፤* 15፥9 ይመ። *ሕይወትን፣ ብልጽግናንና ክብርን፤* ጥበብን የሚሹ ያገኟቸዋል (የ3፥2 ማብ፤ እንዲሁም 3፥16፤ 8፥18 ይመ፤ ከ22፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፥22 *ጠቢብ ... ቅጥር ጥሶ ይገባል፤* "ጥበብ ከኀይል ትበልጣለች" የሚለውን መግለጹ ሳይሆን አይቀርም (መክ9፥16)። በ24፥5፤ በ2ቆሮ10፥4 ላይ የመንፈስ ሰይፍ፣ "ምሽግን ለማፍረስ የመለኮት ኀይል አለው" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ።

*21፥23፤* 13፥3 እና ማብ ይመ፤ 18፥21 ይመ።

21፥24 *"ፌዘኛ" ይባላል፤* የ1፥22 ማብ ይመ። እግዚአብሔር ያላግጥበታል፤ ከመጠን በላይ ለሆነው ኵራቱም ይቀጣዋል (ከ3፥34፤ 19፥25፡29፤ 21፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፥25 *ታካችን ... ምኞቱ፤* የ6፥6፤ 13፥4 ማብ ይመ።

21፥26 *አንዳች ሳያስቀር ይሰጣል፤* የተቸገሩትን ይረዱ ዘንድ ጻድቃን ሀብት ተሰጥቶአቸዋል (መዝ37፥26፤112፥9 ይመ፤ ከኤፌ4፥28 ጋር ያነጻጽሩ)።

21፥27 *የክፉ ሰው መሥዋዕት አስጸያፊ ነው፤* የቍ3፤ 15፥8 ማብ ይመ።

21፥28 *ሐሰተኛ ምስክር ይጠፋል፤* 19፥5፡9፤ እንዲሁም የ6፥19 ማብ ይመ።

21፥29 *በአጕል ድፍረት ይቀርባል፤* አለመታዘዙን በገጽታው ይገልጻል ማለት ነው። በ7፥13 ላይ የተመለከተውን የዝሙት ዐጻሪዋን ጠባይ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

21፥30 *እግዚአብሔርን ለመቋቋም የሚያስችል፣ ... ዕቅድ የለም፤* እርሱ ሕዝቦችንና መንግሥታትን የሚቈጣጠር የበላይ ገዥ በመሆኑ ነው (16፥4፡9 እና ማብ፤ 19፥21፤ 21፥1፤ 1ቆሮ 3፥19-20 ይመ)።

21፥31 *ፈረስ፤* ድል ለመንሣት በፈረስና በሠረገላ ብዛት መተማመን ትክክል እንዳልሆነ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ አስጠንቅቆአል (ለምሳሌ መዝ20፥7፤ ሆሴ1፥7 ይመ፤ ከዘዳ17፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። *ድል ... ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤* 1ሳሙ17፥47፤ መዝ3፥8 ይመ።

22፥1 *መልካም ስም፤* አርአያነት ያለውን ጠባይና የሚያስገኘውን አስደናቂ ዝና ያመለክታል። በ3፥4፤ 10፥7፤ መክ 7፥1 ላይ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ያስገነዝባል። *ከብርና ከወርቅ ይበልጣል፤* ጥበብን የራስ ሀብት እንደ ማድረግ ነው (3፥14፤ 16፥16 ይመ)።

22፥2 *የሁላቸውም ፈጣሪ፤* 14፥31 እና ማብ ይመ።

22፥3 *አስተዋይ ሰው ... መጠጊያ ይሻል፤* ከ14፥8 ጋር ያነጻጽሩ። *ብስለት የጐደለው፤* የ1፥4 ማብ፤ እንዲሁም 9፥16 ይመ።

*22፥4፤* 18፥22 ይመ። *ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት፤* በ15፥33 ላይም ሁለቱ ተዛምደው ይገኛሉ (የ1፥7 ማብ ይመ)። *ሀብትን፣ ክብርንና ሕይወትን፤* ጥበብን የሚሹ ሰዎች የሚያገኙት በረከት ነው (የ3፥2 ማብ፤ እንዲሁም 3፥16፤ 8፥18 ይመ፤ ከ21፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

22፥5 *እሾህና ወጥመድ፤* ክፉ ነገርን ያመለክታሉ (ከ15፥19 ጋር ያነጻጽሩ)። *ከእነዚህ ይርቃል፤* "በቅኖች ጐዳና" (16፥17) በመጓዝ ነው።

22፥6 *አስተምረው፤* በ1ነገ8፥63 ላይ እንደ ተመለከተው "ለየው" ወይም "ቀድሰው" ማለት ሊሆን ይችላል፤ ከዘፍ 18፥19 ጋር ያነጻጽሩ። ምክርና (1፥8) ቅጣት (22፥15) ልጅን ለማሳደግ መሠረታዊ እርምጃዎች ናቸው። *የሚሄድበትን መንገድ፤* ትክክለኛ በሆነው በጥበብ መንገድ ማለት ነው (4፥11 ማብ ይመ)።

በሚሸመግልበት ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ
አይልም።
7ባለጠጋ ድኻን ይገዛል፤
ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው።

8ክፋትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፤
የቍጣውም በትር ይጠፋል።
9ቸር ሰው ራሱ ይባረካል፤
ምግቡን ከድኾች ጋር ይካፈላልና።

10ፌዘኛን አስወጣው፤ ጠብ ይወገዳል፤
ጥልና ስድብም ያከትማል።

11የልብ ንጽሕናን ለሚወድና ንግግሩም
ሞገስ ላለው ሰው፣
ንጉሥ ወዳጁ ይሆናል።

12*የእግዚአብሔር* ዐይኖች ዕውቀትን
ይጠብቃሉ፤
የማይታመኑትን ሰዎች ቃል ግን እርሱ
ከንቱ ያደርጋል።
13ሰነፍ፣ "አንበሳ ውጪ አለ፤
መንገድ ላይ እገደላለሁ" ይላል።

14የአመንዝራ ሴት አፍ ጥልቅ ጕድጓድ
ነው፤
*እግዚአብሔር* የተቈጣውም ይገባበታል።

15ሞኝነት በሕፃን ልብ ታስሮአል፤
የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቅለታል።

16ሀብቱን ለማካበት ድኻን የሚበድል፣
ለባለጠጋም ስጦታ የሚያቀርብ፣ ሁለቱም
ይደኸያሉ።

## የጠቢባን ምክር

17የጠቢባንን ቃል ልብ ብለህ ስማ፤
ልብህም ወደ ትምህርቴ ያዘንብል፤
18በልብህ ስትጠብቃቸው፣
ሁሉም በከንፈሮችህ ላይ የተዘጋጁ
ሲሆኑ ደስ ይላልና።
19ስለዚህ እምነትህ *በእግዚአብሔር* ላይ
እንዲሆን፣
ዛሬ አንተን ራስህን አስተምርሃለሁ።
20የምክርና የዕውቀት ቃል የሆኑ፣
መልካም ትምህርቶችን* አልጻፍሁልህምን?
21ለላከህ ተገቢውን መልስ ትሰጥ ዘንድ፣
እውነተኛውና የታመኑ ቃሎችን
እንዳስተምርህ አይደለምን?
22ድኾች በመሆናቸው ብቻ ድኾችን
አትበዝብዛቸው፤
ችግረኛውንም በአደባባይ አታንገላታው፤
23*እግዚአብሔር* ይፋረድላቸዋልና፤
የሚቀሟቸውንም ይቀማቸዋል።

24ከግልፍተኛ ጋር ወዳጅ አትሁን፤
በቀላሉ ቱግ ከሚልም ሰው ጋር
አትወዳጅ፤
25አለበለዚያ መንገዱን ትማራለህ፤
ራስህም ትጠመድበታለህ።

26በዋስትና ቃል እጅ አትምታ፤
ለብድር ተያዥ አትሁን፤
27የምትከፍለው ካጣህ፣
የምትተኛበት ዐልጋ ከሥርህ
ይወሰድብሃል።
28የቀድሞ አባቶችህ ያስቀመጡትን፣
የጥንቱን የወሰን ምልክት አታፋልስ።
29በሙያው ሥልጡን የሆነውን ሰው

*20 *ወይም አስቀድሜ አልጻፍሁልህምን?፣ ወይም ሠላሳ ትምህርቶችን*

22፥8 ዘፀ1፥20፤ኢዮ 4፥8፤ሆሴ8፥7፤ገላ6፥7-8
22፥9 ዘዳ14፥29፤ ምሳ11፥25፤19፥17፤28፥27
22፥10 ምሳ26፥20
22፥11 ምሳ16፥13፤ ማቴ5፥8
22፥13 ምሳ26፥13
22፥14 ምሳ5፥3-5፤ 23፥27፤መክ7፥26
22፥15 ምሳ13፥24፤ 20፥30
22፥17 ምሳ1፥6፡8፤ ምሳ2፥2፡30፥1፤31፥1
22፥21 መክ12፥10
22፥22 ዘፀ23፥6፤ ዘሌ25፥17፤ኢዮ5፥16
22፥23 አስ8፥1፤9፥1 ፤ኢዮ29፥16፤መዝ 140፥12፤ምሳ 23፥10-11
22፥25 1ቆሮ15፥33
22፥26 ምሳ6፥1-5
22፥27 ምሳ11፥15፤ 17፥18
22፥28 ዘዳ19፥14
22፥29 ዘፍ39፥4፤ 41፥46፤1ነገ11፥28

*በሚሸመግልበት፤* "ባደገ ጊዜ" እንደ ማለት።

22፥7 *ባለጠጋ፤* የ10፥15 ማብ ይመ። *ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው፤* ለሌላ ሰው ዋስ መሆን (ቍ26) የተጠላበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው (ከነህ5፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

22፥8 *ክፋትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል፤* 12፥21 ይመ። *የቍጣውም በትር፤* ሌሎችን ለመጨቆን ያለውን ችሎታ ያመለክታል (መዝ125፥3፤ ኢሳ14፥5-6 ይመ)።

22፥9 *ቸር ሰው ... ይባረካል፤* የ11፥25 ማብ ይመ። *ምግቡን ... ይካፈላልና፤* የ14፥21 ማብ፤ እንዲሁም ዘዳ 15፥8-11 ይመ።

22፥10 *ፌዘኛን አስወጣው፤* የ1፥22 ማብ ይመ፤ ከዘፍ 21፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ። *ጠብ ይወገዳል፤ ... ስድብም፤* ከ17፥14፤ 18፥3፤ 20፥3 ጋር ያነጻጽሩ።

22፥11 *የልብ ንጽሕናን፤* ከመዝ24፥4 ጋር ያነጻጽሩ። *ንግግሩም ሞገስ ላለው ሰው፤* በመክ10፥12 ላይ የተጠቀሰውን የጥበበኛን ሰው ባሕርይ ያመለክታል። *ንጉሥ ወዳጁ ይሆናል፤* ከቍ 29 ጋር ያነጻጽሩ።

22፥12 *የእግዚአብሔር ዐይኖች ... ይጠብቃሉ፤* 5፥21፤ 15፥3፤ ኢዮ31፥4፤ 34፥21፤ ኤር16፥17፤ ዕብ4፥13 ይመ። *ዕውቀትን ...፤* እግዚአብሔር እርሱንና መንገዱን የሚያውቁትን ሰዎች ይጠብቃቸዋል (ከመዝ1፥6፤ 34፥15 ጋር ያነጻጽሩ። *የማይታመኑትን ... ከንቱ ያደርጋል፤* ዕቅዳቸውና ምኞታቸው እንዳይፈጸም ያደርጋል (16፥9 እንዲሁም የ21፥30 ማብ ይመ)።

*22፥13፤* ሰነፍ (6፥6 ማብ ይመ) ሥራ ላለመሥራት ምክንያት ይፈጥራል።

22፥14 *የአመንዝራ ሴት አፍ፤* አታላይ አንደበት ማለት ነው (የ5፥3፤ ማብ እንዲሁም 2፥16፤ 7፥5 ይመ)። *ጥልቅ ጕድጓድ፤* የውሃ ጕድጓድ ወይም አዳኝ ለማጥመጃ የቈፈረው ሊሆን ይችላል፤ (5፥22 እና ማብ እንዲሁም 7፥22 ይመ)።

22፥15 *የተግሣጽ በትር፤* የ13፥24 ማብ ይመ።

22፥16 *ድኻን የሚበድል፤* በ14፥31 እና በ28፥3 ላይም የተወገዘ ነው። *ለባለጠጋም ስጦታ የሚያቀርብ፤* እጅ መንሻ ሊሆን ይችላል (17፥8፤ 18፥16፤ 19፥6 ይመ)። *ይደኸያሉ፤* 21፥5፤ 28፥22 ይመ።

*22፥17-24፤* የዚህ ክፍል ትምህርት አቀራረብ ከሞላ ጐደል ከም1-9 ያለውን ይመስላል። በቍ 17-21 ያለው፣ ከቍ22 ጀምሮ ላሉት ሠላሳ ትምህርቶች መግቢያ ነው 22፥17። *ልብ ብለህ ስማ፤* 4፥20፤ 5፥1 ይመ። *የጠቢባንን ቃል፤* በ10፥1 ላይ "የሰሎሞን ምሳሌዎች" እንደሚለው ሁሉ ይህም ርእስ ነው።

22፥18 *ደስ ይላልና፤* 2፥10፤ 16፥24 ይመ።

22፥19 *እምነትህ በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን፤* የ3፥5 ማብ ይመ።

22፥21 *ተገቢውን መልስ ትሰጥ ዘንድ፤* 1ጴጥ3፥15 ይመ። *ለላከህ፤* ምናልባት ወላጅ ወይም አሳዳጊ ሊሆን ይችላል።

22፥22 *ድኾችን አትበዝብዛቸው፤* ቍ16፤ 14፥31 ይመ። *ችግረኛውንም በአደባባይ አታንገላታው፤* ኢሳ1፥17 ይመ።

22፥23 *እግዚአብሔር ይፋረድላቸዋልና፤* 23፥11፤ መዝ 12፥5፤ 140፥12፤ ኢሳ3፥13-15፤ ሚል3፥5 ይመ። *የሚቀሟቸውንም ይቀማቸዋል፤* ዘፀ22፥22-24 ይመ።

22፥24 *ወዳጅ አትሁን፤* ከ12፥26 ጋር ያነጻጽሩ። *ከግልፍተኛ፤* የዚህ ዐይነቱ ሰው ባሕርይ ምን እንደሚመስል በ14፥16-17፤ 15፥18፤ 29፥22 ላይ ተመልክቶአል።

22፥25 *መንገዱን ትማራለህ፤* "ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል" (1ቆሮ15፥33)። *ትጠመድበታለህ፤* የ5፥22 ማብ፤ እንዲሁም 12፥13፤ 13፥14፤ 29፥6 ይመ።

*22፥26፤* የ6፥1 ማብ ይመ።

22፥27 *የምትተኛበት ዐልጋ ... ይወሰድብሃል፤* ያለህን ሁሉ እስከታጣ ድረስ ድኽነት ውስጥ ትገባለህ።

22፥28 *የጥንቱን የወሰን ምልክት፤* የ15፥25 ማብ እንዲሁም 23፥10 ይመ።

22፥29 *በሙያው ሥልጡን የሆነውን፤* የእጅ ሙያ ያላቸው ሰዎች በሌላውም ነገር ጠቢባን እንደ ሆኑ ይቈጠሩ ነበር

አይተሃልን?
በነገሥታት ዘንድ ባለሟል ይሆናል፤
አልባሌ ሰዎችን አያገለግልም።

# 23

ከገዥ ጋር ለመብላት
በምትቀመጥበት ጊዜ፣
በፊትህ ያለውን በሚገባ[°] አስተውል፤
2ስግብግብም ብትሆን እንኳ፣
በጒሮሮህ ላይ ካራ አጋድምበት፤
3የእርሱ ጣፋጭ መብል አያስጐምጅህ፤
ምግቡ አታላይ ነውና።

4ሀብት ለማግኘት ስትል ራስህን አታድክም፤
ሐሳብህን የመግታት ጥበብ ይኑርህ።
5በሀብት ላይ ዐይንህን ብትጥል፤
ወዲያው ይጠፋል፤
ወደ ሰማይ እንደሚበርር ንስር፣
በእርግጥ ክንፍ አውጥቶ ይበራል፤

6የስስታምን ምግብ አትብላ፤
ጣፋጭ መብሉም አያስጐምጅህ፤
7ሁልጊዜ ስለ ዋጋ የሚያስብ ሰው ነውና፤[+]
"ብላ፣ ጠጣ" ይልሃል፤
ልቡ ግን ከአንተ ጋር አይደለም።
8የበላሃት ትንሿ እንኳ ታስመልስሃለች፤
የምስጋና ቃልህንም ከንቱ ታደርጋለህ።

9ከጅል ጋር አትነጋገር፤
የቃልህን ጥበብ ያንኳስሳልና።

10የጥንቱን የወሰን ምልክት አታፋልስ፤
አባት የሌላቸውንም ልጆች መሬት
አትግፋ፤
11ታዳጊያቸው ብርቱ ነውና፤
እርሱ ይፋረድላቸዋል።

12ልብህን ለምክር፣
ጆሮህንም ለዕውቀት ቃል ስጥ።
13ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል፤
በአርጩሜ ብትገርፈው አይሞትም።
14በአርጩሜ ቅጣው፤
ነፍሱንም ከሞት[*] አድናት።

15ልጄ ሆይ፤ ልብህ ጠቢብ ቢሆን፣
የእኔም ልብ ሐሤት ያደርጋል፤
16ከንፈሮችህ ትክክሉን ቢናገሩ፣
ውስጣዊ ሁለንተናዬ ሐሤት ያደርጋል።

17ልብህ በኀጢአተኞች አይቅና፤
ነገር ግን ዘወትር እግዚአብሔርን
ለመፍራት ትጋ።
18ለነገ እርግጠኛ አለኝታ ይኖርሃል፤
ተስፋህም ከንቱ አይሆንም።

19ልጄ ሆይ አድምጥ፤ ጠቢብም ሁን፤
ልብህም ከትክክለኛው መንገድ
አይውጣ።
20ብዙ የወይን ጠጅ ከሚጠጡ፣
ሥጋ ከሚሰለቅጡ ጋር አትወዳጅ፤
21ሰካራሞችና ሆዳሞች ድኾች ይሆናሉና፤
እንቅልፋምነትም ቡትቶ ያለብሳቸዋል።

22የወለደህን አባትህን አድምጥ፤
እናትህንም ባረጀች ጊዜ አትናቃት።
23እውነትን ግዛት እንጂ አትሸጣት፤
ጥበብን፣ ተግሣጽንና ማስተዋልን ገንዘብህ
አድርግ።
24የጻድቅ ሰው አባት እጅግ ደስ ይለዋል፤

°1 ወይም ማን መሆኑን
+7 ወይም በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና ወይም ግብዣ አዘጋጅቶ
*14 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል

23፥1 ቍ6-8፤መዝ 141፥4
23፥5 ምሳ27፥24፤ ማቴ6፥19
23፥6 ቍ1-3፤ መዝ141፥4
23፥9 ምሳ9፥7
23፥10 ዘዳ19፥14
23፥12 ምሳ2፥2
23፥11 ዘፀ22፥22-24፤ኢዮ19፥25፤መዝ 24፥8፤ምሳ15፥25፤22፥22-23
23፥14 ምሳ13፥24፤19፥18
23፥16 ቍ24፤ምሳ 27፥11፤29፥3
23፥17 መዝ37፥1፤ 73፥3
23፥18 መዝ9፥18፤ 37፥1-4፤ምሳ24፥14፡ 19-20
23፥19 ዘዳ4፥9፤ምሳ 28፥7
23፥20 ኢሳ5፥11፡ 22፤56፥12፤ዕን2፥15
23፥21 ምሳ21፥17
23፥22 ዘሌ19፥32
23፥23 ምሳ4፥7፤ 17፥16
23፥24 ቍ15-16

(የ8፥30 ማብ፤ እንዲሁም ዘፀ 35፥30-35 ይመ)። *በነገሥታት ዘንድ ባለሟል ይሆናል፤* እንደ ዮሴፍ፣ ሹም (ዘፍ41፥46)፣ እንደ ዳዊት ዘማሪ (1ሳሙ 16፥21-23)፣ እንደ ኪራም ናስ ሠራተኛ (1ነገ7፥14) ይሆናል ማለት ነው።

*23፥1-3፤* በተለየ ዐላማ ሊጋበዝ ስለሚችል፣ ማንም ሰው ገዥ ፊት ሲቀርብ መጠንቀቅ ይኖርበታል። *በጒሮሮህ ላይ ካራ አጋድምበት፤* እንደ ምንም ብለህ ራብህን ቻለው፤ የተደረገልህ አቀባበል ተንኰል ሊኖርበት ይችላልና።

23፥2 *ስግብግብም፤* በቍ 20-21 ላይ ከተሰጠው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ጋር ያነጻጽሩ።

23፥3 *የእርሱ ጣፋጭ መብል አያስጐምጅህ፤* በቍ6 ላይ በተለየ አገባብ ተደግሞአል። *አታላይ፤* ገዥ፣ ክፉ ለሆነ ዕቅዱ ድጋፍ እስኪሰጠው ድረስ ግዴታ ውስጥ ለማስገባት አስቦ ሊሆን ይችላል (ከመዝ141፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

23፥4 *ሀብት ለማግኘት ስትል ራስህን አታድክም፤* ሀብታም ለመሆን መጓጓት፣ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ጒዳት ሊያመጣ ይችላል "ገንዘብን መውደድ የክፉት ሁሉ ምንጭ ነውና" (1ጢሞ 6፥10 ይመ፤ ከ15፥27፤ 28፥20፤ ከዕብ 13፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

23፥5 *በሀብት ... ይጠፋል፤* መታመኛችን እግዚአብሔር እንጂ ሀብት የለበትም (ኤር17፥11፤ ሉቃ 12፥21፤ 1ጢሞ 6፥17 ይመ)።

23፥6 *የስስታምን፤* ሀብታም ለመሆን የሚጓጓ ሰው ማለት ነው (28፥22 ይመ)።

23፥7 *ልቡ ግን ከአንተ ጋር አይደለም፤* ከ26፥24-25 ጋር ያነጻጽሩ።

23፥8 *ታስመልስሃለች፤* የአስተናጋጁ ሁኔታ ስሜትን የሚያውክ በመሆኑ ነው።

23፥9 *የቃልህን ጥበብ ያንኳስሳልና፤* ጅሎች ጥበብን ይንቃሉ (1፥7)፤ ዕውቀትንና እርምትን ይጠላሉ (1፥22፤ 12፥1)፤ የሚገሥጻቸውንም ሰው ክፉኛ ይሳደባሉ (9፥7)።

23፥10 *የጥንቱን የወሰን ምልክት፤* የ16፥25 ማብ፤ እንዲሁም 22፥28 ይመ። *አባት የሌላቸውንም ልጆች፤* ባል የሞተባትን ሴትና አባት የሌላቸውን ልጆች ማስጨነቅ በጥብቅ ተወግዞአል (ኢሳ10፥2፤ ኤር22፥3፤ ዘካ7፥10 ይመ)።

23፥11 *ታዳጊያቸው፤* መሬቱ የተወሰደበትን ሰው ይዞታው እንዲመለስለት የሚረዳ የቅርብ ዘመድን (ዘሌ25፥25 እና ማብ ይመ)፣ ወይም ደሙን የሚበቀልለትን ሰው ያመለክታል (ዘኍ 35፥12፡19)። እግዚአብሔር "አባት ለሌላቸው አባት፣ ባሎቻቸው ለሞቱባቸውም ጠበቃ" ነው (መዝ 68፥5)። የሩት 2፥20፤ የኤር 31፥11 ማብ፤ እንዲሁም ኤር 50፥34 ይመ። *ይፋረድላቸዋል፤* መዝ12፥5፤ 140፥12፤ ኢሳ3፥13-15፤ ሚል3፥5 ይመ።

23፥13-14፤ የ13፥24 ማብ ይመ።

23፥15፤ 10፥1 እና ማብ፤ እንዲሁም ቍ24፤ 27፥11፤ 29፥3 ይመ። *ልጄ ሆይ፤* 1፥8፡10 ይመ።

23፥17 *በኀጢአተኞች አይቅና፤* 3፥31፤ 24፥1፡19 ይመ። *እግዚአብሔርን ለመፍራት፤* የ1፥7፤ የ3፥7 ማብ ይመ።

23፥18 *ለነገ ... አለኝታ፤* መዝ37፥37፤ ኤር29፥11 ይመ።

23፥19 *ከትክክለኛው መንገድ፤* ከ4፥25-26 ጋር ያነጻጽሩ።

23፥20 *አትወዳጅ፤* 1፥15፤ 12፥26 ይመ። *ብዙ የወይን ጠጅ ከሚጠጡ፤* ስካር በቍ 29-35፤ በ20፥1 ላይም (የእነዚህን ማብ ይመ)። ከዘዳ21፥20፤ ከማቴ24፥49፤ ከሉቃ21፥34፤ ከሮሜ13፥13፤ ከኤፌ5፥18፤ ከ1ጢሞ3፥3 ጋር ያነጻጽሩ።

23፥21 *ሆዳሞች፤* ቍ2፤ 28፥7 ይመ። ከማቴ11፥19 ጋር ያነጻጽሩ። *ድኾች ይሆናሉና፤* 21፥17 ይመ። *እንቅልፋምነትም፤* በ6፥9 ላይ ታካች ሰው የሚደርስበትን ድኽነት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

23፥22 *እናትህንም ... አትናቃት፤* ከ15፥20፤ 30፥17 ጋር ያነጻጽሩ።

23፥23 *እውነትን ግዛት ... ጥበብን፣ ... ማስተዋልን ገንዘብህ አድርግ፤* 4፥5፤ እንዲሁም 4፥7 እና ማብ ይመ።

*23፥24-25፤* ቍ 27፥11፤ እንዲሁም 10፥1 እና ማብ

ጠቢብ ልጅ ያለውም በእርሱ ሐሤት
ያደርጋል።
25አባት እናትህ ደስ ይበላቸው፤
ወላጅ እናትህም ሐሤት ታድርግ።
26ልጄ ሆይ፤ ልብህን ስጠኝ፤
ዐይኖችህም ከመንገዴ አይውጡ፤
27ዘልዛላ ሚስት ጠባብ ጕድጓድ፣
አመንዝራም ሴት ዐዘቅት ናትና፤
28እንደ ወንበዴ ታደባለች፤
በሰዎችም መካከል ወስላቶችን ታበዛለች።
29ዋይታ የማን ነው? ሐዘንስ የማን ነው?
ጠብ የማን ነው? ብሶትስ የማን ነው?
በከንቱ መቍሰል የማን ነው? የዐይን
ቅላትስ የማን ነው?
30የወይን ጠጅ በመጠጣት ጊዜያቸውን
ለሚያባክኑ ነው፤
እየዞሩ ድብልቅ የወይን ጠጅ
ለሚቀማምሱ ሰዎች ነው።
31መልኩ ቀይ ሆኖ፣
በብርጭቆ ውስጥ ሲያንጸባርቅ፣
ስተት ብሎ በሚወርድበትም ጊዜ፣
ወደ ወይን ጠጅ ትክ ብለህ
አትመልከት።
32በመጨረሻው እንደ እባብ ይነድፋል፤
እንደ እፉኝትም መርዙን ይረጫል።
33ዐይኖችህ እንግዳ ነገር ያያሉ፤
አእምሮህም ይቀባዥራል።
34በባሕር ላይ የተኛህ፣
በመርከብ ምሰሶ ጫፍ ላይ የተጋደምህ
ትመስላለህ።
35አንተም፣ "መቱኝ፤ አልተጐዳሁም፤
ደበደቡኝ፤ አልተሰማኝም፤
ታዲያ፣ ሌላ መጠጥ እንዳገኝ፣
መቼ ነው የምነቃው?" ትላለህ።

24 በክፉ ሰዎች አትቅና፤
ጓደኝነታቸውም አይመርህ፤
2ልባቸው ዐመፅን ያውጠነጥናልና፤
ከንፈራቸውም ሸፍጥ ያወራል።
3ቤት በጥበብ ይሠራል፤
በማስተዋልም ይጸናል፤
4በዕውቀትም ውድና ውብ በሆነ ንብረት፣
ክፍሎቹ ይሞላሉ።
5ጠቢብ ሰው ታላቅ ኀይል አለው፤
ዕውቀት ያለውም ሰው ብርታትን
ይጨምራል፤
6ጦርነት ለመግጠም መልካም ምክር፣
ድል ለማድረግም ብዙ አማካሪዎች
ያስፈልጋሉ።
7ጥበብ ለተላላ በጣም ሩቅ ናት፤
በከተማዪቱ በር ሸንጎ ላይም መናገር
አይችልም።
8ክፋት የሚያውጠነጥን፣
'ተንኰለኛ' በመባል ይታወቃል።
9የተላላ ዕቅድ ኀጢአት ነው፤
ሰዎችም ፌዘኛን ይጸየፋሉ።
10በመከራ ጊዜ ፈራ ተባ ካልህ፣
ዐቅምህ ምንኛ ደካማ ነው!
11ወደ ሞት የሚነዱትን ታደጋቸው፤
እየተጐተቱ ለእርድ የሚሄዱትን
አድናቸው።
12አንተም፣ "ስለዚህ ነገር ምንም
አላውቅም" ብትል፣
ልብን የሚመረምር እርሱ
አያስተውልምን?
ሕይወትህን የሚጠብቃት እርሱ
አያውቅምን?
ለእያንዳንዱስ እንደ ሥራው መጠን
አይከፍለውምን?

23፥25 ምሳ10፥1
23፥26 መዝ18፥21 ፤ምሳ5፥1-6
23፥27 ምሳ22፥14
23፥28 ምሳ7፥11-12
23፥30 ቍ20-21፤ ኢሳ5፥11
23፥35 ምሳ20፥1
24፥1 ምሳ3፥31-32 ፤23፥17-18
24፥2 መዝ2፥1፤10፥7፤ኢሳ32፥6፤55፥7-8 ፤59፥7፤65፥2፤66፥18፤ ሆሴ4፥1
24፥3 ምሳ14፥1
24፥4 ምሳ8፥21
24፥6 ምሳ11፥14፤ 20፥18፤ሉቃ14፥31
24፥10 ኢዮ4፥5
24፥11 መዝ82፥4
24፥12 1ሳሙ2፥3፤ ኢዮ34፥11፤መዝ54፥5 ፤62፥12፤139፥2፤ማቴ 16፥27፤ሮሜ2፥6

ይመ።

23፥27 *ዐዘቅት፤* የ22፥14 ማብ ይመ። *ዘልዛላ ሚስት፤* የ2፥16 ማብ፤ እንዲሁም5፥20፤ 7፥17-23 ይመ።

23፥28 *ታደባለች፤* 6፥26፤ 7፥12፤ መክ7፥26 ይመ። *ወስላቶችን ታበዛለች፤* ከ7፥26 ጋር ያነጻጽሩ።

23፥29-35፤ ስካር በአካል ላይ የሚያደርሰውን ጕዳትና በልቦና ላይ የሚያስከትለውን ቀውስ በግልጽ የሚያመለክት ነው።

23፥29 *ዋይታ የማን ነው?* ስለ ሰካራሞች በኢሳ5፥11፡22 ላይ የተነገረውን ዋይታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። *ጠብ፤* 20፥1 ይመ። *መቍሰል፤* በ19፥29 ላይ ለተላሉች ጀርባ ጅራፍ ተዘጋጅ ቶአል» የሚለውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

23፥30 *የወይን ጠጅ በመጠጣት ጊዜያቸውን ለሚያባክኑ፤* 1ሳሙ25፥36 ይመ። *ድብልቅ የወይን ጠጅ፤* ኀይል እንዲኖረው ቅመማ ቅመም የተጨመረበት ሊሆን ይችላል (9፥2፤ መዝ 75፥8 ይመ)።

23፥32 *እንደ እባብ ይነድፋል፤* የመጨረሻ ውጤቱ ሞት ይሆናል (ከዘኍ 21፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

23፥33 *እንግዳ ነገር ያያሉ … ይቀባዥራል፤* የሰከረ ሰው የሚደርስበትን የአእምሮ መቃወስ ያመለክታል።

23፥34 *በባሕር ላይ የተኛህ … ትመስላለህ፤* ናላህ የዞረብህ ትሆናለህ ማለት ነው።

23፥35 *መቱኝ፤ አልተጐዳሁም፤* በኤር5፥3 ላይ የተገለጠውን የእስራኤልን ሁኔታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ። *ታዲያ፣ ሌላ መጠጥ እንዳገኝ፤* የደረሰበት ዋይታና ችግር ስሕተቱን ከመድገም አላዳነውም (ከ26፥11፤ 27፥22፤ ኢሳ56፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

24፥1 *አትቅና፤* ቍ19፤ መዝ37፥1 ይመ። *ጓደኝነታቸውም አይመርህ፤* 1፥15፤ 12፥26፤ 23፥20 ይመ።

24፥2 *ዐመፅን ያውጠነጥናልና፤* 1፥10-11፤ 6፥14፤ ኢዮ 15፥35፤ መዝ38፥12 ይመ።

24፥3 *ቤት፤* የአንድን ግለሰብ ወይም ቤተ ሰብ ሕይወት ለማመልከት የገባ ቃል ነው። *ይሠራል፤* በ9፥1 ላይ ከሚገኘው ተመሳሳይ አገላለጽ ጋር ያነጻጽሩ።

24፥4 *ውድና ውብ በሆነ ንብረት፤* ጥበብ፣ ለሚናፍቋትና ለሚወዷት ባለጠግነትን እንደምታጐናጽፍ ተስፋ ትሰጣለች (8፥21)።

24፥5 *ታላቅ ኀይል አለው፤* የ21፥22 ማብ ይመ።

24፥7 *በር፤* የከተማዋ ዐዋቂዎችና አዛውንት ለተለያዩ ማኅበራዊ ጕዳዮች የሚሰበሰቡበት ቦታ (የሩት 4፥1) ማብ እንዲሁም ሩት 4፥11 ይመ) በተጨማሪም የታወቀ ሥራ ይካሄድበት ነበር (የ1፥21 ማብ ይመ)።

24፥8 *ክፋት የሚያውጠነጥን፤* ቍ2፤ እንዲሁም 1፥10-11፤ 6፥14፤ ኢዮ 15፥35፤ መዝ 38፥12 ይመ። *ተንኰለኛ፤* 12፥2፤ 14፥17 ይመ።

24፥9 *የተላላ ዕቅድ ኀጢአት ነው፤* ከ1፥11-16፤ 9፥13-18 ጋር ያነጻጽሩ። *ሰዎችም ፌዘኛን ይጸየፋሉ፤* ትዕቢተኛ፣ ተሳዳቢ (9፥7) ጠበኛም (22፥10) በመሆኑ ነው፤ የ1፥22 ማብ ይመ።

*24፥10፤* ከኤር12፥5፤ ከገላ6፥9 ጋር ያነጻጽሩ።

24፥11 *ወደ ሞት የሚነዱትን፤* በደለኛ ሳይሆኑ የሞት ፍርድ የተበየነባቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ (ከ17፥15፤ ከኢሳ 58፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

24፥12 *ልብን የሚመረምር እርሱ አያስተውልምን?* እግዚአብሔር ሐሳባችንንና ዓላማችንን እንኳ ሳይቀር ያውቃል (16፥2፤ 21፥2፤ መዝ 94፥9-11 ይመ)።

13 ልጄ ሆይ፤ መልካም ነውና ማር ብላ፤
የማር ወለላም ባዕም ይጣፍጥሃል።
14 ጥበብም ለነፍስህ እንደዚሁ ጣፋጭ
እንደ ሆነች ዕወቅ፤
ብታገኛት ለነገ አለኝታ ይኖርሃል፤
ተስፋህም ከንቱ አይሆንም።

15 በጻድቅ ሰው ቤት ላይ እንደ ወንበዴ
አታድፍጥ፤
መኖሪያውንም በድንገት አታጥቃ፤
16 ጻድቅ ሰባት ጊዜ እንኳ ቢወድቅ
ይነሣልና፤
ክፉዎች ግን በጥፋት ይወድቃሉ።

17 ጠላትህ ሲወድቅ ደስ አይበልህ፤
ሲሰናከልም ልብህ ሐሤት አያድርግ፤
18 አለዚያ እግዚአብሔር ይህን አይቶ
ደስ አይለውም፤
ቍጣውንም ከእርሱ ይመልሳል።

19 በጨካኞች ድርጊት አትጨነቅ፤
በክፉዎችም አትቅና፤
20 ግፈኛ ተስፋ የለውምና፤
የክፉዎችም መብራት ድርግም ብላ
ትጠፋለች።

21 ልጄ ሆይ፤ እግዚአብሔርንና ንጉሥን
ፍራ፤
ከዐመፀኞችም ጋር አትተባበር፤
22 ሁለቱም የሚያመጡት መዓት፤
ምን እንደሚሆን ማን ያውቃል?

## ተጨማሪ የጠቢባን ምሳሌዎች

23 እነዚህም ደግሞ የጠቢባን ምሳሌዎች ናቸው:-

በዳኝነት አድልዎ ማድረግ ተገቢ
አይደለም፤
24 በደለኛውን፣ "አንተ ንጹሕ ነህ"
የሚለውን፣
ሕዝቦች ይረግሙታል፤ መንግሥታትም
ያወግዙታል።
25 በደለኛውን፣ "አንተ ጥፋተኛ ነህ"
የሚሉት ግን መልካም ነገር ይገጥማቸዋል፤
የተትረፈረፈ በረከትም ይወርድላቸዋል።
26 እውነተኛ መልስ መስጠት፣
ከንፈርን እንደ መሳም ነው።

27 በደጅ ያለውን ሥራህን ፈጽም፤
ዕርሻህን አዘጋጅ፤
ከዚያም በኋላ ቤትህን ሥራ።
28 በባልንጀራህ ላይ ያለ ምክንያት
አትመስክር፤
በከንፈርህም አትሸንግል።
29 "በእኔ ላይ እንደሠራብኝ እሠራለታለሁ፤
ስለ አድራጎቱም የጁን እመልስለታለሁ"
አትበል።

30 በሰነፍ ሰው ዕርሻ በኩል አለፍሁ፤
ማስተዋል የጐደለውን ሰው የወይን ቦታ
አልፌ ሄድሁ፤
31 በያለበት እሾህ በቅሎበታል፤
መሬቱም ዐረም ለብሶአል፤
ቅጥሩም ፈራርሷል።
32 ያየሁትን ነገር አወጣሁ አወረድሁ፤
ካስተዋልሁትም ትምህርት አገኘሁ፤
33 "ጥቂት ላንቀላፋ፣ ጥቂት ላሸልብ፣
እጄን አጣጥፌ ጥቂት ልረፍ" ብትል፣
34 ድኽነት እንደ ወንበዴ፣
እጦትም እንደ ታጠቀ ሰው
ይመጣብሃል።[ጎ]

## የሰሎሞን ተጨማሪ ምሳሌዎች

25 እነዚህ የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ
ሰዎች የቀዷቸው ሌሎች የሰሎሞን

24፥14 መዝ119፥103፤ ምሳ16፥24፤ 23፥18
24፥16 ኢዮ5፥19፤ መዝ 34፥21
24፥17 2ሳሙ3፥32፤አብ1፥12፤ሚክ7፥8
24፥18 ኢዮ31፥29
24፥19 መዝ37፥1
24፥20 ኢዮ18፥5፤ ምሳ23፥17-18
24፥21 ሮሜ13፥1-5
24፥22 መዝ73፥19
24፥23 ዘፀ18፥16፤ ዘሌ19፥15፤መዝ72፥2፤ምሳ1፥6፤28፥21፤31፥8-9፤ኤር22፥16
24፥24 ምሳ17፥15
24፥28 መዝ7፥4
24፥29 ምሳ20፥22፤ ማቴ5፥38-41
24፥30 ምሳ6፥6-11፤26፥13-16
24፥33 ምሳ6፥10
24፥34 ምሳ10፥4፤ መክ10፥18
25፥1 1ነገ4፥32፤ ምሳ1፥1

[ጎ]34 ወይም *እንደ በዘኔ/ እጦትም እንደ ለማኝ*

24፥14 *ጥበብም ለነፍስህ ... ጣፋጭ እንደ ሆነች*፤ ጥበብ ታለመልማለች፤ ፈውስንም ታስገኛለች (16፥24 እና ማብ ይመ)። *ለነገ አለኝታ፤* መዝ9፥18፤ 37፥37፤ ኤር29፥11 ይመ።

24፥15 *አታድፍጥ፤* ከ1፥11፤ 12፥6፤ ከመዝ10፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ።

24፥16 *ሰባት ጊዜ፤* ብዙ ጊዜ ለማለት ነው (6፥16፤ ኢዮ 5፥19 እና ማብ ይመ)። *ይነሣልና፤* እግዚአብሔር፣ ጻድቁን እንደ ሚደግፍና እንደሚታደግ ቃል ገብቶአል (ከመዝ34፥19፤ 37፥24፤ ከሚክ7፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። *ክፉዎች ... ይወድቃሉ፤* 22፤ 4፥19፤ 6፥15፤ 11፥3፡5 ይመ።

24፥17 *ደስ አይበልህ፤* የ17፥5 ማብ ይመ።

24፥18 *ቍጣውንም ከእርሱ ይመልሳል*፤ ኤዶምያስ ባድማ የሆነችው በእስራኤል ጥፋት በመፈንጠዟ ነበር (ሕዝ 35፥15 ይመ)።

*24፥19፤* ከመዝ 37፥1 ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ቍ1፤ 23፥17 ይመ።

24፥20 *ተስፋ የለውምና*፤ ለራሱ ወይም ከእርሱ ለሚወለዱ ዘሮቹ ማለት ነው (መዝ37፥2፡28፡38 ይመ፤ ከቍ14፤ 23፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። *መብራት ... ትጠፋለች*፤ የ13፥9 ማብ ይመ።

24፥21 *እግዚአብሔርንና ንጉሥን ፍራ፤* ለባለሥልጣኖች መገዛት ተገቢ እንደ ሆነ በመክ8፥2-5 ላይም ታዞአል። በ1ጴጥ 2፥17 "እግዚአብሔርን ፍራ፤ ንጉሥን አክብር" ይላል፤ በሮሜ 13፥1-7 ያለው ክፍልም ይህንኑ ይመክራል (ከ20፥8፡26 ጋር ያነጻጽሩ)።

24፥22 *ሁለቱም፤* እግዚአብሔርና ንጉሥ ማለት ነው። *የሚያመጡት መዓት*፤ የእግዚአብሔር ፍርድ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ አል (6፥15፤ 11፥3፡5)፤ ነገር ግን የንጉሥ ሥልጣን ምን ያህል ብርቱ እንደ ሆነ የተገለጸው በ20፥26 ላይ ነው።

*24፥23-34፤* ይህ ክፍል የጠቢቡን ጥቂት ተጨማሪ አባባሎች ያዘለ የ22፥17-24፥22 ቅጥያ ነው።

24፥23 *በዳኝነት አድልዎ ማድረግ ተገቢ አይደለም*፤ 18፥5 እና ማብ ይመ።

24፥24 *አንተ ንጹሕ ነህ፤* 17፥15 ይመ። *ሕዝቦች ይረግሙታል፤* "በድብቅ እህል የሚያከማቸውን ሰው፣ ሕዝብ ይረግመዋል" (11፥26) እንደ ተባለው ነው።

24፥25 *የተትረፈረፈ በረከትም*፤ 10፥6፤ ዘዳ16፥20 ይመ።

24፥26 *እውነተኛ መልስ*፤ ከ16፥13 ጋር ያነጻጽሩ። *እንደ መሳም*፤ በ16፥24 ላይ፣ "ለነፍስ ጣፋጭ" የተባለችውን "መልካም ቃል" ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ።

24፥27 *እርሻህን አዘጋጅ*፤ ቤትህን በምትሠራበት ጊዜ፣ ዕቅድህን በጥንቃቄ አዘጋጅ፤ ለግንባታውም የሚያስፈልጉህን ነገሮች አሰናዳ። *ቤትህን፤* የቍ3 ማብ ይመ።

24፥28 *ያለ ምክንያት አትመስክር*፤ 3፥30 ይመ። *በከንፈርህም አትሸንግል*፤ 6፥19 እና ማብ፤ 12፥17፤ 25፥18 ይመ።

24፥29 *የጁን እመልስለታለሁ፤* የበቀል ሐሳብ በ20፥22 ላይም ተከልክሎአል (የዚያኑ ማብ ይመ)፤ ከ25፥21-22፤ ከማቴ 5፥43-45፤ ከሮሜ12፥17 ጋር ያነጻጽሩ።

24፥30 *በሰነፍ ሰው*፤ የ6፥6 ማብ፤ እንዲሁም 20፥4 ይመ።

24፥31 *እሾህ ... ዐረም፤* 15፥19፤ ከኢሳ 34፥13 ጋር ያነጻጽሩ።

*24፥33-34፤* 6፥10-11 እና የ6፥11 ማብ ይመ።

25፥1 *የሰሎሞን ምሳሌዎች*፤ የ1፥1፤ 10፥1 ማብ ይመ፤ *የሕዝቅያስ ሰዎች የቀዷቸው*፤ በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ ነበር (715-686 ዓ.ቅ.ክ)፤ ንጉሡም ዜማዎቹ

ምሳሌዎች ናቸው:-

2ነገርን መሰወር ስእግዚአብሔር ክብሩ ነው፤
ነገርን ፈልፍሎ ማውጣት ግን
ለነገሥታት ክብራቸው ነው::

3ሰማያት ከፍ ያሉ እንደ ሆኑ፣ ምድርም
ጥልቅ እንደ ሆነች ሁሉ፣
የነገሥታትም ልብ እንደዚሁ
አይመረመርም::

4ከብር ዝገትን አስወግድ፤
አንጥረኛውም ንጹህ ነገር' ያገኛል፤
5ክፉን ከንጉሥ ፊት አርቅ፤
ዙፋኑም በጽድቅ ትጸናለች::
6በንጉሥ ፊት ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ፤
በታላላቆች መካከል መገኘትም
አይመርህ፤
7በትልቅ ሰው ፊት ከሚያዋርድህ፣
ራሱ፣ "ወደዚህ ከፍ በል" ቢልህ
ይሻላልና::

በዐይንህ ያየኸውን ሁሉ፣
8ወደ ፍርድ አደባባይ በችኰላ አታውጣው፤'
ባልንጀራህ ካሳፈረህ፣
ኋላ ምን ይውጥሃል?

9ስለ ራስህ ጒዳይ ከባልንጀራህ ጋር
በምትከራከርበት ጊዜ፣
የሌላውን ሰው ምስጢር አታውጣ፤
10ያለዚያ ይህን የሚሰማ ያሳፍርሃል፤
አንዴ የጠፋውን ስምህንም ፈጽሞ
መመለስ አትችልም::

11ባግባቡ የተነገረ ቃል፣
በብር መደብ ላይ እንደ ተቀረጸ የወርቅ
እንኮይ ነው::
12የጠቢብ ሰው ዘለፋ ለሚሰማ ጆሮ፣
እንደ ወርቅ ጒትቻ ወይም እንደ ጥሩ
የወርቅ ጌጥ ነው::

13በመከር ጊዜ የበረዶ ቅዝቃዜ ለሰስ
እንደሚያደርግ ሁሉ፣
ታማኝ መልእክተኛም ለላኩት እንደዚሁ
ነው፤
የጌቶቹን መንፈስ ያሳርፋልና::

14የማይለግሰውን ስጦታ እቸራለሁ ብሎ
ጒራ የሚነዛ ሰው፣
ዝናብ እንደ ሌለው ደመናና ነፋስ ነው::
15በትዕግሥት ገዥን ማግባባት ይቻላል፤
ለስላሳ አንደበትም ዐጥንት ይሰብራል::

16ማር ስታገኝ በልክ ብላ፤
ከበዛ ያስመልስሃል::

17ወደ ባልንጀራህ ቤት እግር አታብዛ፤
ታሰለቸውና ይጠላሃል::

18በባልንጀራው ላይ በሐሰት የሚመሰክር፣
እንደ ቈመጥ፣ እንደ ሰይፍና እንደ ተሳለ
ፍላጻ ነው::
19በመከራ ጊዜ በወስላታ ሰው መተማመን፣
በተበላሸ ጥርስና በሰለለ እግር እንደ
መታመን ነው::

20ላዘነ ልብ የሚዘምር፣
በብርድ ቀን ልብሱን እንደሚያወልቅ፣
ወይም በሶዳ ላይ እንደ ተጨመረ

'4 ወይም *ጽዋ*
'7:8 ወይም *ዐይንህን የማልህበት ሰው፣* 8... *አትውጣ*

25፥2 ምሳ16፥10-15
25፥5 2ሳሙ7፥13፤ምሳ16፥12፤20፥8፤29፥14
25፥7 ሉቃ14፥7-10
25፥8 ማቴ5፥25-26
25፥11 ቍ12፤ምሳ15፥23
25፥12 ቍ11፤መዝ141፥5፤13፥18
25፥13 ምሳ10፥26፤13፥17
25፥15 ምሳ15፥1፤መክ10፥4
25፥16 ቍ27
25፥18 ምሳ12፥18

ቀድሞ ይቀርቡ በነበረበት ሁኔታ እንዲቀርቡ አደረገ (2ዜና 29፥30):: ንጉሡ በዳዊት ቅኔ ደስ መሰኘቱ፣ የሰሎሞን ምሳሌዎች በአንድ ላይ እንዲሰበሰቡ ከሰጠው ድጋፍ ጋር ይጣጣማል:: የእስራኤል መንግሥት ከመከፋፈሉ በፊት ሰሎሞን የመጨረሻ ንጉሥ ነበር:: ሕዝቅያስ መላውን እስራኤልን ማለት በዚህ ጊዜ በደቡብ ግዛት ብቻ የተወሰነውን በመግዛት የመጀመሪያ ነበር::

25፥2 *ነገርን መሰወር፤* ሰው፣ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደ ፈጠረና እንዴት እንደሚያስተዳድር መረዳት ባለመቻሉ እግዚአብሔር ይከብራል:: (ዘዳ29፥29፤ ኢዮ26፥14 እና ማብ፤ ኢሳ40፥12-24፤ ሮሜ11፥33-36 ይመ):: *ነገርን ፈልፍሎ ማውጣት፤* ንጉሥ እውነትን መግለጥና በፍትሕ ማስተዳደር ሲችል ክብርን ያገኛል (1ነገ3፥9፤ 4፥34 ይመ)::

25፥3 *አይመረመርም፤* በ30፥18-19 ላይ እንደ ተመለከቱት አራት ነገሮች የነገሥታትም ልብ ሊደርስበት ወይም ሊታወቅ አይችልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የነገሥታትን ልብ ይቈጣጠራል (21፥1 ማብ ይመ)::

25፥4 *ከብር ዝገትን አስወግድ፤* በኢሳ1፥22-25፤ በሕዝ 22፥18፤ በሚል3፥2-3 ላይ በአጠቃላይ ከኀብረተ ሰብ መታደስ በተለይ ደግሞ ከገዦች ንጽሕና ጋር የሚነጻጸር ሂደት ነው::

25፥5 *ዙፋኑም በጽድቅ ትጸናለች፤* የ16፥12 ማብ፤ እንዲሁም 20፥26 ይመ::

25፥6 *በንጉሥ ፊት፤* በግብዣ ላይ ሊሆን ይችላል (ከ23፥1 ጋር ያነጻጽሩ):: ጌታ ኢየሱስ በሰርግ ግብዣ ላይ ስላለ የክብር ስፍራ ተናግሮአል (ሉቃ14፥7-11)::

25፥7 *"ወደዚህ ከፍ በል"፤* ሉቃ14፥10 ላይ "ወዳጄ ሆይ፤ ወደተሻለው ስፍራ ከፍ በል" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ፤ ከኢሳ 22፥15-19 ጋር ያስተያዩ::

25፥8 *ወደ ፍርድ አደባባይ በችኰላ አታውጣው፤* ጭቅጭቅ ውስጥ መግባት ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነና (17፥14 ይመ) ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ (24፥28 ይመ) የሚያሳስብ ምክር ነው::

25፥9 *የሌላውን ሰው ምስጢር አታውጣ፤* ብታወጣ ሐሜተኛ ትሆናለህ (11፥13፤ 20፥19 ይመ)::

25፥10 *የጠፋውን ስምህንም፤* መልካም ስም በሕይወት ዘመን እንደ ትልቅ ሀብት ከሚቈጠሩት ነገሮች አንዱ ነው (22፥1 እና ማብ ይመ)::

25፥11 *በብር ... የወርቅ፤* በ8፥19 ላይ ከተመለከተው የጥበብ ፍሬ ጋር ያነጻጽሩ::

25፥12 ... *ወርቅ ጒትቻ፤* የጥበብን ውበትና ጤናማ ትምህርት ከሚገልጽ የአበባ ጒንጒንና የዐንገት ጌጥ ጋር ይወዳደራል (1፥9፤3፥22፤4፥9 ይመ):: *የጠቢብ ሰው ዘለፋ፤* በ15፥31 ላይ "ሕይወትን የሚሰጥ ተግሣጽ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ::

25፥13 *የበረዶ ቅዝቃዜ፤* በረዶ ካለበት ተራራ የሚወርድ ቀዝቃዛ ውሃ ወይም ከዚያ የሚመጣ ቀዝቃዛ አየር ሊሆን ይችላል:: *ታማኝ መልእክተኛም፤* 13፥17 እና ማብ ይመ::

25፥14 *ዝናብ እንደ ሌለው ደመናና፤* ይህ ሐረግ የይሁዳ መልእክት ቍ12 ላይ ፍሬ የሌላቸውን ከንቱ ሰዎች ለመግለጽ ገብቶአል::

25፥15 *በትዕግሥት ገዥን ማግባባት ይቻላል፤* ከ14፥29 ጋር ያነጻጽሩ:: *ለስላሳ አንደበት፤* የ15፥1 ማብ ይመ::

25፥18 *ቈመጥ ... ሰይፍና ... ፍላጻ፤* ከመዝ57፥4፤ ከኤር 9፥8 ጋር ያነጻጽሩ:: *በሐሰት የሚመሰክር፤* የ6፥19 ማብ፤ እንዲሁም 24፥28፤ ዘፀ20፥16 ይመ::

25፥19 *በተበላሸ ጥርስና በሰለለ እግር፤* በግብፅ መተማመን የተቀጠቀጠ ሸንበቆን እንደ መደገፍ ነበር (ኢሳ30፥6)::

25፥20 *በሶዳ ላይ ... ሆምጣጤ፤* 'ናትሮን' በመባል የሚታወቅ (ኤር2፥22 ይመ)፣ መልኩ ጨው የሚመስል ማዕድን (ሶዲየም ካርቦኔት) ሳይሆን አይቀርም፤ በጥንት ዘመን ለልብስ ማጠቢያ ይጠቀሙበት ነበር:: ሆምጣጤ ሲገባበት ኀይለኛ መብላላት ያሳያል:: *ላዘነ ልብ የሚዘምር፤* በባቢሎን ምድር የነበሩ ስደተኞች የጽዮንን መዝሙር ለመዘመር ፈቃደኞች አልነበሩም (መዝ137፥3-4)::

ሆምባጤ ነው።

21 ጠላትህ ቢራብ አብላው፤
ቢጠማም ውሃ አጠጣው።

22 ይህን በማድረግህም፣ በራሱ ላይ ፍም
ትከምራለህ፤
እግዚአብሔርም ዋጋህን ይከፍልሃል።

23 የሰሜን ነፋስ ዝናብ እንደሚያመጣ ሁሉ፣
ሐሜተኛ ምላስም ቍጡ ፊት
ታስከትላለች።

24 ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር በአንድ ቤት
ከመኖር፣
በጣራ ማዕዘን ላይ መኖር ይሻላል።

25 ከሩቅ የሚመጣ መልካም ዜና፣
የተጠማችን ነፍስ እንደሚያረካ ቀዝቃዛ
ውሃ ነው።

26 ለክፉ ሰው የሚንበረከክ ጻድቅ፣
እንደ ደፈረሰ ምንጭ ወይም እንደ
ተበከለ የጒድጓድ ውሃ ነው።

27 ከመጠን በላይ ማር መብላት ጥሩ
አይደለም፤
የራስንም ክብር መሻት አያስከብርም።

28 ራሱን የማይቈጣጠር ሰው፣
ቅጥሩ እንደ ፈረሰ ከተማ ነው።

## 26

1 በረዶ በበጋ፣ ዝናብ በመከር እንደ
ማያስፈልግ ሁሉ፣
ክብርም ለተላላ አይገባውም።

2 ከንፎቿን እንደምታርገበግብ ድንቢጥ
ወይም ቱር እንደምትል ጨረባ፣
ከንቱ ርግማንም በማንም ላይ
አይደርስም።

3 ለፈረስ አለንጋ፣ ለአህያ መሸበቢያ፣
ለተላላ ጀርባም በትር ይገባዋል።

4 ቂልን እንደ ቂልነቱ አትመልስለት፤
አለዚያ አንተም ራስህ እንደ እርሱ
ትሆናለህ።

5 ቂልን እንደ ቂልነቱ መልስለት፤
አለዚያ ጠቢብ የሆነ ይመስለዋል።

6 በቂል እጅ መልእክትን መላክ፣
የገዛ እግርን እንደ መቍረጥ ወይም
ዐመፃን እንደ መጋት ነው።

7 በተላላ አንደበት የሚነገር ምሳሌ፣
ሰላላ የሽባ ሰው እግር ነው።

8 ለተላላ ክብር መስጠት፣
በወንጭፍ ላይ ድንጋይ እንደ ማሰር
ነው።

9 በአላዋቂ አንደበት የሚነገር ምሳሌ፣
በሰካራም እጅ እንዳለ እሾኽ ነው።

10 ቂልን ወይም የትኛውንም ዐላፊ አግዳሚ
የሚቀጥር፣
ፍላጻውን በነሲብ እየወረወረ ወገኖቹን
እንደሚያቈስል ቀስተኛ ነው።

11 ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ሁሉ፣
ተላላም ቂልነቱን ይደጋግማል።

25፥22 2ዜና28፥15፤መዝ18፥8፤ማቴ5፥44፤ሮሜ12፥20
25፥24 ምሳ21፥9
25፥25 ምሳ15፥30
25፥27 ቍ16፤ምሳ27፥2፤ማቴ23፥12
26፥1 ቍ8፤1ሳሙ12፥17፤ምሳ19፥10
26፥2 ዘዳ23፥5
26፥3 መዝ32፥9፤ምሳ10፥13
26፥4 ቍ5፤ኢሳ36፥21
26፥5 ቍ4፤ምሳ3፥7
26፥6 ምሳ10፥26
26፥7 ቍ9
26፥8 ቍ1
26፥9 ቍ7
26፥11 መዝ85፥8፤2ጴጥ2፥22

*25፥21-22፤* ይህ ክፍል ክፉን በመልካም እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል በማመልከት በሮሜ 12፥20 ላይ ተጠቅሶአል።

*25፥21፤* ጠላት ለሆነ ሰው በጎ ማድረግ ተገቢ መሆኑ በ20፥22፤ በዘፀ23፥4-5 ላይ ተመልክቶአል። *አብላው፤ ... ውሃ አጠጣው፤* በቍጥጥር ሥር የዋለው የሶርያ ሰራዊት ነቢዩ ኤልሳዕ በሰጠው ምክር መሠረት ትልቅ ግብዣ ተደርጎለት ወደ አገሩ ተመልሶአል (2ነገ6፥21-23 ይመ፤ ከ2ዜና28፥15 ጋር ያነጻጽሩ)።

25፥22 *በራሱ ላይ ፍም ትከምራለህ፤* ለክፉዎች የተመደበ ከባድ ቅጣት ነው (መዝ140፥10 ይመ)። እዚህ ላይ ግን ጠላትን የሚጐዳው የሚደረግለት በጎነት ነው (በቍ15 ላይ "ዐጥንት ይሰብራል" የሚለውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)፤ ምናልባትም ይህ ደግነት ወደ መልካም መንገድ ሊመራው ይችላል። በሌላም በኩል፣ ይህ አባባል በግብፅ የነበረውን ከበደል የመንጻት ሥርዐት፣ ይኸውም በደለኛ ሰው ንስሓ መግባቱን ለማመልከት በጐድጓዳ ሳሕን የእሳት ፍም በራሱ ላይ የመሸከም ልማድን ሊያንጸባርቅ ይችላል። እንግዲህ በዚህ መሠረት ለጠላትህ በጎ መመለስ፣ ወደ ንስሓ ልታመጣው ወይም መልካም ልታደርግ ትችላለህ ማለት ነው። *እግዚአብሔርም ዋጋህን ይከፍልሃል፤* ጠላትህ በክፋቱ ቢቀጥልም፣ አንተን ግን እግዚአብሔር ይክስሃል (ከ11፥18፤ 19፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

25፥23 *የሰሜን፤* ለእስራኤል አገር ዝናብ የሚመጣው በምዕራብ በኩል ስለ ሆነ፣ ሰሜን ምዕራብ ለማለት ይሆናል (ከሉቃ12፥54፤ ከ1ነገ18፥41-44 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሐሜተኛ ምላስም፤* በየቦታው ስም የሚያጠፋ አንደበት ነው (ከ10፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

25፥25 *ከሩቅ የሚመጣ መልካም ዜና፤* ዘፍ45፥25-28 ይመ።

25፥26 *የሚንበረከክ ጻድቅ፤* ምናልባት እጅ መንሻ በማቅረብ ሊሆን ይችላል (ከ17፥8፤ 29፥4፤ ከኢሳ 1፥21-23 ጋር ያነጻጽሩ)። *እንደ ደፈረሰ ምንጭ፤* ከሕዝ 34፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ።

25፥27 *የራስንም ክብር መሻት፤* ቍ6-7 እና ማብ ይመ።

25፥28 *ቅጥሩ እንደ ፈረሰ ከተማ፤* የተጋለጠችና የተዋረደች ለማለት ነው (ከነህ1፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። *ራሱን የማይቈጣጠር ሰው፤* 16፥32 እና ማብ ይመ።

26፥1 *ዝናብ በመከር፤* ከሰኔ እስከ መስከረም ባሉት ወራት በመካከለኛው ምሥራቅ ብዙውን ጊዜ ዝናብ አይዘንብም፤ ይሁን እንጂ 1ሳሙ12፥17-18 ይመ። *ክብርም ለተላላ አይገባውም፤* ቍ8፤ 30፥22 ይመ።

26፥2 *ከንቱ ርግማንም በማንም ላይ አይደርስም፤* ሳሚ ዳዊትን በረገመው ጊዜ፣ ርግማኑ እንደማይደርስበት ዳዊት አስተውሎአል፤ ምክንያቱም የሳኦልን ቤተ ሰብ ገድሎአል የተባለው ሐሰት ነበር (2ሳሙ16፥8፡12)።

26፥3 *ለተላላ ጀርባም በትር፤* 14፥3፤ 19፥29 ይመ።

*26፥4-5፤* እነዚህ ቍጥሮች እርስ በርስ የሚቃረኑ ሳይሆኑ፣ የሚደጋገፉ ናቸው። ከቂል ጋርም እንኳ ዝቅ ብሎ መከራከርና ሐሳቡን ማክበር ተገቢ ቢሆንም (ቍ4፤ 23፥9፤ ማቴ7፥6 ይመ) አንዳንድ ጊዜ ግን ሐሳቡ ትክክል እንዳልሆነ በአግባቡ መንገር ያስፈልጋል (ቍ5)፤ አለበለዚያ ከንቱ ሐሳቡን የተደገፈለት ይመስለዋል።

26፥6 *ዐመፃን እንደ መጋት፤* 4፥17፤ ኢዮ34፥7 ይመ። *በተላላ እጅ መልእክትን መላክ፤* የላከውን በትክክል ላይወክል ይችላል፤ የላኪውንም ዓላማ ሊያዛባ ይችላል (13፥17 ይመ)።

26፥8 *በወንጭፍ ላይ ድንጋይ እንደ ማሰር፤* ለተላላ ክብርን መስጠት ጅልነት ነው፤ ይኸውም በወንጭፍ ላይ የታሰረ ድንጋይ እንደማይወረወርና ግቡን እንደማይመታ ሁሉ ተላላውን ሰው ማክበርም ጥቅም የለውም።

*26፥9፤* እሾሃማ የሆነን እንጨት በእጁ የያዘ ሰካራም ለራሱና ለሌሎች አደገኛ እንደ ሆነ ሁሉ አላዋቂም አጠቃቀሙን ስለማያውቅበት በእርሱ አንደበት የሚነገር ምሳሌ ሁሉ አደገኛ ነው።

26፥10 *ቂልን ወይም የትኛውንም ዐላፊ አግዳሚ የሚቀጥር፤* አቤሜሌክ ወንድሞቹን ለማስገደልና ግብ ያልመታውን የአጭር ጊዜ መንግሥቱን ለማቋቋም እንዲረዱት ወሮበሎች ቀጥሮ ነበር (መሳ9፥4-6)።

26፥11 *ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ፤* ክርስቶስን ተከትለው፣ የጽድቅንም መንገድ ዐውቀው ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን

12 ራሱን እንደ ጠቢብ የሚቈጥረውን ሰው
አይተሃልን?
ከእርሱ ይልቅ ለተላላ ተስፋ አለው።

13 ሰነፍ፣ “በመንገድ ላይ አንበሳ አለ፤
አስፈሪ አንበሳ በአውራ ጐዳና ላይ
ይጐማለላል” ይላል።

14 መዝጊያ በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣
ሰነፍም በዐልጋው ላይ ይገላበጣል።

15 ሰነፍ እጁን ወጭት ውስጥ ያጠልቃል፤
ወደ አፉ ለመመለስ ግን እጅግ
ይታክታል።

16 በማስተዋል መልስ ከሚሰጡ ከሰባት
ሰዎች ይልቅ፣
ሰነፍ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥራል።

17 በሌሎች ጠብ ጥልቅ የሚል መንገደኛ፣
የውሻ ጆሮ እንደሚይዝ ሰው ነው።

18 ትንታግ ወይም የሚገድል ፍላጻ
እንደሚወረውር ዕብድ፣

19 “ቀልዴን እኮ ነው” እያለ
ባልንጀራውን የሚያታልል ሰውም
እንደዚሁ ነው።

20 ዕንጨት ከሌለ እሳት ይጠፋል፤
አሾክሻኪ ከሌለም ጠብ ይበርዳል።

21 ከሰል ፍምን፣ ዕንጨትም እሳትን
እንደሚያቀጣጥል፣
አዋኪ ሰውም ጠብን ያባብሳል።

22 የሐሜተኛ ቃል እንደ ጣፋጭ ጕርሻ
ነው፤
ወደ ሰው ውስጠኛው ክፍል ዘልቆ
ይገባል።

23 ክፋትን በልብ ቋጥሮ ለስላሳ ቃል
የሚናገር ከንፈር፣
በብር ፈሳሽ^ እንደ ተለበጠ የሸክላ ዕቃ
ነው።

24 ተንኰለኛ በከንፈሩ ይሸነግላል፤
በልቡ ግን ክፋትን ይቋጥራል።

25 ንግግሩ ማራኪ ቢሆንም አትመነው፤
ሰባት ርኵሰት ልቡን ሞልቶታልና።

26 ተንኰሉ በሽንገላው ይሸፈን ይሆናል፤
ነገር ግን ክፋቱ በጉባኤ ይገለጣል።

27 ጕድጓድ የሚምስ ራሱ ይገባበታል፤
ድንጋይ የሚያንከባልልም ተመልሶ በላዩ
ላይ ይገለበጥበታል።

28 ሐሰተኛ ምላስ የጐዳቻቸውን ትጠላለች፤
ሽንጋይ አንደበትም ጥፋትን
ታመጣለች።

# 27

ነገ በሚሆነው አትመካ፤
ቀን የሚያመጣውን
አታውቅምና።

2 ሌላው ያመስግንህ እንጂ የገዛ አፍህ
አይደለም፤
ሌላ ሰው ያወድስህ እንጂ የገዛ ከንፈርህ
አይሁን።

3 ድንጋይ ይከብዳል፤ አሸዋም ሸክም ነው፤
የተላላ ሰው ጕንጣ ግን ከሁለቱም
ይከብዳል።

4 ንዴት ጨካኝ፣ ቍጣም ጎርፍ ነው፤
በቅናት ፊት ግን ማን መቆም ይችላል?

5 የተገለጠ ዘለፋ፣
ከተደበቀ ፍቅር ይሻላል።

6 ከጠላት ደጋግሞ መሳም ይልቅ፣
የወዳጅ ማቍሰል ይታመናል።

^23 ወይም *በሚያብለጨልጭ ነገር*

26፥12 ምሳ3፥7፤ 29፥20
26፥13 ምሳ6፥6-11፤22፥13፤24፥30-34
26፥14 ምሳ6፥9
26፥15 ምሳ19፥24
26፥20 ምሳ22፥10
26፥21 ምሳ14፥17
26፥22 ምሳ18፥18
26፥24 መዝ31፥18፤141፥6
26፥25 መዝ28፥3፤ኤር9፥4
26፥27 አስ2፥23፤6፥13፤7፥9፤መዝ7፥15፤35፥8፤141፥10፤ምሳ28፥10፤29፥6፤ኢሳ50፥11
26፥28 መዝ12፥3፤ምሳ29፥5
27፥1 1ነገ20፥11፤ማቴ6፥34፤ያዕ4፣13-16
27፥2 ምሳ25፥27
27፥3 ኢዮ 6፥3
27፥4 ዘኍ 5፥14
27፥6 መዝ141፥5፤ምሳ28፥23

ቅዱስ ትእዛዝ በመተው፣ እንደ ገና ወደ ኀጢአት ሕይወት ስለተመለሱት፣ ጴጥሮስ ይህን ምሳሌ ተጠቅሞአል (2ጴጥ2፥20-22)። *ተላላም፣ ቂልነቱን ይደጋግማል፤* ስካራም ወደ ስካሩ ይመለሳል (23፥35)።

26፥12 *ራሱን እንደ ጠቢብ የሚቈጥረውን፤* ይህ ትዕቢት በቍ16 ላይ የተጠቀሰውን ታካችና በ28፥11 ላይ የተመለከተውን ሀብታም ለመግለጽ ገብቶአል፤ ከ26፥5 ጋር ያነጻጽሩ።

*26፥13፤* 22፥13 እና ማብ ይመ።

26፥14 *ሰነፍም በዐልጋው ላይ ይገላበጣል፤* መዝጊያ ከማጠፊያው ጋር እንደሚያያዝ ሁሉ፣ እርሱም ዐልጋውን የሙጥኝ ይላል።

26፥16 *ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥራል፤* ቍ12 እና ማብ ይመ።

26፥17 *የውሻ ጆሮ እንደሚይዝ፤* እንዲህ ማድረግ ችግርን ፈጥኖ መጋበዝ ነው።

26፥18 *እንደሚወረውር ዕብድ፤* በቍ10 ላይ ከተመለከተው ቀስተኛ ጋር ያነጻጽሩ። *ትንታግ፤* የእህልን ነዶ በቀላሉ ያቀጣጥላል (ከዘካ12፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

26፥19 *ቀልዴን እኮ ነው፤* ሰውን የሚጐዳ የማይገባ ሥራ እየሠሩ፣ ለጨዋታ ነው ማለት አጥጋቢ ምክንያት አይሆንም።

26፥21 *ጠብን ያባብሳል፤* የ6፥14 ማብ ይመ።

*26፥22፤* የ18፥8 ማብ ይመ።

26፥23 *በብር ፈሳሽ እንደ ተለበጠ የሸክላ ዕቃ፤* “የጽዋና የሳሕን ውጫዊ ንጽሕና” የተባለውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ሉቃ 11፥39 ይመ፤ ከማቴ23፥27 ጋር ያነጻጽሩ)። *ክፋትን በልብ ቋጥሮ ለስላሳ ቃል፤* የአመንዝራ አነጋገር ያሳስታል (2፥16፤5፥3)።

26፥24 *በልቡ ግን ክፋትን ይቋጥራል፤* 12፥20 ይመ።

26፥25 *ንግግሩ ማራኪ፤* ኤር9፥8 ይመ። *ሰባት፤* ብዙ ለማለት ነው (የኢዮ5፥19 ማብ ይመ)። ጌታ የሚጸየፋቸውን ሰባት ነገሮች በ6፥6-19 ላይ ይመ።

26፥26 *በጉባኤ ይገለጣል፤* 5፥14፤ ሉቃ8፥17 ይመ።

26፥27 *ጕድጓድ የሚምስ ራሱ ይገባበታል፤* “እርሱ የቀሰቀሰው ችግር ተመልሶ በራሱ ላይ ይመጣል” (መዝ7፥16)፤ 1፥18 እና ማብ፤ 28፥10፤ 29፥6፤ አስ 7፥10፤ መዝ 7፥15፤ መክ10፥8-9 ይመ።

26፥28 *ሐሰተኛ ምላስ የጐዳቻቸውን ትጠላለች፤* 10፥18 ይመ። *ሽንጋይ አንደበትም ጥፋትን ታመጣለች፤* 29፥5 ይመ፤ ከ16፥13 ጋር ያነጻጽሩ።

27፥1 *ነገ በሚሆነው አትመካ፤* ያዕቆብ፣ “ነገ ስለሚሆነው እንኳ አታውቁም፤ ሕይወታችሁ ምንድን ናት? ለጥቂት ጊዜ ታይቶ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ” (4፥14) በማለት ከጸፈው ጋር ይዛመዳል። ሕይወት አጭር ከመሆኗም በላይ አስተማማኝ ስላይደለች ዕቅዳችን መመሥረት ያለበት በእኛ ዕውቀት ወይም ግምት ላይ ሳይሆን በጌታ ፈቃድ ላይ ነው (ያዕ4፥15)። በሉቃ 12፥19-20 ላይ ካለው ከሞኙ ባለ ጠጋ ንግግር ጋር ያነጻጽሩ፤ ምሳ16፥9፤ ኢሳ56፥12 ይመ።

27፥2 *ሌላው ያመስግንህ፤* 2ቆሮ10፥12፡18 ይመ።

27፥4 *በቅናት ፊት ... ማን መቆም ይችላል?* 6፥34፤ ማሕ8፥6 ይመ።

27፥5 *የተገለጠ ዘለፋ፤* በ15፥31 ላይ፣ “ሕይወት የሚሰጥ ተግሣጽ” ተብሎአል፤ ከገላ2፥14 ጋር ያነጻጽሩ።

27፥6 *የወዳጅ ማቍሰል ይታመናል፤* በወዳጆች መካከል መቍሰል ሊከሠት ይችላል፤ ይሁን እንጂ ወዳጅነት እስካለ ድረስ ቍስሉ ይድናል(በመዝ 141፥5 ይመ)። አታላይ ጠላት ግን የሚያባብል ቃል ቢናገርም፣ ቃሉ አንዳች የሚረባ ነገር የለውም። *ከጠላት ደጋግሞ መሳም ይልቅ፤* 5፥3-4፤ ማቴ26፥49 ይመ።

7 ለጠገበ ማር አይጥመውም፤
ለተራበ ግን እሬት እንኳ ይጣፍጠዋል።
8 ከቤቱ ወጥቶ የሚባዝን ሰው፣
ጎጆዋን ለቃ እንደ ምትባዝን ወፍ ነው።
9 ሽቱና ዕጣን ልብን ደስ ያሰኛሉ፤
የወዳጅ ማስደሰትም ከቅን ምክሩ
ይመነጫል።
10 የራስህንም ሆነ የአባትህን ወዳጅ
አትተው፤
መከራ በሚያጋጥምህ ጊዜ ወደ ወንድምህ
ቤት አትሂድ፤
ሩቅ ካለ ወንድም ቅርብ ያለ ጎረቤት
ይሻላል።
11 ልጄ ሆይ፤ ጠቢብ ሁን፤ ልቤን ደስ
አሰኘው፤
ለሚንቁኝ ሁሉ መልስ መስጠት እችል
ዘንድ።
12 ጥንቁቅ አደጋን አይቶ ይሸሸጋል፤
ማስተዋል የጐደለው ግን ወደዚያው
ይሄዳል፤ ይጐዳልም።
13 ለማይታወቅ ሰው የተዋሰን ልብሱን
ግፈፈው፤
ለዘልዛላ ሴት ከተዋሰማ አግተው።
14 ሰው ድምፁን ከፍ አድርጎ ባልንጀራውን
በማለዳ ቢመርቅ፣
እንደ ርግማን ይቈጠራል።
15 ጨቅጫቃ ሚስት፣
በዝናብ ቀን እንደሚወርድ የማያቋርጥ
ጠፈጠፍ ናት፤
16 እርሷን ለመግታት መሞከር፣
ነፋስን እንደ መግታት ወይም ዘይትን
በእጅ እንደ መጨበጥ ነው።

27፥8 ኢሳ16፥2
27፥9 አስ2፥12፤ መዝ45፥8
27፥10 ምሳ17፥17
27፥11 ዘፍ24፥60፤ ምሳ10፥1፤23፥15-16
27፥12 ምሳ 22፥3
27፥13 ምሳ20፥16
27፥15 አስ 1፥18
27፥18 ሉቃ19፥12-27፤1ቆሮ9፥7
27፥20 ምሳ30፥15-16፤መክ1፥8፤6፥7፤ ዕን 2፥5
27፥21 ምሳ17፥3
27፥23 ምሳ12፥10
27፥24 ምሳ23፥5

17 ብረት ብረትን እንደሚስል፣
ሰውም ሌላውን ሰው እንደዚሁ
ይስለዋል።
18 በለስን የሚንከባከብ ፍሬዋን ይበላል፤
ጌታውን የሚያገለግልም ክብርን
ይጐናጸፋል።
19 ውሃ ፊትን እንደሚያሳይ፣
የሰውም ልብ ማንነቱን ገልጦ ያሳያል።
20 ሲኦልና የሙታን ዓለም[ሀ] እንደማይጠግቡ
ሁሉ፣
የሰውም ዐይን አይረካም።
21 ብር በማቅለጫ፣ ወርቅ በከውር
እንደሚፈተን፣
ሰውም በሚቀበለው ምስጋና ይፈተናል።
22 ጅልን በሙቀጫ ብትወቅጠው፣
እንደ እህልም በዘነዘና ብታደቀው፣
ጅልነቱን ልታስወግድለት አትችልም።
23 በጎችህ በምን ሁኔታ እንዳሉ ደህና
አድርገህ ዕወቅ፤
መንጋህንም ተንከባከብ፤
24 ሀብት ለዘላለም አይኖርምና፤
ዘውድም ከትውልድ ወደ ትውልድ
ጸንቶ አይኖርም።
25 ደረቁ ሣር ተወግዶ፣ አዲሱ ብቅ ሲል፣
በየኰረብታው ላይ ያለው ሣር ተሰብስቦ
ሲገባ፣
26 ከበግ ጠቦቶች ልብስ ታገኛለህ፤
ፍየሎችም የዕርሻ መሬት መግዣ
ይሆኑሃል።
27 አንተንና ቤተ ሰብህን፣
ገረዶችህንም ጭምር ለመመገብ፣
የተትረፈረፈ የፍየል ወተት ይኖርሃል።

[ሀ] 20 ወይም ሞትና ጥፋት

27፥7 *ማር አይጥመውም፤* ከ25፥16፡27 ጋር ያነጻጽሩ።

27፥8 *ከቤቱ ወጥቶ የሚባዝን ሰው፤* መጠጊያ ያጣ በመሆኑ ለፈተና የተጋለጠ ይሆናል፤ (ከ7፥21-23 ጋር ያነጻጽሩ)።

27፥9 *ሽቱና፤* በ21፥17 ማብ ላይ "ዘይት" የሚለውን ይመ። *ዕጣን፤* በመሓ3፥6 ላይ "መዐዛም እንደ ከርቤና እንደ ዕጣን የሆነችው" የሚለውን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (መሓ3፥6)። *የወዳጅ ማስደሰትም፤* ከ16፥21፡24 ጋር ያነጻጽሩ።

*27፥10፤* የተቸገረ ወዳጅህን ፊት አትንሣው፤ በችግር ጊዜ የሥጋ ዝምድና ብቻ ሳይሆን፣ ከሰው ጋር ያለህ ጓደኝነትና ቅርበት ወሳኝ ነው።

27፥11 *ልጄ ሆይ፤ ጠቢብ ሁን፤* 10፥1 እና ማብ ይመ። *ለሚንቁኝ ሁሉ መልስ መስጠት እችል ዘንድ፤* ጠቢብ ልጅ ወይም ተማሪ ያሳደገውን አባቱን ወይም መምህሩን የሚያስከብር ትልቅ ምስክር ነው።

27፥12 *ማስተዋል የጐደለው፤* የ1፥4 ማብ ይመ። *ወደዚያው ይሄዳል፤ ይጐዳልም፤* 7፥22-23፤ 9፥16-18 ይመ።

*27፥13፤* ከ20፥16 ጋር አንድ ናቸው (የዚያኑ ማብ ይመ)።

27፥14 *ባልንጀራውን ... የሚመርቅ፤* ወዳጅነቱን ለማትረፍ ሳይሆን አይቀርም (ከመዝ12፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

*27፥15፤* የ19፥13 ማብ ይመ።

27፥17 *ሌላውን ... ይስለዋል፤* ጠባዩን ይቀርጻል፤ ያሻሽለዋልም ማለት ነው።

27፥18 *ፍሬዋን ይበላል፤* ከ2ጢሞ2፥6 ጋር ያነጻጽሩ። *ክብርን ይጐናጸፋል፤* ከዘፍ39፥4 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም ማቴ 25፥21፤ ሉቃ12፥42-44፤ ዮሐ12፥26 ይመ።

27፥19 *የሰውም ልብ ማንነቱን ገልጦ ያሳያል፤* የሰው ልብ ሁኔታ የሰውየውን እውነተኛ ባሕርይ ያመለክታል (ማቴ5፥8 ይመ)።

27፥20 *ሲኦልና የሙታን ዓለም፤* የኢዮ26፥6 ማብ ፤ እንዲሁም 15፥11 ይመ። *እንደማይጠግቡ፤* ፍላጎታቸው ርካታ የለውም (ኢሳ5፥14 ይመ)። *የሰውም ዐይን አይረካም፤* መክ4፥8 ይመ።

27፥21 *ወርቅ በከውር፤* ብርና ወርቅ በእሳት (ከኢሳ1፥25፤ ከሚል3፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሰውም በሚቀበለው ምስጋና ይፈተናል፤* ሰው በከንቱ ሙገሳ ተደልሎ እንዳይኩራራ መጠንቀቅ አለበት (ከ12፥8፤ ከሉቃ6፥26 ጋር ያነጻጽሩ)።

27፥22 *ጅልነቱን ልታስወግድለት አትችልም፤* ብርቱ ቅጣት ቢቀጡም፣ ቂሎች ከስሕተታቸው አይመለሱም (የ20፥30 ማብ፤ እንዲሁም 26፥11፤ ኤር5፥3 ይመ)።

*27፥23-27፤* በዕርሻ ላይ የተመሠረተውን የጥንቱን ማኅበረሰብ ምጣኔ ሀብት በማንጸባረቅ፣ የግብርና ሥራ ምን ያህል ዋስትና ይሰጥ እንደ ነበር የሚያሳይ ክፍል ነው።

27፥23 *መንጋህንም ተንከባከብ፤* ያዕቆብ የላባን መንጋ ተግቶ ይጠብቅ እንደነበር (ዘፍ31፥38-40)።

27፥24 *ሀብት ለዘላለም አይኖርምና፤* የ23፥5 ማብ ይመ። *ዘውድም ... ጸንቶ አይኖርም፤* ነገሥታት እንኳ ሀብታቸውንና ሥልጣናቸውን ሊያጡ ይችላሉ (ኢዮ19፥9፤ ሰቆ5፥16 ይመ)።

27፥25 *ደረቁ ሣር ተወግዶ፤* በዚያ አገር ይህ የሚሆነው በመጋቢት ወይም በሚያዝያ ወር ነበር።

27፥26 *የዕርሻ መሬት መግዣ፤* 31፥16 ይመ። በጎችና ፍየሎች አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ገንዘብ ሆነው ግብር ለመክፈል ያገለግሉ ነበር (2ነገ3፥4 ይመ)።

27፥27 *የፍየል ወተት፤* እንደ ላም ወተት ይጠጣ ነበር 32፥13-14፤ ኢሳ7፥21-22 ይመ)። *ገረዶችህንም፤* 31፥15 ይመ።

**28** ክፉ ሰው ማንም ሳያሳድደው ይሸሻል፤
ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ልበ ሙሉ ነው።
[2]አገር ስታምፅ፣ ገዦቿ ይበዛሉ፤
አስተዋይና ዕዋቂ ሰው ግን ሥርዐትን ያሰፍናል።
[3]ድኾችን የሚያስጨንቅ ሰው፣[ኀ]
ሰብል እንደሚያጠፋ ኀይለኛ ዝናብ ነው።
[4]ሕግን የሚተዉ ክፉዎችን ያወድሳሉ፤
ሕግን የሚጠብቁ ግን ይቋቋሟቸዋል።
[5]ክፉዎች ፍትሕን አያስተውሉም፤
እግዚአብሔርን የሚሹ ግን ሙሉ በሙሉ ያውቁታል።
[6]በአካሄዱ ነውር የሌለበት ድኻ፣
መንገዱ ጠማማ ከሆነ ባለጠጋ ይሻላል።
[7]ሕግን የሚጠብቅ አስተዋይ ልጅ ነው፤
ከሆዳሞች ጋር ጓደኛ የሚሆን ግን አባቱን ያዋርዳል።
[8]በከፍተኛ ወለድ ሀብቱን የሚያካብት፣
ለድኻ ለሚራራ፣ ለሌላው ሰው ያከማችለታል።
[9]ሕግን ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፣
ጸሎቱ እንኳ አስጸያፊ ነው።
[10]ቅኖችን በክፉ መንገድ የሚመራ፣
በቈፈረው ጒድጓድ ይገባል፤
ንጹሓን ግን መልካም ነገርን ይወርሳሉ።
[11]ባለጠጋ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥር ይሆናል፤
አስተዋይ የሆነ ድኻ ግን መርምሮ ያውቀዋል።
[12]ጻድቃን ድል ሲነሡ ታላቅ ደስታ ይሆናል፤
ክፉዎች ሥልጣን ሲይዙ ግን ሕዝብ ይሸሸጋል።
[13]ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤
የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል።
[14]እግዚአብሔርን ዘወትር የሚፈራ ሰው ቡሩክ ነው፤
ልቡን የሚያደነድን ግን መከራ ላይ ይወድቃል።
[15]ታዳጊ በሌለው ሕዝብ ላይ የተሾመ ጨካኝ ገዥ፣
እንደሚያገሣ አንበሳ ወይም ተንደንድሮ እንደሚይዝ ድብ ነው።
[16]ጨካኝ ገዥ ማመዛዘን ይጎድለዋል፤
ያላግባብ የሚገኝን ጥቅም የሚጸየፍ ግን ዕድሜው ይረዝማል።
[17]የሰው ደም ያለበት ሰው፣
ዕድሜ ልኩን ሲቅበዘበዝ ይኖራል፤
ማንም ሰው አይርዳው።
[18]አካሄዱ ነቀፋ የሌለበት ሰው ክፉ አያገኘውም፤
መንገዱ ጠማማ የሆነ ግን ድንገት ይወድቃል።

28፥1 ዘሌ 26፥17፤ 2ነገ7፥7፤መዝ138፥3
28፥6 ምሳ 19፥1
28፥7 ምሳ 23፥19-21
28፥8 ዘፀ18፥21፤ ኢዮ3፥15፤27፥17፤ መዝ112፥9፤ሉቃ14፥12-14፤ሉቃ14፥12-14
28፥9 መዝ109፥7፤ ምሳ15፥8፤ኢሳ1፥13
28፥10 መዝ57፥6፤ ምሳ26፥27
28፥12 ቍ28፤2ነገ 11፥20፤ኢዮ24፥4፤ ምሳ29፥2
28፥13 ዘሌ5፥5፤ 2ሳሙ12፥13፤ኢዮ 31፥33፤መዝ32፥1-5 ፤ዳን4፥27፤1ዮሐ1፥9
28፥17 1ሳሙ30፥17 ፤ 1ነገ20፥20፤ኤር 41፥15፤44፥14
28፥18 አስ6፥13፤ ምሳ10፥9፤ኤር39፥18

[ኀ]3 ወይም ድኻ

28፥1 *ክፉ ሰው ... ይሸሻል፤* ዘሌ26፥17:36፤ መዝ53፥5 ይመ። *እንደ አንበሳ ልበ ሙሉ ነው፤* ዳዊት በ1ሳሙ17፥46 ላይ እንዳደረገው፤ ከመዝ18፥33-38 ጋር ያነጻጽሩ።

28፥2 *ገዦቿ ይበዛሉ፤* የእስራኤል ዐመፅ ብዙ ጊዜ ፈጣን የመሪዎች መለዋወጥ አስከትሏል (1ነገ16፥8-28፤ 2ነገ 15፥8-15 ይመ)። *አስተዋይና ... ሥርዐትን ያሰፍናል፤* አስተዋይ ገዥ ይሳካለታል (8፥15-16፤ 24፥5፤ 29፥4 ይመ)።

28፥3 *ድኾችን የሚያስጨንቅ፤* 14፥31 ይመ። *ኀይለኛ ዝናብ፤* በኢሳ28፥2 ላይ አውዳሚ የነበረው የአሦር ሰራዊት ብርታት በዚህ ተመስሏል። በመዝ72፥6-7፤ ላይ ደግሞ ጠቃሚ የሆነው ዝናብ ከጽድቅ ንጉሥ ጋር ተነጻጽሮአል።

28፥4 *ሕግን፤* ከጥበብ የሚገኝ ትምህርት (3፥1፤ 7፥2) ወይም የሙሴ ሕግ ሊሆን ይችላል (መዝ119፥53)። *ክፉዎችን ያወድሳሉ፤* ከሮሜ 1፥32 ጋር ያነጻጽሩ። *ሕግን የሚጠብቁ፤* ቍ7፤ 29፥18 ይመ፤ ከቍ9 ጋር ያነጻጽሩ። *ይቋቋሟቸዋል፤* ኤፌ5፥11 ይመ፤ ከሮሜ1፥32 ጋር ያነጻጽሩ።

28፥5 *እግዚአብሔርን የሚሹ፤* እርሱን የሚፈሩ ናቸው (የ1፥7 ማብ ይመ)። *ሙሉ በሙሉ ያውቁታል፤* "ጽድቅን፣ ፍትሕን፣ ሚዛናዊነትን" (2፥9) ያውቃሉ።

28፥6 *ነውር የሌለበት፤* 2፥7 ማብ ይመ።

28፥7 *ሕግን የሚጠብቅ፤* የቍ4 ማብ ይመ። *ከሆዳሞች ጋር ጓደኛ የሚሆን፤* የ23፥ 20-21 ማብ ይመ።

28፥8 *በከፍተኛ ወለድ፤* በዘፀ22፥25፤ በዘሌ25፥35-37፤ ዘዳ 23፥19-20፤ በሕዝ 22፥12 ላይ ተከልክሎአል። *ለሌላው ሰው ያከማችለታል፤* 13፥22 እና ማብ ይመ። *ለድኻ ለሚራራ፤* 14፥31 እንዲሁም 14፥21 ይመ።

28፥9 *ሕግን፤* የቍ4 ማብ ይመ። *ጸሎቱ ... አስጸያፊ ነው፤* በ15፥8 ላይ እንደ ተመለከተው እንደ ክፉ ሰው መሥዋዕት ማለት ነው (የ3፥32 ማብ እንዲሁም መዝ66፥18፤ ኢሳ1፥15፤ 59፥1-2 ይመ)።

28፥10 *በቈፈረው ጒድጓድ፤* የ26፥27 ማብ ይመ። *ንጹሓን፤* የ2፥7 ማብ ይመ። *መልካም ነገርን፤* 3፥35፤ ዕብ 6፥12፤ 1ጴጥ3፥9 ይመ።

28፥11 *ባለጠጋ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥር ይሆናል፤* እንደ ቂሉ (26፥5) ወይም እንደ ሰነፉ ሰው ማለት ነው (26፥16)።

28፥12 *ታላቅ ደስታ ይሆናል፤* 11፥10 እና ማብ ይመ። *ሕዝብ ይሸሸጋል፤* ሰዎች ከጨካኝ ገዦች ራሳቸውን ለመጠበቅ የልባቸውን አሳብ ሰውረው ይኖራሉ፤ ከክፉባቸውም አካባቢውን ጥለው ይጠፋሉ። በአክዓብ ዘመን መንግሥትም አብድዩ መቶ ነቢያትን ሸሸገ (1ነገ18፥13)፤ ጨካኟ ጎቶልያ ገዥ በነበረች ጊዜም (2ነገ11፥2-3) ኢዮአስ ለስድስት ዓመት ተሸሽጎ ነበር።

28፥13 *ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤* በመዝ32፥3 ላይ ኀጢአቱን የማይናዘዝ ሰው የሚደርስበትን ሥቃይ አስተውል። *የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል፤* በመዝ32፥5:10-11 ላይ ይቅርታ ማግኘት የሚሰጠውን ደስታ አስተውል።

28፥14 *እግዚአብሔርን ... የሚፈራ፤* የ1፥7 ማብ፤ እንዲሁም 23፥17 ይመ። *ልቡን የሚያደነድን፤* እንደ ፈርዖን (ዘፀ 7፥13)፣ እስራኤላውያን በከራቢ ምድር እግዚአብሔርን እንደ ተፈታተኑት ማለት ነው (ዘፀ 17፥7 ይመ፤ ከመዝ 95፥8፤ ከሮሜ 2፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

28፥15 *እንደሚያገሣ አንበሳ፤* በቍጣ ተሞልቶ ነፍስን ለማጥፋት የተነሣሣ (ከ19፥12፤ ከማቴ2፥16፤ ከ1ጴጥ5፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። *ተንደርድሮ እንደሚይዝ ድብ፤* የ17፥12 ማብ ይመ። *ጨካኝ ገዥ፤* ቍ12 ይመ።

28፥16 *ያላግባብ የሚገኝን ጥቅም የሚጸየፍ ... ዕድሜው ይረዝማል፤* ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚያገኘውን ጥቅም ከሚሹ ሰዎች የተለየ ነው ማለት ነው (1፥19 ይመ)።

28፥17 *ዕድሜ ልኩን ሲቅበዘበዝ ይኖራል፤* ቃየን ለሕይወቱ በመሥጋት "ተቅበዝባዥ" ነበር (ዘፍ4፥14)። ነፍስ ገዳይ በሞት ያስቀጣ ነበር (ዘፍ9፥6፤ ዘፀ21፥14 ይመ)።

28፥18 *ነቀፋ የሌለበት ... ጠማማ የሆነ፤* በቍ6 እና በ19፥1 ላይ ተነጻጽሮአል። *ድንገት ይወድቃል፤* ከ15፥5 ጋር ያነጻጽሩ።

19 መሬቱን የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ
ያገኛል፤
ከንቱ ተስፋን ይዞ የሚኳዝ ግን ድኽነትን
ይወርሳል::
20 ታማኝ ሰው እጅግ ይባረካል፤
ሀብት ለማግኘት የሚባደፍ ግን ከቅጣት
አያመልጥም::
21 አድልዎ ማድረግ መልካም አይደለም፤
ሰው ግን ለቍራሽ እንጀራ ሲል በደል
ይፈጽማል::
22 ስስታም፣ ሀብት ለማከማቸት ይስገበገባል፤
ድኽነት እንደሚጠብቀውም አያውቅም::
23 ሸንጋይ አንደበት ካለው ይልቅ፣
ሰውን የሚገሥጽ ውሎ ዐድሮ ይወደዳል::
24 ከአባት ከእናቱ ሰርቆ፣
"ይህ ጥፋት አይደለም" የሚል
የአጥፊ ተባባሪ ነው::
25 ስስታም ሰው ጠብን ያነሣሣል፤
በእግዚአብሔር የሚታመን ግን
ይባረካል::
26 በራሱ የሚታመን ተላላ ነው፤
በጥበብ የሚመላለስ ግን ከፉ
አያገኘውም::
27 ለድኾች የሚሰጥ አይቸገርም፤
አይቶአቸው እንዳላየ የሚሆን ግን ብዙ
ርግማን ይደርስበታል::
28 ክፉዎች ሥልጣን በሚይዙ ጊዜ ሕዝብ
ይሸሸጋል፤
ክፉዎች በሚጠፉበት ጊዜ ግን ጻድቃን
ይበዛሉ::

28፥19 ምሳ12፥11
28፥20 ቍ22
28፥21 ዘሌ19፥15፤ መዝ94፥21፤ምሳ18፥5፤ሕዝ13፥19
28፥22 ቍ20
28፥23 ምሳ27፥5-6
28፥24 ምሳ18፥9፤ 19፥26
28፥25 ምሳ14፥17፤29፥25
28፥26 መዝ4፥5፤ 1ቆሮ3፥18
28፥27 ዘዳ24፥19፤ መዝ109፥17፤ምሳ22፥9
28፥28 ቍ12፤ኢዮ 20፥19
29፥1 ዘፀ32፥9፤ዘዳ 9፥27፤2ዜና36፥16፤ምሳ6፥15፤ኤር19፥15፤36፥31፤ዕን32፥7
29፥2 2ነገ11፥20፤ ምሳ28፥12፤30፥22፤ መክ10፥6
29፥3 ምሳ5፥8-10፤ 10፥1፤23፥15-16፤ ሉቃ5፥11-32
29፥4 ቍ14፤ምሳ 8፥15-16
29፥5 ኢዮ32፥21፤ ምሳ26፥28
29፥6 ኢዮ5፥13፤ ምሳ26፥27፤መክ9፥12
29፥7 ምሳ31፥8-9
29፥8 ምሳ11፥11፤16፥14
29፥10 ቍ27፤ 1ዮሐ3፥12

29 ከብዙ ተግሣጽ ጸኋላ ዐንገቱን
የሚያደነድን ሰው፣
በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም::
2 ጻድቃን ሥልጣን ሲይዙ ሕዝብ ሐሤት
ያደርጋል፤
ክፉዎች ሲገዙ ግን ሕዝብ ያቃስታል::
3 ጥበብን የሚወድ ሰው አባቱን ደስ
ያሰኛል፤
የአመንዝራዎች ወዳጅ ግን ሀብቱን
ያባክናል::
4 ፍትሕን በማስፈን ንጉሥ አገርን
ያረጋጋል፤
ጉቦ ለማግኘት የሚጎመጅ ግን
ያፈራርሳታል::
5 ባልንጀራውን የሚሸነግል፣
ለገዛ እግሩ መረብ ይዘረጋል::
6 ክፉ ሰው በራሱ ኀጢአት ይጠመዳል፤
ጻድቅ ግን ይዘምራል፤ ደስም ይለዋል::
7 ጻድቅ ለድኾች ፍትሕ ይጨነቃል፤
ክፉ ሰው ግን ደንታ የለውም::
8 ተሳዳቢዎች ከተማን ያውካሉ፤
ጠቢባን ግን ቍጣን ያበርዳሉ::
9 ጠቢብ ሰው ከተላላ ጋር ወደ ሸንጎ
ቢሄድ፣
ተላላ ይቈጣል፤ ያፌዛል፤ ሰላምም
አይኖርም::
10 ደም የተጠሙ ሰዎች ሐቀኛን ሰው
ይጠላሉ፤
ቅን የሆነውንም ለመግደል ይሻሉ::

28፥19 *ከንቱ ተስፋን ይዞ የሚኳዝ፤* ገንዘብን እንዲሁ ለማግኘት የሚያልም ማለት ነው::

28፥20 *እጅግ ይባረካል፤* ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሣ (3፥13-18፤ 10፥6፤ ዘፍ 49፥26፤ ዘዳ33፥16 ይመ):: *ሀብት ለማግኘት የሚባደፍ ... ከቅጣት አያመልጥም፤* በ20፥21፤ በ23፥4 ላይ ካለው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ጋር ያነጻጽሩ፤ ማብ ይመ::

28፥21 *አድልዎ ማድረግ መልካም አይደለም፤* 18፥5 እና ማብ፤ እንዲሁም 24፥23 ይመ:: *ለቍራሽ እንጀራ ሲል በደል ይፈጽማል፤* አነስተኛውን ጉቦ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ከሕዝ13፥19 ጋር ያነጻጽሩ)::

28፥22 *ስስታም፤* ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል (በ29፥21፤ በ23፥4 ላይ ካለው ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ጋር ያነጻጽሩ):: *ድኽነት እንደሚጠብቀውም፤* ሀብታም የሚሆነው የሚለግስ ሰው ነውና (የ11፥25 ማብ ይመ)::

28፥23 *የሚገሥጽ፤* ገላ2፥14 ይመ፤ ከ15፥31፤ 25፥12 ጋር ያነጻጽሩ:: *ሸንጋይ፤* ከ16፥13፤ 26፥28፤ 29፥5 ጋር ያነጻጽሩ::

28፥24 *ከአባት ከእናቱ ሰርቆ፤* የ19፥26 ማብ ይመ፤ ከማቴ 15፥4-6፤ ከማር7፥10-12 ጋር ያነጻጽሩ::

28፥25 *ጠብን ያነሣሣል፤* የ6፥14 ማብ ይመ:: *ይባረካል፤* ቸር ሰው (11፥25) እንዲሁም ትጉህ ሰው (13፥4) እንደሚበለጽግ ሁሉ ማለት ነው::

28፥26 *በጥበብ የሚመላለስ፤* በ29፥25 ላይ "በእግዚአብሔር የሚተማመን" ከሚለው ጋር አንድ ነው፤ ከ3፥5 ጋር ያነጻጽሩ::

28፥27 *ለድኾች የሚሰጥ፤* የ14፥21 ማብ ይመ:: *አይቸገርም፤* ልግስና ወደ በረከት ይመራል (11፥24፤28፥22 እና ማብ፤ 14፥21፤ 19፥17 ይመ):: *አይቶአቸው እንዳላየ የሚሆን፤* 21፥13 ይመ::

28፥28 *ሕዝብ ይሸሸጋል፤* ቍ12 ማብ ይመ:: *ጻድቃን ይበዛሉ፤* 11፥10፤ 29፥2 ይመ::

29፥1 *ከብዙ ተግሣጽ በኋላ ዐንገቱን የሚያደነድን፤* የዔሊ ልጆች የሞቱት ልባቸውን በማደንደናቸው ነው (1ሳሙ 2፥24 ይመ፤ ከዘዳ 9፥6፡13 ጋር ያነጻጽሩ):: *በድንገት ይጠፋል፤ መዳኛም የለውም፤* ከ6፥15 ጋር አንድ ነው:: በ1፥22-27 ላይ የተመለከተውን የፌዘኞችን ዕጣ ፈንታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ::

29፥2 *ጻድቃን ሥልጣን ሲይዙ ሕዝብ ሐሤት ያደርጋል፤* 11፥10 እና ማብ ይመ:: *ክፉዎች ሲገዙ ግን ሕዝብ ያቃስታል፤* 28፥12 እና ማብ፤ እንዲሁም መሳ 2፥18 ይመ:: እስራኤላውያን በግብፅ ምድር ሲማቀቁ ኖረዋል (ከዘፀ 2፥23-24)::

29፥3 *ጥበብን የሚወድ ሰው አባቱን ደስ ያሰኛል፤* 10፥1 እና ማብ ይመ:: *የአመንዝራዎች ወዳጅ ግን ሀብቱን ያባክናል፤* 5፥10፤ 6፥26 እና ማብ ይመ::

29፥4 *ፍትሕን በማስፈን ንጉሥ አገርን ያረጋጋል፤* የ16፥12 ማብ ይመ:: *ጉቦ፤* የ17፥8 ማብ ይመ::

29፥6 *በራሱ ኀጢአት ይጠመዳል፤* 1፥18 እና ማብ፤ እንዲሁም 22፥5 ይመ::

29፥7 *ለድኾች ፍትሕ ይጨነቃል፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ጽድቅ የሚመዘነው አንድም ለድኾችና ለችግረኞች በማሰብ የሚደረገው ነገር ነበር (ዘዳ 24፥11-15):: ኢዮብ ለድኾች የሚያስብ ሰው ነበር (ኢዮ 29፥16)፤ ከቍ 14፤ 19፥17፤ 22፥22 ጋር ያነጻጽሩ::

29፥8 *ተሳዳቢዎች ከተማን ያውካሉ፤* የ6፥14፤ 11፥11 ማብ፤ እንዲሁም 26፥21 ይመ:: *ተሳዳቢዎች፤* 1፥22 እና ማብ ይመ:: *ጠቢባን ግን ቍጣን ያበርዳሉ፤* ያዕ 3፥17-18 ይመ::

29፥9 *ተላላ ይቈጣል፤ ያፌዛል፤* እንደ ቍጡ ድብ (17፥12) ወይም እንደሚናወጥ ባሕር (ኢሳ 57፥20-21) ማለት ነው::

29፥10 *ደም የተጠሙ ሰዎች ሐቀኛን ሰው ይጠላሉ፤* የተንኰል ዕቅዳቸው በ1፥11-16 ላይ ተገልጾአል፤ ከመዝ 5፥6 ያነጻጽሩ::

[11]ተላላ ሰው ቍጣውን ያለ ገደብ
ይለቀዋል፤
ጠቢብ ሰው ግን ራሱን ይቈጣጠራል።
[12]ገዥ የሐሰት ወሬ የሚሰማ ከሆነ፣
ሹማምንቱ ሁሉ ክፉዎች ይሆናሉ።
[13]ድኻውና ጨቋኙ የጋራ ነገር አላቸው፤
እግዚአብሔር ለሁለቱም የዐይን ብርሃንን
ሰጥቶአቸዋል።
[14]ንጉሥ ለድኻ ትክክለኛ ፍርድ ቢሰጥ፣
ዙፋኑ ዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
[15]የተግሣጽ በትር ጥበብን ታጐናጽፋለች፤
መረን የተለቀቀ ልጅ ግን እናቱን
ያሳፍራል።
[16]ክፉዎች ሥልጣን ሲይዙ ኀጢአት
ይበዛል፤
ጻድቃን ግን የእነርሱን ውድቀት ያያሉ።
[17]ልጅህን ቅጣው፤ ሰላም ይሰጥሃል፤
ነፍስህንም ደስ ያሰኛታል።
[18]ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፤
ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው።
[19]አገልጋይ በቃል ብቻ ሊታረም
አይችልም፤
ቢያስተውለውም እንኳ በጀ አይልም።
[20]በችኰላ የሚናገርን ሰው ታያለህን?
ከእርሱ ይልቅ ተላላ ተስፋ አለው።
[21]ሰው አገልጋዩን ከልጅነቱ ጀምሮ
ቢያቀማጥል፣
የኋላ ኋላ ሐዘን[*] ያገኘዋል።
[22]ቍጡ ሰው ጠብን ይጭራል፤
ግልፍተኛም ብዙ ኀጢአት ይሠራል።

29፥11 ኢዮ15፥13፤ምሳ12፥16
29፥12 2ነገ21፥9፤ኢዮ34፥30
29፥13 ምሳ22፥2፤ማቴ5፥45
29፥14 ቍ4፤መዝ72፥1-5፤ምሳ16፥12
29፥15 ቍ17፤ምሳ13፥24
29፥16 መዝ91፥8፤92፥11
29፥17 ቍ15
29፥18 መዝ1፥1-2፤19፥11፤119፥1-2
29፥20 ምሳ19፥2፤26፥12
29፥22 ምሳ14፥17
29፥23 አስ5፥12፤ምሳ11፥2፤15፥33፤16፥18
29፥24 ዘሌ5፥1
29፥25 1ሳሙ15፥24፤ምሳ16፥20፤28፥25
29፥26 ምሳ16፥33፤19፥6
29፥27 ቍ10
30፥1 ምሳ22፥17
30፥3 ምሳ9፥10
30፥4 ዘፍ1፥2፤ዘዳ30፥12፤ኢዮ26፥8፤መዝ24፥1-2፤ምሳ8፥22-31፤ኢሳ40፥12፤ዮሐ3፥13፤ኤፌ4፥7-10፤ራእ19፥12

[23]ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤
ትሑት መንፈስ ያለው ግን ክብርን
ይጐናጸፋል።
[24]የሌባ ግብረ አበር የገዛ ራሱ ጠላት ነው፤
የመሐላውን ርግማን እየሰማ ጭጭ
ይላል።
[25]ሰውን መፍራት ወጥመድ ነው፤
በእግዚአብሔር የሚታመን ግን በሰላም
ይኖራል።
[26]ብዙዎች በገዥ ፊት ተደማጭነት
ማግኘት ይሻሉ፤
ሰው ፍትሕ የሚያገኘው ግን ከእግዚ
አብሔር ዘንድ ነው።
[27]ጻድቃን አታላዮችን ይጸየፋሉ፤
ክፉዎችም ቅኖችን ይጠላሉ።

## አጉር የተናገራቸው ምሳሌዎች

30 የያቄ ልጅ የአጉር ቃል ይህ ነው፤[°]
ይህ ሰው ለኢቲኤል፣
ለኢቲኤልና ለኡካል ተናገረ፤[*]
[2]"እኔ ከሰው ሁሉ ይልቅ ጅል ነኝ፤
ሰው ያለው ማስተዋል የለኝም።
[3]ጥበብን አልተማርሁም፤
ስለ ቅዱሱም ዕውቀት የለኝም።
[4]ወደ ሰማይ የወጣ፣ የወረደስ ማነው?
ነፋስን በእጁ ሰብስቦ የያዘ ማነው?
ውሆችንስ በመጐናጸፊያው የጠቀለለ
ማነው?

*21 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጓሜ በእርግጠኝነት አይታወቅም
°1 ወይም የማሳው ያቄ
*1 የማስሬቲክ ጽሑፍ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የዕብራይስጡ ግን ተናገረ፤ "አቤቱ እግዚአብሔር፤ እኔ ደክሜአለሁ/ አቤቱ እግዚአብሔር፤ እኔ ደክሜአለሁ፤ እንደ ሞተ ሰውም ሆኛለሁ" ይላል።

29፥11 *ቍጣውን ያለ ገደብ ይለቀዋል፤* ቍ9፤ 14፥16-17 ይመ። *ራሱን ይቈጣጠራል፤* የ16፥32 ማብ ይመ።

*29፥13፤* እግዚአብሔር ለጨቋኙና ለድኻው ሕይወት የሚያስፈልጉትን ነገሮች እኩል ይሰጣል (ማቴ5፥45 ይመ)።

*29፥14፤* የ16፥12፤ እንዲሁም ቍ4፤ ኢሳ9፥7 ይመ።

29፥15 *የተግሣጽ በትር፤* የ13፥2 ማብ ይመ።

29፥16 *ክፉዎች ሥልጣን ሲይዙ፤* ቍ2፤ 11፥11፤ 28፥12፡28 ይመ። *ጻድቃን ... የእነርሱን ውድቀት ያያሉ፤* 10፥25 እና ማብ፤ 14፥11፤ 21፥12 ይመ።

29፥17 *ልጅህን ቅጣው፤* አስተምረው፤ አሠልጥነው ማለት ነው (13፥24 እና ማብ፤ 22፥6 ይመ)።

29፥18 *ራእይ፤* ትንቢታዊ መገለጥ በነቢይ በኩል ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ነው (1ሳሙ3፥1፤ ኢሳ1፥1፤ አሞ 8፥11-12 ይመ)። *ሕዝብ መረን ይሆናል፤* ሙሴ በሲና ተራራ ላይ በነበረ ጊዜ፣ እስራኤላውያን ያደረጉትን ኀጢአት በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ዘፀ32፥25 እና ማብ ይመ)። *ሕግን የሚጠብቅ ... የተባረከ ነው፤* 28፥4 እና ማብ እንዲሁም 8፥32፤ 28፥14 ይመ።

29፥19 *በቃል ብቻ ሊታረም አይችልም፤* አገልጋዮችም እንደ ልጆች (ቍ 15፡17) መቀጣት አለባቸው (የ22፥6 ማብ ይመ)።

29፥20 *በችኰላ የሚናገርን፤* 10፥19፤ 17፥27-28፤ ያዕ 1፥19 ይመ። *ከእርሱ ይልቅ ተላላ ተስፋ አለው፤* ከ26፥12 ጋር አንድ ነው።

29፥21 *አገልጋዩን,... ቢያቀማጥል፤* ቍ19 ይመ።

29፥22 *ቍጡ ሰው ጠብን ይጭራል፤* የ6፥14 ማብ፤ እንዲሁም 15፥18 ይመ።

*29፥23፤* 15፥33 እና ማብ፤ እንዲሁም 18፥12 ይመ።

29፥24 *የመሐላውን ርግማን፤* ከዘሌ5፥1 ጋር ያነጻጽሩ።

29፥25 *ሰውን መፍራት፤* ከ1ሳሙ 15፥24፤ ከኢሳ 51፥12፤ ከዮሐ 12፥42-43 ጋር ያነጻጽሩ። *በእግዚአብሔር የሚታመን ግን በሰላም ይኖራል፤* 18፥10 እና ማብ ይመ። ከ3፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ።

29፥26 *ብዙዎች ... ተደማጭነት ማግኘት ይሻሉ፤* 1ነገ 10፥24 ይመ። *ሰው ፍትሕ የሚያገኘው ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤* እግዚአብሔር የንጉሥን አሠራር ይቈጣጠራል (የ21፥1 ማብ ይመ)፤ ለድኻውና ለጻድቁም ጠበቃ ሆኖ ይቆማል (ከኢዮ 36፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

*30፥1-33፤* የመጽሐፈ ምሳሌ ተጨማሪ በመሆን ከተጻፉት ሁለት የመጨረሻ ምዕራፎች ይህ የመጀመሪያው ነው።

30፥1 *የያቄ ልጅ የአጉር፤* እንደ ኤታንና እንደ ሄማን እስ ተዋይ ሳይሆን አይቀርም (1ነገ4፥31)። *ቃል፤* እዚህ ላይ 'ቃል' የተባለው ንግር ወይም ትንቢት ነው (የኢሳ13፥1 ማብ ይመ)። "ማሳ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የቦታ ስም ከሆነ አጉር ከእስማኤላውያን ጋር ሊዛመድ ይችላል (ከዘፍ25፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ)። *ኢቲኤል ... ኡካል፤* የአጉር ተማሪዎች ሳይሆኑ አይቀርም።

30፥2 *እኔ ከሰው ሁሉ ይልቅ ጅል ነኝ፤* ጳውሎስም ስለ ራሱ፣ "ከኀጢአተኞች ዋና እኔ ነኝ" ብሎአል (1ጢሞ1፥16፤ ከ1ቆሮ8፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

30፥3 *ስለ ቅዱሱም ዕውቀት፤* የ2፥5 ማብ ይመ። ይህ ሐረግ ከዚህ ሌላ በመጽሐፈ ምሳሌ የሚገኘው በ9፥10 ላይ ብቻ ነው።

*30፥4፤* እግዚአብሔር በፈጣሪነቱ ያለውን ኀያልነት ለማመልከት፣ ይህን መሳይ መልስ ዐዘል ጥያቄዎች የተጠቀሱት በኢዮ 38፥4-11፤ በኢሳ40፥12 ላይ ነው (ከዮሐ3፥13፤ ራእ19፥12፤ ከሮሜ10፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)። *ነፋስን ... ሰብስቦ፤* ከመዝ135፥7 ጋር ያነጻጽሩ። *ውሆችንስ በመጐናጸፊያው የጠቀለለ፤* ኢዮ26፥8፤

የምድርን ዳርቻዎች ሁሉ የወሰነ ማነው?
ስሙ ማን ነው? የልጁስ ስም ማን ይባላል?
የምታውቅ ከሆነ እስቲ ንገረኝ!

[5]“የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንከን የለበትም፤
እርሱ ለሚታመኑበት ሁሉ ጋሻቸው
ነው።
[6]በእርሱ ቃል ላይ አንዳች አትጨምር፤
አለዚያ ይዘልፍሃል፤ ሐሰተኛም
ያደርግሃል።

[7]“እግዚአብሔር ሆይ፤ ሁለት ነገር
እለምንሃለሁ፤
እነዚህንም ከመሞቴ በፊት አትከልክለኝ፤
[8]ሐሰትንና ሐሰት መናገርን ከእኔ
አርቅልኝ፤
ድኽነትንም ሆነ ብልጽግናን አትስጠኝ፤
ብቻ የዕለት እንጀራዬን ስጠኝ።
[9]ያለዚያ ግን ያለ ልክ እጠግብና
እክድሃለሁ፤
‘እግዚአብሔር ማን ነው?’ እላለሁ፤
ወይም ድኻ እሆንና እሰርቃለሁ፤
የአምላኬንም ስም አሰድባለሁ።
[10]“አገልጋይን በጌታው ፊት በክፉ
አታንሣው፤
አለዚያ ይረግምሃና ጕዳት ያገኝሃል።

[11]“አባቱን የሚረግም፣
እናቱን የማይባርክ ትውልድ አለ፤
[12]ራሳቸውን ንጹሓን አድርገው የሚቈጥሩ፣
ሆኖም ከርኵሰታቸው ያልነጹ አሉ፤
[13]ዐይናቸው ትዕቢተኛ የሆነ፣
አስተያያቸው ንቀት የሞላበት፣
[14]ድኾችን ከምድር፣
ችግረኞችንም ከሰው ዘር መካከል

30፥5 ዘዳ15፥11 መዝ12፥6፤18፥30
30፥6 ዘዳ4፥2
30፥8 ማቴ6፥11
30፥9 ዘዳ6፥12፤ 8፥10-14፤ኢሱ24፥27 ፤ኢሳ1፥4፤59፥13፤ ሆሴ13፥6
30፥11 ምሳ20፥20
30፥12 ምሳ16፥2፤ ኤር2፥23፡25
30፥13 2ሳሙ22፥28 ፤ኢዮ41፥34
30፥14 ኢዮ4፥11፤ 19፥22፤24፥9፤መዝ3፥ 7፤57፥4፤አሞ8፥4፤ ሚክ2፥2
30፥15 ምሳ27፥20
30፥16 ኢሳ5፥14፤ 14፥9፡11፤ዕን2፥5
30፥17 ዘዳ21፥18- 21፤ኢዮ15፥23
30፥20 ምሳ5፥6
30፥22 ምሳ19፥10

ለማጥፋት፣
ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣
መንጋጋቸውም ካራ የሆነ አሉ።

[15]“አልቅት ሁለት ሴት ልጆች አሉት፤
‘ስጡን! ስጡን!’ እያሉ ይጮኻሉ፤
“ፈጽሞ የማይጠግቡ ሦስት ነገሮች አሉ፤
‘በቃኝን’ ከቶ የማያውቁ አራት ናቸው፤
[16]እነርሱም መቃብር፣* መካን ማኅፀን፣
ውሃ ጠጥታ የማትረካ ምድር፣
‘በቃኝ’ የማይል እሳት ናቸው።

[17]“በአባት ላይ የምታፌዝ ዐይን፣
የእናትንም ትእዛዝ የምትንቅ፣
የሸለቆ ቍራዎች ይጐጠጕጧታል፤
ጆፌ አሞሮችም ይበሏታል።

[18]“እጅግ የሚያስደንቁኝ ሦስት ነገሮች
አሉ፤
የማላስተውላቸውም አራት ናቸው፤
[19]የንስር መንገድ በሰማይ፣
የእባብ መንገድ በቋጥኝ፣
የመርከብ መንገድ በባሕር፣
የሰውም መንገድ ከሴት ልጅ ጋር
ናቸው።

[20]“የአመንዝራዪቱ መንገድ ይህ ነው፤
በልታ አፏን በማበስ፣
‘ምንም የሠራሁት ጥፋት የለም’
ትላለች።
[21]“ምድር በሦስት ነገር ትናወጣለች፤
እንዲያውም መሸከም የማትችላቸው
አራት ነገሮች ናቸው፤
[22]ባሪያ ሲነግሥ፣

*16 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል

38፥8-9 ይመ። *የምታውቅ ከሆነ እስቲ ንገረኝ!* ይህን የሚመስል ከባድ ጥያቄ እግዚአብሔር ኢዮብን ጠይቆት ነበር (ኢዮ38፥4)።

*30፥5፤* ከመዝ18፥30 ጋር ተቀራራቢ ነው። *ጋሻቸው፤* የ2፥7 ማብ ይመ። *ለሚታመኑበት፤* 14፥32፤ 18፥10 ይመ።

30፥7 *ሁለት ነገር፤* የአጕር አባባል ተለይቶ የሚታወቀው ነገሮችን በቅደም ተከተል በመደርደሩ ነው (15፥18፡21፡24፡29 ይመ)።

30፥8 *የዕለት እንጀራዬን፤* ከኢዮ 23፥12 ከጌታ ጸሎት (ማቴ6፥11) ጋር ያነጻጽሩ።

30፥9 *ያለ ልክ እጠግብና እክድሃለሁ፤* እስራኤላውያን ምርታቸው ሲትረፈረፍ መንጋቸው ሲበዛ እግዚአብሔርን እንደ ሚረሱት ሙሴ አስቀድሞ ተናግሮአል (ዘዳ8፥12-17፤ 31፥20)። *እግዚአብሔር ማን ነው?* ወይም ለምን አገለግለዋለሁ? (ኢዮ 21፥14-16 ይመ) እንደ ማለት ነው። *ድኻ እሆንና እሰርቃለሁ፤* ከ6፥30 ጋር ያነጻጽሩ።

30፥10 *ጕዳት ያገኝሃል፤* ነገሩ ማሳበቅ በመሆኑ፣ የአገ ልጋዩ ርግማን ሊደርስ ይችላል (ከ26፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ስለዚህ አንድን አገልጋይ እንደ ዝቅተኛ ተመልክተህ እበልጠዋለሁ ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም።

*30፥11-14፤* አራት ዐይነት ክፉ ሰዎችን ይገልጻል። እነዚ ህም ተራጋሚዎች፣ ግብዞች፣ ትዕቢተኞችና ስስታሞች ናቸው።

30፥11 *አባቱን የሚረግም፤* በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው (ዘጸ21፥17፤ ዘሌ20፥9 ይመ፤ ከቍ 17 ጋር ያነጻጽሩ)።

30፥12 *ራሳቸውን ንጹሓን አድርገው የሚቈጥሩ፤* እንደ ፈሪሳውያን ማለት ነው (ሉቃ18፥11 ይመ፤ ከኢሳ65፥5 ጋር ያነጻ ጽሩ)።

30፥13 *ዐይናቸው ትዕቢተኛ የሆነ፤* የ6፥17 ማብ፤ እንዲ ሁም ኢሳ3፥16 ይመ።

30፥14 *ጥርሳቸው ሰይፍ የሆነ፣ መንጋጋቸው ካራ የሆነ፤* ክፉ ሰዎች ያገኙትን እንደሚውጡ የተራቡ እንስሳት ናቸው (ኢዮ29፥17 ይመ)። *ድኾችን ... ችግረኞችንም ... ለማጥፋት፤* ከመዝ 14፥4፤ ከሚክ 3፥2-3 ጋር ያነጻጽሩ።

30፥15፡18፡21፡29 *ሦስት ... አራት፤* የ6፥16 ማብ ይመ።

30፥16 *መቃብር፤* ከቶ አይጠግብም (ኢሳ5፥14፤ ዕን2፥5)። *መካን ማሕፀን፤* በጥንታዊት እስራኤል ልጅ ያልወለደች ሴት የተናቀችና ሐዘንተኛ ነበረች (ከዘፍ16፥2፤ 30፥1፤ ከሩት1፥11-13፡ 20-21፤ ከ1ሳሙ 1፥6፡10-11፤ ከ2ነገ 4፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

30፥17 *ዐይን፤* የምትታበይና የምትንቅ ተብላለች (ቍ13 ይመ)። *በአባት ላይ የምታፌዝ፣ የእናትንም ...፤* ቍ11 እና ማብ፤ እንዲሁም 15፥20 ይመ። *ቍራዎች ይጐጠጕጧታል፤ ጆፌ አሞሮችም ...፤* ዐይንን ማጣት ከባድ ርግማን ነበር (የሶምሶን ታሪክ በመሳ16፥21 ላይ ይመ)። በመሠረቱ አሞሮች የሚበሉት ጥንብ ስለ ሆነ፣ (ኤር16፥4፤ ማቴ24፥28) የተረገመ ልጅ ሬሳ ሳይቀበር ሜዳ ላይ ይጣላል ለማለት ሳይሆን አልቀረም።

*30፥18-19፤* “አራቱን መንገዶች” የሚያመሳስላቸው አቅጣ ጫቸው ዱካ የሌለው መሆኑ ነው።

30፥19 *የንስር መንገድ፤* በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ ላይ ይወጣል፤ ወደታችም ሽው ብሎ ይወርዳል። ግርማ ባለው ሁኔታ ወደ ላይ ይወጣል፤ ይወነጨፋልም (ከኢሳ39፥27፤ ከኤር 48፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *የሰውም መንገድ ከሴት ልጅ ጋር፤* አንድ ወንድ የአንዲትን ሴት ልብ ለማግኘትና አሳቡን ከግቡ ለማድረስ የሚያ ደርገውን ጥረት ሳያመለክት አይቀርም።

30፥20 *የአመንዝራዪቱ፤* 2፥16 እና ማብ ይመ። *በልታ አፏን በማበስ፤* በ9፥17 ላይ በወንድና በሴት መካከል ፍቅርን የመግለጥ ጕዳይ ምግብ ከመመገብ ጋር ተነጻጽሮአል (የዚያኑ ማብ ይመ፤ እንዲሁም 7፥18 እና ማብ ይመ)።

30፥22 *ባሪያ ሲነግሥ፤* የ19፥10 ማብ ይመ።

ስነፍ እንጀራ ሲጠግብ፣
23የተጠላች ሴት ባል ስታገባ፣
ሴት ባሪያ በእመቤቷ እግር ስትተካ::

24"በምድር ላይ አራት ነገሮች ትንንሽ
ናቸው፤
ሆኖም እጅግ ጠቢባን ናቸው፤
25ጕንዳኖች ደካማ ፍጡራን ናቸው፤
ሆኖም ምግባቸውን በበጋ ያከማቻሉ::
26ሽኮኮዎች ዐቅመ ደካማ ናቸው፤
ሆኖም መኖሪያቸውን በቋጥኞች መካከል
ይሠራሉ፤
27አንበጦች ንጉሥ የላቸውም፤
ሆኖም ቅደም ተከተል ይዘው ይጓዛሉ፤
28እንሽላሊት በእጅ ትያዛለች፤
ሆኖም በቤተ መንግሥት ትገኛለች::

29"አረማመዳቸው ግርማዊ የሆነ ሦስት
ነገሮች አሉ፤
እንዲያውም በሞገስ የሚጎማለሉ አራት
ናቸው፤
30ከአራዊት መካከል ኀይለኛ የሆነው፣
ከምንም ነገር ፊት ግንባሩን የማያጥፈው
አንበሳ፤
31ጕርደድ ጕርደድ የሚል አውራ ዶሮ፣
አውራ ፍየል፣
እንዲሁም በሰራዊቱ የታጀበ ንጉሥ
ናቸው::[f]

32ተላላ ሆነህ ራስህን ከፍ ከፍ ካደረግህ፣
ወይም ክፉ ነገር ካቀድህ፣
እጅህን በአፍህ ላይ አድርግ::
33ወተት ሲናጥ ቅቤ እንደሚወጣው፣
አፍንጫን ሲያሹት እንደሚደማ፣
ቍጣን ማነሣሣትም ጥልን ይፈጥራል::

## ንጉሥ ልሙኤል የተናገራቸው ምሳሌዎች

31 1ንጉሥ ልሙኤልን እናቱ
ያስተማረችው ቃል ይህ ነው፤

2"ልጄ ሆይ፤ የማሕፀኔ ልጅ ሆይ፤
የስእለቴ ልጅ ሆይ፤[g]
3ጕልበትህን በሴት አትጨርስ፤
ብርታትህንም ነገሥታትን ለሚያጠፉ
አታውል::

4"ልሙኤል ሆይ፤ ነገሥታት ይህን ማድረግ
የለባቸውም፤
ነገሥታት የወይን ጠጅ ሊጠጡ፣
ገዦችም የሚያሰክር መጠጥ
ሊያስጐመጃቸው አይገባም፤
5አለዚያ ጠጥተው የሕጉን ድንጋጌ
ይረሳሉ፤
የተጨቈኑትን ሁሉ መብት ይገፋሉ::
6ለሚጠፉት የሚያሰክር መጠጥ፣
በሥቃይ ላሉትም የወይን ጠጅ
ስጧቸው፤
7ጠጥተው ድኽነታቸውን ይርሱ፤
ችግራቸውንም ከእንግዲህ አያስቡ::

8"ስለ ራሳቸው መናገር ለማይችሉት፣
ለችግረኞችም ሁሉ መብት ተሟገት::
9ተናገር፤ በቅንነትም ፍረድ፤
የምስኪኖችንና የድኾችን መብት
አስከብር::"

## መዝጊያ ክፍል፤ ጠባየ መልካም ሚስት

10ጠባየ መልካምን ሚስት ማን ያገኛታል?[h]

[f]31 *ወይም ከተቃውሞ የተጠበቀ ንጉሥ*
[g]2 *ወይም የጸሎቴ መልስ ሆይ*
[h]10 ከ10-31 ያለው እያንዳንዱ ቍጥር የሚጀምረው በዕብራይስጡ ሆህያት ቅደም ተከተል መሠረት ነው::

፤29፥2
30፥25 ምሳ6፥6-8
30፥26 መዝ104፥18
30፥27 ዘፀ10፥4
30፥32 ኢዮ29፥9
31፥1 ምሳ22፥17
31፥2 መሳ11፥30
31፥3 ዘዳ17፥17፤ 1ነገ11፥3፤ምሳ5፥1-14
31፥4 ምሳ20፥1፤ መክ10፥16-17፤ ኢሳ5፥22
31፥5 1ነገ16፥9፤ ምሳ16፥12
31፥6 ዘፍ14፥18
31፥7 አስ1፥10
31፥8 1ሳሙ19፥4
31፥9 ምሳ24፥23፤29፥7
31፥10 ሩት3፥11፤ ምሳ8፥35፤18፥22

30፥23 *የተጠላች ሴት ባል ስታገባ፤* ከመልክ ጥፉነቷ ወይም ከሌላ ሁኔታ የተነሣ ባል ዐጥታ የኖረች ሴት በምታገባበት ጊዜ፤ ከልክ ያለፈ ኵራት ታሳያለች:: *ሴት ባሪያ በእመቤቷ እግር ስትተካ፤* እመቤቷ መካን ሆና እርሷ ግን ልጅ መውለድ በመቻሏ ወይም በሌላ ምክንያት ሊሆን ይችላል (በዘፍ16፥1-6 ላይ ያለውን የአጋርና የሣራን ሁኔታ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)::

30፥26 *በቋጥኞች መካከል፤* ሽኮኮዎች ይሸሸጉበታል (መዝ 104፥18 ይመ)::

30፥27 *አንበጦች ንጉሥ የላቸውም፤* ከ6፥7 ጋር ያነጻጽሩ:: *ቅደም ተከተል ይዘው ይጓዛሉ፤* በኢዩ2፥3-9 ላይ አንበጦች በኀያል ሰራዊት ተመስለዋል::

30፥28 *በቤተ መንግሥት ትገኛለች፤* እንሽላሊት በቀላሉ ግንብ ላይ መውጣት ትችላለች::

30፥30 *ከአራዊት መካከል ኀይለኛ የሆነው ... አንበሳ፤* 2ሳሙ1፥23፤ ሚክ5፥8 ይመ::

30፥31 *አውራ ፍየል፤* ፍየሎች የበግ መንጋን በመምራት አገልግሎት ይሰጡ ነበር (ኤር50፥8፤ ዳን8፥5 ይመ)::

30፥32 *ራስህን ከፍ ከፍ ካደረግህ፤* በ8፥13፤ በ11፥2፤ በ16፥18 ላይ ትዕቢት ተወግዟል:: *ክፉ ነገር ካቀድህ፤* ከ6፥14፤ 16፥27 ጋር ያነጻጽሩ:: *እጅህን በአፍህ ላይ አድርግ፤* ከማሤር ተቈጠብ ማለት ነው (ከኢዮ21፥5፤ 40፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

30፥33 *ቍጣን ማነሣሣትም ጥልን ይፈጥራል፤* የ6፥14፤ የ15፥1 ማብ እንዲሁም 29፥22 ይመ)::

*31፥1-9፤* ይህ አጭር ክፍል እስራኤላዊ መሠረት ያለው አይመስልም፤ ንጉሥ ልሙኤልም እዚህ ላይ ከመጠቀሱ በስተቀር በሌላ ቦታ አይታወቅም::

31፥1 *ቃል፤* የ30፥1 ማብ ይመ:: *እናቱ፤* ይህ ምዕራፍ በሙሉ ጥበበኛ ሴቶች በኑሮ ውስጥ ያላቸውን ሚናና አስፈላጊነት ይገልጻል:: የንጉሥ እናት በምታቀርበው አሳብ ተሰሚነት ነበራት (1ነገ1፥11-13፤ 15፥13 ይመ)::

31፥2 *የስእለቴ ልጅ፤* ሀና ልጅ ለማግኘት በጸለየች ጊዜ ተስላ ነበር (1ሳሙ 1፥11):: *ስእለት፤* 20፥25 እና ማብ ይመ::

31፥3 *ጕልበትህን በሴት፤* ብዙ ሴቶችን ቅምጥ ማድረግና ዝሙት መፈጸም ተገቢ ላለመሆኑ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው (5፥9-11 እና ማብ፤ 1ነገ11፥1፤ ነህ13፥26 ይመ)::

31፥4 *ነገሥታት የወይን ጠጅ ሊጠጡ ... አይገባም፤* መሪዎች ሰካራም ለሆኑባት ምድር ወዮላት (መክ 10፥16-17፤ 20፥1 እና ማብ፤ ሆሴ7፥5 ይመ)::

31፥5 *የተጨቈኑትን ሁሉ መብት ይገፋሉ፤* 30፥14 እና ማብ፤ እንዲሁም 17፥15፤ ኢሳ5፥23፤ 10፥2 ይመ::

31፥7 *ጠጥተው ... ይርሱ፤* በቍ5 ላይ "ጠጥተው ... ይረሳሉ" ከሚለው ጋር ያስተያዩ::

*31፥8-9፤* ንጉሥ የእግዚአብሔር ተወካይ ሆኖ፣ ድኾችንና ችግረኞችን ይጠብቃል:: (16፥10፤ መዝ 82፥3 ይመ፤ ከዘሌ 19፥15፤ ከኢዮ 29፥12-17፤ ከኢሳ 1፥17 ጋር ያነጻጽሩ)::

*31፥10-31፤* ይህ የመጽሐፉ መደምደሚያ ክፍል ነው፤ የግጥሙም አቀራረብ፣ የየስንኙ የመጀመሪያው ፊደል ቍልቍል ሲነበብ፣ የዕብራይስጡን የፊደል ተርታ ይዞ ነው:: ዓላማው "ጠባየ መልካም ሚስት" የተባለችውን (ቍ10) ማድነቅ ነው:: በመግቢያው ላይ እንደ ተገለጸው (1፥1-7) "እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት"ን (ቍ30፤ የ1፥7 ማብ ይመ)፣ ከሚገልጸው ጋር ይመሳሰላል:: እንደዚህ ዐይነቷ ሚስት የጥበብ ምሳሌ ናት:: እንደ ጥበብ፣ "ከቀይ እንቍ ትበልጣለች" (ቍ 10፤ 3:15፤ 8፥11)፤ የሚያገኛትም፣ "ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ያገኛል" (8፥35፤ 18፥22)::

31፥10 *ጠባየ መልካምን ሚስት፤* እንደ ሩት ያለች ሴት ማለት ነው (ሩት3፥11)፤ እርሷም "ለባሏ ዘውድ ናት" (12፥4)::

ከቀይ ዕንቍ እጅግ ትበልጣለች።
11ባሏ ሙሉ በሙሉ ይተማመንባታል፤
የሚጐድልበትም ነገር የለም።
12በሕይወት ዘመኗ ሁሉ፣
መልካም ታደርግለታለች እንጂ
አትጐዳውም።
13የበግ ጠጕርና የተልባ እግር መርጣ፣
ሥራ በሚወዱ እጆቿ ትፈትላቸዋለች።
14እንደ ንግድ መርከብ፣
ምግቧን ከሩቅ ትሰበስባለች።
15ገና ሳይነጋ ትነሣለች፤
ለቤተሰቧ ምግብ፣
ለሴት አገልጋዮቿም ድርሻቸውን
ትሰጣለች።
16ራሷ አስባ የዕርሻ መሬት ትገዛለች፤
በምታገኘውም ገንዘብ ወይን ትተክላለች።
17ብርታትን ታጥቃ ሥራዋን
ታከናውናለች፤
ክንዶቿም ለሥራ ብርቱ ናቸው።
18ሥራዋ ትርፋማ መሆኑን ታስተውላለች፤
በሌሊትም መብራቷ አይጠፋም።
19በእጇ እንዝርት ትይዛለች፤
በጣቶቿም ዘንጕን ታሾራለች።
20ክንዶቿን ለድኾች ትዘረጋለች፣
እጆቿንም ለችግረኞች ፈታ ታደርጋለች።
21በረዶ ቢጥል ለቤተ ሰዎቿ አትሠጋም፤
ሁሉም ቀይ ልብስ ለብሰዋልና።
22ለመኝታዋ የዐልጋ ልብስ ትሠራለች፤
ቀጭን በፍታና ሐምራዊ ልብስ ለብሳለች።
23ባሏ በአገር ሽማግሌዎች መካከል
በአደባባይ በተቀመጠ ጊዜ የተከበረ ነው።
24የበፍታ መጐናጸፊያዎችን ሠርታ
ትሸጣለች፤
ለነጋዴዎችም ድግ ታቀርባለች።
25ብርታትንና ሞገስን ተጐናጽፋለች፤
መጭውን ጊዜ በደስታ ትቀበላለች።
26በጥበብ ትናገራለች፤
በአንደበቷም ቀና ምክር አለ።
27የቤተ ሰዎቿን ጕዳይ በትጋት
ትከታተላለች፤
የስንፍና እንጀራ አትበላም።
28ልጆቿ ተነሥተው፤ ቡርክት ይሏታል፤
ባሏም እንዲሁ፤ ሲያመሰግናትም እንዲህ
ይላል፤
29"ብዙ ሴቶች መልካም አድርገዋል፤
አንቺ ግን ሁሉንም ትበልጫለሽ።"
30ቍንጅና አታላይ ነው፤ ውበትም
ይረግፋል፤
እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን
የተመሰገነች ናት።
31የሚገባትን ሽልማት ስጧት፤
ሥራዋም በየአደባባዩ ያስመስግናት።

31፥11 ዘፍ2፥18፤ምሳ12፥4
31፥13 1ጢሞ2፥9-10
31፥20 ዘዳ15፥11
31፥23 ዘፀ3፥16
31፥26 ምሳ10፥31
31፥31 ምሳ11፥16

31፥12 *መልካም ታደርግለታለች*፤ 18፥22፤ 19፥14 ይመ።

31፥13 *የተልባ እግር*፤ ቃጫው በፍታ ለመሥራት ያገለግል ነበር (ቍ19፥22፡24 ይመ፤ ከኢሳ19፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

31፥14 *እንደ ንግድ መርከብ*፤ ሥራ ለመሥራት ቍርጣ የተነሣች ሴት ናት (ቍ18 ይመ)።

31፥15 *ገና ሳይነጋ ትነሣለች*፤ የሰነፍ ሰው ተቃራኒ ናት (16፥9-10፤ 20፥13 ይመ)። *ለሴት አገልጋዮቿም ድርሻቸውን*፤ 27፥27፤ ሉቃ12፥42 ይመ።

31፥16 *ራሷ አስባ የዕርሻ መሬት ... ወይን ትተክላለች*፤ በወይን ዕርሻው ላይ ዐረም እንደ ሞላበት (24፥30-31) እንደ ሰነፍ ሰው ሳትሆን፣ ሁኔታዎችን በማጤን መሥራት የሚገባትን በወቅቱ ታከናውናለች።

31፥17 *ብርታትን ታጥቃ ሥራዋን ታከናውናለች*፤ 10፥4 እና ማብ ይመ።

31፥18 *ሥራዋ ትርፋማ መሆኑን*፤ እንደ ጥበብ፣ "ዋጋዋ ከቀይ እንቍ ይበልጣል" (ከቍ10፤ 3፥15፤ 8፥11)። ጥበብ "ከብር ይልቅ ትርፍ የምታመጣ" (3፥14) ናት።

31፥19 *እንዝርት ... ዘንጕን*፤ ጥጥ መፍተል የሴቶች ሙያ ነበር።

31፥20 *እጆቿንም ለችግረኞች ፈታ ታደርጋለች*፤ የ14፥21 ማብ እንዲሁም 22፥9፤ ኢዮ31፥16-20 ይመ።

31፥21 *ቀይ ልብስ ለብሰዋልና*፤ ከሱፍ የተሠራ ውድ ልብስ ሳይሆን አይቀርም (ከ2ሳሙ1፥24፤ ከራእ18፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

31፥22 *ቀጭን በፍታና*፤ ከመኳንንት አለባበስ ጋር የተየያያዘ ነው (የ7፥16 ማብና ዘፍ41፥42 ይመ)። *ሐምራዊ*፤ ከነገሥታት (መሳ8፥26፤ ማሕ3፥10) ወይም ከሀብታሞች አለባበስ ጋር የተያያዘ ነው (ሉቃ16፥19፤ ራእ18፥16)።

31፥24 *የበፍታ መጐናጸፊያዎችን*፤ መሳ14፥12-13፤ ኢሳ 3፥23 ይመ። *ለነጋዴዎችም*፤ ከቍ18 ጋር ያነጻጽሩ።

31፥25 *ብርታትንና ሞገስን ተጐናጽፋለች*፤ ኢሳ52፥1፤ 1ጢሞ2፥9-10 ይመ። እንደ እርሷ ያልሆኑት ግን፣ "እፍረትና ጕስቍልና ይለብሳሉ" (መዝ35፥26)። በፊቷ ባለው ዘመን ሁሉ ደስ ብሎአት ትኖራለች፤ ከሐዘንና ከጭንቀት ነጻ ናት (ከኢዮ 39፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

31፥26 *ቀና ምክር*፤ ሴትዮዋ ለልጆቿና ለወዳጆቿ የምታካፍለው ነው፤ በማስተዋልና በፍቅር የምትመክር ናት (1፥8፤ 6፥20 ይመ)።

31፥28 *ቡርክት*፤ ደስታ ያለበትን ሁኔታ የምትወድና ለሌሎችም የደስታ ምንጭ የምትሆን፤ ዘፍ 30፥13፤ መዝ72፥17፤ ማሕ6፥9፤ ሚል3፥12 ይመ፤ ከሩት4፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ።

31፥30 *ቍንጅና አታላይ ነው*፤ ከ5፥3 ጋር ያነጻጽሩ። *ውበትም ይረግፋል*፤ ከኢዮ14፥2፤ ከ1ጴጥ3፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ። *እግዚአብሔርን የምትፈራ*፤ የ1፥7 ማብ ይመ።

31፥31 *ሥራዋም*፤ 12፥14 እና ማብ ይመ። *ያስመስግናት*፤ ክብር የሚገኘው፣ "በትሕትናና እግዚአብሔርን በመፍራት" ነው (22፥4)። *በየአደባባዩ*፤ ቍ23 እና የ1፥7 ማብ ይመ።